# ምዕራፍ ሃምሣ ሶስት
# ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር

ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የእንግሊዝ ጦር የተንቀሳቀሰው በሦስት አቅጣጫ እንደነበር ቀደም ብሎ ተገልጾአል። ከእነዚህም ንጉሠ ነገሥቱን በማገዝ በጉጃም በኩል የገባው ጦር የሠራውን ሥራ ተመልክተናል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በሌሎች ሁለት አቅጣጫዎች፣ ማለትም በሰሜንና በደቡብ የተሠማራው ጦር የሠራውን ሥራ እናያለን።

ኢትዮጵያን ነፃ በማውጣት ረገድ ከፍተኛውን ሥራ የሠራው ከናይሮቢ የተንቀሳቀሰው ነበር። አዲስ አበባ ቀድሞ የገባ እሱ ነው። ምንም የሰሜኑን ጦር ቢያግዘው የጠላትን ጦር አባርሮ አምባለጌ ላይ የማረከ እሱ ነው። ስለዚህ የእሱን አካሄድ አስቀድመን እንመረምራለን።

ይህ በጄነራል ካኒንግሐም የበላይ አዛዥነት እየተመራ በምሥራቅ አፍሪካ ላይ የዘመተ ጦር፤ ከደቡብ አፍሪካ ጀምሮ ካሉት የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ተቀስቅሶ የተሰለፈው በሦስት ረድፍ ነበር። አንዱና ዋነኛው ጦር ከኬንያ በኪሲማዩ በኩል ደቡብ ሶማሊያ ገባ። ሁለተኛው ከየመን በኤደን በኩል አድርጐ በሰሜን ትንሽ ቀደም ብሎ በኢጣልያ ወታደሮች ተይዛ የነበረችውን ሰሜን ሶማሊያን አጠቃ። ሦስተኛው በደቡብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገባ።

ጣልያንን ከምሥራቅ አፍሪካ ለማባረር የተፈለገው ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ተብሎ አልነበረም። የጦርነቱ ሚዛን በጀርመንና በኢጣልያ ላይ ለማክበድ እንጂ። የምሥራቅ አፍሪካ መያዝ ከሕንድ ውቅያኖስ እስከ ሜድትራንያን ያለውን የባህር መንገድ በእንግሊዝ እጅ ያስገባዋል። የኢጣልያ ከምሥራቅ አፍሪካ መባረር ጣልያኖችን ተስፋ ያስቆርጣል። ምናልባትም ከጀርመን ጐን መቆማቸውን በመተው ከጦርነቱ እንዲወጡ ያስገድዳቸዋል። ያለሥራ ኬንያ ላይ ሠፍሮ የነበረው ጦር ግዳጁን ከተወጣ ወደ ምሥራቅ አውሮፓ መጥቶ እንዲሰለፍ ማድረግ ያስችላል። ይህንንም ውጤት ማግኘት የሚቻለው ሁሉም ጦር በአንድ ጊዜ የተንቀሳቀሰ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ሁሉም ጦር በአንድ ጊዜ ተንቀሳቀሰ።

በኪሲማዩ በኩል ሠብሮ ሞቃድሾ ለመግባት የተደረገው እንቅስቃሴ ከየካቲት 2 ቀን እስከ 8 ቀን 1933 ዓ.ም /ፌብሬዋሪ 10 እስከ 18 ቀን 1941/ ተካሄደ። ጣልያኖች ስድስት ብርጌድ ኢጣልያውያንና ሌላ ስድስት ብርጌድ የሀገር ተወላጆች ጁባ ወንዝ ላይ አሰለፉ። ዋናው የጣልያን ጦር ከወደብዋ በስተሰሜን ትንሽ ራቅ ብላ በምትገኝ ጂሊብ በተባለችው ቦታ ላይ ተሰለፈ። ይህ ጦር የካቲት 14 ቀን /ፌብረዋሪ 22 ቀን/ በተደረገው ግጥሚያ ድል ሆነ። ሠላሣ ሺህ ጦር በአንድ ቀን ውጊያ ድምጥማጡ ጠፋ። እኩሉ ሞተ፣ እኩሉ



ቆሰለ፣ ወይም ተማረከ። የቀረው ሸሽቶ ጫካ ገባ። የሞቃድሾ በር ተከፈተ። የጣልያን አየር ኃይል በደቡብ አፍሪካ አየር ኃይል ተመታ።

በመኪና የሚንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር የካቲት 17 ቀን /ፌብሪዋሪ 25 ቀን/ ሞቃድሾ ገባ። በአየርፕላን ጣቢያው ሃያ አንድ የኢጣልያ አይሮፕላኖች ተቃጥለው ከሰላቸው ይታያል። የልዩ ልዩ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ክምችት ተገኘ። ከሁሉም ጠቃሚው በከተማይቱ የተገኘው 400 ሺህ ሊትር ቤንዚን ሆነ። ቀጥሎ የሚደረገው ጉዞ ወደ ጅጅጋ ነበር። እዚያም ለመድረስ በኦጋዴን በረሃ ውስጥ 1180 ኪሎ ሜትር መንገድ ማቋረጥ ብቻ ነው። የጦርነት ጉዳይ አሳሳቢነት የለውም። ከድሬዳዋ እየተነሱ ለመከላከል የሞከሩትን የጣልያን አይሮፕላኖች ከሞቃድሾና ከኤደን በሚነሱ አይሮፕላኖች በማጥቃት፤ የእንግሊዝ መካናይዝድ ጦር መጋቢት 8 ቀን /ማርች 17/ ጅጅጋን ያዘ።

ከኤደን የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 7 ቀን /ማርች 16 ቀን/ በርበራን ከጣልያን አስለቀቀ። ከዚያም ጅጅጋ ከዋናው ጦር ጋር በመቀላቀል መንገዱን ቀጠለ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዲላኖ ሩዝቬልትም የሊቢያውን ጦርነት ለማቀላጠፍ ምሥራቅ አፍሪካን በፍጥነት ማስለቀቅ እንደሚያስፈልግ አስታወቁ።

የጣልያን ጦር በበኩሉ ካራማራ ላይ መሽጐ ለመከላከል ሞከረ። ነገር ግን አልቻለም። ከዚያም በባሌ ላይ ተከማቸ። እዚያም አንዳች ማድረግ አልቻለም። በቀላሉ ተበታትኖ ሁሉም በየፊናው ሽሽቱን ያዘ። ባንዳው ራሱ እየከዳ ይጠዘጥዘው ጀመር። ሌላው ቀርቶ እስከ መጨረሻው ድረስ በታማኝነት ይቆሙልናል ብለው ተማምነውባቸው የነበሩት ኤርትራውያንም እየከዱ ጣልያኖችን መልሰው ደበደቡአቸው። በጥይትና በቦምብ የሚያወርዱባቸው ውርጅብኝ ጣልያኖችን በእግር እንጂ በክብት መንቀሳቀስ ከለከሉአቸው። ጣልያናውያን ወታደሮች ተሸበሩ። ቢሆንም እሳት ከተባለው ቦታ ለሕይወታቸው ሲሉ በርትተው ሙሉ ቀን ተዋጉ። ያም ሆኖ መመከት አልቻሉም። በዚህ ዓይነት ጥሶ የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 16 ቀን 1933 ዓ.ም /ማርች 26 ቀን 1941/ ሐረር ከተማ ገባ። ከዚያም መጋቢት 19 ቀን ድሬዳዋን ያዘ።[1] ነገር ግን የፈረንሳይ መንግሥት ስለአልፈቀደ በጅቡቲ ወደብ መጠቀም አልተቻለም።

ከኬንያ በጋሞ ጎፋ በኩል የገባው የእንግሊዝ ጦር በኢትዮጵያ ስደተኞች እየታገዘ ጨንቻ ገባ። ከዚያም ወደ ጅማ ተጉዞ ከአዲስ አበባ ከወረደው የኢትዮጵያ ጦር ጋር ተቀላቅሎ፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ የነበረውን የጣልያን ጦር መመንጠር ያዘ።[2] በኬንያ ከነበሩት ስደተኞች መካከል ተመልምለው ወደ ሱዳን ያልሄዱት ጦር ተሰርቶ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ወልደማርያም፣ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ታደመ ዘለቀና

በፊታውራሪ/ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተሚካኤል መሪነት በሞያሌ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ከዚያም የበኩሉን እየሠራ በያቤሎ አድርጐ ቦረና ነገሌን ያዘ።

ኢጣልያኖች አዲስ አበባን ላለማስያዝ ሊከላከሉ አሰቡ። ነገር ግን በዜጐቻቸው ላይ አንዳች ውጤት ለማግኘት እንደማይችሉ ከኢትዮጵያውያን አማካሪዎቻቸው በተረዱ ጊዜ በናዝሬትና በመተሐራ መካከል ባለው ቦታ ላይ ለመዋጋት ከጀሉ።[3] ነገር ግን ለመከላከያ አፍርሰውት የነበረውን የአዋሽን ድልድይ ጠባቂ ስለአላደረጉበት እንግሊዞች መልሰው በመሥራት ወንዙን ተሻግረው ስለነበረ ሳይቻል ቀረ። ስለዚህ ዱካ ደ አዎስታ አዲስ አበባን ለእንግሊዞች በሰላም እንዲያስረክብ የከተማይቱን ኃላፊ ወክሎ ወደ ሰሜን ጉዞውን ቀጠለ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሁኔታ ከባድ ነበር። ዙሪያዋን በአርበኞች ተከባለች። ወታደራቸው ቀደም ብሎ ከተማይቱን ለቅቆ ስለወጣ፤ ሰላማውያን ጣልያኖች አርፈው ዕድላቸውን ከመጠበቅ በስተቀር መፈናፈኒን የሚችሉበት መንገድ አልነበራቸውም። ብስጭት የከበደው አርበኛ ገብቶ ነጮቹን እንዳያርዳቸው ተፈርቶአል። አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ 25,000 ነጮች ጉዳይ እጅግ አሳሰበ። ከዚህም የተነሳ እንግሊዝ ጦርነቱን አላቆምም ስለአለ ኃላፊነቱ የዱካ ደ አዎስታ ነው አለች። ጣልያን ደግሞ የእንግሊዝ ነው አለች።[4] በከተማይቱ ዙሪያ 35 ምሽጐች ተሠርተዋል። ደግሞም በእሾህማ ሽቦ ከተማዋን አጥረዋል። በጣልያኖች መኖሪያ አካባቢ ዋሻ ቆፍረው የአደጋ ድምፅ በተሰማ ጊዜ ዜጐቻቸውን ከዚያ እንዲሸሸጉ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል። ነገር ግን ይህ ሁሉ ከንቱ ሆነ። በከተማይቱ ዙሪያ የነበረው አርበኛ አንዳች ጉዳት አላደረሰም። የከተማይቱን ፀጥታ ለመጠበቅ የቻለው አዲስ የገባው የእንግሊዝ ጦር አልነበረም። የንጉሠ ነገሥቱም ትዕዛዝ ብቻ አልነበረም። የአርበኛው ትዕግስትና የሕዝቡ ሥርዓት አክባሪነት እንጂ።

በጄኔራል ዊዝሮል የሚመራው የእንግሊዝ ጦር አቃቂ ደረሰ። የቡልጋ አርበኛ በራስ አበበ እየተመራ የአዲስ አበባን ዙሪያ ያዘ። የኢጣልያ ሹማምንት ያለ አንዳች ጥያቄ ከተማይቱን ከማስረከብ በስተቀር አንዳች የሚያደርጉት አልነበራቸውም። የእንግሊዝ ጦር ሃምሣ ሺህ የጣልያን ጦር አራግፎ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም እሑድ ጥዋት አዲስ አበባ ገባ። ጄኔራል ዊዝሮል ገነተ ልዑል ይባል ከነበረው ዛሬ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሆነው ቤተ መንግሥት ገብቶ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማ ተከለ።

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ታላቅ ቅሬታ ፈጠረ። የነጭ ለነጩ ቅብብሎሽ ሆነ። ሌላ አዲስ ብጥብጥ ሊነሣ ተቃረበ። ብልሆቹ የእንግሊዝ መሪዎች ይህንን ሲገነዘቡ ፈጣን የማረጋጊያ እርምጃ ወሰዱ። እሱም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በታላቁ የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ላይ መስቀል ነበር። ጄኔራል ዊዘሮል ከቀትር በኋላ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሄደው፤ የኢጣልያን ሰንደቅ ዓላማ አውርደው ከላዩ ላይ ቆመው የኢትዮጵያን



ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ። ሰንደቅ ዓላማይቱን ከሰቀሉ በኋላ በአቶ /ብላታ/ ዳዊት ዑቁበእግዜአብሔር አስተርጓሚነት ንግግር አደረጉ። ባደረጉትም ንግግር ያቺ ቀን በመላ ሕይወታቸው ስትታወስ የምትኖር ታላቅ ቀን መሆንዋን ገልጸው፤ ንጉሠ ነገሥቱ በቅርብ ቀን ከመናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ እንደሚገቡ አረጋገጡ። ታላቅ ደስታ ሆነ።[5]

ከኬንያ በጄኔራል ካኒንግሐም እየተመራ የተንቀሳቀሰው ጦር በዚህ ዓይነት ደቡብና ሰሜን ሶማሊያን በተለይም ኢትዮጵያን ነፃ አወጣ። አሁን ደግሞ በጄኔራል ፕላት መሪነት ከካርቱም በሰሜን በኩል የተንቀሳቀሰው ምን እንደ አደረገ እንመለከታለን።

በሰሜን የነበረው የኢጣልያ ጦር ከረን ላይ ሊሟሟት ተዘጋጅቶ ነበር። ከረን በሦስት ታላላቅ ተራሮች የተከበበች በመሆኗ ለመከላከል ምቹ ናት። ከዚያም አልፎ በአቆርዳትና በተሰነይ በተለይም በከሰላ አካባቢ የመከላከያ ዝግጅት አደረገ። በእንግሊዞችም በኩል ለማጥቃት ዝግጅት ተደርጐ ጦርነቱ በጥር 1933 ዓ.ም ተከፈተ።

ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም አድርገው ሐምሌ 1 ቀን 1932 ዓ.ም በትግርኛ ቋንቋ አዋጅ ነግረው ነበር። አዋጁም በተለይ ለኤርትራ ሕዝብ ያስተላለፈው መልእክት "...የሐማሴን፣ የአከለጉዛይ፣ የሠራየ፣ የበኒአምር፣ የሃባብ፣ ከመረብ ወንዝ ወዲህም ማዶም ያላችሁ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ ጋር ተባበሩ። ለጣልያን መሣሪያ አትሁኑ። እናታችሁን ኢትዮጵያን አትተው። እንግሊዝን አትውጉ.." የሚልና እንግሊዞችን በፍቅር እንዲቀበሉአቸው የሚያሳስብ ነበር።[6] ይህ አዋጅ የኤርትራ አርበኞች በጣልያን እንዲነሱና እንግሊዝን እንዲደግፉ በማድረግ ረገድ በእጅጉ ረዳ። ለጦርነቱም አቶ /ደጃዝማች/ አስጋኸኝ አርአያ የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ሆኑ።

ከዚህ የፖለቲካዊና ወታደራዊ ዝግጅት በኋላ፤ የእንግሊዝ ጦር በተሰነይ በኩል ወደ ኤርትራ ለመግባት ተንቀሳቀሰ። ተሠነይ በቀላሉ ተያዘች። ጣልያኖች ከጐንደር ጭምር ወታደር ወስደው በሬንቱ ላይ ለመመከት አስበውት የነበረው ከሸፈ። አቆርዳትን መያዝም አላስቸገረም። ከዚያ በኋላ ጦርነቱ እየጠጠረ ሄደ። የኢጣልያ አየር ኃይል የተቻለውን አደረገ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ የእንግሊዝ አየር ኃይል የበላይነትን በማግኘቱ፤ በአካባቢው ያለውን የጣልያን ጦር እየደበደበ አደነዘዘው።

ከረንን የማስለቀቅ ፍልሚያ መጋቢት 6 ቀን 1933 ዓ.ም /ማርች 15 ቀን 1941/ ተጀመረ። ለሦስት ቀን ከባድ ሁኔታ ተካሄደ። ሎሬንሲኒ የተባለው የኢጣልያ ኰሎኔል ወጥሮ ያዘ። ከድካም የተነሣ ጦርነቱ ቀዘቀዘ። ሁለተኛው ዙር መጋቢት 16 ቀን /ማርች 25/ ተጀመረ። ሁለት ቀን የፈጀ ከባድ ፍልሚያ ከተካሄደ በኋላ ከረን ተያዘች። የተያዘችውም ሎሬንሲኒ ከሞተ በኋላ ነው። እንግሊዞች ከረንን የያዙት በሦስት ሺህ ወታደር ሕይወት መስዋዕትነት ነው። ከረን ከተያዘ በኋላ ችግሩ ቀለለ። አሥመራ' መጋቢት 23 /አፕሪል 1

ቀን/ ተያዘች። ምፅዋ ደግሞ ሚያዝያ 1 /አፕሪል 8/ ቀን ከአሥር ሺህ ጣልያናውያን ምርኮኞች ጋር ተያዘች። ጦርነቱ ሲከፈት ጣልያን ዘጠኝ የመርከብ ማስጠሚያ መሣሪያ የተጫኑ መርከቦች /ዲስትሮየርስ/፣ ስምንት የባሕር ውስጥ ጠላቂ መርከቦች /ሰብመሪንስ/ እና ሌሎችም ለልዩ ልዩ አገልግሎት የተዘጋጁ መርከቦች በቀይ ባሕር ላይ ነበሩአት። እነዚህን ሁሉ አጣች። ባሕሩ ለአሜሪካን መርከቦች ክፍት የሆነ ሰላማዊ አካባቢ መሆኑን ፕሬዚደንት ሩዝቬልት ገለጹ። በሕንድ ውቅያኖስና በሜዲትራኒያን ባሕር ያለው የውሃ መንገድ ለምዕራባውያን ሚያዝያ 4 /አፕሪል 11/ ቀን ተከፈተ።[7]

ከዚህ በኋላ ዋናው የእንግሊዝ ጦር ወደ ሊቢያ ወጣ። ከቀረው ጦር ከፊሉ ከአሥመራ በአዲኳላ በኩል ወደ ጐንደር፣ ከፊሉ ደግሞ በአዲግራት በኩል ወደ አምባላጌ በመንዝ ግዳጁን ተወጣ።

ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር ምን ያህል እንደ ሆነ በትክክል አልታወቀም። ኢጣልያ ከጦርነቱ የገባችው ባንዳውን ጨምሮ 350,000 ጦር በምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛትዋ አከማችታ ነበር። አርበኛው ከባንድነት የከዳውን ጨምሮ 100,000 ቢሆን ነው። ስለዚህ የእንግሊዝ ጦር 100,000 ያህል ነበር ቢባል ብዙም ከእውነት የራቀ አይሆንም። አሰላለፉም፣

ሀ. ከካርቱም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በጐጃም፣ የኢትዮጵያን ስደተኞች ሳይጨምር 3,000፤

ለ. ከካርቱም በከሰላ በኩል 30,000፤

ሐ. ከካርቱም በአሶሣ በኩል 1,000፤

መ. ከናይሮቢ በሞቃድሾ በኩል፣ ስደተኛውን ሳይጨምር 60,000 ፤

ሠ. ከናይሮቢ በቦረና በኩል 5,000፤

ረ. ከናይሮቢ በጋሞ ጐፋ በኩል 1,000 ሳይሆን አልቀረም።

የክብር ጉዳይ ሆኖባቸው እንግሊዞች ተገቢ ግምት አይሰጡት እንጂ፤ የአርበኛው ኃይል ቀላል አልነበረም። ለጦር ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ዞሮ መሸነፉ አይቀር እንጂ፣ አርበኛው ባይኖር የጣልያን ጦር እንግሊዞችን ብዙ ያስቸግራቸው ነበር። ይህንን ሐቅ መካድ በታሪክ ፊት እውነት አይኖረውም። መሣሪያ ጨብጦ ከጣልያን ጦር ጋር ግንባር ለግንባር ገጥሞ የተዋጋው አርበኛ ቁጥር ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ ይለያያል። በ1933 ዓ.ም ለመጨረሻው ፍልሚያ የተሰለፈው ከ100,000 አያንስም።[8]



## መሣሪያ የጨበጠ የአርበኛ ብዛት በየዘመኑ

| አርበኞች | ለ1927 ዓ/ም ምርመራ የቀረበ | በ1928 ዓ/ም | በ1929 ዓ/ም | በ1930 ዓ/ም | በ1931 ዓ/ም | በ1932 ዓ/ም | በ1933 ዓ/ም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በጐንደር | 15,000 | 1,000 | 2,000 | 6,000 | 10,000 | 7,000 | 25,000 |
| በጐጃም | 28,500 | 500 | 1,500 | 4,000 | 5,000 | 4,000 | 15,000 |
| በትግራይ | 3,400 | 500 | 200 | 500 | 400 | 300 | 2,000 |
| በወሎ | 2,250 | 500 | 100 | 300 | 200 | - | 1,000 |
| በመንዝና ተጉለት | - | 1,000 | 3,000 | 20000 | 10000 | 7,000 | 15 000 |
| በይፋትና አንኮበር | - | 500 | 1,500 | 5,000 | 3,600 | 2,500 | 5,000 |
| በመርሐቤቴ ና ሰላሌ | - | 500 | 1,500 | 5,000 | 4,000 | 3,000 | 5,000 |
| በቡልጋና ሸንኮራ | - | 15,000 | 10,000 | 30,000 | 20,000 | 11,700 | 20,000 |
| በግንደበረት | - | 500 | 200 | 3,000 | 2,500 | 1,500 | 4,000 |
| በጉራጌ | - | 3,000 | 5,000 | 5,000 | 4,000 | 3,000 | 5,000 |
| በሸዋ | 28,000 | 500 | - | - | - | - | - |
| በወለጋ | - | 10,000 | 300 | 300 | 200 | - | 1,000 |
| በኢሉባቡር | - | 1,000 | - | - | - | - | 1,000 |
| በከፋ | 15,000 | - | - | - | - | - | - |
| በሐረርጌ | - | 1,000 | - | - | - | - | - |
| በአርሲ | 500 | - | - | - | - | - | - |
| በባሌና አርሲ | | 500 | 200 | - | - | - | - |
| በጋሞጐፋ | 450 | - | - | - | - | - | - |
| በሲዳሞ | 550 | 5,000 | 3,000 | 200 | 100 | - | - |
| ድምር | 103,650 | 40,000 | 30,000 | 80,000 | 60,000 | 40,000 | 100000 |

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 207-211።
2. Winston Churchil, *The Grand Alliance,* p.6, 7, 16,17,79,90.
3. ከአባ ገብረ መስቀል /ብፅዕ አቡነ ዮሐንስ/ የተነገረኝ።
4. ሕይወቱ ኅደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 413።
5. ከአቶ ዓለመ ሥላሴ ጉላ የተነገረኝ።
6. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 210-212።
7. Churchil, pp.88-90.
8. ሠንጠረዡን ይመልከቱ።

[*] የድል አጥቢያ አርበኞችን ጨምሮ።



# ምዕራፍ ሃምሣ አራት
# የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ፍፃሜ

ሙሶሊኒ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከሂትለር ጐን መቆሙን ለዓለም በይፋ አስታወቀ። ይህ መግለጫ ሲወጣ በኢጣልያ ላይ የፖለቲካ ሰማይ ተሰበረባት፣ የጦርነት እሳት ተቀጣጠለባት። ኢትዮጵያን ለማጥቃት እንዳሻት ትንደረደርበት የነበረው የስዊዝ ካናል የባህር ጉሮሮ ተዘጋባት። በእስፔይን ብጥብጥ ለመርዳት የተላከው የጣልያን ጦር እንደ ወጣ ቀረ። በአልባንያና በግሪክ ላይ የዘመተው ጦር በየተራ ተሸነፈ። በሊቢያ የነበረው ታላቅ ጦር ድል ተመታ። በምሥራቅ አፍሪካ የነበረው ሠራዊት ከጣልያን ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ።

እንግሊዞች ከአፍሪካ፣ ከህንድ፣ ከሩቅ ምሥራቅ፣ ከአውስትራሊያና ከኒውዚላንድ ጦራቸውን ወደ ሰሜን አፍሪካና ከዚያም ወደ ማሕል አውሮፓ በፍጥነት ማንቀሳቀስ አስፈለጋቸው። የደቡቡን ግንባር ለማጠንከር። እንቅስቃሴው ወታደር ብቻ ሳይሆን ስንቅና ትጥቅም ይጨምር ነበር። ለዚህ እንቅስቃሴ የቀይ ባህር መለቀቅ ግድ ሆነ። የቀይ ባህር መለቀቅ ማለት ደግሞ የኢጣልያ ከምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛትዋ መባረር ሆነ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ነፃ የመውጫው ጦርነት በሦስት በር በአንድ ጊዜ ተከፈተ። ባለፉት ምዕራፎች እንዳየነው ንጉሥ ነገሥቱ ከለንደን ካርቱም ደርሰው በቢልያ በኩል ጐጃም ገቡ። የእንግሊዝ ጦር ከኬንያ በሞቃድሾና በበርበራ በኩል ሰብሮ ሐረር ገባ። ከካርቱም የተንቀሳቀሰው ጦር በከሰላ በተሰነይ አድርጐ የከረንን ጉራ ሰበረ። ቀይ ባሕር በእንግሊዝ የባሕር ኃይል ቁጥጥር ሥር ገባ። ጣልያኖችን አርበኛው በተጠናከረ ሁኔታ በየጎጡ አጠቃቸው። ከአሸናፊ ጐን በመቆም ጥቅሙን የማካበት ዘዴ የያዘው ባንዳ ካዳቸው። ከአርበኞችና ከነፃ አውጭው ጦር ጐን እየሆነ በገዛ መሣሪያቸው፣ እነሱ ባስተማሩት ዘዴ መልሶ ይወጋቸው ጀመር።

ይህ ሁኔታ በጣልያኖች ላይ ከፍተኛ ጭንቀት ፈጠረ። በተለይም በመሪዎቹ ላይ። ጄነራል ናዚ በአማራው አገር ያለውን ሁኔታ እየተዘዋወረ ከአየና ከገመገመ በኋላ፤ የተረፈውን ኃይል ሰብስቦ የጐንደርን ከተማና አካባቢ ያዘ። የወንድ ሥራ ለመሥራት የሞከረ እሱ ብቻ ነበር።

ከምሥራቅ የመጣው የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባ ለመግባት ሲያኮበኩብ፤ ዱካ ደ አዖስታ ለከተማው ጥበቃ ወክሎ ወደ ሰሜን ጉዞውን ቀጠለ። ወደ ሰሜን የተጓዘው ተጨንቆ እንጂ ወዶ አልነበረም። አዲስ አበባ ላይ እዋጋለሁ ብሎ ቢፍደለደል በምሥራቅ የመጣው የእንግሊዝ ጦር ጣልያን ያፈረሰውን የአዋሽን ድልድይ መልሶ በመሥራት አዋሽን ተሻግሮ ሸዋ ምድር ገብቷል። አዲስ አበባ ላይ መዋጋት አርበኛው በሺያ የነበሩትን ጣልያናውያን ሴቶችና ልጆች እንዲፈተፍታቸው መንገድ መክፈት ሆነበት። ወደ ኢሉባቡር

መሄድም ጦሩን ከባህር በር ከማራቁም በላይ ጥቅጥቅ ከአለ ጫካ ወስጥ መስጐ የሚያስጠቃው መሆኑን አወቀ። ስለዚህ ወደ ደሴ ሸሸ። ደሴ ሲደርስ ደግሞ ሌላ የባሰ ጭንቅ አጋጠመው። የእንግሊዝ ጦር እያባረረ ደረሰበት። አርበኛውም ተሰብስቦ ጠዘጠዘው። ወደ አሰብ መሄድ በጦርነቱ ጊዜ የመጣውን የጣልያን ጦር አፈር አስግጦ ያስቀረው የአፋር ሕዝብ እንደማይለቀው ተገነዘበ። ወደ ጐንደር የሚወስደው መንገድም በአርበኞች ተዘጋበት። ስለዚህ ከዱካ ደ አምስታ ፊት ከተደቀኑት ውርደቶች ቀላሉ ወደ ሰሜን ተጉዞ አምባለጌ ተራራ ላይ ወጥቶ መሰቀል ሆነ። መጥፎ ምርጫ አልነበረም። ጀነራል ናዚ ግን አልወደደለትም። ከወጥመድ እንደገባ ቆጠረው። ከሐረርጌ ሸሽቶ የመጣው፣ በማሕል ኢትዮጵያ የነበረው፣ ከጐጃም ወደ ሸዋ ከተሻገረው በመርሐቤቴ በኩል ወደ ሰሜን የወጣው፣ በወሎ የነበረው የጣልያን ጦር ጌታውን ተከትሎ አምባለጌ ወጣ።

ሦስተኛው ክፍል የጣልያን ጦር ወደ ኢሉባቡር ሄደ። ከእሱም ገሚሱ ከጐጃም ሸሽቶ ወደ ሸዋ ከተሻገረውና እንደዚሁም በደቡብ ክፍላተ ሀገር ማለትም በሲዳሞ፣ በጋሞጐፋ፣ በከፋ የነበረው ነበር። በኢሉባቡር የነበረውም በዚያው ቦታውን አጠናከረ። በወለጋ የነበረውም ግንኙነት ፈጠረ።

ጠላት በዚህ ዓይነት ሲተረማመስ የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 28 ቀን አዲስ አበባን ያዘ። ንጉሠ ነገሥቱ በጐጃም በኩል አድርገው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከመናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ ገብተው በትረ መንግሥታቸውን እንደገና መልሰው ጨበጡ።

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ሲገቡ የጦርነቱ ሁኔታ ተለወጠ። ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ተመልሳ ቆመች። የኢጣልያ ጦር በተራው ሽፍታ ሆነ። የእንግሊዝ ጦር በኢትዮጵያ መንግሥት ረዳትነት በሦስቱም የጦር ግንባር ማለትም በኢሉባቡር፣ በጐንደርና በአምባለጌ ተሰለፈ። ንጉሠ ነገሥቱ በሦስቱም የጦር ግንባር ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተባብሮ ጠላቱን እንዲወጋ ሠራዊታቸውን አሠለፉ። በጐንደር በፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደገብርኤል አዛዥነት የጐንደርና የጐጃም፣ እንደዚሁም ከሸዋ የተሻገረ አርበኛ ተሰማራ። በአምባለጌ ግንባር የትግራይና የወሎ እንደዚሁም ከሸዋ የተላከ አርበኛ ከበበ። ወደ ኢሉባቡር በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ፤ በወለጋ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ የሚመራ ጦር ተላከ።

ኢትዮጵያ ጣልያንን በቶሎ ከሀገርዋ አስወጥታ ማባረር ነበረባት። የእንግሊዝ ጦርም በምሥራቅ አፍሪካ ያለውን ጉዳይ በፍጥነት አጠናቅቆ ለሰሜን አፍሪካው ጦርነት መድረስ ነበረበት። ስለዚህ ጦርነቱ በሁሉም ግንባር ተፋፋመ።

ፈጥኖ የወደቀው የአምባላጌው ግንባር ስለሆነ አስቀድሞ እሱን ማየት ይሻላል። በዚህ አውድ የትግራይ አርበኞች በየፊናቸው ተራራውን ከበቡ። ራስ /ልዑል ራስ/ ሥዩም እንደገና ተመልሰው በአርበኞች መካከል በመገኘት



የአርበኛውን ግንባር አጠናከሩ። ከአዲስ አበባ የወጣውና ከአሥመራ የመጣው የእንግሊዝ ጦር ደርሶ፤ ከተራራው ላይ ያለውን የጣልያን ምሽግ በመድፍ መደብደብ ጀመረ። አርበኛውም ቀስ በቀስ እየተሳበ ወደ ምሽጉ ተጠጋ።

ውጊያው ቀስ በቀስ እየጋለ ሄዶ ደንበኛው ጦርነት ሚያዝያ 29 ቀን 1933 ዓ.ም /አፕሪል 7 ቀን 1941/ ተከፈተ። በማግስቱ ሚያዝያ 30 ቀን እንግሊዞች አይሮፕላን ከአሥመራ እያስነሱ መደብደብ ያዙ። የጦርነቱ አስጨናቂነት ዕለት በዕለት እያደገ ሄደ። በራሱ በዱካ ደ አምስታ አገላለጽ ገሐነመ እሳት ሆነበት። በሦስተኛው ቀን ማለትም ግንቦት 1 ቀን 1933 ዓ.ም /ሜይ 9 ቀን 1941/ ጠላት ፈለገ እና አምባጐንጫ ከተባሉት ቦታዎች የነበሩትን ምሽጐች ለቀቀ። ግንቦት 2 ቀን ከሁለት መቶ ያላነሱ ባንዶች ከድተው ወደ ወገኖቻቸው ዞሩ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ምሽጉን ለመናድ እያነጣጠሩ ይደበድቡ ጀመር። ግንቦት 3 ቀን አርበኛው የጣልያናውያኑን መታከሚያ ቤት ወሰደው። ግንቦት 4 ቀን አርበኞቹ ለብቻቸው ማጥቃት ጀመሩ። ግንቦት 5 ቀን ድል መሆኑ እየተቃረበ ስለሄደ የጣልያን ወታደር በአዛገፉ ላይ አጉረመረመ። ግንቦት 6 ቀን ዱካ ደ አምስታ የመጣው ቢመጣ ከነበረበት ቦታ ልውስ ላለማለት ወሰነ። ግንቦት 7 ቀን በተደረገው ቆጠራ ከእልቂት የተረፈው የጣልያን ጦር አንድ መቶ ሰባ ብቻ መሆኑ ተረጋገጠ። እንደ ዱካ ደ አምስታ ቃል በኢጣልያ ጦር ላይ ጭለማ ወደቀበት። የኢትዮጵያ እውነተኛ ታሪክ መዝገብ የሚገለጽበት ቀን ተቃረበ። ግንቦት 8 ቀን በተካሄደው ስሌት ምሽጉ በሠላሳ ሺህ ጥይት መደብደቡ ተረጋገጠ። በራሱ በዱካ ደ አምስታ አገላለጽ እልኩ ማለትም እዶቃው ደረሰ። የዕርቅ ንግግር እንዲጀመር ወሰነ።

ግንቦት 9 ቀን በጄነራል ትሬሣኒ አማካይነት የዕርቅ ድርድር ተጀመረ። አብረውት የነበሩት ሁሉ ከወጡ በኋላ ዱካ ደ አምስታ ወጥቶ አርበኞች በገሐድ በተቀመጡበት አደባባይ ለእንግሊዝ ጦር እጁን ሰጠ። ከዚህ በኋላ ግንቦት 10 ቀን ለቁስለኞች እርዳታ ተደረገ። ግንቦት 11 ቀን ክብረ በዓል ተደርጐ አንድ ቡድን የጥቁር /ኢትዮጵያ/፣ አንድ ቡድን የነጭ /እንግሊዝ/፣ አንድ ቡድን የቀይ /ሕንድ/ ወታደር ሰልፍ አሳየ። ጣልያን በመጋቢት ወር 1928 ዓ.ም ያለ አንዳች ችግር የያዘውን የአምባለጌን ተራራ፣ ዱካ ደ አምስታ ግንቦት 12 ቀን 1933 አሣሩን አይቶ ለቅቆ ወጣ። ዱካ ደ አምስታም አንድ የወርቅ ኒሻን ማበቻ ጥብጣብ በእንግሊዙ ጦር አዛዥ በጄነራል ሜይን በአንገቱ ተጠልቆለት የምርኮኝነት ሥራ ጀመረ። በመኪና ወደ አሥመራ ከዚያም በአይሮፕላን ወደ ናይሮቢ ተወሰደ። እዚያም ከጦር ምርኮኞች እሥር እንደ አለ ሞተ።[1]

ሌላው የጦር ግንባር በኢሉባቡር ነበር። በሲዳሞ፣ በጋሞ ጐፋ፣ በአሩሲ፣ በባሌ የነበረው የጣልያን ጦር በሐይቆች አካባቢ ተሰበሰበ። በሞያሌ በኩል የመጣውና ከሞጆ የሄደው ጦር ተከተለው። በፊታውራሪ /ደጃዝማች/

ገረሱ ዱኪና በሻለቃ በቀለ ወያ የሚመራው አርበኛ እየተከታተለ በየቦታው ቀጣው። የጠላት ጦር የኦሞን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ጅማ ተጓዘ። ከጉጃም ወደ ሸዋ የተሻገረው የጣልያን ባንዳ፤ ከብርቱ የአርበኞች ቅጥቀጣ ያመለጠው በተፍኪ፣ በወሊሶ እያደረገ የግቤን ወንዝ ተሻግሮ ጅማ ገባ። አንዱ ጦር የሚደርሰው ቀደም ብሎ የደረሰው ከተፈታ ወይም ከሸሸ በኋላ ስለነበር፤ ጅማ ላይ ለመዋጋት ያሰበው ሃሳብ ውጤት አላስገኘለትም። ስለዚህ ወደ በደሌ ሄደ።[2]

በዚያው የነበረውና ከምዕራብ ሸዋ ሸሽቶ የገባው የጣልያን ጦር ወለጋ ላይ ለመከላከል ሞከረ። በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ ከሚመራው ጦር ጋር በግንቦት ወር 1933 ዓ.ም ገጥሞ አሥራ አራት ቀን ተዋጋ። ያለቀው አልቆ የተረፈው ወደ ነቀምቴ፣ ከዚያም ወደ አርጆ ሸሸ። ከዚያም የወዲሣን ድልድይ አፍርሶ ለሁለተኛ ዙር ጦርነት ተዘጋጀ። አባራሪው ጦር ደርሶ ሰኔ 12 ቀን 1933 ገጠመው። እስከ ሰኔ 14 ቀን ድረስ ከተዋጋ በኋላ ድል ሆኖ ወደ በደሌ በመሄድ እጁን ለኢትዮጵያ ጦር ሰጠ። በደሌ ላይ እጁን የሰጠው የጠላት ጦር ብዛት ከአንድ ሺ.ህ አያንስም ነበር። አብዛኞቹ መኰንኖች ነበሩ።

ጄነራል ጋዜራ እጁን ላለመስጠት የመጨረሻ ሙከራ አደረገ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ድል ሆነ። ዘጠና ከባድ መኪና፣ ሰባት አውቶሞቢል፣ ሃያ ሁለት የመኪና መጐተቻ፣ በርካታ መሣሪያና ጥይት ተማረከ። ሆኖም ጄነራል ጋዜራ አሁንም እጁን ለመስጠት አልፈለገም። የገባንና የሦርን ድልድዮች በዲናሚት አፍርሶ ወደ ዩብዶ አመራ። የኢትዮጵያ ጦር ደርሶበት ትንሽ ከአንገራገረ በኋላ ወገን ያገኘ መስሎት እጁን ለቤልጅግ ጦር ሰጠ።

ከጅማ የሸሸው፣ ከማጂ የመጣውና የከፋው ጦር እየተጠረቃቀመ ወደ ጐሬ ተጓዘ። የጐሬ ከተማ በ1928 ዓ.ም መከላከያ እንድትሆን ተመርጣ እንደነበረችው ሁሉ፤ አሁንም በዚያ አካባቢ ለተከማቸው የጣልያን ጦር የመጨረሻ መፋለሚያ እንድትሆን ተመረጠች። የጠላት ጦር ከአርበኞች በየቦታው ከተቃጣበት ጥቃት እየተከላከለ፤ በዱረኒ በሱጴ አድርጐ በአሣር በመከራ ጐሬ ከተማ ገባ። የኢትዮጵያም ጦር ወዲያው ተከታትሎ ደረሰ።

ጦርነቱ ሰኔ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከጥዋቱ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ተከፈተ። ከሁለቱም ወገን ከባድ ውጊያ ተደረገ። እልቂቱ እጅግ ከባድ ነበር። ከአርበኞች ወገን ከአምስት መቶ ሰው በላይ ሞተ፤ ብዙ ቆሰለ። ከጠላት ወገን ተሰልፎ ከነበረው 12,787 ወታደር መካከል ከአዛዡ በተሰጠው መግለጫ መሠረት ተርፎ በሕይወት የተማረከው 5,553 ብቻ ነበር። የቀረው ከዚያው ከጦር ሜዳው ላይ ተራግፎ ቀርቶአል ማለት ነው። ጊዜው ባያጥር ኖሮ ከዚያም የበለጠ እልቂት ሊደርስ ይችል ነበር። የጦርነቱ ክብደት ጊዜውን አሣጠረው። ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን አቆመ።



ይህ የጦር ጉራ በኢትዮጵያ ሠራዊት ብቻ ተፈታ። ኢትዮጵያውያን አሸነፉ። ጣልያኖች ተሸነፉ። በዚያ የጦር ሜዳ የዋሉ ጀግኖች ነጭ አምራች ገበሬ ተባሉ። ይገባቸዋል። ከላይ ቁጥሩ የተጠቀሰውን የጣልያን ወታደር ጨርሰው 43 የውሃ መትረየስ፣ 150 ድግን መትረየስ፣ ቁጥሩ እጅግ የበዛ መሣሪያና ጥይት ማርከዋል። በጠቅላላው በኢሉባቡር አውድ የተማረከው የጦር መኰንንና ወታደር 19,750 ነበር። በምዕራብ ኢትዮጵያ የተካሄደው ፍልሚያ በእንዲህ ተፈጸመ። "በለው እንበለው" የሚለው በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው አርበኛ ዓርማ ዒላማውን መታ።[3]

የመጨረሻው የፍልሚያ አውድ ጐንደር ከተማ እንደምትሆን እየታወቀ ሄደ። ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደገብርኤል አርበኛውን እያስተባበሩ በንጉሠ ነገሥቱ የተመደበላቸውን ጦር እየመሩ ተጠጉ። ከዚያም የጦር ሠፈራቸውን ከእስቴ ወደ ምክሬ፣ ከዚያም ወደ አመሰ ወንዝ ሊማይ አዘዋወሩ። የእንግሊዝ ጦርም ተባበራቸው። እሳቸውም የእንግሊዝ ጦር፣ አርበኛውና ስደተኛው የደብረ ታቦርን ከተማ ከብቦ እንዲያጠቃ አዘዙ። ጦርነቱ ሰኔ 25 ቀን 1933 ዓ.ም ተከፍቶ በተቀላጠፈ ሁኔታ ተካሄደ። በምሥራቅ በእናቴቱ ማርያም፣ በምዕራብ በጠጌር ገብርኤል፣ በሌላው ቦታ ሁሉ የተሰለፈው ጥሩ ሥራ ሠራ። ጣልያኖች ደግሞ ባልተጠበቀ ሁኔታ አይሮፕላን አስነስተው ሊማዳ ከተባለው ቦታ በነበረው አርበኛ ላይ ብርቱ ጉዳት አደረሱ። በመሆኑም የደብረ ታቦር ከበባ ተጠናከረ። ደግሞም ከደብረ ብርሃን በደሴ በኩል የተላከው የሸዋ አርበኛ ከወሎ አርበኞች ጋር በመሆን በታንታ፣ በደላንታ፣ በዋድላ፣ በላስታ፣ በሣይንት የነበረውን የጠላት ጦር ድል እያደረገና ከየነበረበት ምሽግ እየነቃቀለ በዚሁ በሰኔ 25 ቀን 1933 ዓ.ም ደብረ ታቦር ዙሪያ ደረሰ።

ደብረ ታቦር የውጥር ተያዘች። ሕዝቡ ምሥጢሩን አስቀድሞ ተረድቶት ከተማይቱን ለቅቆ ወጥቶ ስለነበረ ጭንቁ የኰሎኔል አንጀሊኒ ሆነ። ሕዝብ ስንቅ ማቅረቡን ተወ። ጣልያን ከጐንደር ከተማ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ እያረደ ለጦሩ አበላ። ጭንቅ ሲበዛበት ከአለቃው ከጄነራል ናዚ የተሰጠውን ጥብቅ ትዕዛዝ ጥሶ የእጅ መስጠት ንግግር ከፈተ። ንግግሩ ከፍፃሜ ደረሰና ያለአንዳች ማወላወል ከእነሠራዊቱ እጁን ለፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ሰኔ 29 ቀን 1933 ዓ.ም ሰጠ።

ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ለተለቀቀው አገር አስተዳዳሪዎች መደቡ። ከጣልያን አብረው የተማረኩ ባንዶች ለአገራችን እንዋጋለን ስለአሉ ኃላፊ ሰጡአቸው። አካባቢውን በዚህ ዓይነት ከአረጋጉና ጦራቸውን ከአጠናከሩ በኋላ በብዙ ሥራዊት ታጅበው ከደብረ ታቦር ደጐማ ገቡ። በሜጀር ይገለስ የሚመራውም የእንግሊዝ ጦር አብሮአቸው ሄዶ በዚሁ ቦታ ሠፈረ።

ከዚህ በኋላ በፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ሠፈር ምክር ተደረገ። የጐንደር ዙሪያ ሦስት አራት ጊዜ ድርብርብ በሆኑ ተራሮች የተከበበች በመሆንዋ ናዚ

ሁሉንም ጦር አስፍሮባቸው እንደነበር ታወቀ። ሁሉን በአንድ ጊዜ ማስለቀቅ የማይቻል አልሆነም። ስለዚህ እያንዳንዱን ምሽግ እየነጠሉ መምታት እንደሚሻል ታመነበት። መጀመሪያ የሚደመሰሰው ቁልቋል በር ላይ የነበረው ምሽግ እንዲሆን ተወሰነ። የጐንደር አርበኛና እንደዚሁም ከንጉሠ ነገሥቱ የተላከው ስደተኛ በምሥራቅ ያለውን ተራራ ያዙ። ወደ ጐንደር ከተማ የሚወስደውን መንገድ ጭሀራ ላይ እንዲቆርጥ፤ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተሥላሴ በላይነህ የሚመራው የሸዋ አርበኛ ማሕል ደንብያ ሠፈረ። ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ምናልባት ከጐርጐራና ከጀንጓ የሚመጣ ረዳት የጠላት ጦር ቢኖር እንዲጠባበቁ ተደረገ። በሻምበል ማክለይን የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ከጐንደር ከተማ ምሥራቅ ደንቀዝ ዓባይ ላይ ሠፈረ። የቁልቋል በርን ምሽግ ከበቦ ሁሉም በየበኩሉ በጠላት ላይ አደጋ መጣልና ራሱን መከላከል ሥራ አድርጐ ያዘ።

ይህ ሁኔታ ለጀኔራል ናዚ ታውቆት ነበርና፤ ምንዛሮ ዱባ ከተባለው ተራራ ላይ በኰሎኔል ቶሬሊኒ የሚመራ ጦር ቀደም አድርጐ አሥፍሮ ነበር። ቶሬሊኒ የጦር ጥማት ስለነበረበት ቁልቋል በር ለተከበበው የጣልያን ጦር ስንቅ ሊያቀብል ከምሽጉ በካሚዮን ነሐሴ 12 ቀን ወጣ። ጐማሬ ከተባለው ቦታ ሲደርስ ጦርነት ገጠሙት። ከጥዋቱ 3 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ከባድ ጦርነት ተካሄደ። ለሀገራችን እንዋጋለን ብሎ ለፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ቃል ገብቶ የተቀላቀለው የወሎ ባንዳ፤ ከሸዋ አርበኞች ጋር ሆኖ ጥሩ ሥራ ሠራ። የጥይቱ ውጊያ ወደ እጅ በምብ ሲዞር፤ በመቶ አለቃ /አባ/ ገሪማ ታፈረ አገላለጽ ምድር ቁልቢጥ ሆነች። ጦርነቱ የተካሄደበት ቦታ አንድ ትልቅ ከተማ የታቃጠለ እስኪመስል ነደደ። ኰሎኔል ቶሬሊኒ ቀን ሲጨልም ሸሽቶ ከምንዛሮ ምሽጉ ገባ። የቁልቋል በር ከበባ ቀጠለ።

መለቀቅ ከነበረባቸው ቦታዎች አንዱ ጐርጐራ ነበር። አርበኞች የጠላትን ሽሽት ለመግታት ከከተማይቱ ወደ ጐንደር የሚወስደውን የመኪና መንገድ ከእንግሊዝ የተሰጣቸውን ፈንጅ ቀበሩበት። መቶ አለቃ ሶርዚዮ የጥይት ድምፅ መስማት አይወድምና፤ ጦር አዝዞ የተቀበረውን ፈንጅ አስነሣ። አርበኞች ደግሞ ደሐና ከተባለው ቦታ አድፍጠው ጠብቀው፤ ፈንጂውን ያነሱትን ሃምሣ አለቃ ኖይቼንቲና ሌሎች 43 ወታደሮች ከነመቶ አለቃቸው ወዲያው ነሐሴ 29 ቀን 1933 ዓ.ም ጨረሱአቸው። ሃምሣ አለቃ ኖይቼንቲ በስም ተለይቶ በታሪክ መጠቀስ ያለበት ሰው ነው። ከጐጃምና ከጐንደር የሚማረኩትን አርበኞች የፊጥኝ እያሠረ ከነነፍሳቸው ጣና ባህር የሚጨምር ጨካኝ ነበር።

ጐርጐራን የማስለቀቁ ትግል ቀጠለ። ጣልያንም በበኩሉ አካባቢውን በፈንጂ አጥሮ ተቀመጠ። ፈንጂው እርስበርሱ በሲባጐ የተሳሠረ ነበረ። አደገኛ ስለሆነ፣ ደግሞም በጠላት ስለሚጠበቅ ፈንጂውን መፍታት አልተቻለም። ስለዚህ የእንግሊዙ ጦር አዛዥ ሻምበል ፔናሪክ ዘዴ ፈጠረ። ብቼኝ በሚባለው



ሜዳና በአካባቢው ያሉትን የዱር አራዊት አስከብቦ ወደ ጐርጐራ መራቸው። ከምሽጉ አቅራቢያ እንዲያድሩ አድርጐ ሌሊት ሲተኙ በአጠገባቸው ብዙ እሳት በማንደድ አስበረገጋቸው። ሲደነብሩ ሲባጐውን ስለበጣጠሱት ቦምቡ ሁሉ ፈነዳ። እነሱንም ጨረሳቸው። የቦምቡ አጥር ከተሰበረ በኋላ ጦርነቱ ቀጠለ። የጣልያኑ ጦር አዛዥ ያቀረበው የእርቅ ሃሳብ የማታለያ መሆኑ በአርበኞች ዘንድ ስለተደረሰበት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። የእሱ ሃሳብ የጐንደሩ ሁኔታ እስኪታወቅ ለመቆየት ነበር። አርበኛው በአካባቢው የነበሩትን መንደሮች ተቆጣጠረ። ጣልያንም መግቢያ መውጫ ሲያጣ ጠቃሚ ዕቃዎችንና የጦር መሣሪያዎችን ጣና ባህር ጨምሮ ተማረከ።

በጐንደር ክፍለ ሀገር ከተካሄዱት ጠንካራ ጦርነቶች አንዱ የውልክፌትን ምሽግ ለማስለቀቅ የተካሄደ ነበር። የተለየ ባህርይ ስለነበረው ለብቻው ተነጥሎ ቢታይ ይሻላል።

ጣልያን ከሚያዝያ 5 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ በተካሄደበት ጥቃት ተሸንፎ ዳባትን ከለቀቀ በኋላ፤ ውልክፌት በተባለው ተራራ ላይ የነበረውን ምሽግ አጠናከረ። ተራራው ስምንት ሺህ ጫማ የሚረዝምና ከባድ ቅዝቃዜ ያለበት ነበረ። ዳገቱ ቀጥ ብሎ የቆመ ከመሆኑ ጋር ሸርተቴ አፈር የነበረበትና ኮረኮንች ነው። ጣልያን ከባድ ጦር ከበቂ መሣሪያ ጋር አስቀምጦአል። ባንዳቹም እስከ መጨረሻው ለመከላከል ተዘጋጅተው ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ ጣልያን መግቢያውንና መተላለፊያውን ሁሉ ፈንጅ ቀብሮበት ነበር። ስለዚህ ነፃ አውጭው ጦር ይህንን ሁኔታ አልፎ ምሽጉን ለመያዝ ከባድ ችግር ወደቀበት።

የውልክፌትን ምሽግ እንዲሰብር የተመደበው ጦር አዛዥ ሪንግሮስ የተባለ ሻለቃ ነበር። እሱም ችሎታ ስለነበረው ከኢጣልያ እየከዱ ለሀገራችን እንዋጋለን ያሉትን ባንዶች ተቀበሎና ሌሎችንም አስከድቶ፤ የሪንግሮስ ኃይል የተባለ ቡድን አቋቁሞ ከእንግሊዝ ከተመደበለት ጦር ጋር አስተባብሮ ይመራ ጀመር። በኢትዮጵያ ወገን ደግሞ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ኃላፊ ሆነው የሀገሩን አርበኛ አስተባበሩ። የትግራይ አርበኛ በደጃዝማች ገብረሕይወት መሸሻ መሪነት ደረሰ።

ከዚሁ ዓይነት ዝግጅት በኋላ የውልክፌትን ምሽግ የማጥቃቱ ሥራ ተጀመረ። በሚያዝያ ወር ብቻ ስደስት ጊዜ ምሽጉን ለማጥቃት ታላላቅ ውጊያ ነበር፤ ግን ምሽጉ አልተበገረም። ቢሆንም ደባርቅ የነበረውን ምሽግ መስበር ተቻለ። ሌላው አርበኛ ሁሉ ተባብሮ እንደ ትግራይ አርበኛ ተልቡ ተዋግቶ ቢሆን ኖሮ፤ የውልክፌት ምሽግ በመጀመሪያው ዙር ውጊያ ተሰብሮ ጦርነቱ ያበቃና በተከታታይ ውጊያ ያለቀው ሠራዊት ይድን ነበር። ነገር ግን አብዛኛው አርበኛ ከተዋጊነት ይልቅ ተመልካችነት ስላበዛ፤ የውልክፌትን ምሽግ ለመያዝ የተደረገው ሙከራ ተወላከፈ። ከትግራይ አርበኛ ብዙ ሞተ። ሰማንያ አምስት ሰው ቆሰለ። —

የአርበኛው ቸልተኝነት በእንግሊዞች ዘንድ ቅሬታ ፈጠረ። ተመክረና ተከታታይ ማጥቃት የሚደረግበት ዕቅድ ተዘጋጀ። ጣልያንም ስመ ጥር ባንዶቹን ለውጊያ አቀረበ። ሁለተኛው የውልክፌት ጦርነት ተካሄደ። ለባንዶቹ ጣልያን ብዙ ቦምብ እንደ አሸከማቸው ታውቆ ነበር። አርበኛው እያነጣጠረ ሲመታው እየፈነዳ ባንዶቹን ራሳቸውን ፈጃቸው። ጦርነቱ ከጥዋቱ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ቆይቶ ምንም ፋይዳ ሳያገኝ የሁለቱም ወገን ጦር በየፊናው ተበተነ።

እጁን እንዲሰጥ ጥያቄ ቢቀርብለት፤ የጣልያኑ የጦር አዛዥ ኰሎኔል ጐኔላ ለዚህ ጉዳይ የሚጠየቁት ጄነራል ናዚ ናቸው አለ። ከጣልያን ከድተው ከኢትዮጵያ ጦር ጋር የተደባለቁት የቀድሞ ባንዶች፤ ጓደኞቻቸውን በስም እየጠሩ ምክር በመስጠት በአንድ ቀን አምስት መቶ ሰው አስከዱ። ተከትሎም የውልክፌት ምሽግ ከደብባሕር በመድፍ እንዲደበደብ ተደረገ። ነገር ግን የጣልያን ጦር ጉድጓድ ቆፍሮ ከምድር ውስጥ ገብቶ ነበርና እምብዛም አልተጐዳም። ለሦስተኛ ጊዜ ምሽጉን የመስበር ሙከራ ተደረገ። ሆኖም አካባቢው በፈንጂ ታጥሮ ስለነበር መቅረብ አልተቻለም። ጥቂት በመጐንተል የጠላት ጦር ከምሽጉ እንዲወጣ ተደረገ። ከአውላላ ሜዳ ላይ የእጅ ቦምብ ውርዋሮ ተያዘ። ጦርነቱ በሌላ ጊዜ ከተደረጉ ውጊያዎች የተለየ ባሕርይ አሳየ። ለምሣሌ አቶ ደሳለኝ የተባለ አንድ አርበኛና አንድ ባንዳ፤ አንድ የእጅ ቦምብ እንደኳስ እየተቀባበሉ እርስ በርሳቸው ተወራወሩ። እያንዳንዳቸው ሰባት ሰባት ጊዜ ከወረወሩት በኋላ፤ ቦምቡ በባንዳው ላይ ስለአረፈ ወደ ሰማይ አጉኖ ከአንድ ቁጥቋጦ ላይ ሰቀለው። እንግሊዞች እጅግ ተደነቁ። እንዲህም ተደርጐ ምንም ውጤት ሳያገኝ ቀረ። ብዙ አርበኞች ወደቁ።

አራተኛ ሙከራ እንዲደረግ ተወሰነና፤ ግንቦት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ቆልቶ በላ በተባለው ቦታ ከነበረው ምሽግ ላይ ሌሊት አርበኞች አደጋ ጣሉ። አቶ በራሪ ጎላ የተባለ አርበኛ በመንገዱ ላይ ጠምዶበት የነበረው ቦምብ፤ ለዕርዳታ በካሚዮን የመጡትን አሥራ አምስት ጣልያኖች ፈጃቸው። ውጊያው ሞቅ ደመቅ ያለ ነበር። ያም ሆኖ አርበኞች ከጠላት እርድ ውስጥ እየገቡ ጉዳት ከማድረሳቸው በስተቀር ሌላ ውጤት አልተገኘም። የሻለቃ ሪንግሮስ ኃይል ግንቦት 15 ቀን ያደረገውም ሙከራ ውጤት አላስገኘም። በትግሉ አሥራ አራት ያህል ታዋቂ አርበኞች ወደቁ።

ለአምስተኛ ጊዜ ውልክፌትን ለመያዝ ተሞከረ። አርበኛው ጥቂት ዕረፍት ከአደረገ በኋላ፤ ሰኔ 15 ቀን 1933 ዓ.ም ከሌሊቱ በ10 ሰዓት በምሽጉ ላይ አደጋ ጣለ። ጠንካራ ውጊያ ቢካሄድም የጠላት ጦር አልተበገረም። የሞተውን የቆሰለውን እየተራመደ ወደፊት ከማለት አልተመለሰም። ከጣልያን ከድተው አርበኛውን በማስተባበር ያዋጉ የነበሩት ደጃዝማች አያሌው ብሩ ቆስለው ተማረኩ። ጣልያን ለፋከራ በጀው። በሰው ሽክም የቀረበው መድፍ ተማረከ። ሁለት ሀገር ወዳድ ወጣቶች በሁለት አጋሰስ ጥይትና ቦምብ ጭነው



ለኢትዮጵያ ጦር ሊያቀብሉ ሲመጡ ጠላት ስለደረሰባቸው፤ የተጫነውን ቦምብ በማፈንዳት ከመሣሪያው ጋር እራሳቸውን አጠፉ። በጦርነቱ ሠላሳ ስምንት ሰው ሞተ። ሌላም ብዙ ቆሰለ። ሻለቃ ሪንግሮስ ጦሩን ይዞ ወቅን ወደ ተባለው ቦታ አፈገፈገ። ከዚያም ወደ ዘሪማ ወረደ።

ሻለቃ ሪንግሮስ ወደ አሥመራ ሄዶ ምክር ከተደረገ በኋላ፤ በአንድ ኰሎኔል የሚመራ አንድ ሺህ የሕንድ ወታደር የውልክፌትን ምሽግ እንዲሰብር ተላከ። ይህንን አስቸጋሪ ምሽግ ለማጥቃት ለስድስተኛ ጊዜ ሙከራ ተደረገ። ባንዳው ሕንዶችን ባደናገረ ሁኔታ በርትቶ ለጣልያን ተዋጋ። ሁለት ወንድሞቻቸውን ስለአቆሰሉባቸው ተናደው የሕንድ ወታደሮች በግሥጋሤ ደርሰው ሆድ ሆዳቸውን በሣንጃ በመውጋት እያፍተለተሉ በአየር ላይ ስለአንጠለጠሉአቸው ባንዶች ደነገጡ። የጦር አዛዣቸው በቦምብ ተመትቶ ስለሞተ ሕንዶች ደነገጡ። ቢሆንም በቶሎ አንሠራርተው የጠላትን ወታደር በመትረየስ አረፈረፉት። ምንም ውጤት ሳይገኝ ጀምበር ጠለቀች። ቢሆንም ብዙ ምርኮ ተገኘ። ሕንዶች በዚሁ ጦርነት በቃቸውና ወደ አሥመራ ተመለሱ። አርበኛው በየቀኑ መሠራጐዱን ቀጠለ።

ለሰባተኛው ዙር ጦርነት በአርበኞች ዘንድ ዝግጅት ሲደረግ ባንዳ ልቡ ወረደ። እስከ ዛሬ የምንዋጋው ከጥቁር ጋር ነበር፤ አሁን ግን የነጭ ጦር ስለመጣ በተራቸው ነጮች ይዋጉ ብሎ አደመ። ኰሎኔል ጐኔላ ጣልያናውንን ማሰለፍ ግድ ሆነበት። እሱ ራሱ አዝማች ሆኖ ቀረበ። አርበኞች እጁን በጥይት ስለሰበሩት ሽሽቱን ለቀቀው። ብዙ ጣልያኖች ቆሰሉ፤ ሌሎች ብዙ ተማረኩ። ጤናማው ምርኮኛ ቁስለኛውን እየተሸከመ በዛ ወደተባለው የኢትዮጵያ የጦር ሠፈር ወሰደ።

እንደገናም የስምንተኛው ዙር ጦርነት ተያዘ። ጣልያን ጫንቃ ከተባለው ቦታ ሆኖ ሌባ መውጫ የነበረውን የኢትዮጵያን ጦር ይጠባበቅ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ነሐሴ 18 ቀን 1933 ዓ.ም የተጠመደውን ቦምብ ሳይነካ በብልሀት አልፎ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አደጋ ጣለ። ጥይት ሳይተኩስ በእጅ ቦምብ ብቻ ተከሳከሰ። የጣልያን ጦር እጅን ሰጠ። ስድስት ጣልያኖች ሲሞቱ አንድ መቶ አምስት ተማረኩ። ከኢትዮጵያ ወገን ሠላሳ አንድ ሰው ወደቀ። ይህም ሁሉ ሆኖ የውልክፌት ምሽግ አልተነካም።

ዘጠነኛው ዙር ጦርነት ቀጠለ። የኢትዮጵያ ጦር ጫንቃ የተባለውን ቦታ ከያዘ በኋላ ወደ ዋናው ምሽግ ተጠጋ። ጣልያንም በበኩሉ የማጥቃቱን እርምጃ ለመግታት ነሐሴ 25 ቀን አደጋ ጣለ። ከድቼ ከርስዎ ሰው ልደባለቅ ነው በሚል ምክንያት ተጠግቶ፤ አንድ ባንዳ ቀኛዝማች ጣሰው የተባሉትን ጀግና በጥይት ገደላቸው። አገዳደሉ የክህደት ክህደት ነበርና አሟሟታቸው ጓደኞቻቸውን አሰቀቀ። ይልቁንም ለሻለቃ ሪንግሮስ የኰሎኔልነት ማዕረግ ሲሰጥ ለእሳቸውም ከእንግሊዝ መንግሥት ኒሻን አብሮ ደርሶ ነበርና፤

በአንገታቸው ማጥለቅ ቀርቶ በዓይናቸው ሳያዩት መሞታቸው እንግሊዞችን ጭምር አሳዘነ።

ሁኔታዎች በእንዲህ እንደ አሉ የውልክፈትን ምሽግ የሚይዝ በጀነራል የሚመራ ሌላ  የኬንያ ጦር መታዘዙ ተሰማ። ይህ ደግሞ አዲስ ሹመት አግኝተው የተደሰቱትን ኰሎኔል ሪንግሮስን አስቆጣ። ድካማቸውን መና የሚያስቀርባቸው ሆነ። ስለዚህ በወታደሮቻቸው መካከል ቅስቀሳ አካሄደ ውልክፈትን መያዝ ወይም ሞት አሰኙአቸው። ምሽጉን ለመያዝ በሥልት የተቀነባበረ ሙከራ አደረጉ። ከበሩ ተባባሪዎች ውስጥ መሪ አዘጋጁ። ሁለት ዘበኞች ሌሊት ወደ ተራራው ጫፍ ያለ አንዳች ኮሽታ ኰሎኔሉ ራሳቸው የነበሩበትን ቡድን አወጡ። አብረዋቸው የነበሩት 12000 ወታደሮች በሰላም በሩን አለፉ። የመዋጊያ ድንጋዮቻቸውን በየግንባራቸው ኰለኰሉ። ሲነጋ ምሽጉ ከአጠገባቸው መሆኑን አዩ። ጣልያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ይመላለሱ ነበር። ኢትዮጵያውያን ሰንደቅ ዓላማቸውን ከፍ አድርገው በብዙ ቦታ አውለበለቡ።

ጣልያን ይህንን ሲያይ ተኩስ ከፈተ። ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ተዋጉ። እያንዳንዱ ሹም ቁልቁላውን በያለበት በረጅሙ አስነፋ። ድብልቅልቁ ወጣ። ኰሎኔል ጉኔላ እጅ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነ። በኢትዮጵያ ወገን በጸሐፊ ትዕዛዝ ኃይሌ ወልደ ሩፊ የሚመራ ቡድን በአለበት ስብሰባ ንግግር ተደርጎ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። በስምምነቱ መሠረት ኰሎኔል ጉኔላ መስከረም 18 ቀን 1934 ዓ.ም 7,655 ሰው እንደያዘ እጁን ሰጠ። መሣሪያውን አስረክቦ ዕለቱን ወደ ደብ ባህር ወረደ። ከዚያም ነጩ ወታደር 250 በሚሆን ካሚዮን ተጉዞ፤ አሥመራ ባልደሴራ ከሚባለው የጦር እሥር ቤት ታጐረ። የኰሎኔል ሪንግሮስ አመራር በመጨረሻ ግቡን መታ። ምስጋና ይገባቸዋል።

የውልክፈትን ምሽግ ለመያዝ በተደረገው ተጋድሎ ኢትዮጵያውያን ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ነገር ግን የሚያሳፍርም ነገር ታይቶባቸዋል። እንደ ወትሮአቸው ከልብ ተዋግተው ቢሆን ኖሮ በመጀመሪያው ቀን ውጊያ ምሽጉ ይያዝ ነበር። ቢበዛም ከሁለት ወይም ከሦስት ቀን አያልፍም ነበር። በገዛ አረምዋ እባብ ይዛ አስፈራራች እንዳሉ፤ ኢትዮጵያውያን በዚያች ወሣኝ ቀን ችላ አሉ። ይህም በእንግሊዞች ዘንድ ከትዝብት ላይ ጣላቸው። ጦርነቱም የስድስት ወር ጊዜ እንዲወስድና የዘጠኝ ዙር ግጥሚያ እንዲጠይቅ ዕድል ሰጠው። የብዙ ሰው ደም ፈሰሰ።

ሌላም ከጉድ የሚቆጠር ነገር ነበር። ያንን ያህል መሥዋዕት ተከፍሎ 7,655 የጠላት ወታደሮች ሲማረኩ፤ 21.6 በመቶው ኢትዮጵያውያን ሆነው ተገኙ። እነዚህ እስከ ውልክፈት ምሽግ የመጨረሻ ሕቅታ ድረስ በክህደት ፀንተው ከጠላት ጐን በመቆም የተዋጉ በመሆናቸው፤ ለፍርድ ቀርበው መቀጣት ሲገባቸው ተግሳጽ እንኳን ሳያገኛቸው ቀሩ። ይህም የማይበቃ ሆኖ



የተለየ ጥበቃና እንክብካቤ ተደረገላቸው። ባለደሞቻቸው እንዳያጠቁአቸው በመኪና እስከ አድዋ ከተማ ተወስደው በነፃ ተለቀቁ። ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው ገብተው መንግሥት እንደገና ከተቋቋመ ከአምስት ወር በኋላ እንደዚህ ሕግ መረገጡ ሳያስተዛዝብ አልቀረም።

ቀጥሎ መለቀቅ የነበረበት የጀንዳ ምሽግ ነበር። በጐንደር የሚካሄደውን ጦርነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ከጐጃም የተላከው የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ጦር በደንገል በር አድርጎ በግስጋሴ ደልጊ ደረሰ። ከዚያም በደንቢያ በኩል አድርጎ ጀብጀብና ወንበርጼን የተባሉትን ቦታዎች ጥጋት ያዘ። ዝግጅት ሲያደርግ ሰንብቶ መስከረም 27 ቀን 1934 ዓ.ም ሌሊት በምሽጉ ላይ አደጋ ጣለ። ኮሉሪኒ የተባለው የጣልያን መኰንን በጀግንነት ተከላከለ። የኢትዮጵያ ጦር አጠቃ። አሥር አለቃ ዘለቀ ጉየ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጎ በመያዝ ቀጥ ብሎ ቆመ። የመትረየስ ጥይት በዚያው እንደ ዝናብ ሲወርድ በመጨረሻም ሲመታ፤ ምንም ሳይወዛወዝ ሰንደቅ ዓላማውን ቀጥ አድርጎ እንደያዘ ተቀመጠ። የጠበቀ ጦርነት ተካሄዶ ኮሉሪኒ ተማረከ። ከዚያ በኋላ ምርኮን መሰብሰብና ምርኮኛ መንዳት ሆነ።

ኮሉሪኒን ለመርዳት ከጃንጓ የመጣው ፈረስና ጦር ደረሰና አዲስ ጦርነት ተከፈተ። ሙሉ ቀን ሲዋጋ የዋለው የኢትጵያ ጦር ተዳክሞ ነበር። ቢሆንም በብርታት ተከላከለ። ሻምበል ታቲ የተባለ የእንግሊዝ መኰንን በጦርነቱ ሞቶ ነበርና፤ የእሱ ሬሣ የነበረበትን ቦታ የምትፈልግ አይሮፕላን ስለደረሰች የጠላት ጦር ደንግጦ ሽሽቱን ያዘ።

ጣልያንን ከየምሽጐቹ እየነቀሉ የማባረሩ ሥራ ቀጠለ። የኢትዮጵያ ጦር ጃንጓ ላይ የነበረውን ምሽግ ጥቅምት 3 ቀን 1934 ዓ.ም አጠቃ። ደንዲያ፣ ጉራምባ ላይ ተጋጠሙ። የጠላት ጦር ከሦስት ተከፍሎ በፈረስ መጣ። በላይ በኩል በደልኮ የተሻገረው ጦር ደህና አድርጎ ደበደበው። ተጫዋች በሚናህ ተብሎ የጨበጣ ውጊያ ተካሄደ። የጣልያን ጦር አዛዥ ወገጭ ከወንዙ ላይ ተገደለ። ምክትሉም ስለተደገመ ከሞት የተረፈው የጠላት ጦር ሽሽቱን ቀጠለ። ከጣልያን ወገን ሠላሳ አራት ሰው ሞተ። ሰባ ስድስት ቆሰለ፣ ስድሣ ተማረከ። ከኢትዮጵያ ወገን የሞተውም የቆሰለውም ጥቂት ነበር።

የኢትዮጵያ ጦር ድል ስለሸተተው እርምጃውን አፋጠነ። የጣልያንን ጦር ከጃንጓ አባረረ። ከዚያም በመከታተል በሰቀለት፣ በክልል፣ በሩፋኤል፣ በቆላ ድባ፣ በማርያም ደብር፣ በደርስጌ መሽጐ የነበረውን አንድ በአንድ እየወጋ ድል በማድረግ አስወጣው።

በዙሪያዋ የነበሩት ምሽጐች ሁሉ ከተለቀቁ በኋላ፤ የጐንደርን ከተማ ነፃ የማውጣቱ ዕቅድ ተዘረጋ። ከከተማይቱ አቅራቢያ ባሉት ተራሮች ላይ የነበሩት ምሽጐችም አንድ በአንድ በመደብደብ መለቀቅ ነበረባቸው። የቁልቋል በር መያዝ ወደ ጐንደር ከተማ ለመዝለቅ በር ከፋች ሆነ። ይህንን ምሽግ

ለመደምሰስ የመጨረሻው እንቅስቃሴ ኅዳር 5 ቀን 1934 ዓ.ም ተጀመረ። አርበኛና ስደተኛው ከእንግሊዝ ጦር ጋር በመተባበር በአራት በር ከበበ። አድፍጦ መጠበቅ ሲሰለችው በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተሥላሴ በላይነህ የሚራው ጦር ሰብሮ ለመግባት ሞከረ። በምሽጉ ዙሪያ የታጠረው ፈንጂ ፈነዳና ከቆሰለው በስተቀር ከሁለት መቶ በላይ ሰው አለቀ። ጥቂት እረፍት ከተደረገ በኋላ ኅዳር 12 ቀን ጦርነቱ እንደገና ቀጠለ። መነዛነዝ ሆነ። ይህ የሰለቻቸው ሦስት የእንግሊዝ ወጣት ወታደሮች በምቡ የተጠመደበትን ሲባጐ በመቀስ ቆርጠው ሲገቡ ጣልያን በመትረየስ ጨረሳቸው። ረዳቶቹ ምን ያህል መስዋዕትነት እየከፈሉ እንደሆነ ሲያይ፣ አርበኛውና ስደተኛው በያለበት ሥራውን ቀጠለ። የእንግሊዝ መድፎች ምሽጉን ደህና አድርገው ቀጠቀጡት። በአምስት ሰዓት በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተሥላሴ የሚመራው ጦር ፍርቋ በር የነበረውን ምሽግ ያዘ። በስድስት ሰዓት አንድ የእንግሊዝ ታንክ ወደ ምሽጉ ለመግባት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ። በዘጠኝ ሰዓት ሌላ ታንክ መጥቶ እያባረረ ከምሽጉ ገባ። ኰሎኔል አጉሊኒ ነጭ ባንዲራ አሳይቶ እጁን ሰጠ።

ጣልያን የቁልቋል በርን ምሽግ ከለቀቀ ቀሪ ፍልሚያው ለጐንደር ከተማ ሆነ። የኢትዮጵያ ጦር እርምጃ በርምጃ ቦታ በማስለቀቅ ከበባውን አጠናከረ። ወታደርና መሣሪያ፣ ትጥቅና ስንቅ እንደ ልብ ለማቅረብ ጣልያን የሰበራቸውን ድልድዮችና ያበላሻቸውን መንገዶች መልሶ መሥራት አስፈለገ። ከውልክፊት ወደ ጐንደር ከተማ የሚወስድ መንገድ የተሰበረው ገደል፣ በበርሜል አፈር እየተሞላ እንዲደረደርበት ተደርጐ ተመልሶ ተሠራ። መድፎች ወጥተው በምሥጢር ተጠመዱ። ጐንደር ዙሪያ የነበሩት 29 የጣልያን አይሮፕላኖች ተደብድበው ወደሙ። በዚህ ሁኔታ ጄነራል ናዚ ከጀርመን ዕርዳታ የሚደርስለት ለማስመሰል የሚያደርገው ሙከራ ተበላሸበት። እንግሊዞች ዋናውን መንገድ በመተው ከአምባ ጊዮርጊስ በደንቀዝ በኩል አዲስ መንገድ እስከ ግራኝ በር ድረስ ከፈቱ።

የኃይል ድልድል ተሠራ። ልዑል አልጋወራሽ ኃይለሥላሴ ከአዲስ አበባ በደሴ፣ በአድዋና በአክሱም ዞረው ደርሰው ነበርና የአምባ ጊዮርጊስን በር ያዙ። ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደ ገብርኤልና ጄነራል ፎክስ በአዘዞ ተሰለፉ። በትክል ድንጋይና በምባሻ ሽፈርድ እና ቀኛዝማች ጣሹ እንግዳ ተመደቡ። ከወርገምበጭ በድብ በኩል አድርገው ደጃዝማች ብሩ ቃሲምና ሻምበል ካንፑል ተሠማሩ። ከአደባ በድፍጫ በኩል ደጃዝማች ሐጐስ ተሰማና ሻምበል ማክሊይን ተሰለፉ። ከጠዳ በፊንጠር ፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተ ሥላሴ በላይነህና ሻምበል ፒልክቶ ተጠጉ። ከስቅለት በልይታ ስምንት ደጃዝማቾች ሠራዊታቸውን ይዘው ተሰለፉ። ከኋላ አገር በቁስቋም በር ሦስት ደጃዝማቾች ቆሙ። የኢትዮጵያ ጦር የሚመራው በፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደገብርኤልና በጄነራል ፎክስ ነበር። ጥንቃቄው የጐንደር ታሪካዊ ቅርሶች በጦርነቱ እንዳይጐዱ ብቻ ነው። የድሉ ጉዳይ አሳሳቢ አይደለም።



ጣልያንም በበኩሉ ለመጨረሻ ፍልሚያ ተዘጋጀ። ከጐጃም የወጣውን፣ ከወሎ የተሻገረውንና በጐንደር የነበረውን ጦር በሞላ አሰለፈ። ባንዳ ከግንባር ተሰለፈ። ከኤርትራና ከሶማሊያ የመጣው በማሕል ተመድቦ ነጩ ከውስጥ ሆነ። ሁሉም በቂ ምሽግ ነበረው። ምግብ ከገጠር እንዳይገባለት በመደረጉ ቢደክምም፣ ጦሩ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነበር።

ጊዜው በጣልያን ከባድ የፖለቲካ ደመና ያንዣበበት ነበር። የሰሜን አፍሪካው ጦርነት በጦር ኃደኞቹ አሸናፊነት ወደ መጠናቀቅ ተቃርቧአል። በኢጣልያ አገር ታላቅ የፖለቲካ ማዕበል ተነስቶአል። ከሮም የሚሰጥ አመራር፣ ከበርሊን የሚደርስ ዕርዳታ አልነበረም። የሰሜን አፍሪካ ጦርነት በእንግሊዞች አሸናፊነት እየተጠናቀቀ ነው። ሊቢያ የነበረው የጣልያን ጦር ድምጥማጡ ጠፍቶአል። ባንዳ ልብ ስለወረደው የሚያስላስለው ነፍሱን የሚያድንበትን መንገድ ብቻ ነው። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ገብተው አመራር ከያዙ ሰባተኛ ወራቸው ነው። አስተዳደራቸውን አጠናክረዋል። ስለዚህ የጐንደሩ ፍልሚያ ለኢጣልያ በአፍሪካ ምድር የመጨረሻዋ እስትንፋስ ናት።

ኅዳር 18 ቀን 1934 ዓ.ም ከጥዋቱ በአሥራ ሁለት ሰዓት ተኩስ ተጀመረ። መድፎች ከየአሉበት አገሱ። ተከታትለውም መትረየሶች አስካኩ። ጠመንጃዎች ተንጣጡ። ውጤቶች መታየት ጀመሩ። እምቦዘና አጨናቅር የነበሩትን የጣልያን መድፎች፣ ወር ገምቦጭና አይባ ላይ የነበሩት የእንግሊዝ መድፎች ባፍባፋቸው ጥይት እየቀረቀሩ ፀጥ አሰኙአቸው። ብላጅግ ላይ የነበረው የጣልያን መድፍ ተካሾች ጥለውት ሄዱ። እንባ ማልዱባ ላይ የነበረው ቢሠራም፣ ብቻውን ውጤት ማስገኘት ሳይችል ቀረ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ከዳባት እየተነሱ በጐንደር ከተማ አካባቢ የነበሩ የጣልያን የጦር ሠፈሮችን አቃጠሉ። የኢትዮጵያ ጦር ጐንደር ከተማ ለመግባት በየፊናው ተሽቀዳደመ። የእንግሊዝ ታንኮች ጣልያን ሠብሮት በነበረው የመገጭ ድልድይ ላይ መሸጋገሪያ ጥለው በመሻገር፣ የአዘዞን በር በመትረየስ ከፍተው ከጠዳ ወደ ጐንደር ገቡ።

የጣልያን ነጭ ወታደር /ሶልደቶ/ መንገዱን ይዞ ሲርመሰመስ፣ ታንኮች መተላለፊያ አጥተው ጥሩንባ እስከ መንፋት ደርሰው ነበር። ከከተማ በስተደቡብ የነበረው አርበኛ በፊንጠር አድርጐ፣ አዲስ ዓለምንና ፊት አቦን ከብቦ የነበረውን የጣልያን ጦር ሠብሮ፣ ከታንኮቹ ቀድሞ ጐንደር ገብቶ ምርኮ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ናዚ አደባባይ ኢየሱስ ነበር። የአርበኛውን አመጣጥ ሲያይ በፍጥነት ወደ መድኃኔዓለም ወጣና ነጭ ጨርቅ አሳይቶ የእጅ መረከቡ ሥራ ተጀመረ። አርበኛው ጉራያ ማስጫ ከግንቡ ሥር አደረ። የእንግሊዝ ታንክ ወደ አዘዞ ተመለሰ። ነገር ግን በምሥራቅ ወገን የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር በደፈጣ የነበረውን የጠላት ጦር በኃይል ወግቶ ,ከአስለቀቀው በኋላ፣ ወደ

ከተማይቱ ለመግባት ሲሞክር ተቀብሮ የነበረው ፀምብ ፈንድቶ ጉዳት አደረሰበት። እርምጃውንም አዘገየበት።

ኅዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም *ፊታውራሪ /ራስ/* ብሩ ወልደ ገብርኤል ከሜጀር ጄነራል ፎክስ ጋር ጐንደር ከተማ ገቡ። ባለህ እርጋ ተባለ። ረጋ። ናዚ አጁን በውል ለመስጠት ቢጠይቅ በጦር ኃይል ከተሸነፈ በኋላ ውል እንደማይገባለት ተነግሮት ያለ አንዳች ውል እጁን ሰጠ። በማግስቱ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን ኃይለሥላሴ ጐንደር ከተማ ገቡ።

በኢጣልያ አጥቂነት በወልወል መንደር ኅዳር 27 ቀን 1927 ዓ.ም የተከፈተው ጦርነት፤ ከስድስት ዓመት በኋላ ኅዳር 1934 ዓ.ም በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ። የጦርነት ፍፃሜ ያርገው።[4]

የኢጣልያን ጦር ከምሥራቅ አፍሪካ ጠራርጐ ለማስወጣት የተዘጋጀው ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ግቡን መታ። ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችል ለንጉሠ ነገሥቱ በጻፉት ደብዳቤ "...በፋሽስትና ናዚስት ወንጀለኞች ከሀገራቸው ወጥተው ከተሰደዱ መሪዎች የመጀመሪያው እርስዎ እንደነበሩ ሁሉ፤ አሁንም ወደ ሀገርዎ በመመለስ የመጀመሪያው በመሆንዎ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ፤ በእንግሊዝ ሕዝብና መንግሥት ስም ስገልጽልዎ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል" የሚል ሆነ።[5]

የኢጣልያን ጦር ከምሥራቅ አፍሪካ ለማስወጣት በተካሄደው ጦርነት የብዙ አገር ተወላጆች ተከፋይ ሆነዋል። ዋናውና አመራሩን የያዘው ጦር የእንግሊዝ ነው። በውስጡም የሕንድና የፓኪስታን፣ የደቡብ አፍሪካ ማለትም የናሚቢያ፣ የዙምባብዌ፣ የዛምቢያና የቦትስዋና ጭምር፤ ከምሥራቅ የኬንያ፣ የታንዛኒያና የኡጋንዳ፣ የሱዳን፣ የዛየርና የኰንጐ ብራዛቪል ሠራዊት ተዋግቶአል። እነዚህ ሁሉ ደማቸውን ለኢትዮጵያ ነፃነት አፍስሰዋል። ስለዚህ ከልብ እናመስግናቸዋለን።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሙሶሊኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 161-163።
2. Richard Greenfield, <u>*Ethiopia*</u>, pages 263-264.
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 362-364።
4. *ገሪማ ታፈረ*፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 266-294።
5. Winston Churchill, *The Grand Alliance*, p.90-92.



# ምዕራፍ ሃምሣ አምስት
# በጦርነቱ ውስጥ የእምነት ድርጅቶች ሚና

"ኢትዮጵያ ታበጽህ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።" በጦርነት ጊዜ የእምነት ድርጅቶች አቅዋም ወሣኝነት አለው። ይህ ጉዳይ በመጻሕፍት የተገለጸ፣ በታሪክ የሚነበብ፣ በአበው የሚነገር፣ ዕለት ዕለቱም የሚታይ ነው። ማስረጃ ሊቀርብበት፣ ክርክር ሊካሄድበት አይገባም። ከዚህ የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ መነሳት ያለበት ጥያቄ፤ "በኢትዮጵያና ኢጣልያ ጦርነት ጊዜ የእምነት ድርጅቶች አቅዋም እንደምን ነበር?" የሚለው ነው ። በየፈርጁ መመልከት ያስፈልጋል።

ሙሶሊኒ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም /ኦክቶበር 2 ቀን 1935/ ለኢጣልያ ሕዝብ ንግግር አደረገ። የንግግሩ ዓላማ የዓለም ማኅበር በመንግሥቱ ላይ ባደረገበት የኢኮኖሚ ጭቆና የኢጣልያንን ሕዝብ ቁጣ ለመቀስቀስ ነበር። ይህንን ንግግር ያደረገው በጄነራል ደቦኖ አዛዥነት 200,000 ወታደር ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ከአዘመተ በኋላ ነበር። ሊቀ ጳጳሱ አባ ፓየስ 11ኛ ከየጦር መሣሪያው ዓይነት ቀርበላቸው ቡራኬ ሰጡ።[1] በዓለም ላይ ካቶሊኮች በሙሉ የሊቀ ጳጳሱን ድርጊት በጸጥታ ተቀበሉ። አንድ ድምጽ ያሰማ የለም። ኢትዮጵያውያኑም እንኳን።

በአብዛኛው የካቶሊክ ተቆጣጣሪ የእንግሊዝ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ናት። ለወትሮ ይህች ቤተክርስቲያን ጉዳዮችን ተመራማሪ በሆነ አመለካከት ታያለች። ድምፅዋንም ያለ ይሉኝታ ታሰማለች። ይህ ዘወትር የሚታይ ነገር ስለሆነ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ አይሆንም። ነገር ግን በ1928 ዓ.ምቱ የጣልያን ወረራ ጊዜ አንዳች አላለችም። አንዳች አሳደረገችም። ቢሆንም እየቆጠቆጣት ሄደ። የእንግሊዝ የበላይ ምክር ቤት ሐውስ ኦፍ ሎርድስ ግንቦት 10 ቀን 1929 ዓ.ም /ሜይ 18 ቀን 1937/ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ተከራከረ። የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን መሪ የሆኑት የኮንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ፤ ለምክር ቤቱ ኢትዮጵያን በመደገፍ ንግግር አደረጉ። ኢትዮጵያ መሬትዋን ቀንሳ ለዕርቅ ልትሰጥ እንደማታስብ ጠቅሰው ተናገሩ። ምክር ቤቱም የጣልያንን አጥቂነት ተገንዝቦ ይዞታዋን ሳያውቅላት ቀረ።[2]

የአሜሪካን አብያተ ክርስቲያናት የተረጋገጠ አቅዋም አልነበራቸውም። እንደዚሁም እንደ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ። በጀርመን አገር የናዚ ተፅዕኖ ጠንክሮ ስለነበር አንዳች የማለት ዕድል አልነበራቸውም። የስካንድናቪያ አገሮች ማለትም የስዊድን፣ የኖርዌ፣ የዴንማርክና የፊንላንድ አብያተ ክርስቲያናት ዓለሙን በፀጥታ የሚመለከቱ እንጂ፤ እንደ ኢትዮጵያ ላለች ትንሽ አገር ብለው ከነገር አጣብቂኝ ውስጥ የመግባት ፍላጐት አልነበራቸውም።

የራሺያ ቤተክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊት በመሆንዋ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቀረቤታ አላት፡፡ በወቅቱ የኮሚኒዝም ተፅዕኖ ነበረባት፡፡ ቢሆንም መንግሥቱ የኢጣልያ ደጋፊ ስለአልነበረ ድምፅዋን ለማሰማት የሚከለክላት ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን ምንም ድምፅ አላሰማችም፡፡

የእስልምና እምነት የራሱ ጉዳይ እስከ አልሆነ ድረስ ከሌሎች ጉዳይ አይገባም፡፡ ስለዚህ ስለኢትዮጵያ መወረር ድምፁን የሚያሰማበት ሁኔታ አልነበረውም፡፡

በዓለም ዙሪያ የነበሩ የእምነት ድርጅቶች አቅዋም ከቃኘን በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ እንመለሳለን፡፡ በዘመኑ በሀገር የነበሩት እምነቶች ሦስት ነበሩ፡፡ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ ካቶሊክና እስላም፡፡ የፕሮቴስታንቶች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡ ካቶሊኮች ኢትዮጵያውያንም ጭምር ከወራሪዋ ከኢጣልያ ወገን ሆኑ፡፡ እስልምና ከጠላት ወገን የሚነዛውን የጥላቻ ማነሳሻ ፕሮፓጋንዳ ከመታገስ አልፎ በተከላካይነት የመቆም አቅም አልነበረውም፡፡ ስለዚህ ወራሪውን የመከላከል ዕድል ፈንታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሆነ፡፡ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በግብፅ ቤተክርስቲያን ሥር ነበረች፡፡ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም ግብፃዊ ነበሩ፡፡ ደግሞም ከግብፅ መንግሥት እምብዛም ተፅዕኖ አልነበረባትም፡፡ ድምፅዋን ማሰማት ትችልም ይገባትም ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳች አላደረገችም፡፡

አቡነ ማቴዎስ ከአፄ ምኒልክ ጋር አድዋ ድረስ ዘምተው፤ የጦርነቱ ዕለት በገበሬ ሠናይነት ቀድሰው፤ ከጦሩ ግንባር ላይ ታቦታቸውን ይዘው በመቆም አዋግተው ነበር፡፡ ከዚያም በፊት የነበሩ ግብፃውያን ጳጳሳት በጦር ጊዜ ከነገሥታቱ አይለዩም ነበር፡፡ ነገር ግን በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ እንዲህ አላደረጉም፡፡ ብቻ ከታህሣሥ 13 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሣምንት ጾም ጸሎት፣ ሀዘን እንዲደረግ፤ ታህሣሥ 8 ቀን 1928 ዓ.ም መልዕክት ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን አስተላለፉ፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን ግን ምህላውን እስከ ዘለቄታው ተያያዙት፡፡[3] እንደዚሁም ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ጥር 9 ቀን 1928 ዓ.ም ለጐጃም ሕዝብ መልእክት አስተላለፉ፡፡ ጉዳዩ ከጦር ሜዳ ከድተው ወደ ሀገራቸው ስለተመለሱት ስለ እነ ደጃዝማች ገሠሠ ነበር፡፡ ቃሉን ማጤን ደግ ስለሆነ ፍሬ ነገሩን እንጠቅሳለን፡፡

ደብዳቤው መንፈሳዊ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ "...የጣልያኖች ሃሳብ... የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በራሱ እያጣሉና እያፋጁ... ሰተት ብለው ገብተው ርስታችሁንና ገንዘባችሁን ላሽከርነት፣ ሴት ልጃችሁን ለግርድና ለማድረግ ነው..." ብሎ የወረራውን ዓላማ ያስረዳል፡፡ ከዚያም በማያያዝ የደጃች ገሠሠን ክህደት ያስረዳና፤ አገሩን ኢትዮጵያንና ንጉሠ ነገሥቱን የከዳውን ቢሞት ካህናት እንዳይፈቱት፣ በቤተ ክርስቲያንም እንዳይቀብሩት በታህሣሥ 8 ቀን



ያስተላለፉትን ውግዘት ይጠቅሳል፡፡ አያይዞም የርሱን ነገር እንዳይሰሙት፣ እንዳይከተሉት፣ እህል ውሃም እንዳይሰጡት፣ በቤታቸውም እንዳያሳድሩት ያዛል፡፡ ቀጥሎም መልእክቱ "ደጃች ገሠሠንና ሌላውንም እንደርሱ ያለውን ከሐዲ አትከተሉ፡፡ ጣልያኖችም ...በተንኮል የማታለልና የሐሰት ቃል እየጻፉ በአውሮፕላን ቢበትኑላችሁ አትመኑ...ከጥንታዊ ንጉሠ ነገሥታችሁ ኢጣልያ የሚሻል እንዳይመስላችሁ አስጠነቅቃችኂለሁ፡፡ ...ምክሬንና ቃሌን ባትሰሙ ግን እንደ አርዮስ አወግዛችኂላሁ፡፡ ረግሜያችኂለሁ" በማለት ቃሉን ይደመድማል፡፡ ነገር ግን ሊቀ ጳጳሱ ወደ ጦርነቱ ለመሄድ አልተንቀሳቀሱም፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም የፈረንጅ አማካሪ ከማግበስበስ እንደ እኚህ ያሉትን ዕኑዕ መንፈሳዊ አባት ይዘው መዝመት ፀጋ ያስገኝላቸው ነበር፡፡

በዚህ ዓይነት ቤተክርስቲያኒቱ ከውጭ ያለድጋፍ፣ ከሀገር ውስጥ ያለ ዕርዳታ ብቻዋን ቆመች፡፡ ከመንፈሳውያን አባቶች መካከል ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ/ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/፣ ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ ዘመቱ፡፡ በጦርነቱ ላይ ቆሙ፡፡

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ማለትም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ሰባት ሐዋርያዊ መልእክቶች አስተላለፉ፡፡ ከእነዚህ መልዕክቶች የመጀመሪያው ኅዳር 17 ቀን 1928 ዓ.ም ተላለፈ፡፡ እሱም ክርስቲያኖች እንደ ሰማዕታት ደማቸውን ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ እንዲያፈሱላት የሚጠይቅ ነበር፡፡ ደማቸውን የሚያፈሱት፣

1ኛ. ስለ ሃይማኖታቸው፣

2ኛ. ስለ ንጉሠ ነገሥታቸው፣

3ኛ. ስለ ሀገራቸው ነፃነት፣

4ኛ. ስለርስታቸው፣

5ኛ. ከራሳቸው ጀምሮ ስለወገናቸው፣ እንደሚሆን የሚያስገነዝብ ነበር፡፡ አያይዞም እነ ጌዴዮን፣ እነ ሳዶቅ፣ እነ ዮፍታሔ፣ እነ ሳምሶን፣ እነ ዳዊት፣ እነ ሣሙኤል ሌሎችም በሃይማኖታቸው ጸንተው በመዋጋታቸው ድል እንደ አገኙ፤ አነሱም በነፍስ በሥጋ ክብር እንደወረሱ የሚያስረዳ ነበር፡፡ በመጨረሻም "...ጣልያንን በግፍ ከያዘብን ርስታችን ለማባረር የማይረዳውን ሰው፤ ወደሱም ለመክዳት የሚመሳጠረውን ሁሉ...ካባቶቼ ከሐዋርያት ባገኘሁት ሥልጣን ገዝቻለሁ" በማለት ደመደሙ፡፡[4] ምዕመናን ይህንን ቃል ሰሙ፡፡ ምህላም ተያዘ፡፡ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌው ወደ ዘመቻው ሄዱ፡፡

በጥንቱ ሥርዓት የውጭ ወረራ በመጣ ጊዜ ካህናት ታቦተ ሕጉን ይዘው በግንባር ይቆማሉ፡፡ ነገር ግን በሀገር ውስጥ ለሚካሄድ የርስ በርስ ጦርነት ታቦት አይቆምም፡፡ ከልጁ ከአቤሴሎም ጋር ይዋጋ በነበረ ጊዜ ካህናቱ የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘው ወደ እሱ በመጡ ጊዜ ዳዊት "...በእግዚአብሔር ዓይን ሞገስ አግኝቼ እንደሆንሁ መልሶ እርሱንና ማደሪያውን ያሳየኛል፡፡ ነገር ግን አልወድህም ቢለኝ እነሆኝ ደስ የሚያሰኘውን ያድርግብኝ..." ብሎ

የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ መናሪያው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመልስ ሳደቅን አዘት ነበር።[5] ጦርነቱ ከጥፋት ወረራ ለመከላከል በመሆኑ በዚህ ሥርዓት መሠረት ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ እጨጌው ሦስት ታቦቶች ይዘው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ዘመቱ።

ወደ ማይጨው ጦርነት የዘመቱት ታቦቶች

ከተጉለት፣ የደብረ ዊዕ ድንበሮ /ግንባርም/ ቅድስት ማርያም፣

ከአዲስ አበባ፣ የአራዳ ደብረ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣

ከአዲስ አበባ፣ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ነበሩ። ከእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን አለቃውና አሥር ካህናት ዘመቱ። ጉዞው ታቦታቱ ታዝለው በእግር ነበር። በየዕለቱ ጥዋት ምህላ፣ ማታ የማስታኮት ፀሎት ይደረጋል። ታቦታተ ሕጉ በአደሩበት አካባቢ ከአለ ቤተክርስቲያን፣ ከሌለ በድንኳን ያድራሉ። በዕለተ ሰንበት እና በታቦቶቹ በዓላት ቀን ይቀደሳል።

ቀደም ብሎ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ንግግር ተደርጐ፣ አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በካይሮ ከተማ ተሹመው ስለነበር፣ የኢጣልያ ወረራ በተነሣ ጊዜ አንድ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስና አራት ኢትዮጵያውን ጳጳሳት ነበሩ። እነሱም፣

አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ፣

አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ፣

አቡነ ሚካኤል ኢትዮጵያዊ ጳጳስ፣

አቡነ ይስሐቅ ኢትዮጵያዋ ጳጳስ፣

አቡነ አብርሃም ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ነበሩ።[6]

ነገር ግን ከእነዚህ አምስት ሊቃነ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር በጦር ግንባር የቆሙ አቡነ ጴጥሮስ ብቻ ነበሩ። ሌሎች ጸጥ ብለው በየቤታቸው ተቀመጡ። ይህ ግብራቸው በተለይ ለኢትዮጵያኑ ጳጳሳት መንፈሳዊ አባትነታቸውን አረከሰው። የእያንዳንዱ ታሪክ በቦታው ላይ ተነገሮአል።

ከላይ ስማቸው የተዘረዘረው አራት ታቦታት እስከ ማይጨው ተጉዘው በጦርነቱ ግንባር ቆሙ። ከጦርነቱ ላይ ውለው ማታ ወደማደሪያቸው ተመልሰው ገቡ። ከዚያም ተጉዘው ከየቤታቸው በሰላም ገቡ። አንድም ካህን አልሞተም። ይህ ብቻ አይደለም። ሌላም ድንቃ ድንቅ ሥራ ታይቶአል። ኅዳር 27 ቀን 1928 ዓ.ም ደሴ ድንበሬ ማርያም ባለችበት ቦታ ከሚደርሰው ምሕላ ላይ ንጉሠ ነገሡቱ ተገኝተው ነበር። ታቦትዋ ያለችው ቀድሞ የጣልያን ቆንሲል ይኖርበት ከነበረው ቤት ነበር። ጣልያኖች በዚያች ዕለት ጥዋት 21 አይሮፕላኖች ልከው ቤቱንና አካባቢውን አስደበደቡ። ቅድስት ማርያም ባደረችበት ቤት ላይ ከሠላሣ ያላነሰ ቦምብ ወደቀ። በአካባቢው ደግሞ ሌላ ሰባ። በጸሎት ቤቱ ላይ የተጣሉት ቦምቦች እየተንከባለሉ ከመሬት ወደቁ። አንዳቸውም ሳይፈነዱ ቀሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ቦምቦቹን ከአንድ ቦታ አሰባስበው



ከላያቸው ቆመው እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ካህናቱንም የእናንተ ፀሎት እንደዚህ ያለ ድንቅ ሥራ ይሠራልና በርቱ ብለው አመሰገኑአቸው። በዚህ ቀን የጊዮርጊስና የገብርኤል ጽላቶች ደሴ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ውስጥ አድረው ስለነበር ከጸሎት ቤቱ አልነበሩም።[7]

በጦርነቱ ድል ለጣልያን እንደሚሆን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ምልክቶች ነበሩ። ለምሣሌ ቡልጋ ሙገሬ ዛለ የተባለ የመንግሥት ደን አለ። ከዚያ ደን ውስጥ የአምሃየስ ሽንጥ የሚባል መለሎ ረጅም ዛፍ ነበር። በዙሪያው ደግሞ ሌሎች ስድስት መለሎ ዛፎች ነበሩ። በዙሪያ ያሉት ስድስቱ በመካከል ከአለው ከዋና በውፍረትም በቁመትም ጥቂት ጥቂት ያንሱ ነበር። መጋቢት 21 ቀን ሰኞ በመንፈቀ ሌሊት እንደ መብረቅ ያለ ታላቅ ድምፅ ተሰማ። አካባቢው በድንጋጤ ከእንቅልፉ ተቀሰቀሰ። ድምፅ የተሰማው ዛፎች ሲወድቁ ኖሮአል። ስድስቱም ተሰባብረው ወድቀዋል። የተረፈ የለም። ሕዝቡ ይህንን ሲያይ አዘነ፣ ደነገጠ። በነጋታው መጋቢት 22 1928 ዓ.ም ማክሰኞ ንጉሠ ነገሥቱ በቆሙበት በማይጨው ጦር ግንባር ኢትዮጵያ ድል ሆነች።

ሙሶሊኒ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ ከፋፍሎ ለማጨራረስና ሀገሪቱን ለመግዛት የነበረውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በትሪፖሊ ከተማ በ1929 ዓ.ም አዋጅ አስነገረ። አዋጁም "የፋሽስት ኢጣልያ መንግሥት በሊቢያና በኢትዮጵያ ለሚኖሩ እስላሞች የሰላም ዋስትና ለመስጠት አስቦአል። ትክክለኛ ፍትሕና ብልጽግናም ለእስላሞች ያደርጋል። የነቢይ መሐመድንም ሕግ ያከብራል። ከዚያም በላይ ለመላው ዓለም እስላሞች ያለውን ሕግና መልካም አስተሳሰብ ሊገልጥ ይወዳል" የሚል ነበር። ከዚህም በስተቀር ብዙ የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ካህናት የወታደር ልብስ ለብሰው ከኢጣልያ ወታደር ጐን መቆማቸው ታውቆአል። ይህ ሁኔታ ሲታይ የሮም ካቶሊክ ካህናት መሣሪያ ጨብጠው ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን በመጨፍጨፍ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በማቃጠል ሥራ ተሳትፈዋል የሚያሰኝ አሳፋሪ የታሪክ ክስተት ነው።

ጣልያን አዲስ አበባ እንደ ገባ ንጉሠ ነገሡቱ ወደ አውሮፓ እንደሄዱ ሲሰማ ታላቁ ሥራ የዕርቅ ጉዳይ ሆነ። በሰውና ሰው፣ በአገርና አገር የነበረውን መቃቃር ለማብረድ ጥረት ተደረገ። በዚህ ረገድ ዋናውን ሚና የተጫወቱት ካህናት ነበሩ። መስቀል ይዘው በሽማግሌ የተያዘው እርቅ አስኪፈፀም ይቆማሉ። ራሳቸውም ከሽምግልና ውስጥ ይገባሉ። እምቢ ያለውን ወገን ቀሳውስትና መነኮሳት ይገዝታሉ። ጥፋቱን አምኖ ሲመለስ ደግሞ ፀሎት አድርገው ግዝታቸውን ይፈታሉ። እርቅ በተደረገ ቁጥር ጸሎት አድርገው ይባርካሉ።

የኢትዮጵያ አርበኞች አዲስ አበባን ለማስለቀቅ በዘመቱ ጊዜ፣ አቡነ ጴጥሮስ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ሠራዊት ጋር ተሰለፉ። በወታደሩና በእሳቸው መካከል ሁለት ልዩነቶች ነበሩ። ከእነዚያ ልዩነቶች አንደኛውና ዋነኛው፣

እሳቸው ቆራጥ ሠራዊቱ አመንቺ መሆኑ ነው:: በዚህ የተነሣ ሠራዊቱ ወደ ኋላው ተመልሶ እሳቸው ግን ወደፊታቸው ተራመዱ:: ሁለተኛው ልዩነት ሠራዊቱ የታጠቀው መሣሪያ፤ እሳቸው መስቀል መሆኑ ነበር:: ሰተት ብለው ጣልያን ከነበረበት ገቡ:: የጣልያንን ገዥነት ተቀብለው በሰላም እንዲኖሩ ቢጠየቁ አላደርገውም አሉ:: "...ለኢጣልያ የተገዛችሁ ውግዝ ሁኑ:: መሬትዋም አትገዛልህ:: ገዝቻለሁ..." ብለው ጣልያንን ራሱን ጭምር አወገዙ:: በኢጣልያውያን ዳኞች የተወሰነባቸውን የሞት ፅዋ ሐምሌ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ተቀበሉ:: ሬሳቸውም ወደ አልታወቀ ቦታ ተወስዶ ተቀበረ::

ሌላው ሰማዕት አቡነ ሚካኤል ነበሩ:: እሳቸውም ከአርበኛው ጋር ከጐሬ ከተማ በስተምሥራቅ በምትገኘው ሣምቤ ከምትባለው ቦታ በተደረገው ጦርነት ኅዳር 17 ቀን 1929 ዓ.ም ተያዙ:: ወደ ጐሬ ከተማ ተወስደው የጣልያንን መንግሥት ገዥነት አምነው በክብር እንዲኖሩ ቢጠየቁ፤ አላደርገውም በማለታቸው እንዲገደሉ ተወሰነባቸው:: እሳቸውም ለጣልያን እንዳይገዛ ሕዝቡን ገዝተው በጥይት ተደብድበው ከቆሻሻ ቦታ ተቀበሩ::[8]

ግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ የጣልያንን አገዛዝ አልቀበልም፣ ከሮም ካቶሊክ ጋር አልስማማም ብለው አገራቸው ገቡ:: ይህ የእምነት ልጆቻቸውን ከመከራ ላይ ጥለው መሄዳቸው፤ ከነፃነት በኋላ የግብፅን ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ነቀለ:: አባ አብርሃም የጣልያንን አገዛዝ ተቀብለው፤ ታህሣሥ 20 ቀን 1929 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ:: የግብጹ ፓትርያርክ የአቡነ ዮሐንስ 10ኛ ተግሳጽ አልመለሳቸውም:: አባ ይስሐቅ ጣልያንን አልቀበልም አሉ:: ግን አላወገዙም:: ስለዚህ እሥራት እንጂ ሞት አልተፈረደባቸውም:: አባ አብርሃም ሲሞቱ የአዲስ ዓለሙ መምህር ሐዲስ እሹቴ ሊቀ ብፁዓን አባ ዮሐንስ ተብለው መስከረም 7 ቀን 1932 ዓ.ም በቦታቸው ተተኩ::[9]

አርበኞች በእምነት ጸኑ:: ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ጊዜና ቦታ እንለውጥ ብለው የጦር ጓደኞቻቸው ያቀረቡላቸውን ሃሳብ፤ "የማይጨውም የተሸነፍነው እንዲህ ተብሎ ነው" በማለት ሳይቀበሉት ቀሩ:: በዚያቹ በመረጡአት ቦታና ጊዜ ተራቸውን ተወጡ:: ልጅ ግዛቸው ኃይሌ መንዝ "በአንድ ልብ ከጸናን መሥዋዕትነታችን ወደ እግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርብ ጥርጥር የለውም" አሉ::[10] አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ደግሞ "ለሃይማኖቴ እሞታለሁ:: እናንተ እንዳሻችሁ ሁኑ" ብለው በአስቤ አገር ሚካኤል ዳዊት ላይ ጻፉ::

የደብረ ሊባኖስ ካህናት ለጠላት ሸንገላ የማይበገሩ ሆኑ:: ጣልያን መሣሪያ ደብቃችሁአል የሚል ምክንያት ፈጥሮ 350 መነኮሳት በመትረየስ ረሸነ:: የተረፉትን ደግሞ ወደ ደብረ ብርሃን ወስዶ ዲያቆናት እንኳን ሳይተው 42ቱን ገደለ:: ከዝቋላ ገዳምም ብዙ የወደቁ አባቶችን ጭምር ፈጀ:: ከዜና ማርቆስ ገዳምም እንደዚሁ:: ጐንደር ማኅበረ ሥላሴን አቃጥሎ መነካሳቱን



ጨፈጨፈ:: ይህ ሁኔታ ለእምነት አባቶች ጽንአት ሰጠ:: ካህናትንም በይበልጥ አስተባበረ:: ቡልጋ የወክፈሌ ቅዱስ ሚካኤል ካህናት እንግዳ እሸት የተባለውን የልጅ ኢያሱን ልጅ፤ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ብለው ነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም በሥጋ ወደሙ አነገሡ:: የእቲሣ ገዳም አባ ምኔት መምህር በላይ፤ በመጽሐፍ ስማቸው እጨጌ ገብረ ጊየርጊስ ተብለው የቤተክርስቲያን ሥራ እንዲመሩ ተደረገ:: የደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካህናት ጽላታቸውን ይዘው ከአዲስ አበባ በምሥጢር በመውጣት ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ:: የአርሲ የሑሩታ ማርያምና የጽሊላ ገብርኤል፣ እንደዚሁም ከጨንቻ የቅዱስ ጊየርጊስ ካህናት ታቦቶቻቸውን ይዘው ከስደተኛው ጋር ኬንያ ገቡ:: በዚያም ለሦስቱም ታቦቶች ለየብቻ መቃኞ ተሠርቶላቸው፤ ለተወለደው ጥምቀተ ክርስትና በመስጠት፣ የሞተውን በመፍታት ሲያገለግሉ እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ቆይተው ወደየቦታቸው ተመለሱ::[11]

በኢየሩሳሌም የነበሩ መነኮሳት የመድኃኔ ዓለምን ጽላት ይዘው፤ በጥር ወር 1929 ዓ.ም ለንደን ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ገቡ:: የጸሎት ቤት አቋቋሙ:: እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ከዚያ ቆይተው፤ ነሐሴ 23 ቀን 1933 ታቦታቸውን ይዘው አዲስ አበባ ገቡ:: እሱም አሁንም ስደተኛው መድኃኒ ዓለም እየተባለ የሚጠራው የምስካየ ኅዙናን መድኃኒ ዓለም ነው::[12]

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከስደተኞች ወንድሞቻቸው ጋር በመተባበር፤ የኢጣልያ መንግሥት በዚያ ያለውን የኢትዮጵያ ገዳም ለመውሰድ ያደረገውን ሙከራ አከሸፉ:: የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከገዳሙ ለማውረድ ያደረገውን ጥረት ዋጋ አሳጡበት:: ከጠላት ጋር ለመተባበር በሞከሩት መነኮሳትና መነኮሳይያት ላይ ችግር ፈጠሩባቸው:: ጠበቃ ገዝተው ከኢጣልያ ቆንሲል ጋር በሕግ ተከራክረው፤ ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ በባለሥልጣኖች ትዕዛዝ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች መብትና ጥቅም እንዳይነካ አሳዘዙ::[13]

የአርበኞች እንቅስቃሴ እያየለባቸው ሲሄድ፣ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ጥቃት አካሄዱ:: በድምሩ 2000 አብያተ ክርስቲያናት አቃጠሉ:: ግንቦት 28 እና 29 ቀን 1930 ዓ.ም በሁለቱ ቀናት በአንድ አካባቢ ሰባት ቤተክርስቲያኖች ማቃጠላቸውን እኔ ራሴ አይቻለሁ:: ቦታው ሙገሬ ዛለ ነበር:: የአለ ከሴ እግዚአብሔርን፣ አማኑኤል ገዳምን፣ ሥላሴ ገዳምን፣ ጭንቂት ማርያምን፣ ጉርባ አገረ ማርያምን፣ ጀሉ አገረ ማርያምን፣ አሰቤ አገር ሚካኤልን አቃጠሉ:: ካህናቱን ከቤተ ክርስቲያኖቹ እያስወጡ፤ የደበቁአቸውን መጻሕፍት እና ንዋየ ቅድሳት ሲያቃጥሉና ሲቀዱ ታይተዋል::

ብዙ ቤተክርስቲያኖች ሳይቃጠሉ ቀሩ:: ቡልጋ የቅዱስ ጊዮርጊስ አልቃጠል ስለአለ፤ ጣልያን አጠገቡ ምሽግ መሽጐ የአጋሰስ ማሠሪያ አደረገው:: የድንጋይ ጥረና የእመየት አገር ጊዮርጊስ እንደዚሁም የሰበርንሐ

ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያኖች አሸንፈው ሳይቃጠሉ ቀሩ። የጓሎ አገረ ማርያም በ25 መድፍ ቢደበድባት ሳትቃጠል ቀረች።[14]

ከሁሉም የሚገርመው ቅምብቢት፣ ገነ ጊዮርጊስ የታየው ነው። በእግር ቀርበው በእሳት ቢለኩሱት አልቃጠል አለ። በመድፍም ቢመቱት የማይሆን ሆነ። በአይሮፕላን በቦምብ ደጋግመው ደበደቡት። ቦምቡ ወደ ሌላ ቦታ እየሄደ ወደቀ። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ቦምብ ከቅጽር ግቢው አርፎ ሳይፈነዳ ቀረ። ይህ የሆነው በጥቅምት ወር 1930 ዓ.ም በተካሄደው ታላቅ ጦርነት ጊዜ ነበር። ቦምቡ የወደቀው ማክሰኞ ቀን ነው። እስከ ቅዳሜ ድረስ ሳይፈነዳ ቆየ። ለእሁድ ቅዳሴ ችግር ፈጠረ። ሁለት ሽማግሌዎች ቦምቡን ለማውጣት በፈቃደኝነት ገቡ። በቁርበት ቀላጥም ተሸክመው አወጡት። ከቤተክርስቲያኑ በታች ከነበረ ቅብቅብ ውስጥ በጥንቃቄ አስቀመጡት። እነሱ ቦምቡን ባወጡ ጊዜ ካህናትና ምእመናኑ ከቤተ ክርስቲያን ገብተው እግዝዮታ ያደርሱ ነበር። ሽማግሌዎቹ ተመልሰው ከቤተክርስቲያኑ ሲገቡ ቦምቡ ፈነዳ። የተጠበቀውም እንደዚሁ ይሆናል ተብሎ ነበር። በዚያ የነበሩትን ከብቶች ቦምቡ ፈጃቸው። ሮጣ ገብታ ከቆመ ሰው ከተጠጋችው አንድ ጊደር በስተቀር የዳነ ከብት የለም። ሰው ግን ከቤተክርስቲያን ገብቶ ዳነ።[15] እንደዚሁም ጣልያን በሸዋ፣ በጐንደርና በጐጃም አብያተ ክርስቲያናት ላይ ተመሳሳይ ጥቃት ፈጽሞአል። ሂደቱና አድራጐቱ ተመሳሳይ ነው።

ይህ ሁኔታ በኢጣልያውያን ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ፈጠረ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጣልያኖችን እምነት የሌላቸው አሕዛቦች አድርጐ ቆጠረ። ቀደም ብሎ በሁለቱ ቤተክርስቲያኖች ማለትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሮም ካቶሊክ መንበር መካከል ጸንቶ የኖረው መቃቃር በይበልጥ ተካረረ። በአንፃሩ ደግሞ በርካታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አለቆችና ካህናት ከጣልያን ጋር ተባበሩ። በስብከት የአርበኞችን ክንድ ለማላላት ሞከሩ። ምሥጢር ለጠላት እያሳለፉ ሰጡ። ይህ ደግሞ በካህናት መካከል የተካረረ የአመለካከት ልዩነት ፈጠረ።

የአርበኞች መበርታትና የመልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መንገሥ በለንደን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘንድ ሥጋት እንደፈጠረ ሁሉ፤ የመምሕር በላይ እጨጌ መሆን ኢየሩሳሌም በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ዘንድ ድንጋጤ ፈጠረ። ስለዚህም እጨጌው ከመጀመሪያው በተጨማሪ ሌሎች ስድስት ሐዋርያዊ መልእክቶች በተከታታይ አስተላለፉ። የተላለፉበትን ጊዜ፣ ቅርጻቸውንና ይዘታቸውን መመልከት አንዳንድ ግንዛቤ ይሰጣል።

የመጀመሪያው የእጨጌ መልእክት የተላለፈው ኅዳር 17 ቀን 1928 ዓ.ም እንደነበር ቀደም ብለን ተመልክተናል። ሁለተኛው መልእክት ከእኚህ አባት የተላለፈው ሰኔ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ነበር። በዚህ ጊዜ እጨጌነትን በተመለከተ ቡልጋ ውስጥ ሌላ ተለዋጭ እንቅስቃሴ እንደነበር ማጤን



ይገባል። ሦስተኛው መልእክት ደግሞ ሰኔ 27 ቀን 1931 ዓ.ም ነበር። ከአንድ ሣምንት በኋላ መሆኑ ነው። አራተኛው መልእክት በኅዳር ወር 1932 ዓ.ም ነበር። አምስተኛው ታህሣሥ 24 ቀን ስድስተኛውም በዚያው በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም ነበር። ከኅዳር 17 ቀን 1928 ዓ.ም እስከ ሰኔ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ሦስት ዓመት ከሰባት ወር ጸጥ ብሎ የነበረውን መልእክት ምን አንቀሳቀሰው?

ሌላው መታየት ያለበት የመልእክቶቹ አድራሻ ነበር። ሁለተኛውና ሦስተኛው ሐዋርያዊ መልእክቶች የተላለፉት ለኢትዮጵያ ሊቃውንት፣ ካህናት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ መኳንንት፣ ባላባትና ሕዝብ ነበር። አራተኛው ከእጨጌው ጋር ልዑል ራስ ካሣና ሌሎች ታላላቅ መኳንንቶች ጭምር ሰላምታ እንደሚያቀርቡ ተገልጦ፤ ለሃያ አንድ መኳንንቶች በየስማቸው የተጻፈ ነበር። አምስተኛው ሐዋርያዊ መልእክት ደግሞ በዚያው በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም የተጻፈ አድራሻው በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሆነ ነበር። ላኪው... "እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ" ተባለ ለምን? ስድስተኛው ሐዋርያዊ መልእክት፣ በኢትዮጵያ አውራጃ ላለ ለእያንዳንዱ የአርበኛ አለቃ በዚያው በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም ተጻፈ። ሰባተኛው ደግሞ እንደገና ላኪው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው። አሁንስ ለምን?

የመልእክቶቹ ይዘት ተመሳሳይ ነበር። ከሦስት ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ ትኩረት ተደርጐአል። አንደኛውና ዋናው ጉዳይ አርበኛው በርትቶ እንዲዋጋ በነገረ መለከት ላይ የተመሠረተ ምክር መስጠት ነው። ሁለተኛው መልእክት ይህንን በተመለከተ...ጣልያን ...ዘራችንን፣ ሃይማኖታችንን፣ እያዋረደ፣ ሕዝባችንን በዓለም ፊት ነውረኛ ለማድረግ መስበኩን አትዘንጋ..." ይላል። ሲደመድምም "...እግዚአብሔር ኃይሉን እንዲሰጣችሁ...እንለምናለን" ይላል። ሦስተኛው መልእክት ቅዱስ ዳዊት "...እግዚአብሔር በኢ አሕዛብ ውስተ ርስትከ" የሚለውን መመልከት እንደሚገባ ያስገነዝባል።[16] አራተኛው ሐዋርያዊ መልእክት አንድም ቃለ እግዚአብሔር የለበትም። አምስተኛው መልእክት "...ስለ ሀገሩ የገደለም፣ የሞተም ሰማዕት ነው..." ይልና ሙሴ ስለወገኑ እንደ ገደለ ይዘክራል። ስድስተኛው መልእክት "...ሁሉን የሚችል አምላክ የዳዊትን ሁብተ መዊዕ ይስጣችሁ..." ይላል። ሰባተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ኤሳው ብኩርናውን ላንዲት ሙብል እንደሸጠ ያስገነዝባል "...ለጠላት ወገን ሆኖ ወንድሙን የሚወጋውን፣ ሰላይም ሆኖ ለጠላት የሚረዳውን፣ ...ሰባኪ ሆኖ...የሕዝቡን ልብ የሚያሰንፈውን መምህራንም፣ መነኮሳትም፣ ቀሳውስትም፣ ዲያቆናትም ቢሆኑ ከቤተ ክርስቲያን የተለዩ ከሥልጣናቸውም የተሻሩ ናቸውና፤ የሊቀ ጳጳሳቱን /የእስክንድርያውን አቡነ ዮሐንስ 14ኛ ማለት ነው/ መሠረት አድርጌ በሥልጣነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የተለዩ እንዲሆኑ ገዝቻለሁ" በማለት ይደመድማል።



ይህ ስዕል ካህናቱ በመንቀጥቀጥ ለጀኔራል ናዚ ፋሽስታዊ ሰላምታ እንዲሰጡት ያመለክታል ።

የመልእክቶቹ ሁለተኛ ጉዳይ አርበኛው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት ላይ እንዳያወላውል ማድረግ ነው። ይህንን በተመለከተ ሁለተኛው መልእክት ለኢትዮጵያ አርበኞች፣ ካህናትም ንጉሠ ነገሥቱ ለዓለም መንግሥታትና ሕዝብ እያመለከቱ እንደሆነ ማየት መስማታቸውን ያስረዳል። ስለንጉሠ ነገሥቱ በክርክር ላይ መሆን ያመለክታል። አራተኛው መልእክት "...ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በተሠራው ግፍና በፈሰሰው ደም ስለሀገራቸው ነፃነት ለመከራከር የተሰደዱበት ጉዳይ መፈጸሚያው ጊዜ የደረሰ ይመስለናል..." የሚል ትንቢት በስም ለተጻፈላቸው መኳንንት ይገልጻል። ለሕዝብ የተላለፈው አምስተኛው ግን ስለዚህ ጉዳይ አንዳች አይልም። ለአርበኛው አለቆች በስም የተጻፈው ስድስተኛው መልእክት ደግሞ "...በመከራው ጸንተህ ንጉሥህ ያዘዘውን ሥራ አገልግሎትህንም ፈጽም..." ብሎ የጤሞቲዎስን ሁለተኛ መልእክት ይጠቅሳል። ሰባተኛውና የመጨረሻው መልእክት "...ወይኩን ንጉሥ ዘትሠይሞ እምአኃዊከ፣ ወኢይደሉ ከመትሢም ላዕሌክ ብእሲ ነኪረ..." ተብሎ በፍተሐ ነገሥት አንቀጽ 44 የታዘዘው በሃይማኖት ለማይመሳሰል፣ በምግባር ለማይተባበር መገዛት የማይገባ መሆኑን እንደሚያሳይ የሚገልጽ ነበር። ብእሲ ነኪረ ያለውን "ባዕድ" ብሎ ተርጉሞታል።

የመልእክቶቹ ሦስተኛው ጉዳይ እጨጌው አገር ጥለው በመሄድ ሊያጡት የተቃረቡትን በትረ ሥልጣን እንደገና መልሶ የመጨበጥ ነበር። ይህንን በተመለከተ ሁለተኛው መልእክት ማለትም በተሰደዱ በሦስት ዓመት ከሰባት ወር ከኢየሩሳሌም የጻፉት ስለአካሄዳቸው እንዲህ ይላል። በዘመቻው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እንደነበሩ ያወሳና "...አሁንም ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዝባቸው ነፃነት በዓለም መንግሥታት ፊት ቀርበው ለመከራከርና ፍርድ ለመጠየቅ ወደ ኢሮፕ ሲመጡ አብሬ መምጣቴን ሰምታችሁ ይሆናል።




ይኸው እኔም በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ገዳማችን እንዳይደፈር፣ የሃይማኖታችን መሠረት እንዳይናወጥ በሀዘንና በጸሎት ተጠምጄ በሃሳብ ከእናንተ ሳልለይ እኖራለሁ..." በማለት ይጀምራል። ሦስተኛው መልእክት "በዓይነ ሥጋ ለመገናኘት ያብቃን" ብሎ በመደምደም ስለግላቸው ጉዳይ አያነሱም። አራተኛው መልእክት ብቻቸውን አለመሆናቸውን ለማስገንዘብ የዘጠኝ መኳንንት ስም ይዘረዝራል። ነገር ግን ስለራሳቸው አይናገርም። በአምስተኛው መልእክት "...በሥጋዬ ከናንተ ጋራ ባልኖርም በልቡናዬ ከናንተ ጋራ ነኝ..." የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ጠቅሰው፤ እሳቸውም በልቡናቸው ከኢትዮጵያን ጋር መሆናቸውን ገልጸዋል። በስድስተኛው መልእክታቸው ቅዱስ ጳውሎስ በካልዕ ተሰሎንቄ የጻፈውን በመጥቀሥ፤ እሳቸውም መልእክቶቹን በእጃቸው መጻፋቸውን ገለጹ። እንዲህም አሉ "...ይኸን ሰላምታ በእጄ ጻፍሁ። በምጽፈው ደብዳቤ ሁሉ ምልክቴ ይህ ነው። እንዲህ እጽፋለሁ..." አሉ። ሌሎች እጨጌዎች የሳቸውን እያስመሰሉ እንዳይጽፉባቸው ይሆን? በወቅቱ የንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ፣ የኢጣልያ መንግሥት እጨጌ ሐዲስ እሼቱ ነበሩና። በሰባተኛው መልእክታቸው ስለዚህ ጉዳይ አላነሱም።[17]

ጣልያኖች በፊናቸው ጦርነቱ ከውስጥ፣ ከውጭ እየከበደባቸው ሲሄድ ባለምዋሎቻቸው ሕዝቡን እንዲሰብኩላቸው ጉትጐታቸውን አጠናከሩ። እውነትም ሳያፍሩ ሳይፈሩ ሰበኩላቸው። አንዳንድ ማስረጃ መጥቀስ ይበጃል። የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ አባ አብርሃም የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሣርን ለቄሣር የሚለውን ቃል እየፈጸሙ መኖር እንደሚገባ አስታወቁለት። ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት "...የኢጣልያ መንግሥት ኃይማኖት ያስለውጣል፣ ያገር ልማድ ያስቀራል እያለ የሚያወራ እሱ ራሱ ከሀዲ ነው።..." ብለው አስተያየታቸውን ገለጹ። እጨጌው ደግሞ "...ይህን ድሀ ጠባቂ የሆነ ትክክለኛ መንግሥት ለዘለዓለም አኑርልን..." አሉ።[18]

በአንፃሩ በገጠር ቄስ መነኩሴው "ለሀገርህ ነፃነት፣ ለወገንህ ደህንነት ብትሞት በልዑል እግዚአብሔር ፊት ሰማዕትነት ይሆንልሀል። ሞተ ነፍሥን እንጂ፣ ሞተ ሥጋን አትፍራ" እያሉ ሰበኩ በቀኝም ሆነ በግራ የኢትዮጵያውያን ዕድል ሞት ሆነ። ሞት ከአርበኛውም ወገን ቢሆኑ ከጣልያንም ወገን አልቀረም። ያለው ዕድል ለየትኛው ወገን መሞት እንደሚሻል መምረጥ ሆነ። ከአርበኞች ጐን መሆን ሞት፣ ከጣልያን ወገን መሆን የሞት ሞት እንደሚያስከትል ግልጽ እየሆነ ሄደ። ስለዚህ ልባሞች ከሞት ሞት ይልቅ፣ ሞትን መረጡ።

አርበኛው በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸና፤ የሃይማኖት አባቶችም ጠነከሩ። ራሳቸው ከጦር ሜዳ እየገቡ ቆሙ። ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ሲሞቱ እጨጌአቸው የነበሩት ገብረ ጊዮርጊስ መነኑ። የራስ አበበ የነፍስ አባት የነበሩት መምሬ ደምሴ ቁርሎስ ቆስለው በመማረክ ደናኔ እሥር ቤት ገቡ።



ይህ ስዕል ካህናቱ በመንቀጥቀጥ ለጀኔራል ናዚ ፋሽስታዊ ሰላምታ እንዲሰጡት ያመለክ

በጐንደርም፣ በጐጃምም ከጦር ሜዳ እየገቡ ሲያዋጉ ብዙ ካህናት ከዚያው ከጦር ሜዳ ሞቱ።

እንደእኔ አስተያዬት ልዑል እግዚአብሔር እንደ ወትሮው ሁሉ ከተጠቂዎች ጐን ቆመ። ብዙ አንባቢያን በዚህ አባባሌ ልትስማሙ እንደምትችሉት በመገመት እቀጥላለሁ። ለመቆሙም ብዙ ምልክት አሳየ። ምስጋና ለማቅረብ ያህል ጥቂቱን ማየት ይገባል። ዝናምና ደመና እየሆነ የጣልያንን አይሮፕላን እንቅስቃሴ ብዙ ጊዜ ገታ። የሚወድቀውም ቦምብ በአፍንጫው ከጭቃ ውስጥ እየተገደገደ የማይፈነዳ ሆነ። ለጣልያን ወታደር የሚጣለውን ስንቅና ጥይት ነፋስ እያዞረ ለአርበኞች ሰጠው። ለምሣሌ በመንዝና በቡልጋ አይሮፕላኖች በቤተክርስቲያን አካባቢ ሲበሩ እየተበላሹ ወደቁ። እንደዚሁም ለምሣሌ ጐንደር በማህበረ ሥላሴ ጦርነት ጠላት ሲያሸንፍ ከባድ ዝናም ይጥላል።[19] የባላምባራስ /ራስ/ አበበ ሠራዊት ከኩርፎ ጦርነት ላይ ያመለጠው በዚህ ዓይነት ተአምር ነው። በየቤተክርስቲያኑ ያሉት ጠበሎች ከወትሮ የበለጠ ፈዋሽነት አገኙ። እኔም ከብቴም በአንድ ጊዜ በጠና ታምመን ሙገሬ ዛላ በአማኑኤል ገዳም ጠበል ዳንን። ጀሎ አገር ገዳም ደጋ ያለ አንድ ሾላ 105 ነፍስ ለሦስት ወር መገበ። ታቦቶች የከዳውን ፈጥነው ይቀጣሉ። ለምሣሌ ቡልጋ አጋፋሪ አሣምነው ላይከዱ በአስቤ አገር ቅዱስ ሚካኤል ማሉ። መሐላቸውን ባፈረሱ በሦስተኛው ቀን ሁለት ዓይናቸውን ታወሩ።[20]

እንደእኔ፣ በእነኛ ቀውጢ አመታት የነበርን ብዞዎቻችን፣ ኢትዮጵያ ከፋሽስት ወረራ ነፃ ልትወጣ የቻለችው በእግዚአብሔር ኃይል ነው ብለን እናምናለን። የአርበኝነት ትግል ከዳር የደረሰው በእግዚአብሔር አጋዥነት ነው። ይህንን አርበኞች ሁሉ መስክረዋል። በትግሉ ውስጥ የነበርን ሁሉ አምነናል። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዙፋናቸው የተመለሱት በእግዚአብሔር ጥበብ ነው። እሳቸውም አዲስ አበባ በገቡበት ዕለት ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ያደረጉትን ንግግር የጀመሩት "የሰማይ መላዕክት የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊያውቁት ይቻላቸው ባልነበረ በዚህ ቀን፤ ቸር እግዚአብሔር በመካከላችሁ ለመገኘት ስለአበቃኝ በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና የሚበቃ አይደለም..." በማለት ነበር።[21] እውነት ነው ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ያፀናት፤ በማይመረመር ረቂቅ ጥበቡ የጥበበኞችን ሤራ አፍርሶ ኃይላቸውን ደምስሶ ነው። ለዚህ ታላቅ ችሮታው በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና በቂ አይደለም።

የኢትዮጵያ ልጆች ይህንን እውነት ከልብ እንዲያምኑና እንዲረዱ ያስፈልጋል። ይህንን ካላደረጉ በዓለሙ ላይ አንዳች ብቃት አይኖራቸውም። በፈጣሪ፣ በእግዚአብሔር ካላመኑ ልፋታቸው ሁሉ መና ይሆናል። እነሱ የለፉበትን ጠላቶቻቸው ይበሉባቸዋል። በእግዚአብሔር ካመኑና ትዕዛዙን ከፈጸሙ ግን ማንም ኃያል፣ ማንም ጥበበኛ አንዳች አያደርጋቸውም።[22]



ልዑል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ምን እንዳረገላት ለመገንዘብ ከሚያስችሉት ነገሮች አንዱ የጣልያን ባለሥልጣኖችን ፍፃሜ መመልከት ነው። ንጉሠ ነገሥት ኢማኑኤል ሣልሣዊ ከሥልጣኑ ወረደ። ሥርወ ወንግሥቱ ተነቀለ። አባ ፖኦስ 11ኛ የካቲት 5 ቀን 1931 ዓ.ም ሞቱ። ዱቼ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ሚያዝያ 21 ቀን 1933 ዓ.ም በሰሜን በኩል አምልጦ ወደ ስዊስ አገር ሊገባ ጥቂት ሲቀረው ተይዞ ተጨናገፈ። ዲንጉ በተባለች ትንሽ መንደር ውስጥ በአምስት የመትረየስ ጥይት ተደብድቦ ሞተ። አብራው የተገደለችው ክላራ ፔታኪ የተባለችው ታማኝ ቀባቱ ጋር ሬሣሳቸው የዝቅዝቂት ተሰቀለ። ሙሶሊኒ የተገደለው በገዛ ወገኖቹ በኢጣልያውያን ነበር። የሞተውም ጣልያኖችን ምን በደልኩና እያለ ነበር። ያቋቋመውም የፋሽስት ፓርቲ ከእሱ ጋር አብሮ ጠፋ። ማርሻል ግራዚያኒ በሊቢያ በተካሄደው ጦርነት ኢጣልያን እንደከዳ ተቀጥሮ ከግበረ አበሮቹ ጋር እሥራት ተፈረደበት፤ የእሱ ድርሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሆነ። ዱካ ደ አዎስታ አምባለጌ ተማርኮ ኬንያ ከተወሰደ በኋላ ናይሮቢ አገር እሥር ቤት ሞተ። ክንትቺያኖ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን ሆና ከጦርነቱ በመግባትዋ ባለመስማማቱ፤ ከሌሎች ስድስት ሚኒስትሮች ጋር በአማቱ በሙሶሊኒ ትዕዛዝ ተገደለ። በልዩ ልዩ ምክንያት እየተልፈሰፈሰ ኢትዮጵያን ያስወረራት የዓለም መንግሥታት ማኅበር ፈረሰ። የኢትዮጵያን መወረር የተሰቀቀው አውሮፓ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እሳት ከዳር እስከ ዳር ተጠበሰ።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች


1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ፣ 203-206፡፡
2. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 82-93፡፡
3. ከኢትዮጵያ ምርምርና ጥናት ክምችት የተገኘ፡፡
4. አክሊሉ ገብረ ክርስቶስ፣ *ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት*፣ ገጽ 15-17፡፡
5. መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሳሙኤል ካልዕ፣ ምዕራፍ 15 ቁጥር 25-27፡፡
6. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 84-92፡፡
7. ከመልአከ መዊዕ የተካነ በንቲ የተነገረኝ፡፡
8. "የኢሉባቡር ታሪክ"፣ የኢሠፓ ጥናት፣ ገጽ 31 /ያልታተመ/፡፡
9. *የቄሣር መንግሥት መልእክተኛ*፣ ሣምንታዊ ጋዜጣ፣ ሐምሌ 14 ቀን 1932 ዓ.ም፡፡
10. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 214፡፡
11. አባ ተክለ ማርያም፣ *የምስካየ ኅዙናን ገዳም አመሠራረት*፣ ገጽ 19-34፡፡
12. ከአቶ እሸቴ ባዩ የተነገረኝ፡፡
13. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 173-193፡፡
14. እኔ ራሴ ያየሁት፡፡
15. ከመምህር ገብረሕይወት ወልደፃድቅ የተነገረኝ፡፡
16. መዝሙረ ዳዊት ቁ.73፡፡
17. አፈ ሊቀ ሊቃውንት አክሊሉ ገብረ ኪሮስ /የጽሑፍ ተጠባባቂ/ ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ገጽ 15-29፡፡
18. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 84-87፡፡
19. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 284፡፡
20. በአቶ ወልደፃድቅ ሸንቁጤ የተነገረኝ፡፡
21. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 311፡፡
22. ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ምዕራፍ 26 ቁጥር ከ1-47፡፡




# ምዕራፍ ሃምሣ ስድስት
# ጦርነቱ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያደረሰው ጉዳት

በማንኛውም ጦርነት ጊዜ ዝርፊያ ይካሄዳል፡፡ የሀብት ውድመት ይደርሳል፡፡ በኢትዮጵያና በኢጣልያ ጦርነት ጊዜ የተካሄደው ከሁሉም የከበደ ነው፡፡ ሁኔታውን በትክክል ለመገንዘብ የሚቻለው በሁለቱም ወገን የደረሰውን በማየት ሳይሆን አልቀረም፡፡ ችግሩ በቂ ማስረጃ አለመገኘቱ ነው፡፡ ቢሆንም የተገኙትን ጥቂት ማስረጃዎች መነሻ በማድረግ የደረሰውን ጉዳት ለመገመት እንሞክራለን፡፡

የኢኮኖሚ ጉዳት የደረሰው በአራት ዓይነት ነው፡፡ አንዱ የሥልጣን ልውውጥ በተደረገ ጊዜ ባለሥልጣኖቹ ያካሄዱት ገፈፋ ነው፡፡ ሁለተኛው በእነዚያው የሥልጣን ሽግግሮች ወቅት ሕዝብ እርስበርስ ሲዘራረፍ የደረሰው ጉዳት ነው፡፡ ሦስተኛው በጦርነቶቹ ጊዜ የወደመው ሐብትና ንብረት ሲሆን፤ አራተኛው ደግሞ መንግሥቶቹ የሚጠቅም እየመሰላቸው ባካሄዱት ሥራ የደረሰው ኪሣራ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ማለትም በገፈፋ፣ በዘረፋ፣ በውድመት ጉዳት የደረሰው በኢትዮጵያ ላይ ሲሆን፤ አራተኛው ማለትም ኪሣራ የደረሰው በጣልያን ላይ ነው፡፡

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ የተሻገሩት አንድ መቶ አሥራ አንድ ሣጥን ወርቅና ብር፣ ሌላም ዕቃ ይዘው እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቦአል፡፡ መኳንንቱም እንደዚሁ የቻሉትን ያህል ይዘው ነው የሄዱት፡፡ ይህንን ከስህተት መቁጠር አይገባም፡፡ ምክንያቱም ትተውት ቢሄዱ ከጠላት እጅ ገብቶ ይበልጥ ከሚያስጠቃ በስተቀር ሊጠቅም አይችልም ነበር፡፡ እንዲያውም ንጉሠ ነገሥቱ፣ መኳንንቱና መሣፍንቱ መትረፋቸው የኢትዮጵያን ትንሣዔ አስገኝቶአልና በጥቅም ላይ እንደዋለ መቁጠርም ይቻላል፡፡' ነገር ግን ከኢትዮጵያ ውጭ ሄዶ በሰው አገር የፈሰሰ በመሆኑ በኢኮኖሚ አመለካከት እንደባከነ የሚቆጠር ነው፡፡ በዚህ ዓይነት 10 ሚሊዮን ብር ከሀገር ሳይወጣ አልቀረም፡፡

የኢጣልያ ሹማምንትና የጦር አለቆች ኢትዮጵያ ሲገቡ ያካሄዱት ሥራ እንደ ገፈፋ ነው፡፡ ማንኛቸውም ምን ያህል እንደወሰዱ ማስረጃ የለም፤ ደረሰኝ እየሰጡ አይወስዱም፡፡ የታሪክ ጸሐፊዎቻቸውም ይህንን የመሳሰለውን ነገር አይጽፉም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ምልክቶች ታይተዋል፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ከኢትዮጵያ ወደ ኢጣልያ የሚመለሱ ሁሉ ባዶ እጃቸውን አልሄዱም፡፡ ወደ ሀገራቸው የሚገቡት ብዙ ሀብት እየተሸከሙ ነበር፡፡ ለማስረጃም ያህል ማርሻል በዶሊዮ አገሩ የገባው ሦስት መቶ ሣጥን አጋትሎ ነው፡፡ ማርሻል ግራዚያኒም ሰባ ዘጠኝ ይዞ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ባዶሊዮ በኢትዮጵያ ባንክ ከነበረው 1.7 ሚሊዮን የማርትሬዛ ብር ግማሹን ለግሉ ዘርፎ ነው፡፡[1] ቀሪውንም ጭፍሮቹ ተከፋፍለውታል ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ጣልያኖች

በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ገፈፋ አካሂደዋል። ይህም ገፈፋ በገንዘብና በሐብት ላይ ብቻ ላይ ያተኮረ አልነበረም። በታሪካዊ ቅርስ ላይ ጭምር እንጂ። ለዚህም የአክሱም ሐውልት የዚያን ጊዜ ተወስዶ እስከቅርብ ጊዜ አለመመለሱ፤ በባቡር ጣቢያ የሚገኘውም ይይሁዳ አንበሳ ሐውልት ወደ ሮም ተወስዶ እንደነበረ ማስታወሱ በቂ ይሆናል። ጣልያኖች ገፈፋ ያካሄዱት ሲገቡ ብቻ አልነበረም። ሲወጡም ነው።

ከዚህ ላይ አንድ ማስረጃ መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህም መጥቀስ የሚገባው ደብዛው ጠፍቶ የቀረው አርባ ኩንታል ወርቅና አልማዝ፣ የሌሎችም ክቡር ዕቃዎች ጉዳይ ነው። የእሱም ታሪክ ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

ጦርነቱ ከአለቀ ከአሥራ አምስት በኋላ[2] ደቡብ አፍሪካ፣ ኬፕታውን ከተማ በመጠጥ ቤት ፒተር ሀሎራንና ዋከር የተባሉ ሰዎች ተገናኝተው ሲጫዎወቱ ተቀብሮ ስለቀረ ወርቅ ዋከር ለሀሎራን ነገረው። ወሬውን የሰማው ሀሎራን የጥቅም አገኛኘት ዘዴ የሚያውቅ ሰው ስለነበር በጉዳዩ ላይ ጥናት አደረገ። የሚያውቀውን ሦስተኛ ሰው ካርቴዝን በመጨመር ወርቁን አውጥተው እኩል ለመከፋፈል የሚችሉበትን መንገድ አሰበ። ወርቁ የተቀበረው በጣልያን አገር ነው። የተቀበረውም በእንግሊዝ ወታደሮች ነው። የተማረከው ከ17 የጀርመን ወታደሮች ሲሆን፤ ወሬውን እንዳያወጡ እነሱም አብረው ተቀብረዋል። ምሥጢሩን ከሚያውቁት የእንግሊዝ ወታደሮች አራቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ሲሞቱ በሕይወት የቆዩት ሁለቱ ብቻ ነበሩ። እነሱም እርስበርሳቸው ለመገዳደል እየተፈላለጉ ናቸው። ሀሎራን በብዙ ምክር ሁለቱን የቀድሞ ወታደሮች እርስበርሳቸው አገናኛቸው። በእሱ ሃሳብ እንዲስማሙ አድርጎ ወርቁን አውጥተው እኩል ሊካፈሉ ተነጋገሩ። እሱም ወጭአቸውን ችሎ ራሱ ባሠራት መርከብ አንቀሳቀሳቸው።

በአትላንቲክ ባህር ላይ ተጉዘው ታንጀር ደረሱ። ከዚያም ስለ ወርቅ ገበያ ከአንድ ነጋዴ ጋር ተመካክረው ጉዞአቸውን በመቀጠል ሞንቴ ካርሉ፣ ከዚያም ራፖሉ ከተባለቸው ትንሽ ወደብ ደረሱ። ከዚያ ደግሞ ፍራንሲስካ የተባለች የኢጣልያ መኳንንት ተወላጅ የሆነች ሌላ የጥቅም ተጋሪ ተገናኙ። ፍራንሲስካ የሙሶሊኒን መንግሥት በመቃወም በአርበኝነት ከተዋጋ አባትዋ ጕን ሆና የተዋጋችና የወርቁን ምሥጢር አውቃ ቦታውን በማፈላለግ ላይ ስለነበረች ከጥቅሙ ተካፋይነት ማገድ ሳይቻል ቀረ። እሷ ደግሞ ብቻዋን አልነበረችም። ሃምሣ የሚያህሉ የአባትዋን ጭፍሮች ይዛ ቀረበች። ከብዙ ክርክር በኋላ ወርቁ ከሦስት ሳይሆን ከአምስት ቦታ እንዲከፈል ማድረግ አስፈለገ። ይህም ሆኖ እያንዳንዱ ቅርጫ እስከ ሦስት ሚሊዮን ብር እንደሚደርስ ስለተገመተ፤ ክፍፍሎሹ ባያስደስትም ጠብ አላስነሳም።[3]

ሦስት ካሚዮኖች በመከራየትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በመግዛት፤ ወርቁ ወደሚገኝበት ቦታ ጉዞ ተደረገ። ወራቱ ጥር ሲሆን ወርቁ



ታንጀር መድረስና ለገበያ መቅረብ የነበረበት ከመጋቢት የመጀመሪያ ሣምንት በፊት ስለነበር ሥራው አጣዳፊ ሆነ። ቡድኑ በእቅዱ መሠረት ከቦታው ከደረሰ በኋላ የእርስበርስ መጨራረስ አደጋ እንዳይደርስ የመሣሪያ ገፈፋ ተደረገ። መርዝና አደንዛዥ ነገር አለመኖሩ በርስበርስ ምርመራ ተረጋገጠ። ከዚያም ከዋሻው ውስጥ ተገባ። በዋሻው ውስጥ ሦስት ካሚዎኖች ቆመው ነበር። ከዋሻው ውስጥ የከተቱአቸው ወታደሮች ሃሳብ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሰው ነድተው ለመውሰድ ስለነበር አልተራገፉም። ከውጭ ወገን ከአለው ካሚዎን ሠላሣ፣ በመካከል ከአለው 10 ሣጥን ወርቅ፣ ከውስጠኛው ደግሞ ብዙ አልማዝና የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ፣ የጣልያን ወረቀት ሌሬና የእንግሊዝ ፖውንድ፣ ብዙ የጣልያን መንግሥት የምሥጢር ሰነዶች ተገኙ። ወርቅና አልማዝ ዘውዱ የኢትዮጵያ ነበር።

ቡድኑ የወረቀት ገንዘቡንና የምስጢር ሰነዶችን ትቶ ወርቅና አልማዝ ዘውዱን በካሚዮን ጭኖ ማንም ሳያየው ወጣ። ከዚያም በማቅለጥና በመጋዝ በመቁረጥ ወርቁን አስተካከለው። በጀልባው ጭኖ ምሥጢሩን አውቆ የተነሳሳበትን ሌላ የወንበዴ ቡድን እየተከላከለ ጉዞውን ወደ ታንጀር ቀጠለ። ወይዘሮ ፍራንሲስካም ባልዋን ትታ አቶ ሀሎራን አግብታ አዲስ በተገኘው ወርቅ ልትንደላቀቅ፤ ታላቁን የእንቁ ሐብል ተሸልማ፣ ሽማግሌ አባትዋን አስፈቅዳ ከቡድኑ ጋር አብራ ሄደች። ሕልማቸው እውን መሆን ጀመረ። ቢሆንም ይህ ወርቅ ከሀገሩ ወጥቶ ጦሱ ሰው እያባላ ነው። እኛንም ይዞን ይጠፋ ይሆን? እያሉ መስጋታቸው አልቀረም።

ከሜዲትራንያን ባሕር ማዕከል ሲደርሱ ከባድ አውሎ ነፋስ ተነሳባቸው። ከእሱ እየተናነቁ ጉዞአቸውን ሲቀጥሉ አቶ ክሩፒክ የተባለ የመርከብ ወንበዴ ጠንካራ ቡድን ይዞ ደረሰባቸው። ከመጠነኛ ድብድብና ከጥቂት የተኩስ ልውውጥ በኋላ ንግግር ጀመሩ። የወርቁን ሲሦ እንስጥህ ቢሉት ግማሹን ካልሆነ ብሎ እምቢ አለ። በዚህ ንግግሩ ፈርሶ ትግሉ ቀጠለ። እነ ሀሎራን ከወንበዴው ቡድን ለማምለጥ ከረጋው ባሕር ወደ ኋላቸው ተመልሰው ማዕበል ከአየለበት ባህር ገቡ። ጀልባቸው መስጠም ስትጀምር ወንበዴዎቹ ደረሱባቸው። በዚያን ጊዜ ከወርቁ የተረፈው አሥር ኩንታል ብቻ ነበር። እሱንም ማዳን ሳይቻል ቀርቶ ከጀርባዋ ጋር አብሮ ሰጠመ። እነሱን ወንበዴዎቹ አዳኑአቸው።

ይህንን ያህል አታግሎ ከሜድትራኒያን ባሕር ውስጥ አሰጠመው። አርባ ኩንታል ወርቅና አልማዝ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት ነበር። ዘውዱም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ነበር። ወርቅና አልማዙ፣ ዘውዱ ከጣልያኖች በጀርመኖች ተዘረፈ። ከጀርመኖች በኢጣልያ አርበኞች ተማርኮ ቀድሞ የድኚ ማዕድን ይወጣበት ከነበረ ታላቅ ዋሻ ውስጥ ተደፈነ። ከዋሻው ውስጥ በአቶ ፒተር ሀሎራን ቡድን በምሥጢር ተፈልፍሎ ወጣ።

ከሀሎራን ቡድን ለመንጠቅ የክሩፒክ ቡድን ባኬሄደው ትንንቅ ለአንዳቸውም ሳይሆን ከሜዲትራንያን ባህር ውስጥ ሰጠመ።[4]

ከዚህ ላይ ገና ምላሽ ያላገኘው ጥያቄ ወርቅና አልማዙ፣ ዘውዱ ጭምር እንደምን ከጣልያኖች ገባ የሚለው ጥያቄ ነው። አንደኛ ነገር ከላይ የተዘረዘረው ክስተት እውነት እንጂ ልብ ወለድ አይደለም። ሁለተኛ ነገር ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ ወርቅና ብሩ ከጠላት እንዳይወድቅ ተጭኖ ሄዶአል?[5] በጥድፊያው ጊዜ ጥቂትም ቢተርፍ አርባ ኩንታል ሀገር ውስጥ ሊቀር አይችልም። እጅግ ቢያንስ ለንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ስለዚህ በጉዳዩ ተከታታይ ጥናት ሊደረግበት ይገባል።

ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ ዝርፊያ ያካሄዱት ሲገቡ ብቻ አይደለም፤ ሲወጡም እንጂ። በድምሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ 250,000 የሚጠጉ ጣልያናውያን ነበሩ። እነዚህ የሄዱት የቻሉትን ያህል ተሸክመው ነው። እያንዳንዱ ኢጣልያዊ እጅግ ቢያንስ 200 ብር ይዞ ሳይሄድ አልቀረም። እጅግ ቢያንስ 50 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ገንዘብ ሀብት ወስደዋል ማለት ነው።

እንግሊዞች አዲስ አበባ ሲገቡ ዋና የተከላከሉት ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው እንዳይገቡ፤ አርበኛውም ከከተማይቱ አካባቢ እንዳይደርስ ነበር። ይህ መከላከል ከፀጥታውና ከፖለቲካው ጉዳይ የኢኮኖሚም ጉዳይ ነበረበት። መኪናዎችንና ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ነቃቅለው ወሰዱ። ከአዲስ አበባ እስከ አሥመራ የስልክ መሥመር የተዘረጋው ስምንት እጥፍ ነበር። እነሱ አራቱን ፈትተው ወሰዱ። በጦር ኃይል አሸንፈው የገቡበት አገር በመሆኑ ተው ማለት አልተቻለም፤ ተው ባይም አልነበረም። ምን ያህል እንደገፈፉ አይታወቅም። ጣልያኖች ሲወጡ የገፈፉትን ሳያህል ይቀር ይሆን? ሌላ ሃምሣ ሚሊዮን ማለት ነው። ነገር ግን የዓለም አመለካከት እንግሊዞች በመግባታቸው ሊካሄድ ይችል የነበረውን ዝርፊያ እንደአስቀሩ ነው።

የኢጣልያ ጦር በየተዋጋበት አገር ዝርፊያ እንደ አካሄደ ነው የኖረው። በምግብ፣ በልብስ፣ በዕቃ ያካሄደው ዝርፊያ እጅግ ብዙ ነው። እያንዳንዱ ወታደር በቀን እጅግ ቢያንስ አንድ ስሙኒ ያህል ዝርፊያ ሳያካሂድ አልቀረም። በወረራ ግዳጅ ሥር በቆየበት በአምስት ዓመት ውስጥ እያንዳንዱ ወታደር ለ500 ቀን እንደተቀሰቀሰ ቢቆጠር፤ እጅግ ቢያንስ የ37.5 ሚሊዮን ብር ዝርፊያ አካሂዶአል ማለት ነው።

መጀመሪያ ጣልያኖች ሲገቡ፣ ኋላም እያነሱ ወጥተው እንግሊዞች ሲተኩ ሕዝብ እርስበርስ መዘራረፉ አልቀረም። በግንቦት ወር 1933 ዓ.ም ኢሕአዲግ እንደገባበት ጊዜ አይብዛ እንጂ። ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተዘረፈው ከጠላት እጅ ከመግባት እንደዳነ እንጂ እንደተዘረፈ ባይቆጠር ይሻልም ይሆናል። ለምሣሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ግምጃ ቤቱን ክፍቱን ትተውት እንደሄዱና በሦስተኛው ቀን ሲመለሱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ



እንደተወሰደ ባዩ ጊዜ ደስ እንደአላቸው "መልካም ሥራ ተሠራ" እንዳሉ ይነገራል። ቢሆንም ቢገመት ከ3 ሚሊዮን ብር ሳያንስ ይችላል።

ጣልያኖች አገር በመግፈፍ ሕዝብ በመዝረፍ ብቻ አይደለም በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ጉዳት ያደረሱት። በገዛ ሕጋቸው የተወሰነለትንም ነጥቀውታል። ለምሣሌ ከሕዝብ ለተወሰደ መሬት 6 ሚሊዮን ሌሬ እንዲከፈል ከመንግሥታቸው ተፈቅዶ ሳለ፤ ለሕዝብ የተከፈለው 1,127,175 ሊሬ ብቻ ነው።[6] ይህ ማለት ለኢትዮጵያ ገበሬዎች እንዲከፈል ከተወሰነው ገንዘብ ውስጥ 4,872,825 ሊሬ ማለትም 2,175,300 ብር ነጥቀውታል ማለት ነው።

ሌላው ጉዳት ያካሄዱት ሥራ በማስፈታት ነው። ጣልያኖች የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥራ ከአስፈቱበት መንገድ አንዱ እሥራት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከግምት አግብቶ ካሣ የጠየቀው በእሥር ቤት ላለቁት 35,000 ሰዎች ብቻ ነው። በእሥራት ከማቀቁ በኋላ የተለቀቁ እጅግ ብዙ ናቸው። የእሥራታቸውም ጊዜ ረዣዥም ነው። ሃምሣ ሺህ ሰዎች እያንዳንዳቸው ለሁለት ዓመት ቢታሠሩ ሠርተው የሚጠቀሙበት 36.5 ሚሊዮን የሥራ ቀን አጥተዋል ማለት ነው። በዚያ ጊዜ ውስጥ 18 ሚሊዮን 250 ሺህ ብር ሊያገኙ ይችሉ ነበር።

ጣልያኖች ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ሠርተዋል። እነዚህን ሥራዎች ያሠሩት የእነሱን ዜጎች ኃላፊ እያደረጉ ኢትዮጵያውያኑን ግን እያስገደዱ ነበር። በሥራው 32,000 ሰው ተካፋይ ሆኖአል። ከዚህ ውስጥ እጅግ ቢያንስ ሁለት ሲሦው ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ አልቀሩም። የእጅ ሙያ ለነበራቸው ወይም በዚያው በሥራ ላይ ልምድ ለአገኙ ጥቂቶች እንጂ፤ ለብዙሀኑ የጉልበት ሠራተኛ ለአብዛኛው ጊዜ ገንዘብ አልከፈሉም። በሥራው ላይ የተሰለፉት 21,300 ሠራተኞች እያንዳንዳቸው በዓመት ለ200 ቀን ለአራት ዓመት እንደሠሩ ቢቆጠርና፤ ሳይከፈላቸው የቀረው በቀን.ሃያ አምስት ሣንቲም ሊሆን እንደሚችል ቢገመት፤ 8,520,000 ብር ተበዝብዞአል ማለት ነው።

ጣልያኖች በአርበኛው ላይ ለአምስት ዓመት ጦርነት ያካሄዱት ገበሬውን እያስገደዱ ለጦርነት በማጋፈጥ ነው። ቀጥለው ደመወዝ እየከፈሉ ያዋጉአቸው እጅግ ጥቂቱን ነው። በድምሩ 920,000 ባንዳ እያንዳንዱ ለአንድ ዓመት አገልግሎአቸዋል።[7] የሙሉ ጊዜ እንኳን ባይሆን በተለይ ለዘመቻ ለተንቀሳቀሰበት ጊዜ ሊታሰብለት ይገባል። እያንዳንዱ ባንዳ ለሁለት መቶ ቀናት እንዲዘምትላቸው ቢታሰብ 92,000,000 ብር በዝብዘውታል ማለት ነው።

አርበኛውም በእነሱ ወረራ ምክንያት ሥራ ፈትቶአል። የእሱም ሊታሰብለት ይገባል። አራት መቶ ሃምሣ ሺህ ሠራዊት ለአንዳንድ ዓመት በአርበኝነት ሥራ ተሳትፎአል። ይህ ሠራዊት ደግሞ ሥራ የፈታው

ሙሉውን ዓመት ነው። ስለዚህ ሠርቶ ሊገኝ የሚችለውን 82,125,000 ብር አጥቶአል።

የስደተኛውም ጉዳይ እንደዚሁ ነው በሱዳን 10,000፣ በኬንያ 5,000፣ በእየሩሳሌምና በሌሎች ቦታዎች 1,000 በድምሩ 16,000 ያህል ስደተኛ እንደነበር መገመት እምብዛም ከእውነት የራቀ አይሆንም። የሰደቱ ጊዜ በአብዛኛው ለአራት ዓመት ነበር። ስለዚህ እሷም 11,680,000 አጥቶአል ማለት ነው።

ሌላው ሊታሰብበት የሚገባው ቁስለኛው ነው። በጦርነቱ የቆሰለና ጣልያን ዘር ለማጥፋት ባካሄደው ዘመቻ የተሰለበ እጅግ ብዙ ነው። በእሥራትና በድብደባ የዕድሜ ልክ አካለ ጉደሎ የሆኑ አሉ። ብዙው በዚያው በጦርነቱ ወቅት አልቋል። ቢሆንም የተረፈው ሠላሣ ሺህ አያንስም። በዚያን ወቅት ኢትዮጵያውያን ይኖሩበት የነበረው ዕድሜ ረዥም አልነበረም። እያንዳንዱ የአካል ጉዳተኛው ለአሥራ አምስት ዓመት በአካለ ጐዶሎነት እንደሚኖር፤ የአካል ጉድለቱ የመሥራት አቅሙን በግማሽ እንደቀነሰበት ቢታሰብ 82,125,000 ብር አጥቶአል ማለት ይሆናል።

የዱር አራዊት ታላቅ ሃብቶች ናቸው። በጦርነቱ ጊዜ ብዙ አልቀዋል። ቁጥራቸው ስንት እንደነበረ የሚያስረዳ ምንም ነገር የለም። ሦስት ሚሊዮን ያህል እንደሞቱ ቢቆጠር ብዙ አያሳስትም ዓይነታቸውም ብዙ ስለሆነ ዋጋቸውን በአስተማማኝ ለመገመት ያመቻል። የጦጣም፣ የዝሆንም፣ የቀጭኔም፣ የአንበሳም ዋጋ በአማካይ ቢወሰድ ይሻል ይሆናል። ለአንድ አውሬ በአማካይ ግምት 20 ብር ቢሰጥ የ60,000,000 ብር ሀብት ወድሞአል ማለት ነው። ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም በሕዝብ ጉልበት የተሠራው መንገድ ግምት ከ300 ሚሊዮን ብር አያንስም። ስለዚህ በአነስተኛ ግምት ጦርነቱ በኢትዮጵያ ላይ ከ3,980,135,500 ብር ያላነሰ የኢኮኖሚ ጉዳት አድርሶአል። (በተጨማሪ «አባሪ ሠሌዳ*» ይመልከቱ።)

**ኢጣልያኖች ከሕዝብ የገፈፉት መሣሪያና ዋጋው**

| የመሣሪያው ዓይነት | ከአዲስ አበባ[11] | ከሐረርጌ[12] | ከአንኮበር[13] | ከኢትዮጵያ[14] | ድምር | ዋጋ[15] |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠመንጃ | 11,353 | 1,420 | 447 | 383,559 | 396,779 | 79,355,800 |
| መትረየስ | 191 | 24 | 4 | 1238 | 1457 | 7,285,000 |
| ሽጉጥ | 169 | - | - | 2259 | 2428 | 121,400 |
| ድምር | | | | | | 86,762,200 |



ሁኔታውን ለማሳየት ነው እንጂ፣ ጦርነቱ ያደረሰውን ጉዳት በምልአት ለማሳየት የሚቻል አይደለም። ለምሣሌ በሕዝቡ ላይ የደረሰው የሞራል ጉዳት በምን ይገመታል? በዓለም የተዋረደው ውርደት በምን ይገመታል? ከቤተክርስቲያን ጋር የተቃጠሉ ንዋየ ቅድሳት ለዘለዓለም የጠፉ ናቸው። ገንዘብ የተገኘ ዕለት ከሱቅ የሚገዙ አይደሉም። የአክሱምም ሐውልት አንዱ ነው።

ጦርነቱ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን የኢኮኖሚ ጉዳት ተመልክተናል። በተለይ በኢኮኖሚ ረገድ ስንመለከተው ኢትዮጵያ ያገኘችውም ጥቅም አለ። ጉዳቱን ተመልክተን ጥቅሙን ወደ ጐን ብንተው አመለካከታችን ምሉዕ አይሆንም። ስለዚህ የተገኘውንም ጥቅም አጣምረን መመልከት ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ ከጦርነቱ የደረሰባት አንዱ ጉዳት በማኅበራዊ ጉዳይ ረገድ የደረሰው ለውጥ ነው። በዚህ ረገድ አስመራሪ የርክሰት ጉዳዮች ደርሰዋል። ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ህገ ወጥ የብልግና ሥራ ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ወጣቱ ለወላጆች መታዘዝ ተወ። ስካር፣ ሲጃራ ማጤስ ያዘ። አነጋገርም የጣልያንኛ ቃላትን በመቀላቀል ሆነ። የኢጣልያ ወታደር ከሴቶች ለመገናኘት የገባው እስኪወጣ ድረስ ይጠብቃል። ከሥራ ሰዓት ውጭ ዋናው ሥራ መጠጥና ፈቃድ ሥጋ መፈፀም ሆነ።[16] ይህ ሁኔታ በማኅበራዊ ጉዳይ ረገድ ከደረሱት ጉዳቶች አንዱ ገጽታ ነው።

ሂደቱ አንዳንድ ጠቃሚ ጐንም ነበረው። በሕግና በሥርዓት ሊፈታ ያልቻለው የባሪያ ነፃነት ጉዳይ ከግብ ደረሰ።[17] የባሪያ ቁጥር ከኅብረተሰቡ ከሩብ እስከ ሲሦ በሚገመትበት ሥርዓት ይህ ፈጣን ክስተት ቀላል አልነበረም። መሣፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ገባሩ እፎይታ አገኘ። ይህ እፎይታ ከጦርነቱም በኋላ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ቀጠለበት። የገባር ሥርዓት ፈረሰ። ገበሬ ለመልከኛ፣ ለጉልተኛ፣ ለሻለቃ ሲሦ የመጥመድ ሥርዓት ተሻረ። ማር መቅዳት ቀረ።

በመኳንንቱና በመሣፍንቱ ወገ አጥባቂነት ተቀነሰ። ሠርቶ የመኖር መንፈስ ተቀሰቀሰ። የመማር የማወቅ ፍላጐት ከፍ አለ። ሰው ዘመናዊውን ያኗኗር ሥርዓትና የአሠራር ዘዴ ተለማመደ። ለወንዱ የመካኒክነት፣ የኤሌክትሪክ ሥራ፣ ግንበኝነት አናጢነት፣ ድንጋይ እያነጠፉ መንገድ መሥራት አስተማረው። ለሴቱ የጽዳት ሥራ፣ የአውሮፓውያን የምግብ አሠራር፣ የመስተንግዶ ሥርዓት አስለመደው። መንግሥታቸው ትምህርት ለኢትዮጵያውያን ለመስጠት ክጅሎት አይኑረው እንጂ፣ ጣልያኖች የቴክኒክ እውቀት ለመስጠት ትጉህን ነበሩ። በዚህ ሥራቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

የእስፖርት እንቅስቃሴ ተጠናከረ። ምንም ዓላማው ወጣቱን ለሀገሩ ነፃነት እንዳይታገል ሽፋን ለመስጠት ቢሆን፤ እንደነ አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ያሉትን የስፖርት ሰዎች ኮትኩቶ ማሳደጉ ለኢትዮጵያ ጥቅም ሆነ። ሲኒማ

የማየት፣ ሬዲዮ የማድመጥ፣ ጋዜጣ የማንበብ ልምድም በከተማ ነዋሪው ወገን ዳበረ። ይህም ንቃት ሰጠ።

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ካካሄደቻቸው የልማት ሥራዎች ሁሉ ከፍተኛው የመንገድ ሥራ ነው። መንገድ እስከየት እንደተሠራ ቀደም ብሎ ተገልጾአል። ከዚህ የምንመለከተው የወጭውን ሁኔታ ነው። በመንገድ ሥራ ረገድ ኢጣልያ ወጭ ያደረገችው ጠቅላላ ገንዘብ እስከ አንድ ቢሊዮን ብር እንደሚደርስ ይገመታል።

ጣልያኖች ጠቅላላ ቁጥራቸው 4007 የሚሆን ልዩ ልዩ እንዱስትሪዎች አቋቁመው ነበር። ለእነሱም በድምሩ 1,205,357,100 ብር እንደ አወጡ ተመዝግቦአል።

ሌላው የጣልያኖች የልማት ሥራ እንቅስቃሴ በእርሻ ነበር። ለባለርስቶች ግምት ከፍለዋል። ልዩ ልዩ የእርሻ መሣሪያዎች አስገብተዋል። ሦስት መቶ ሰባ ሦስት ቤቶች በእርሻዎቹ አካባቢ አሠርተዋል። የአንዱን ቤት ዋጋ 75 ሺህ ሊሬ አነሱ ራሳቸው ገምተውታል። ስለዚህ ለእርሻ ሥራ ማካሄጃ 191,563,400 ብር እንቨስት ሳያደርጉ አልቀሩም።

ዋና ዋና ከተሞችን የሚያገናኝ የስልክ መሥመር ዘርግተዋል። ለፕሮፓጋንዳቸው ሥራ ማካሄጃ ሬዲዮ ጣቢያና ማተሚያ ቤቶች አቋቁመዋል። ለዚህም ሃምሣ ሚሊዮን ያህል ብር ሳያፈስሱ የቀሩ አይመስልም።

ጣልያኖች ከአካሄዱአቸው ሥራዎች እንደ መንገድ ሥራቸው ኢትዮጵያን የጠቀመ የለም። የሆቴል ሥራዎችም አገልግለዋል። በአዲስ አበባ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በጐንደር፣ በጅማ፣ በሌሎችም ቤቶች ተሠሩ። ገሚሶቹ ሸክላዎች፣ ከፊሎች ፎቅ ቤቶች ነበሩ። በድምሩ ከ3,000 የማያንሱ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ሳይሠሩ አልቀሩም።

የተሠሩቱም፣

በአዲስ አበባና አካባቢው...............1000.
በጐንደርና አካባቢው....................500
በድሬዳዋ.................................700
በጅማና አካባቢው.......................300
በሌሎችም ትናንሽ ከተሞች.............500
3,000

እንደሆነ ይገመታል። ከጠላት መባረር በኋላ በትምህርት ቤትነት፣ በሃኪም ቤትነት፣ በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤትነት፣ በመኖሪያ ቤትነት አገልግለዋል። እስከ ዛሬም እንደ አገለገሉ ናቸው። የመሣሪያ ዋጋቸው፣ ከ133,928,500 ብር የማያንስ አይመስልም።

ከብዙ ክርክር በኋላ አርባ ሚሊዮን ብር የጦር ካሣም ከፍለዋል። የጦርነት ዓላማቸውን ለመፈፀምና የአስተዳዳሩን ሥራ ለማካሔድ ከፍተኛ



ገንዘብ ወጭ አድርገዋል። እሱ የራሳቸው ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያን የሚመለከት አይደለም። መጠኑን ወደ መገመትም አንገባም። እኛ የምንመለከተው ኢትዮጵያ ላይ በልማት ረገድ እንቨስት ያደረጉትን ብቻ ነው። እሱም ከ2,620,843,000 ብር አይበልጥም። /ሠንጠረዥ1/ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሱት ጉዳት ግን ከ4,006,897,900 ብር አላነሰም። /ሠንጠረዥ 2/ ስለዚህ በኢኮኖሚ ረገድ ብቻ ከ1,446,054,900፣ በአጠቃላይ ከ1.5 ቢሊዮን ብር ያላነሰ ኪሣራ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ አድርሳለች። የዓለም ኅብረተሰብ አርባ ሚሊዮን ብር ካሣ የቆጠረው እንደ ልማዱ በኢትዮጵያ ላይ አድልቶ ነው።

## ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ እንቨስት ያደረገችው ገንዘብ

1. ለ6995 ኪ.ሎ ሜት መንገድ ሥራ
   /በእንግሊዞች ግምት/[18]......................1,000,000,000
2. ለ4007 ኢንዱስትሪዎች ማቋቋሚያ......1,205,357,100
3. ለእርሻ ሥራዎች መቋቋሚያ [19]
   ሀ. ለመሬት ግምት የተከፈለ.......................503,200
   ለ. ለእርሻ ሥራዎች መቋቋሚያ...............178,571,400
   ሐ. ለ373 ቤቶች ማሠሪያ.......................12,488,800
   ድምር.........................................191,563,400
4. ለስልክ መሥመር መዘርጊያና ለሬዲዮ
   ጣቢያ-ማቋቋሚያ...................................50,000,000
5. ለ300 የከተማ ቤቶች ማሠሪያ..................133,928,500
6. ኢጣልያ የከፈለችው የጦር ካሣ...................40,000,000
   ጠቅላላ ድምር[20]...................................2,620,843,000.

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Alberto Sabacchi, *Ethiopia Under Mussolini*, p.47.
2. ጦርነቱ በአውሮፓ ያለቀው በሚያዝያ 1937 ዓ.ም ነበር።
3. አንድ ፓውንድ በአሥር ብር ምንዛሬ ሂሣብ።
4. ቢ.ዴዝሞንድ፣ ትርጉም ታደሰ በየነ እርገጤ፣ *የኢትዮጵያ አርባ ኩንታል ወርቅ የት ደረሰ?* ፣ገጽ 115-120፣ 156-159፣ 345-349።
5. ጆን ስፔንሰር፣ *ፕርሥ የገባች ሀገር* ፣ትርጉም መንግሥቱ ኃይለማርያም አርአያ፣ መዝገቡ ተክሌ ቢልልኝ፣ ገጽ 91።
6. Sabacchi, p.105.
7. ሠሌዳውን ይመልከቱ።
8. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 224-225።
9. ምንዛሬ አንድ አንድ ፓውንድ 10 ብር።
10. በጸሐፊው ግምት። የሥራ ዋጋ በቀን ሃምሣ ሂሣብ።
11. እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 150።
12. እስከ ነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ ፣ገጽ 154።
13. ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ ፣ገጽ 151።
14. ከመስከረም 30 ቀን 1929 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1932 ዓ.ም። Sabacchi, p.180.
15. በፀሐፊው ግምት ጠመንጃ በ300፣ መትረየስ በ1000፣ ሽጉጥ በ50 ብር። መድፍ 222 ሲወሰድም የሕዝብ ባለመሆኑ አልታሰበም።
16. ገሪማ ታፈረ፣ ጎንደሬ በጋሻው፣ ገጽ 69-70።
17. ለጸስ ጌ ደሴቦ፣ *የኢትዮጵያ የገበሬ ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዚም*፣ ገጽ 67።
18. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 202።
19. Sabacchi, p.100-104.
20. የምንዛሬ ሂሣብ፣
    ሀ. አንድ የእንግሊዝ ፓውንድ 10 ብር።
    ለ. አንድ ብር 2.24 ሊሬ።



# ምዕራፍ ሃምሣ ሰባት
# የጦርነቱ ጠቅላላ ግምጋሜ

በአጠቃላይ የጦርነቱን ሁኔታ መገምገም ግንዛቤን ለማዳበር ይረዳል። በግምገማው ሂደት ውስጥ አንዳንድ ድግግሞሽ ቢያጋጥም መታገስ ነው።

ጦርነቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ተካሂዶ ከትክክለኛ ፈፃሜ የደረሰ ታላቅ ገድል ነው። ጦርነቱ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጫረበት ክብሪትና ይኸው ጦርነት ከፍፃሜ የደረሰበትን ድል ያበሠረ ነው። ይህንን አለማመን ታላቅ የታሪክ ጭብጥ በዝንጋኤ መልቀቅ ነው።

ይህ ጦርነት በቅኝ ገዥነት በቆመው በነጩ ዘርና፣ በቅኝ ተገዥነት በሚማቅቀው ነጭ ባልሆነው ዘር መካከል ለምዕተ ዓመት ሲካሄድ ለቆየው ትንቅንቅ መደምደሚያ የሆነውን የነፃነት በር ከፈተ። በአድዋ ጦርነት የነጭ የበላይነት ከጥያቄ ላይ እንደወደቀ ሁሉ፤ በዚህኛው ጦርነት ደግሞ የነጭ የበላይነት ቀረ። የቅኝ አገዛዝ ዘይቤ ከመጥበቅ ወደ መላላት፣ ከመያዝ ወደ መልቀቅ ዞረ። የጭቁን ሕዝቦች የነፃነት እንቅስቃሴ ተጀመረ። ይህንን እውነታ ዓለም መቀበል አይችልም። ይጉመዝዘዋል። ስለዚህ አንዳንድ ማስረጃ ማቅረብ ግድ ይሆናል።

ጦርነቱ የተቀሰቀሰው በኢጣልያ እብሪት ነው። ሌላ ምክንያት ኖሮ አይደለም። የተካሄደውም በኢጣልያ አጥቂነትና በኢትዮጵያ ተከላካይነት ነው።

በኢጣልያ ወገን ጦርነቱ በደንብ ታስቦበታል። የአርባ ዓመት ዝግጅት ተደርጉበታል። በፖለቲካ ረገድ በአውሮፓ ተቃውሞ እንዳይነሣ የዲፕሎማሲ እርምጃ ተወሰደ። ታላቅ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተካሄደ። ኢትዮጵያን ለማስነወር ያልተደረገ ነገር አልነበረም። የጣልያናውያንን ልቡና አንድ አድርጎ ለጦርነት ለማነሳሳት ጥረት ተደረገ። ሕዝቡም ተስማማ። ንጉሡ ኢማኑኤል ሣልሣዊ አሥመራ ድረስ መጥቶ ጉብኝት በማድረግ ሀሳቡን አፀደቀ። ቤተ ክህነቱ ተስማማ። ሊቀ ጳጳሱ ቡራኬ ሰጠ።

በመሣሪያ ረገድ ልዩ ዝግጅት ተደረገ። ከሽጉጥ እስከ መድፍ፣ ከቦምብ እስከ መርዝ ድረስ ተዘጋጀ። የጉደለውም ተገዛ። ወታደር ከኢጣልያ፣ ከሊቢያ፣ ከኤርትራና ከሶማሊያ ተመለመለ ሠለጠነ። በመርከብ ተጓጉዞ ኤርትራና ሶማሊያ ሠፈረ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሠርጎ በመግባት ልዩ ልዩ ምሥጢራትን ለማወቅ ጥረት ተደረገ። የሀገሪቱ መልክአ ምድራዊ ጥናት ለጦርነትም፣ ለሠፈራም፣ ለልማት ሥራም በሚረዳ መልክ ተካሄደ። ሕዝቡን እርስ በርስ በዘር፣ በጐሣ፣ በሃይማኖት ለመለያየት ታላቅ ሙከራ ተደረገ። መሣፍንቱንና መኳንንቱን በጥቅም ለመደለል ተሞከረ። ለዚህ ሥራ ሚስዮናውያን በብዛት ተሰማሩ። በልዩ ልዩ ቦታ የተተከሉ ቆንስላዎችን በመተገን የዲፕሎማቲክ ሰዎች ተልእኮአቸውን በሚገባ አከናወኑ።

በኢትዮጵያ ወገን ሁኔታው በሰላም ለመኖር በሚደረግ ጥረት ላይ የተመሠረተ ነበር። ስል ሥልጣንና ጥቅም ሽሚያ እንጂ፣ ስለሀገር መከላከል ያሰበ የለም። ከ1900 ዓ.ም በኋላ ኢትዮጵያ የዝቅዝቂት ነው የተጓዘችው። ችግሩ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የረጅም ጊዜ ሕመም ጀመረ። ንጉሠ ነገሥቱ ከነጭ ሰው እጅ ወደቁ። በደዌ ላይ ጥልፍልፍ ነገር መጣባቸው። ለአልጋ ወራሽነት የተመረጡት ልጅ ኢያሱ ለተመረጡበት ሥራ ብቃት አላሳዩም። ችግሩ አፄ ምኒልክ ከሞቱም በኋላ ቀጠለ። ወጣቱን መሥፍን ከሥልጣን አስወርዶ ንግሥት ዘውዲቱን የመተካት ሥራ ተካሄደ። እሱም ብቻውን በቂ ሊሆን ስለአልቻለ፤ በቅርብ የሚረዳቸው ሌላ ወጣት መሥፍን አስፈለገ። ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ራስ ተብለው ባለሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽ ሆኑ። ይህም የራሱ የሆነ ችግር ነበረው። ይህ የፖለቲካ ቀውስ የርስበርስ ግጭት አስከተለ። መንግሥት ከወሎና ከጐንደር ጋር ተዋጋ። ውጊያው በሸዋ ስም ተካሄደ። ነገር ግን ሸዋ በተደረገው ለውጥ አላመነበትም። የውስጥ ቀውስ አጋጠመው።

በዚህ ዓይነት ለውጭ ኃይል መግቢያ በር ተከፈተ። አፄ ምኒልክ "ልጄን የከዳ ርጉም ይሁን። ጥቁር ውሻ ይውለድ" በማለት የረገሙት እርግማን፤ "ነፋስ እንዳይገባባችሁ" ብለው የሰጡት ምክር አድማጭ ሳያገኝ ቀረ። በዚህ ሁሉ ምክንያት በሀገር መከላከያ ረገድ አንዳች ዝግጅት ሳይደረግ የ1928 ዓ.ም ጦርነት ተቀሰቀሰ። ጦርነቱ ሲቀሰቀስ በኢትዮጵያ እጅ ላይ የነበረው፤ በ1915 ዓ.ም አባል የሆነችበት የዓለም መንግሥታት ውል የተፃፈበት ወረቀት ብቻ ሆነ። የፈረንጅ መካር ተሰበሰበ። ገሚሱ ረዳት በመምሰል፣ ሌላው አስታራቂ በመምሰል። አንዱም ለኢትዮጵያ የሚበጅ አልሆነም። በማወቅም ባለማወቅም አብዛኛው ኢትዮጵያን የሚጐዳ ሆነ።

ኢጣልያ በሰሜን ከአሥመራ በደቡብ ከሞቃድሾ እየተነሣች፤ እንደ አሰኛት በመንደርደር ኢትዮጵያን አጠቃች። በጥይት በቦምብ በመርዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፈጀች። ድንበር ጥሣ በሁለቱም ወገን ገባች። የዓለም ማኅበር አንዳች ከማድረግ ስሞታ በማድመጥ ብቻ ሞቱን አሸለበ። እንግሊዝ ፈረንሣይን ተቀጽላ በማድረግ አስታራቂ በመምሰል ኢትዮጵያን የሚጐዳ፣ ኢጣልያን የሚጠቅም፣ የእንግሊዝን የራስዋን ጥቅም የሚያዳብር ሃሳብ ይዛ ብዙ ነገር አጠነጠነች።

ጣልያን ድል አድርጐ ሲገባ ንጉሠ ነገሥቱ አገር ጥለው ሄዱ። ከጣልያን ጋር የውስጥ ግንኙነት ያልነበራቸው መኳንንትና መሣፍንትም እንደዚሁ አደረጉ። አብዛኞቹ መኳንንትና መሣፍንት ወራሪውን ወድደው ለምደው ከእሱ ጐን ቆሙ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻውን ፍኖተ መስቀሉን ተሸክሞ ሀገር የመከላከል ሥራውን ቀጠለ። በመዓልት በሌሊት ተዋጋ። አጥንቱን ከሰከሰ፣ ደሙን አፈሰሰ። ቀደም ብሎ በልዩ ልዩ ስም ገብቶ



ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰገሰገ ነጭ ዘመዱን አገኘ። ፈነጠዘ። በተለይም ግሪክና አርመን።

የኢትዮጵያን ውድቀት ያፋጠኑት ነገሮች ብዙ ናቸው። የርስ በርስ አለማመስማማት ዋናው ነው። ሥልጣን በማዕከላዊ ደረጃ በጥብቅ መያዙም አንዱ ችግር ሆነ። በዚህ ላይ ደግሞ ከሹማምንቱ የሚበዙት ኢትዮጵያዊነታቸውን የሸጡ ከሀዲዎቹ ነበሩ። ተው ባይም አልነበራቸውም። ማንኛውም የቤተ መንግሥቱ ምሥጢር፣ የንጉሠ ነገሥቱ መልዕክት ጭምር ለጣልያኖች ክፍት ሆነ።

በጦርነቱ አካሄድም ላይ ብዙ ጉድለት ነበር። ባለው የሰው ኃይልና መሣሪያ ለመጠቀም በቂ ጥረት አልተደረገም። ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪነት ከነበራቸው መሪዎች አብዛኞቹ ከእሥራትና ከግዞት ገቡ። በሥልጣን የሚንቧቹት ከሀዲያን ሆኑ። ራስ ብሩን የመሰለ የጦር ሰው ከሥልጣን አስወርዶ በፊታውራሪነት መሸምቀቅ ለምን ነበር? ኮርማሽ የነበረው የጦር መሣሪያ ለስገሌ ጊዜ ተፈልጐ ነበር። ለምን ለጣልያን ወረራ እንዲውል ሳይደረግ ቀረ? ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የመኪና መንገድ ተሠራ። ጠላት ስተት ብሎ ገባበት። እንደካራማራ ያሉ የተፈጥሮ መከላከያነት ያላቸው በሮች ተለቀው ጦሩ አጋዬን በረሃ ውስጥ ወርዶ አለቀ። አምባላጌን የሚያህል የተፈጥሮ ምሽግ እንዴት በነፃ ለጠላት ተለቀቀ? መጋቢት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ጦርነት እንዲደረግ የተሰጠው ትዕዛዝ ተለውጦ፤ ሠራዊቱን ለምን ለሙሉ ቀን የአየር ድብደባ አጋለጠ? ለጊዜው መልስ የለም። ነገር ግን እነዚህ ስህተቶች ትውልድ የሚረሳቸው አይደሉም።

እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር ምን እንደ አደረገ መመልከት ግንዛቤ ይሰጣል። ተቀፍድዶ ከታሠረበት ከማዕከላዊ እዝ ስለተለቀቀ፤ የኢትዮጵያ ጀግና ጠላቱን በራሱ ሃሳብና ዘዴ ገጠመው። የገዛ መሣሪያውን እየቀማ ተለቀቀበት። የፍልሚያው ሥራ ጣልያን በገባባቸው በትግራይና በወሎ ተካሄደ። ዋና ዋናዎቹ የጦር ቦታዎች ጐንደር፣ ውሎ አድሮም ጐጃም ሆኑ። በሸዋ መንዝና ተጉለት፣ ቡልጋና ሸንኮራ፣ ይፋትና አንኮበር፣ መርሐቤቴና ሰላሌ፣ ግንደ በረትና የጉራጌ አገር ሆኑ። ኢሉባቡርና ከፋ ለመጀመሪያው ጊዜ ደህና አዝማሚያ አሳዩ። ነገር ግን ወዲያው ቀዘቀዙ። በሐረርጌ፣ በባሌና በአርሲ የነበረው ጦር የተቻለውን ያህል ሠራ። ነፍጠኛ ወደ ስደት አመራ። ሲዳሞ በመጀመሪያው ጊዜ ታላቅ ሥራ ሠራ። ነገር ግን ዕድሜ አላገኘም። ጋሞ ጐፋ ወደ ኬንያ የተጓዘውን ስደተኛ አገዘ። የተቻለውን ያህል ተዋጋ። ወለጋ የተቻለውን ያህል ተከላከለ። አፋር በቡልጋ፣ በአንኮበርና በይፋት በኩል የነበሩትን አርበኞች ረዳ። በጐ ፈቃደኛ የሆኑ ኤርትራውያን ከጣልያን እየከዱ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጐን በመቆም የማይናቅ ድጋፍ ሰጡ።

አርበኞች ይህንን ይሥሩ እንጂ ድክመቶችም ነበሩባቸው። ከድክመቶቻቸው ዋነኛው በጋራ የሚመሩበት ድርጅት ለማቋቋም

አለመቻላቸው ነው። የነፃነት እንቅስቃሴን ከሚያጠናክሩ ነገሮች ዋነኛው የአስተባባሪ ድርጅት መኖር ነው። ነገር ግን አርበኞች እንደዚህ አላደረጉም። ሁሉም በየፊናው የወደደውንና የቻለውን አደረገ። ድርጅት እንዳያቋቁም አፍራሽ ኃይሎች ነበሩ። ከእነዚህ አፍራሽ ኃይሎች አንዱ ጣልያን ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ የቀድሞዎቹ የገዥ ወገኖች ነበሩ።

ይህም ሆኖ አርበኛ አሰባሳቢ አካል ለመፍጠር ጥረት ማድረጉን አላቋረጠም። በቡልጋ የመልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መንገሥ፣ የሆለታ መኰንኖች የጥቁር አንበሳን ድርጅት ማቋቋም፣ በወሎና በጐንደር ልጅ ዮሐንስን አስተባባሪ ለማድረግ መሞከር፣ በተጉለት የኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር መመሥረት የዚህ ጥረት አካል ናቸው። በጐንደር አርበኛ መከረና መርጦ መሪዎች ተሾሙ። በጐጃም ልዩ ልዩ ማኅበራት ተቋቋሙ። የሪፐብሊክ መንግሥት ለመመሥረት የሞከሩም ነበሩ። ነገር ግን ከአገር ባህል ጋር ሥምረት ስለአልነበረው ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። ሌሎቹ ግን በተወሰነ መጠን ለተወሰነ ጊዜ ይሁን እንጂ ውጤት አስገኝተዋል። የእነራስ አበበ፣ የእነ ራስ ውብነህ፣ የእነ በላይ ዘለቀ ጥንካሬ በእነዚህ ድርጅቶች ተመሥርቶ የተገነባ ነው። ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ወደ ሥልጣን የተመለሱት ደጋፊዎቻቸው በብርታት ስለሠሩ መሆኑ ነው። ከዚህ ሁኔታ ትምህርት ሊወሰድበት ይገባል። ድርጅት ዋና አጠናካሪ ኃይል ነው። ነገር ግን በሀገር ባሕልም ሥርዓት ላይ ካልተመሠረተ ዘለቄታ አይኖረውም። ይህ በደንብ ሊጤን ይገባል።

ሌላው የአርበኞች ድክመት የርስበርስ አለመስማማት ነው። በቁም ነገር ብቻ ሳይሆን በጥቃቅን ጉዳይ የተጋጩበት ሁኔታ ተከስቶአል። በሥልጣን ምክንያት ለተነሣው ጠብ ጎንደር የልጅ ወሰን ኃይሉና የደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ፤ በሴት ምክንያት ለደረሰው ቡልጋ የፊታውራሪ ዝቅ አርጌና የፊታውራሪ ሞገሴ መኩሪያን እልቂት፤ በአሰባልታ ምክንያት ለሚነሣ ጠብ ቡልጋ በፊታውራሪ ወልደፃድቅና በፊታውራሪ ደባልቄ መካከል የተከሰተው ግጭት፤ ቃልን ባለማክበር ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ቡልጋ በረከት የእነ ፊታውራሪ አጉናፍር እልቂት ለአብነት ሊጠቀስ ይችላል። በዚያ ቀውጢ ቀን በጥቃቅን ምክንያት አለመግባባት እየተፈጠረ ኃይልን መቀነሱ ያሳዝናል። ለወደፊቱም ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

ኢትዮጵያን ለማዳን የተደረገው ፍልሚያ በአንድ የጦር ሜዳ ማለትም በማይጨው ብቻ ማክተሙ ያሳዝናል። መጋቢት 21 ቀን ሲዋጋ ከሠልፍ የገባው በዚያው ቀን ተዋግቶ፤ ከኋላ ይጠብቅ የነበረው ጦር በማግሥቱ መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ደግሞ ቢሆን የተሻለ ውጤት ይታይ ነበር። ከዚህም በስተቀር በየቦታው ተበትኖ ቢከላከል ጠላቱን መመለስ ባይችል እንኳን፤ የጦርነቱን ዕድሜ ማስረዘምና የሀገሪቱን ሕልውና ከውድቀት ላይ የመጣሉ ፍጥነት ይቀነስ ነበር። በጦርነቱ ጊዜና ቦታ እየመረጥን ከቦታ ወደ



ቦታ እየተዘዋወርን በዝግታ እንዋጋ የሚለው አመለካከት ብስለት የሚለካው ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ሲታይ ነው። የጦርነቱ በአንድ ጊዜ ማለቅ የአውሮፓ የጦር መሪዎችን ጭምር አስደንቆአል። ሁለትና ሦስት ዓመት የወሰደ ቢሆን፤ የአውሮፓም ልቡና ተለውጦ ኢትዮጵያን ወደ መደገፍ ይመለስ ነበር። በአንድ ቀን ድል የኢትዮጵያ ጦር ተበተነ። መበተኑ ከእልቂት አዳነው። ከእልቂት መዳኑ በመጠነኛ ሁኔታም እንኳን ቢሆን አርበኝነትን ለማቋቋም ረዳ።

ንጉሠ ነገሥቱንና መንግሥታቸውን የሚያስመሰግን ሥራ የተሠራው በውጭ ግንኙነት ረገድ ነው። የአጥቂውን በደል ለማሳየትና ለኢትዮጵያ ዕርዳታ ለማግኘት የተደረገው ጥሩ ነበር። ነገር ግን እሱም እንደሌላው ጉዳይ ሁሉ እንከን አላጣውም። የመጀመሪያው ችግር ንጉሠ ነገሥቱ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ የነበራቸው ትምምን እጅግ ጠንካራ ሆኖ መፈናፈኛ ማሳጣቱ ሆነ። ሌላው ችግር በሀገር ውስጥ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎችን ለመቆጣጠር አለመቻሉ ነበር። እጅግ ቢያንስ የኢጣልያ ዜጐች ከሀገር መውጣት ነበረባቸው። ሌላው ችግር እንደ ሌላው ሥራ ሁሉ በውጭ ጉዳይም ከሐዲያን ተሰገሰጉበት። ሮም የነበረው አምባሳደር አፈወርቅ ገብረኢየሱስ አፈ ቄሣር ተብሎ በኢትዮጵያ ያሻውን ተናገረ። ፓሪስን ያህል የፖለቲካ ማዕከል ወልደማርያም አየለ ለቀቀው። ከዚህ ሁሉ ጋር እነ አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንዞ ትዕዛዝ በውጭ ጉዳይ ረገድ የሚደነቅ ሥራ ሠሩ።

ሀገር በጠላት እጅ በወደቀች ጊዜ ጥሎ መሔድ ተገቢ ነው ተገቢ አይደለም የሚለው ክርክር ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የታሪክ ሥራ ይሆናል። ከአሁኑ ትውልድ በዚህ ረገድ የሚጠበቅ ነገር የለም። ነገር ግን ለተከታዩ ትውልድ ጥቅም ሲባል ጉዳዩ ሲነሣ ይገባዋል። ስለስደት ያለውን ክርክር ከዚህ ላይ ትተን በወጭ አገር የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን የፈጸሙትን ወደ መመልከት እንሻገራለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ንጉሠ ነገሥቱ ሦስት መልካም ሥራዎች ሠርተዋል። ከነዚህ መልካም ሥራዎች አንዱ በጀኔቭ ጉባዔ ላይ በመገኘት የኢትዮጵያን አቤቱታ ለዓለም ኅብረተሰብ ማሰማታቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሥልጣን እንዲለቁ በጥቅም ለመደለል ጣልያኖች ያደረጉትን ሙከራ ማክሸፋቸው ነው። በዚህ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ ፅንዐት ባያሳዩ ኢትዮጵያ እጅግ አስነዋሪ ከሆነ ነገር ላይ ትወድቅ ነበር። ሦስተኛው በጐ ነገር የነበረባቸውን የጦርና የነገር ወጥመድ በጥበብ አልፈው ኢትዮጵያን ለድል ያበቃ አመራር መስጠታቸው ነው። ወደ ቀድሞ ሥልጣናቸው ሊመለሱ የቻሉትም ስለዚሁ ነው።

ሌሎችም ስደተኞች የተቻላቸውን ያህል አገራቸውን ረድተዋል። በለንደን የነበረው ቡድን ኢትዮጵያ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ እንዳትረሣ ጥረት አድርጐአል። በፓሪስም የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጀርመኖች እስከ ገቡበት ቀን ድረስ ሥራውን ቀጥሎአል። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ቤተክርስቲያን ገዳም ሲተርፍ የቻለው በስደተኛው ብርታት ነው። በሱዳን የነበረው ስደተኛ ነፃነትን ለማስመለስ ከተደረገው ፍልሚያ አስኳል ሆነ። በኬንያ የነበረው የተጣለበትን የኑሮ አሽክላ በጣጥሶ ከጦርነቱ በመግባት ድርሻውን ተወጣ። በአሜሪካ የነበሩትም ማኅበር በማቋቋምና ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የኢትዮጵያን በደል ለሕዝብ በማሰማት፤ መንግሥቱ ይዞት የነበረውን ጣልያንን የመደገፍ አዝማሚያ አስጥለዋል። በጅቡቲና በበርበራ የነበሩም እንደዚሁ የተቻላቸውን አድርገዋል። ተሰደናል ብለው እናት አገራቸውን አልዘነጉትም፤ በተቻላቸው መጠን ተጋድለዋል። ዘርዓይ ደረስና ሻምበል አብዲሣ አጋም ቁጥራቸው ከእነዚህ ተጋዳዮች ውስጥ ነው። የሀገራቸውን ክብር ለማስጠበቅ እሥረኞች ስንኳን ቸል አላሉም። ራስ እምሩ ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች ያሳዩት ንቀት ከዚህ ሊጠቀስ ይገባል።

አዲስ አበባ የሀገሪቱ መናገሻ ከተማ እንደ መሆንዋ መጠን፤ ስለ ሀገሪቱ ነፃነት የበኩልዋን አስተዋጽኦ ማድረግ ነበረባት። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም። የጠላትን አገባብና ቆይታ የተቀበለው በጸጥታ ነው። ሐምሌ 21 ቀን 1928 ዓ.ም የውጭው ጦር ሰብሮ ለመግባትና ከተማይቱን ለማስለቀቅ ሙከራ በአደረገበት ጊዜ በከተማይቱ የውስጥ እንቅስቃሴ አልታየም። የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጣልያኖች ሴት ወንዱን ሲፈጁ ፍርግጥ ያለ የለም። ጠላት አዲስ አበባ የገባው ከአንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ ሰው ገድሎ ነው። ነገር ግን የእነዚህ ሰዎች ሙከራ የግለሰብ እንጂ የተቀነባበረ አልነበረም።

በበጎው በኩል ደግሞ ያልተገባ የፀጥታ መናጋት አልደረሰም። በከተማይቱ የሠፈረው የዲፕሎማቲክ ሰው አንዳች ችግር አልደረሰበትም። ጣልያኖች በገቡ ጊዜ አዲስ አበባ ላይ የታየው ሁኔታ ይህንን የሚመስል ሲሆን፤ ሲወጡም ምንም ችግር አልነበረም። የእንግሊዞችም አገባብ ሰላማዊ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ የገቡት ከበቂ ዝግጅት በኋላ ስለነበር ማንኛውም ነገር ሠመረ።

ይህንን በመሰል አጠቃላይ ግምገማ ከህዲያን በሀገራቸውና በወገናቸው ላይ የፈጸሙት በደል እንደገና መነገር አለበት። የኢትዮጵያ መኳንንትና መሣፍንት በጣልያኖች ዘንድ ሞገስ ለማግኘት ያደረጉት ርብርቦሽ አስገራሚ ነው። ግብራቸው ሲመዘን ቀድሞውኑ የተመረጡት በክህደት ሥራ ችሎታቸው እየተመለመሉ ነበርን የሚያሰኝ ነው። የደጃዝማች ኃይለሥላሴ ክህደት የኢትዮጵያን ምሥጢር ለጠላት አሳልፎ ከመስጠት አደረሰ። የእነደጃዝማች ገሠሠ ከጦር ሜዳ መመለስ የሀገርን ሞገስ ቀነሰ። የአባ ጆቢር ጭካኔ የሚዘገንን ነው። በራስ እምሩ የሚመራውን ጦር ከውድቀት አደረሰ። የእነ ደጃዝማች አበራ ካሣ ለፈስፋሳነት ለራሳቸውም ለወገኖቻቸውም ጥፋትን አስከተለ። በአዲስ አበባ የነበሩ ራስ ደጃዝማቾች ሽርጉድ ግድ ነው። ሀገርን ወገንን በመከራ በጭንቅ ጊዜ መክዳቱ እጅግ አሳፋሪ ጉዳይ ነው። መጭው ትውልድ ከአለፈው ትውልድ መማርና ማወቅ ያለበት ይህንን ነው።



በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሀገር የመቆምም የክህደትም ሥራ ተካሄደ። የአባ አብርሃምን ክህደት ጵጵስና የሰጡአቸው የእስክንድርያው ፓትርያርክ ውግዘት አልመለሰውም። ከሁሉ በላይ የሚገርመው ገና ጠላት ከመግባቱ በፊት ለዚሁ ሥራ ተዘጋጅተው፤ በአደራ የተሰጣቸውን ለኢትዮጵያ ጦር ልብስና መድኃኒት የሚገዛበትን ገንዘብ መከልከላቸው ነው። ከእምነት ወንድማቸው ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር በሰማይ ቤት ሲገናኙ ምንኛ ትዝብት ይሆንባቸው? አባ አብርሃም ሲሞቱ አባ ዮሐንስ ተተኩ። በታሪክ ፊት የእሳቸውም ዕድል ከአባ አብርሃም አንድ ነው።

የደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የመንበረ መንግሥት ገብርኤልና ከተጉለት የድንበሬ /ግንባርዋ/ ማርያም ማይጨው ዘመቱ። አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ በጦር ሜዳ ላይ ቆሙ። አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ፣ አቡነ ገብርኤል በጎሬ በእምነት ጸንተው የሰማዕትነት ጽዋ ተቀበሉ። የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ከአርበኛ ጋር ቆሙ። የአራዳ ደብረ ጽጌ ጊዮርጊስ ጽላት በቡልጋ አዋጋ። ከአርሲ የሁሩታ ማርያምና የዲሲሳ ገብርኤል፤ እንደዚሁም ከጋሞ ጐፋ የጨንቻ ጊዮርጊስ ወደ ኬንያ ተወሰደ። ካህናት ለተወለደው ጥምቀት ክርስትና በመስጠት፣ የሞተውን በመፍታት፣ የተጣላ በማስታረቅ፣ ለሀገርና ለወገን ጸሎት በማድረግ ታላቅ ዕርዳታ አደረጉ።

በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው የኢካኖሚ ጉዳት ከአራት ቢሊዮን ብር አላነሰም። ጣልያን ኢትዮጵያ ላይ ለልማት አዋለች የሚባለው ገንዘብ 2.6 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው። በዚያውም ኢትዮጵያ እምብዛም አልተጠቀመችበትም። ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ ከ1.4 ቢሊዮን ብር በላይ እንደ ከሠረች ቀርታለች ማለት ነው። ዳግመኛ ተመልሰው በገንዘብ የማይገኙ ብዙ ቅርሶች ተዘርፈዋል፣ ተቃጥለዋል፣ ወድመዋል።

ጦርነቱ የኢትዮጵያን ነፃነት በዓለም ፊት መልሶ አረጋገጠ፡፡ ከነበረባት የውስጥ አንዳንድ የኂሊት ጉታች ኃይል አላቀቃትም። ለአዲስ ሥራ አዘጋጃት። በዚህ ዕድል ምን ያህል እንደ ተጠቀመችበት በቀጣዩ የታሪክ ምርመራ የሚታይ ይሆናል። አጠቃላይ ሁኔታው ይህ ሲሆን፤ ዝርዝሩንና ማስረጃውን ከዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ማየት ያስፈልጋል።

# ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት
# የአድዋና የማይጨው ጦርነት ንፅፅር

ታሪክ ነውና የአድዋንና የማይጨውን ሁኔታ ማነፃፃር ይገባል፡፡ ልዩነታቸው ይብዛ እንጂ አድዋና ማይጨው ተመሳሳይነትም አላቸው፡፡ ተመሣሣይነታቸውን ብናስቀድም የሁለቱም ጦርነት ዓላማ አንድ ነው፡፡ ጣልያን ቅኝ ግዛት አድርጌ ልግዛ፤ ኢትዮጵያ አይደረግም አልገዛም ነው፡፡ ጠብ አጫሪዋ በሁለቱም ጦርነት ጣልያን ነች፡፡ ምንም መሬቶችዋ ተሸራርፈው የተወሰዱባት ቢሆን ኢትዮጵያ ጠብ አልቆሰቆሰችም፡፡

የአድዋን ጦርነት የቀሰቀሰው ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም ወሎ ውስጥ ውጫሌ በተባለ ቦታ የተዋዋሉት ውል 17ኛው ምዕራፍ ነው፡፡ ውሉ የተጻፈው በአማርኛና በጣልያንኛ ቋንቋዎች ብቻ ነው፡፡ አፄ ምኒልክ የፈረሙት በአማርኛ በተጻፈው ላይ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በተለይ ስለውጭ ጉዳይ በሚናገረው በአንዱ አንቀጽ ላይ ብቻ ልዩነት ተፈጠረ፡፡ ይህም በአማርኛው ጽሑፍ የኢትዮጵያ መንግሥት "ፈቃዱ የሆነ እንደሆነ" የሚለው ቃል፤ በጣልያንኛ ቋንቋ በተጻፈው ላይ "ይገባዋል" ይላል ስለተባለ ጠብ ተነሣ፡፡ ጣልያኖች ለአውሮፓ አገሮች አስተላልፈውት የነበረውን የሐሰት ወሬ አፄ ምኒልክ አስተባበሉ፡፡ ሁለቱም ወገኖች በአቋማቸው ጸኑ፡፡ ጦርነቱ ተነሣ፡፡[1] በማይጨው ጊዜ ግን ጠብ የተቀሰቀሰው ኢጣልያ የኢትዮጵያ ግዛት ከሆነችው ከወልወል ውስጥ ገብታ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሱማሌ መካከል ይካሄድ የነበረውን የወሰን ክልል ስለአገደች ነው፡፡ ቢሆንም ሁለቱም ጦርነቶች የተካሄዱት ኢጣልያ ወሰን አልፋ ከኢትዮጵያ ግዛት እየገባች ነው፡፡

በአድዋ ጊዜ ኢትዮጵያ አፄ ምኒልክ፤ የማይጨው ጊዜ ኢጣልያ ቤኒቶ ሙሶሊኒ ነበሩአቸው፡፡ ሁለቱም ለጦርነቱ በቂ ዝግጅት አደረጉ፡፡ አፄ ምኒልክ የትግሬን መኳንንት እነ ራስ መንገሻ ዮሐንስን፣ ራስ አሉላ አባ ነጋን፣ ራስ ሐጎስን ከእነ ሠራዊታቸው አስተባበሩ፡፡ የጅማን፣ የሌቃን፣ የቤኒሻንጉልን፣ የወላሞን የሌላውንም ጐሣ ባላባቶችና ሹሞች ድጋፍ አገኙ፡፡ ጐጃምን በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት አስነሱ፡፡ ጐንደርን በእቴጌ ጣይቱ፡፡ አዲስ ከተያዘው ከደቡብ አገርም የሚበዛው ወገን ተባበራቸው፡፡ ወሎን በራስ /ንጉሥ/ ሚካኤል አማካይነት ያዙ፡፡ ሙሶሊኒም በማይጨው ጊዜ እንዲሁ አደረገ፡፡ የኢጣልያን ሕዝብ ለጦርነቱ በአንድ ልብ አስነሣ፡፡ ሴት ወንዱ፣ ልጅ አዋቂው እንዲተባበረው አደረገ፡፡

በመሣሪያ ረገድ አፄ ምኒልክ ልዩ ጥረት አደረጉ፡፡ ከፈረንሣይ፣ ከኢጣልያ፣ ከግብፅ፣ ከሩስያ፣ ከእንግሊዝ መሣሪያ እየገዙ በታጁራ፣ በአሰብ፣ በዘይላ በኩል በሚራራ እያስጫኑ አስገቡ፡፡ በአድዋ ጦርነት ጊዜ በጠቅላላው ከ3,348,000 ጠመንጃና ከ9,410,000 ጥይት፣ ከ70 በላይ መድፎች ነበሩአቸው፡፡ ከጠመንጃዎቹ 15% እንደዚሁም ከጥይት 43% የተገዛው



ከጣልያን ከራስዋ ነበር፡፡ አፄ ምኒልክ ሠራዊታቸውን መሣሪያ ለማስታጠቅ ያደረጉት ጥረት የሚታወቀው፤ በ1868 እስከ 1870 ዓ.ም አካባቢ በእጃቸው የነበረው መሣሪያ ከ3,000 ይበልጥ እንዳልነበረ ሲታወስ ነው፡፡ በ1988 ዓ.ም የአድዋ ጦርነት አፄ ምኒልክ ከጣልያን ጋር ለመዋጋት የተሰለፉት፣

| | ኢትዮጵያ | ጣልያን | ሚዛን |
|---|---|---|---|
| ወታደር | 145,000 | 22,000 | 1ለ 6+ |
| ጠመንጃ | 110,000 | 17,000 | 1ለ 6+ |
| መድፍ | 42 | 56 | 3ለ 4 |

በሆነ የኃይል ሚዛን ነበር፡፡[2]

በ1928 ዓ.ም የማይጨው ጦርነት፤

| | ኢትዮጵያ | ጣልያን | ሚዛን |
|---|---|---|---|
| ወታደር | 700,000 | 510,000 | 1ለ1 ቅርብ |
| ጠመንጃ | 400,000[3] | 782,320 | 1ለ2 |
| መትረየስ | 3,500 | 23,251 | 1ለ6+ |
| መድፍ | 200 | 2,608 | 1ለ13 |
| ታንክ | ምንም | 2,000 | - |
| ጥይት | 40,000,000[4] | 1,289,416,100 | 1ለ32 |
| የጦር አይሮፕላን | ምንም | 300 | - |
| ፀረ አይሮጵላን | 50 | አላስፈለጋቸውም፡፡[5] | ለኢጣልያን አሸናፊነት ዋናው ምክንያት ይህ ነበር፡፡ |

ሁለቱ ወገኖች ከላይ እንደቀረበው ይዘው ስለነበረ ከአድዋ እስከ ማይጨው ኢትዮጵያ ምን ያህል ወደ ታች እንደዘቀጠች በጉልህ ማየት ይቻላል፡፡

ሌላው መታየት ያለበት በመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ረገድ የነበረው ልዩነት ነው፡፡ አፄ ምኒልክ በሁለት ዓይነት ጥበብ ሠሩ፡፡ ከትግራይ ሽማግሌዎች ጋር ቀደም ብለው በምሥጢር በመስማማት፤ ጣልያኖች ለጦርነቱ ማካሄጃ ያዘጋጁትን ካርታ አበላሹባቸው፡፡ ያበላሹባቸውም የአንዱን ተራራ ስም ለሌላው ተራራ፣ የአንዱን ወንዝ ስም ለሌላው ወንዝ፣ የአንዱን ቤተክርስቲያን ስም ለሌላው ቤተክርስቲያን እንዲያስመዘግቡና ምስቅልቅሉሽ

በታመኑ ወጣቶች እንዲጠና በማድረግ ነበር። ጄነራል አልቤርቶኒ ሲማረክና ሌሎች ሦስት ጄነራሎች የጦር እዛቸው ዝብርቅርቁ ወጥቶ[6] የተሸነፉት በዚህ ጥበብ የተነሣ ነው። ሌላው የምኒልክ ጥበባቸው የጣልያኖች ሰላይ የነበሩትን የኤርትራ ተወላጅ አቶ አውዐሎምን መያዝ ነበር። ጣልያንን ለኢትዮጵያውያን በተመቸ ሁኔታ አምጥተው ከጦር ላይ አጋፍጠው ዘወር አሉ። ጣልያኑ አለቃቸው ጩንቆት "አውዐሎም" እያለ ደጋግሞ ቢጠራቸው፤ "በዋልክበት አያውለኝ" ብለውት ጉዞአቸውን ቀጠሉ ይባላል።[7] በማይጨው ጊዜ ግን ኢትዮጵያ አንዳችም ምሥጢር ከኢጣልያ አላገኘችም። ጣልያኖች ግን ማንኛውንም ምሥጢር ያገኙ ነበር። በንጉሠ ነገሥቱና በእቴጌይቱ መካከል ይደረግ የነበረውን የሃሳብ ልውውጥ ጭምር።

ዳግማዊ ምኒልክ ጦራቸውን ወደ አድዋ ያዘመቱት በምሥጢር ነው። ጥቂት የውጭ አገር ሰዎች በመሣሪያ አጠቃቀም ረገድ ለጥቂት ኢትዮጵያውያን ሥልጠና ከመስጠት በስተቀር፤ ስለጦርነቱ ሁኔታ አንዳች ነገር የማወቅ ዕድል አልነበራቸውም። በአድዋ ጊዜ ማንኛውም ዝግጅት የተደረገው በምሥጢር ነው። ከመሣሪያው በስተቀር ማንኛውም የጦር ሥልት የኢትዮጵያ ነበር። በማይጨው ግን እንዲህ አልነበረም። ለመዋጋት የተሞከረው በፈረንጆች ዘዴ ሆነ። ምክር ከፈረንጆች ሆነ። ጦሩ በአዲስ አበባ አደባባይ ላይ ሰልፍ እያሳየ ዘመተ። እነዚህ ሁኔታዎች ለጠላት አጋለጡት። በማይጨው ጊዜ ትልቅ ተጋድሎ የተደረገው በዲፕሎማሲው ደረጃ ነው። በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ ያልተገባ ተአምኖ ተደረገ። በአድዋ ጊዜ ግን ስሞታ ማሰሚያ አደባባይ አልነበረም። ስለሆነም እዚሁ መክናወን ነበረበት።

የአፄ ምኒልክ አዋጅ የሕዝብን ልብ በፍቅር የሚስብ እንጂ፣ ሥልጣንን የሚያሳይ ትዕዛዝ አልነበረም። አዋጃቸው "...ያገሬ ሰው ካሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም፣ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። ...ለልጅህ፣ ለሚስትህ፣ ለሃይማኖትህና ለእርስትህ ስትል እርዳኝ..." የሚል ቃል ይገኝበታል።

በአድዋ ጊዜ የአውሣ በር በደንብ ተጠብቆ ነበር። አምባለጌ በኢትዮጵያ እጅ ነበር። እቴጌ ጣይቱ ሴት ወይዛዝርቱን ይዘው በድጋፍ ሰጭነት ቆመው ሠራዊቱን እያደፋፈሩ ነበር። ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ታቦታተ ማርያምንና ጊዮርጊስን ይዘው፣ አክሱም ሥዕለ ማርያምን ይዘው፣ ሰንደቅ ዓላማቸውን ጨምረው፣ የጽዮን መልዕክተኞችን እፊት እፊት እያስነሱ ከጦርነቱ ግንባር ላይ ቆመው ነበር። ዳባ የለበሱ፣ የሰሌን ቆብ ያደረጉ እጅግ ብዙ መነኮሳት ከጦሩ ግንባር ገብተው፤ ወደ ፍልሚያ የሚገባውን እያናዘዙ፣ የደከመውን እያወገዙ አዋጉ። በዚህ ላይ ደግሞ የአፄ ምኒልክ ደግነት ሠራዊቱን ወንዱን ሴቱን መነኩሴውን አጀገነው። ስለዚህ ድል ለኢትዮጵያ ሆነ።



በማይጨው ግን እንዲህ አልነበረም።[8] በማይጨው ጊዜ ጦርነቱ አራት ታላላቅ በር አበጀ። በሰሜን በወሎና በጉንደር፣ በደቡብ በኦጋዴንና በቦረና፣ አምስተኛው በር አየር ሆነ። ይህ ሁኔታ በጦርነቱ ሂደት ላይ ታላቅ ልዩነት አመጣ። ኢትዮጵያን ለመሸነፍ፤ ኢጣልያን ለማሸነፍ አበቃ።

## <u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>


1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ 89-86። እና ገጽ 192-196።
2. ላጲሶ ጌ ዲሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግስት ታሪክ*፡
3. በአፄ ምኒልክ የተሰበሰበው ጭሳም በረት ጭምር።
4. ለአንድ ጠመንጃ 100 ጥይት ሂሣብ።
5. የኢትዮጵያ ማስታወቂያ ሚኒስትር፣ የድል መታሰቢያ 25ኛ ዓመት፣ ገጽ 52።
6. ጆርጅ ኤፍ ኤች በርክሌይ፣ ትርጉም ዳኘው ወልደሥላሴ፣ *የአድዋ ዘመቻና የአፄ ምኒልክ አነሳስ*፣ ገጽ 92-115።
7. ከአቶ ገብረመስቀል ክፍለእግዚአ የተነገረኝ።
8. ገብረ ሥላሴ፣ *ታሪክ ዘመን ዘይርዋዊ*፣ ገጽ 218-268።

# ምዕራፍ ሃምሣ ዘጠኝ
# የኢጣልያ ሕልምና ውጤቱ

ኢጣልያ በቅኝ አገር አያያዝ ረገድ ምን ያህል እንደቀረች፤ ይህም ምን ያህል እንዳስቆጫት ቀደም ተገልጾአል። አዲሱ አስተሳሰብም በፋሽስት ፓርቲ አማካይነትና በሙሶሊኒ መሪነት ይህንን ጉድለት ለማምዋላት ብዙ ጥረት አደረገች። ዝርዝሩ ቀደም ብሎ ስለተገለጸ አሁን አንመለስበትም። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው በተለይ በ1931 እና 1932 ዓ.ም አካባቢ የነበረችውን ኢጣልያ ይሆናል።

ይህ ዘመን የኢጣልያ ሁኔታ በደግ ነገር ረገድ ሊገኝ የሚችለው የተገኘበት ወቅት ነበር። ሕልም የነበረው የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እጅ ከገባ አራት ዓመት ሆኖታል። በዓለም ጉባዔያት ተደማጭነት ተገኝቶአል። እንግሊዝም ጀርመንም ከእኔ ሁኚ ከእኔ ሁኚ እያሉ ማባበል አብዝተዋል። አብዛኞች አገሮች ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ገዥነት አውቀዋል። የዓለም መንግሥታት ማህበር ተዳክሟል። የ1931 ዘመን የተጀመረው በዚህ ዓይነት ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ነበር። ነገር ግን በዚሁ አልቀጠለም። ነገሮች እየተለወጡ ሄዱ፤ አለዋወጡም ፈጣንና ተደራራቢ ሆነ።

ኢጣልያ ይብቃኝ አላለችም፤ ተደራራቢ ጥቅም ፈለገች። ከፈረንሣይ ናይስንና ሳቮይን፣ ኮርሲካን፤ እንደዚሁም ከአፍሪካ ቅኝ ግዛቶችዋ ደግሞ ቱኒዝያንና ጅቡቲን መጠቅለል አማራት። ከአውሮፓም ትሪኤስትን መውሰድና አልባንያንና ግሪክን መያዝ ፈለገች። ከእንግሊዝ የአፍሪካ ቅኝ ግዛት ደግሞ ግብፅንና ሱዳንን፣ እንደዚሁም ሰሜን ሶማሊያን ከግዛትዋ ለመቀላቀል አሰበች። የዩጎዝላቭያንም ለመያዝ ከጀለች።

ይህ ሕልም እውን ቢሆን እውነትም ኢጣልያን አንድ ታላቅ መንግሥት ያደርጋታል። በአውሮፓ በቂ ግዛት ይኖራታል። የሜዲትራኒያንን ባሕር መቆጣጠር ትችላለች። የአድርያቲክ ባሕር ሙሉ በሙሉ የግልዋ ይሆናል። በቀይ ባሕር ላይ ማዘዝ ትችላለች። የነጭና የጥቁር ዓባይ ወንዞች የእሷ ይሆናሉ። ግዛትዋ ከአውሮፓ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጣልቃ ገብ ሳይኖርበት ይዘረጋል።

ሁኔታው በሃሳብ ደረጃ አመርቂ ሆኖ ሳለ፤ በአፈጻጸም ግን ችግር አስከተለ። ይህ ዓይነቱ ሥራ በኃይል እንጂ በሰላም ሊሆን አይችልም። በዓለም ማኅበር ጉባዔ ላይ ጉምዛዛ ስሜት ፈጠረ። ሃሳቡን መደበቅ አልተቻለም። ምሥጢሩ ሲታወቅ በማኅበሩ አባልነት መቀጠል የማይሆን ሆነ። የዓለም ማኅበር አባልነትንም ተወች። ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጋር ያለው ግንኙነት ከፍቅር ወደ ጦር ዞረ።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ደመና እየከበደ ሲሄድ ከአንዱ ወገን መሆን የግድ አስፈለገ። ገለልተኛ መሆን አልተቻለም። ጊዜ ለማግኘት



የተደረጉት አንዳንድ ምርጫን የማዘግያ ዘዴዎች ተራ፣ በተራ አለቁ። ቁርጠኛ ውሣኔ ማድረግ ለነገ የማይባልበት ጊዜ እየተቃረበ ሄደ። ሕዝብ የመረጠው ምክር ቤት ቀደም ብሎ ተዘግቶ ስለነበር፤ ሁኔታዎች በፋሽስት ምክር ቤት ላይ ተፅዕኖ አመጡ። ምክር ቤቱም እርስበርሱ እየተከፋፈለ ሄደ። ከጀርመን ወይም ከእንግሊዝ መሆንን መምረጥ ባስፈለገ ጊዜ፤ ጉዳዩ ለፋሽስት ምክር ቤት ሊቀርብ አልቻለም። በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲወሰን ማድረግ አስፈለገ።

ሙሶሊኒ ጉዳዩን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቀረበ። ወደ ጀርመን አገር በምሥጢር ሄዶ የተነጋገረውንና ያየውን አስረዳ። በዚያን ጊዜ የፖለቲካ ውሣኔ የማድረግ ሥልጣን የነበራቸው ምኒስትሮች አሥራ አራት ነበሩ። ከእነሱም አንዱ የሙሶሊኒን ሴት ልጅ አግብቶ ሁለት ወንዶች ልጆች የወለደላት ካውንት /መሥፍን/ ቺያኖ ነበር። ሚኒትስሮቹ በሃሳብ እኩል በእኩል ከሁለት ተከፈሉ። ሰባቱ ከእንግሊዝ፣ ሌሎቹ ሰባት ከጀርመን እንሁን አሉ።

ሙሶሊኒ የሦስት ቀን ቀጠሮ ሰጣቸው። በቀጠሮውም የሚኒስትሮቹ ሃሳብ ያው ሆነ። ውሣኔውን እንዲያስታውቅ ከሂትለር የተሰጠው ቀነ ቀጠሮ ስለደረሰ ጉዳዮን ማዘግየት አልቻለም። ስለዚህ ውሣኔ መስጠት ግድ ሆነበት። ለነፍስና ለሥጋው የመጨረሻይቱ ማሕደት የሆነችውን ውሣኔ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ሰጠ።

ውሣኔው ከሂትለር ጐን ለመቆም ሆነ። ከዚህ ውሣኔ ላይ የደረሰው ሦስት ታላላቅ ምክንያቶችን ምክንያት በማድረግ ነው። እነዚህም ምክንያቶች የኃይል ሚዛን፣ የርዕዮተ ዓለም ጓደኝነትና ጉርብትና ነበሩ። ምክንያቶቹንም ለሚኒስትሮቹ አስረዳ። በእሱና በመሰሎቹ ዘንድ ወሣኙ ነገር ኃይል መሆኑ፣ በዚያው ወቅት ጀርመን በኃይል የበላይነትን መያዙ፣ በዚያ ላይ ደግሞ የአውቶሚክን ምሥጢር ለማግኘት መቃረቡ ታመነበት። በርእዮተ ዓለም ደግሞ የጀርመን ለውጥ አራማጅነት ለርምጃው ክብደት ሰጠው። ጉርብትናውም እንደዚሁ። ነገር ግን እነ ቺያኖ በዚያው በቀድሞው ከእንግሊዝ እንሁን በሚለው ሃሳባቸው ጸኑ። ሙሶሊኒ በአማቹና በሌሎችም ሚኒስትሮቹ ላይ ጨክኖ አስገደላቸው።

ከጦርነቱ ሲገባ የተገደሉት ሚኒስትሮች ደጋፊዎችና ሌሎች የእሱና የሃሳቡ ተቃዋሚዎች ተቃውሞአቸውን አጠናከሩ። ብጥብጥ ተነሣ። በመንግሥቱ ያመፁ ወንበዴዎች በዙ ጠነከሩ። ሙሶሊኒም መከላከሉን በሀገር ውስጥ ቀጠለ። ሕልሙን እውን ለማድረግ የሚያስችል ኃይል ያለው መሆኑን ለማስገንዘብ፤ አንድ ታላቅ የወታደር ሠልፍ ሮማ ላይ አሳየ። ከምሥራቅ አፍሪካ ለተመለመለው ብዛቱ ወደ ግማሽ ሚሊዮን ለሚደርስ ወታደር ናሙና በማድረግ፤ ከኢትዮጵያ 12,000 ወታደሮች ወስዶ አሰለፈ።[1] የኢትዮጵያ ባንዳ መኳንንትም ሮም ሄደው ለባለሥልጣኖች እጅ እንዲነሱ፣ ሀገርም እንዲጐበኙ

ተደረገ። የጀርመን የጦር መኰንኖች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጥናት አደረጉ።[2]

ሙሶሊኒ በውጭ አገር ጦርነት አልባንያን ያዘ። ግሪክን ወረረ። ቀደም ብሎ በተደረገው ስምምነት መሠረት በዩጉዛላቪያ፣ በቡልጋሪያና በሩማንያ ለመስፋፋት የነበረውን ዓላማ ገፋበት። በአፍሪካ በኩልም ግብፅን ለመያዝ ከአንድ መቶ ሃምሣ ኪሎ ሜትር በላይ በጦር ኃይል ሰብሮ ገባ። በጋለባት፣ በመተማና በከሰላ በኩል ሱዳንን አጠቃ። ሰሜን ሶማሊያን ወረረ። የጀርመንና የኢጣልያ ወረራ መላውን አውሮፓ እንደ ሰደድ እሳት በያለበት ተቀጣጠለበት። የሙሶሊኒ ሕልም ወደ እውነት መለወጥ ጀመረ። ሬድዮና ጋዜጦች መጽሔቶች ይህንኑ ለማብሠር ተቅጨለጨሉ።

ነገር ግን ሁኔታዎች ወዲያው እየተለወጡ ሄዱ። ከላይ የተዘረዘሩት የጦር ግንባሮች አንድ በአንድ ተሰበሩ። እኛ ግን በተለይ የኢጣልያኑን እንመለከታለን። ጉዳያችን እሱ ነውና።

ከሰኔ 1931 ዓ.ም የቀጠለው የሙሶሊኒ ጭፍራ በጥቅምት እና ኅዳር 1932 ቀዘቀዘ። የፋሽስት ምክር ቤት እንደገና ተጠናከረ። ሙሶሊኒን ማገድ አልቻለም። መቆጣጠርም የማይሆንለት ሆነ። ስለዚህ ለመተባበር ሞከረ። ምክር ቤቱ በሀገሪቱ ጉዳይ መነጋገር ያዘ። ሙሶሊኒ የበኩሉን ግንዛቤ በተከታታይ አስረዳ። የምክር ቤቱ ስሜት እየሞቀ በሙሶሊኒ ላይ ያለው ተቃውሞ እየጠነከረ ሄደ። አንዳንድ ባለ ሥልጣኖች ከንጉሥ ኢማኑኤል ሣልሣዊ ጋር በምሥጢር ግንኙነት መሠረቱ። ማርሻል ባዶሊዮ የጦር ምክር ቤት /ቺፍ ኦፍ እስታፍ/ ሥራውን በፈቃዱ ለቅቆ የሙሶሊኒ ተቃዋሚ በመሆን ቆመ።

ጦርነቱ በኢጣልያ ላይ አመዘነ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከለንደን ካርቱም ገብተው ከሐምሌ 1 ቀን 1932 ዓ.ም ጀምሮ ኃይሎቻቸውን አንቀሳቀሱ። በኢትዮጵያ ሲንከተከተክ የኖረው ጦርነት መፍላት ጀመረ። እንግሊዞች የተወሰዱባቸውን ቦታዎች ለማስለቀቅ ተንቀሳቀሱ። ጀርመን እንደ ሀንጋሪ፣ ሩማንያ፣ ዮጉዝላቭያ ያሉ አገሮችን መውረሩ የጥቅም ግጭት ፈጠረ። የጣልያንና የጀርመንን ግንኙነት አሸከረ። ኅዳር 30 ቀን 1932 ዓ.ም /ዲሰምበር 10 ቀን 1940/ ሲዲ ባርራኒ በተባለችው ቦታ 113000 የጣልያን ወታደር ከሞላ ትጠቁ ጋር በእንግሊዝ ጦር ሰሜን አፍሪካ ተማረከ። ታራንቶ የተባለውም የሊቢያ ወደብ በእንግሊዝ አየር ኃይል ተደብድቦ ብዙ የጣልያን የጦር መርከቦች ወደሙ። ሙሶሊኒ በዚህ ሲገረም በርዲያ በተባለው ቦታ የነበረው 40000 ወታደር ታህሣሥ 26 ቀን 1933 ዓ.ም /ጃንዋሪ 5 ቀን 1941/ ለእንግሊዝ ወታደሮች እጁን ሰጠ። በጥር 10 /ጃንዋሪ 19/ ቀን ከሰላ ተያዘ። በአልባንያና በግሪክ በኩል የተከፈተው ጦር ፈጽሞ ተስፋ የሌለው መሆኑን፤ ጄነራል ሶዶ የተባለው ታማኝ የጦር አዛዥ ለሙሶሊኒ አስታወቀው። ሰሜን ሶማሊያ ተመልሳ እንግሊዝ እጅ ገባች። የቁባቱ የክላሬታ



ፔታኪ ማርገዝና ማስወረድ ሙሶሊኒ አንድ ወር ሙሉ አልጋዋ ሥር ተክራምቶ እንዲተኛ አደረገው። ሙሶሊኒ የመጣበትን አበሳ መቻል አቃተው ተርገደገደ። ብዙዎች የአእምሮውን ትክክለኛነት መጠራጠር አመጡ።[3]

ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የልማት ሥራ ለማንቀሳቀስ እንሸስት ያደረገው 2.6 ቢሊዮን ብር መና እንደቀረ ታወቀ። በሀገሪቱ ሰላም ለማስፈን የተደረጉት የእርቅና የሽንገላ ሥራዎች ሁሉ ከንቱ መሆናቸው ተረጋገጠ። ታላቁ የጣልያን ጭንቅ በምሥራቅ አፍሪካ አዲስ የተከፈተውን ጦር ማቋቋምና፤ በቅኝ ግዛቱ የሚገኙትን ከግማሽ ሚሊዮን የማያንሱ ኢጣልያውያን ነፍስ ማትረፍ ሆነ። ነገር ግን ለሙሶሊኒ የዚህ ጉዳይ ክብደት አልታወቀህ አለው። በደነ። ይህ መበደን ደግሞ የሕዝቡን ድጋፍ ከመቀነስ አልፎ ተቃውሞ አስነሳበት። በቀናው ጊዜ በዙሪያው የጨፈሩ ሁሉ ጥለውት ዘወር ስለአሉ፤ የአበሳውን ድምር ብቻውን መሸከም ግድ ሆነበት። ዕጣ ፈንታው በስንት ዓይነት ዘዴ የገነባውን የኢትዮጵያ፣ የኤርትራ፣ የሶማሊያ፣ የሊብያ ቅኝ ግዛቶች አንድ በአንድ ሲፈርሱ ቁጭ ብሎ ማየት ብቻ ሆነ። የሙሶሊኒ ኢጣልያ ሕልም ውጤቱ እንዲህ ቅገርት ሆኖ ቀረ። "ምንም ኃይል ሊሠብረው ሊያሸንፈው ቀርቶ ሊቋቋመው አይችልም" ተብሎ ታምኖበት የነበረውን የፋሽስትና የናዚስት ኃይል ኢትዮጵያ ልክ አድርጋ አንከታከተችው። ታዳጊ ኃይል መስሎ የነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከሥር ከመሠረቱ ተነቅሎ ወደቀ። ሙሶሊኒ ከታማኝ ቁባቱ ጋር የዝቅዝቂት ተሰቀለ። ግብረ አበሮቹም አለቁ።


<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 2ኛ መጽሐፍ፣* ገጽ 175።
2. በኪሾኖ ሽ. ዩኒቨርስቲ መምህር የተነገረኝ።
3. Stanley Cooperman, *Mussolini* p.124-141.

# ምዕራፍ ስድሳ
# የኢትዮጵያ የጦር ፍርድ ቤት

በአንድ ሀገር ላይ ጦርነት ተካሂዶ ከፍፃሜ ሲደርስ የጦር ፍርድ የመስጠቱ ጉዳይ የነበረና ያለ፤ ወደፊትም ጦርነት እስከ አለ ድረስ የሚኖር ነገር ነው። የችሎቱ አመሠራረት፣ የዳኞቹ አመራረጥ፣ የሚሠራበት ሕግ ዓይነት ሊያነጋግር ይችላል። ይህንን የመሰለውን ጥያቄ ለባለሙያዎች እንተወው። በኢትዮጵያ በጦርነቱ ጊዜ ብዙ ከሀዲዎች ብዙ ዓይነት የክህደት ሥራ መፈጸማቸው ማስረጃ እየነጠረ ቀደም ብሎ ተገልጾአል። የአሁኑ ጥያቆ "ታዲያ ምን ተደረገ?" የሚል መሆን አለበት።

ንጉሠ ነገሥቱ ኅዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም ከካርቱም ለሸዋ ሕዝብ ባወጡት አዋጅ "...ስለኢትዮጵያ ጥቅም ነው እያሉ ለባዕድ የሚያገለግሉት ለራስ ኃይሉ፣ ለራስ ሥዩም፣ ለራስ ጌታቸው፣ ለራስ ከበደ፣ ለራስ ገብረ ሕይወት፣ ለደጃዝማች አባውቃው ብሩ፣ ለደጃዝማች አመዴ አሊ፣ ለደጃዝማች አያሌው ብሩ፣ ለደጃዝማች ሃብተ ሚካኤል፣ ለደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ፣ ለደጃዝማች መሥፍንና እነሱንም ለመሳሰሉት ያለ አንዳች ርኅራሄ የተገባቸውን ቅጣት እንሰጣችዋለን..." በማለት ዝተው ነበር።[1]

የታሪክ ጥናት ነውና ይህንን አዋጅ በየልዩ ልዩ ገጹ መመልከት፣ ጥያቄዎችንም ማንሳት ይገባል። ጉዳዩን በጥያቄ መጀመር ይሻላል።

1ኛ. በአዋጅ የሰዎችን ስም መዘርዘር ለምን አስፈለገ?

2ኛ. የሰዎች ስም ዝርዝር ማውጣት ከአስፈለገ የእነ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ፣ የእነ ቀኛዝማች ተክለማርቆስ፣ የእነ አፈቄሣር አፈወርቅ ስም ለምን ሳይጠቀስ ቀረ?

3ኛ. ጉዳዩ የሀገር ሰዎቹ በልዩ ዘር፣ አዋጁ ለምን ለሸዋ ተነገረ?

4ኛ. የመጨረሻውና ዋነኛው ጥያቄ፡- ታዲያ በፍርድ አሰጣጥ ረገድ ምን ተደረገ? መሆን አለበት። አንባቢ የራሱን መልስ መስጠት ይችላል። እኛ ግን የተደረገውን ነገር መመልከታችንን እንቀጥላለን።

የጦር ፍርድ ቤት ተቋቋመ። የፍርድ ሥራም ተከፈተ። ነገር ግን የተከሰሰው ኃይለሥላሴ ጉግሣ ብቻ ነው። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ፣ የክህደት ሥራዎች ጀማሪ መሆኑ እርግጥ ነው። ለጣሊያን መንግሥት ስለሰጠውም አገልግሎት የራስነት ማዕረግ አግኝቶ ነበር። ሁኔታው እንደዚህ ሆኖ ሳለ የእርሱ ጉዳይ ብቻ ተለይቶ በአደባባይ ፍርድ መስጠቱ ትክክል አልሆነም። ፍርዱ ሳይፈጸም መቅረቱ ደግሞ ሌላ አጠያያቂ ጉዳይ ወጣው። መታሰር ሌሎችም ታሠሩ። ለምሣሌ ራስ ጌታቸው አባተ። ነገር ግን ጉዳያቸው በአደባባይ አልታየም። ከዚህ ሌላ፣ የተሸለ የተደረገ ነገር ለምን የለም?



ስለዚህ በኢትዮጵያ ከጦርነቱ በኋላ በከሀዲዎች ላይ የጦር ፍርድ ተሰጠ ከማለት ይልቅ አልተሰጠም ማለቱ ይቀላል። ቀድሞውኑ አዋጁ በተነገረበት አኳኋን የወጣው ከዚህ ሁኔታ ላይ እንዲያደርስ ታስቦ ሳይሆን አልቀረም። ምክንያቱም ወንጀለኞቹ ይቀጡ ቢባል ሸዋ ደም እንዲቃባ፤ አይቀጡ ቢባል ሀገሩን ሸዋ እንደተወ አድርጐ ለማሳየት። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በሀገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች፤ አንዳችም ጥያቄ ሳይነሳባቸው በየቤታቸው እንደተቀመጡ ነፃ ወጡ።

እርግጥ ኢትዮጵያ በዚያ ወቅት ብዙ ችግሮች ነበሩባት። መንግሥቱም አያሌ አጣዳፊ ሥራዎች ነበሩበት። በሥልጣን ላይ ከነበሩት ሰዎችም አንዳንዶቹ ከማክረር ይልቅ ማርገብ፣ ከማክበድ ይልቅ ማቅለል የተሻለ መሆኑ እንደሚመክሩ ግልጽ ይሆናል። ቢሆንም ሁሉንም ነፃ መልቀቅ፤ ለሀገሪቱ የወደፊት ሕልውና እንዲያ ያለ የሕግ ጥበቃ መስጠት መፍትሄ አልነበረም። እንደእኔ ይሻል የነበረው ሊቀጡ የሚገባቸውን አጣርቶና የሚቀጡትን የቅጣት ዓይነት ቀለል አድርጐ፤ ለቅጣቱም ደረጃ አውጥቶ፤ ፍርድ እንዲሰጥ ማድረግ ነበር።

ለምሣሌ፡-

ሀ. አልጋ የፈረሰው ንጉሠ ነገሥቱ ከሀገር በወጡ ጊዜ ነው። እስከዚያው ቀን ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ነበር። በሀገር ላይ መንግሥት ባለበት ጊዜ ያጠፋ ሰው መቀጣት አለበት። ስለዚህ ከሚያዝያ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጥፋቱ የፈጸሙ፤

ለ. በዚሁ ዓይነት አመለካከት ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ጥፋት የፈጸሙ መቀጣት ነበረባቸው። እጅግ ቢያንስ ንጉሠ ነገሥቱ ከደረሱበት ቀን ጀምሮ የበደሉ፤

ሐ. ወንጀለኞቹ በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ የነበራቸው አቅዋምም አንድ መለኪያ መሆን ነበረበት። በጦር ማዕረግ ፊታውራሪና ከዚያም በላይ የነበሩ፤ በሲቪል ሥራ ዳሬክተርና ከዚያም በላይ የነበሩ፤ አልጋ ከፈረሰ በኋላ ለጠላት በሰጡት አገልግሎት፤

መ. ለጠላት የጦር መሪ እየሆኑ ሠራዊት ያዘመቱ፣ ሰው የገደሉ፤

ሠ. ከኢጣልያ መንግሥት የራስ፣ የደጃዝማችነትና የፊታውራሪነት፤ እንደዚሁም በሲቪል ሥራ በዳሬክተርነትና ከዚያም በላይ በሆነ ሥራ የተመደቡ፤

ሌላው እንኳን ቢቀር ነውራቸው በሕዝብ እንዲታወቅና እነሱም አመክሮ እንዲያገኙ ማድረግ በተገባ ነበር። ይህ ሁሉ አልተደረገም። ይህ ባለመደረጉ በሀገራችን ላይ ማንም እየተነሣ ሲጨፍርባት ይኖራል። ከሁሉም በላይ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ከትዝብት ላይ የጣለው፤ ከእነዚህ ከሀዲዎች ብዙዎቹ ተመልሰው ከሥልጣን ላይ መውጣት ነው። ስለራስ

ኃይሉ ተክለሃይማኖት ነፃ መውጣት፣ ስለበላይ ዘለቀ ስቅላት ከመገረም በስተቀር ታሪክ ምን ሊል ይችላል?

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ፣ "ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ለነበረችበት ሁኔታ ምን ሊደረግ ይችል ኖሮአል?" ይሆናል። ከፍ ብሎ ከሀ እስከ ሠ ድረስ በተዘረዘሩት ወንጀሎች የሚጠየቁ ብዛት ከሁለት ሺህ አይበልጥም። የዳኝነቱን ሥራ እንዲያዩ ለአርበኞች ዕድል ቢሰጣቸው፣ ትክክለኛ ፍርድ ሊሰጡ ይችሉ እንደነበረ እኔ ራሴ አውቃለሁ። ምንም ሕፃን ብሆን ብዙ ጊዜ የአርበኞችን ፍርድ አይቼ ነበርና በችሎታቸው አልጠራጠርም። በሕግም ረገድ ጉዳዩን በፍትሐ ነገሥት ሊፈቱት ይችል ነበር።[2]

አሸናፊዎቹ ታላላቅ መንግሥታት የጀርመንን የጦር ወንጀለኞች በፍርድ ቀጧቸው። የተከሰሱባቸው ወንጀሎች ሰላም በማደፍረስ፣ በጦር ወንጀለኝነትና በሰው ልጆች ባደረሱት እልቂት ነበር። በእነዚህ ሦስት ወንጀሎች፣

በአሜሪካን ከ1,814 ተከሳሾች 450፣
በእንግሊዝ ከ1,085 ተከሳሾች 240፣
በፈረንሣይ ከ2,107 ተከሳሾች 104፣
በጀርመን ከ12,846 ተከሳሾች 5,426፣

በድምሩ ከ17,852 ተከሳሾች 6,220፣ ማለትም 35% በመቶ በሞት ሲቀጡ፣ ሌሎች ብዙዎች የዕድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶባቸዋል። በቀድሞዋ ሶቪየት ራሺያ 10000 ያህል ወንጀለኞች ከመወሰዳቸው በስተቀር ሌላ የታወቀ ነገር የለም።[3] በጃፓን የጦር ወንጀለኞች ላይም ተመሳሳይ ፍርድ ተሰጥቶባቸዋል። ነገር ግን የጣልያን የጦር ወንጀለኞች በኢትዮጵያ ላይ ስለፈፀሙት ወንጀል አንዳች አላሉአቸውም። የጥቁር ደም ለነጭ ምኑም አይደለምና። ይህም ሌላው የታሪክ ትዝብት ነው።

### ማጣቀሻ ፅሑፎች

[1] ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 337።
[2] ፍትሐ ነገሥት።
[3] ክፍለ ጽዮን ማሞ፣ ማለዳ ጋዜጣ፣ አንደኛ ዓመት፣ ቁጥር 2፣ ጥር 14 ቀን 1985 ዓ.ም፣ ገጽ 18።



# ምዕራፍ ስድሣ አንድ
# ከድል በኋላ ትግል

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያጋጠማት ችግር ከእርስዋ ጋር ከሀገር አልተባረረም። ገጹን እየለዋወጠ ቀጠለ። ከድል በኋላ የነበረው ትግል ሁሉንም የሚጎንጥ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱንም እንኳን አልተወም። ምንም በድል አድራጊነት የገቡበት ሁኔታ አንጸባራቂ ቢሆን፣ በችግሩ ጊዜ ለጠላት አጋፍጠውት በሄዱት ሕዝብ መልሶ ሞገስ ማግኘት በአደባባይ የሚታየውን ያህል ቀላል አልሆን አለ። በተለይ በአርበኞች ዘንድ አክብሮትና ፍቅር ማግኘት አልተቻለም። ማስፈራራቱ አላዋጣም። መጨቆንና ማንገላታቱም ቅርታውን ይበልጡኑ አባባሰው። ከስደተኛው አብዛኛው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሞገስ አገኙ። እንደ ግብር ጓደኛ ሆኖ ተቆጠረ። የውስጥ አርበኛም እንደዚሁ። ባንዳም የአዲሱ ዋጋ ተቋዳሽ ለመሆን ከጀለ። ከጣልያን የተደረገለት እንክብካቤ ኑሮውን አሻሽሎት፣ አመለካከቱን ወደ ዘመናዊነት ለውጦለት ስለነበር በዚያው ዓይነት መቀጠልን ፈለገ። በጠቅላላው ሕዝቡ ከንጉሠ ነገሥቱ በልዩ ልዩ አዋጆችና ንግግሮች የተገለጹት የአስተዳደር ማሻሻያዎች እንደሚደረጉለት ተማምኖ ጠበቀ። እንደዚህ አልሆነም፣ አዳዲስ ችግሮች ተፈጠሩ።

እንግሊዞች በመቅደላ ዘመቻቸው ጊዜ እንደ አደረጉት ስተት ብለው መውጣት አልፈለጉም። ገዥነት አማራቸው። የሚስተር ዊንስተን ቸርቺል መንግሥት ጦርነቱን ለማካሄድ እንጂ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ወደ ሥልጣን ለመመለስ የገባው ቃል አልነበረም። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሚስተር አንቶኒ ኤደን ድጋፍ ብቻውን ብቁ አልሆነም። የእንግሊዝ ምክር ቤት ዘይቤ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሲቀርብለት ሰምቶ ዝም ሆነ። የእንግሊዝ ጦር አዛዦች ኢትዮጵያ ከጠላት ከተወሰዱ አገሮች እንደ አንድዋ በመቁጠር የፖለቲካ መረባቸውን ለመጣል ሞከሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ግንቦት 2 ቀን 1933 ዓ.ም ለሰባት ሚኒስትሮች የሰጡትን ሹመት ተቃወሙ። ችግሩ በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ላይ ያተኮረ ብቻ አልነበረም። በሀገሪቱ ሕልውና ላይ ጭምር እንጂ።

1ኛ. እንግሊዞች "የተያዙ የጠላት ግዛቶች አስተዳደር" የሚል ስም ቀርጸው ኢትዮጵያን ከጣልያን ከነጠቁአቸው ከሶማሊያ፣ ከኤርትራና ከሊቢያ ጋር ቀላቅለው ማስተዳደር ጀመሩ።

2ኛ. ብርጋዴየር ለሽ የተባለ የፖለቲካ ሹም መደቡ። እሱም የእንግሊዝን ይዞታ ለማጠናከርና የኢትዮጵያን አቅዋም ለማዳከም ብዙ ጥረት አደረገ። የማይታይ ሥውር እጅ ዘረጋ።'ሲዳሞ ውስጥ በጀምጀም፣

ሐረርጌ ውስጥ በገሪቆጨር፣ በትግራይ ውስጥ ወያኔን እየቀሰቀሰ ብጥብጥ አስነሣ። በዙ ደም ፈሰሰ። ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ ሕዝብ ዘንድ ለማስጠላት ታላቅ የፕሮፖጋንዳ ሥራ ተካሄደ። ባሪያ ይነገድበታል፣ ሁከትና ብጥብጥ በዝቶበታል ተባለ።

3ኛ. በጐንደር፣ በአምባለጌ፣ በአጅባር፣ በወሊጋና በኢሉባቡር ጦርነት ከጣልያን ጋር ቀጠለ። ከጣልያን የተማረከው መሣሪያ በእንግሊዞች ተወሰደ። እሱ ተዋግቶ የማረከውን መሣሪያ እንግሊዞች የሚወስዱበት ምክንያት ለአርበኛው የማይገባው ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱም ማስጣል ስለአልቻሉ፤ የእነሱው ተባባሪ አስመስሎ አስገመታቸው።

4ኛ. ኢኮኖሚው የሚንቀሳቀሰው እንግሊዞች ለምሥራቅ አፍሪካ ግዛታቸው ባዘጋጁት ሽልንግ ሆነ። ዝርዝሩ ገንዘብ እንደ ዶቃ በገመድ እየተሰካ የሚንጠለጠል ስለነበር ስሙ ቀይ ቀዳዳ ተባለ።

5ኛ. የኤርትራን ሕዝብ ንጉሠ ነገሥትህን ይዘንልህ መጣን እያሉ፤ ንጉሠ ነገሥቱን አዋጅ እያናገሩ ከአዋጉት በኋላ፤ ድል ሲያገኙ እጅ አደረጉት። እንዲያውም ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥለው ከኤርትራ በመቀላቀል፤ ግዛታቸውን ማስፋፋት የሚችሉበትን የነገር ድር ማጠንጠን ጀመሩ።

6ኛ. ከምሥራቅ ኦጋዴንን፣ ከምዕራብ ጋምቤላን አጥብቀው ያዙ።

7ኛ. ይህ አያያዛቸው ለእነሱ ሚዛን እስኪያስገኝ ድረስ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ስምምነት እንዳይፈረም አዘገዩ።

8ኛ. የፍርድን፣ የፓሊስን፣ የትምህርትን፣ የውጭ ጉዳይን ሥራ እጃቸው አደረጉ።

በጠቅላላው ኢትዮጵያ አዲስ መሥገርት ውስጥ ገባች። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ ድንጋጤን ፈጠረ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከፈረንጅ ጋር ያላቸው ቀረቤታ ምን ጊዜም አስደስቶት የማያውቀውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሥጋት ላይ ጣለው። ጉዞውንም ከድጥ ወደ ማጥ አደረጉበት። ራስ እሞራው ውብነህ "የነጭ የነጭ ጣልያን ምን አለኝ" ያሉት ትክክል ሆነ። ሀገርን ከዚህ ሁኔታ ማላቀቅ ግድ አለ። የልማት ሥራዎች ማካሄድና አስተዳደርን ለማሻሻል ፋታ አልተገኘም። እንዲያውም ሀገሪቱን ከመፍረስ ለማዳን አሐዳዊውን አስተዳደር ለማጠናከር አስፈለገ። እንደዚሁም ተደረገ።

ኢትዮጵያን እንደገና የማዳኑ ሥራ በዝግታ መሄድና በትዕግሥት መያዝ ነበረበት። ቀድሞ በጣልያን የተመዘበረውን፣ ኋላ ደግሞ በእንግሊዝ ነገር የተተበተበውን መፍታት አስፈለገ። በዚህ ረገድ ከተወሰዱት እርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።



ሀ. በተቻለ ፍጥነት የኢትዮጵያን የመከላከያ ኃይል ማቋቋም።

ለ. የራስን ገንዘብ ማሳተም። የሚታተመውም ገንዘብ ከአዲሱ የኢኮኖሚ ኃይል ማለትም ከአሜሪካን ገንዘብ ጋር ጤናማ ትሥሥር እንዲኖረው ማድረግ።

ሐ. በእንግሊዞች ለተያዙት ሥራዎች ማለትም ለፍርድ፣ ለፖሊስ፣ ለውጭ ጉዳይ ብቁ ኢትዮጵያውያን በመመደብ፤ መጀመሪያ በውስጥ ቀጥሎም በሙሉ ሥራውን መልሶ መረከብ።

መ. ከእንግሊዞች ጋር ሕጋዊነት ያለው፣ በእኩልነትና በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ስምምነት መፈራረም።

ሠ. ለልዩ ሥራ የሚፈለጉ ባለሙያዎችን ለማግኘት የሚያስችል የትምህርት ሥራዎች ማካሄድ።

ረ. በጦርነት ለደረሰው ጉዳት አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የጦር ካሣ መጠየቅ።

ሰ. ቀደም ብለው ከኢትዮጵያ የተወሰዱ ግዛቶችን ማለትም ኤርትራና ሶማሊያን ማስመለስ። እነዚህ ሥራዎች ቅድሚያ ተሰጣቸው።

ከእንግሊዝ የፖለቲካ ውሽንፍር ለመጠለል አንድ ተገን መያዝ አስፈለገ። የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትርና የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ሚስተር ሩዝቬልት፤ በምድረ ግብፅ በምሥጢር ተገናኝተው እንደሚነጋገሩ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ዘንድ ታወቀ። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ የተኙት የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ሳያውቁ ሌሊት በአይሮፕላን በርረው በመሄድ፤ መጀመሪያ ከፕሬዜዳንቱ በኋላም ከሁለቱ ባለሥልጣኖች ተገናኝተው ተነጋገሩ። ይህ ግንኙነት ለጊዜው የእንግሊዝን ባለሥልጣኖች ቅር ቢያሰኝም፤ ለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አዲስ በር ከፈተ። እጅግ ጠብቆ የነበረው የእንግሊዝ አያያዝ ላላ።

በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መንግሥታት መካከል ጥር 23 ቀን 1934 ዓ.ም አዲስ ውል አዲስ አበባ ላይ ተፈረመ። በዚህ ውል፦

- የሃያ ሚሊዮን ብር /የሁለት ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ/ ብድር ተገኘ።
- በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የእንግሊዝ ዳኞች እንዲቀመጡ ተወሰነ።
- እንግሊዞች የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት በአስተዳደር እንዲረዱ፤ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት እንዲያሠለጥኑ ስምምነት ተደረገ።
- በጣልያኖች እጅ ያሉ ኢትዮጵያውን እሥረኞችና ምርኮኞች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ተወሰነ፡፡

- ከኢትዮጵያ ወደ ኢጣልያ የተወሰዱ የባህል ቅርሶች እንዲመለሱ ቃል ተገባ።
- በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ በሀገርዋ ውስጥ ለሚቆዩ የእንግሊዝ ወታደሮች ለሚያርፉበት ቦታ ኪራይ ላይጠየቅ ተወሰነ።[1]

የዚህ ስምምነት መፈረም ለእንግሊዝ እምብዛም አልጣማትም። ለኢትዮጵያ ግን ትልቅ ነገር ሆነ። ሦስት ታላላቅ ጉዳዮች መልካም ፍፃሜ አገኙ። እነዚህም:

1ኛ. የኢትዮጵያ ነፃነት መታወቁ፣

2ኛ. የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት መረጋገጡ፣

3ኛ.ጣልያንን ለማባረር ለተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያ ለእንግሊዝ የምትከፍለው ገንዘብ አለመኖሩ። ለጊዜው መንቀሳቀሻ የሚሆን ገንዘብ መገኘቱም ቀላል ጉዳይ አልነበረም።

ሆኖም ውሉ ቢፈረምም የአፈፃፀም ችግር ነበር። የእንግሊዞች ተፅዕኖ በየሥራ ዘርፉ ሥር ሰድዶ ነበርና፤ ሰንኮፉን እየነቀሉ የማውጣቱ ሥራ ቀላል አልሆነም። ለማስረጃ በትምህርት ላይ ጭቆና ለማድረግ ያደረጉት ጥረት፤ በ1941 ዓ.ም በአዲስ አበባ መምህራን ማሠልጠኛ እንስቲትዮት ተማሪዎች አድማ ቀስቅሶ ኢንስቲትዩቱን ለቅቀው እንዲወጡ አስገደዳቸው። ከጦር ሠራዊት፣ ከፖሊስ፣ ከፍርድ ቤት እንዲወጡ የማድረጉ ሥራ ቀላል አልነበረም። የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ ጉዳይ ተባበሩ፤ መልካም ሥራ ሠሩ። ይህ ጉዳይ በትዕግስትና በጥበብ ባይያዝ ኖሮ እንግሊዞች በሰላም አይወጡም ነበር። አለመግባባት ቢፈጠር ብዙ ደም ሊፈስና ምናልባትም የሀገሪቱ አንድነት ሊፈርስ ይችል ነበር። በዚህ ረገድ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለሀገሪቱና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ውለታ ውለዋል። ሌላ መሪ የማይችለው ሥራ ሠርተዋል። ስለዚህ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

የንጉሠ ነገሥቱ አቀዋም በመጠናከሩ አንድ ችግር ተቃለለ። ነገር ግን አዲስ በተቋቋመው መንግሥት ላይ ከባባድ ችግሮች ተደቀኑ። ሕዝቡ ደህይቶአል። ትንሽ ሀብት ያለው ከጠላት ጉያ ተሸጉጦ የነበረው ወገን ነው። ሕዝብ እርስ በርሱ ተቋስሎአል። ደም የተቃባው ብዙ ነው። በተለይም በአርበኛው መካከል ታላላቅ ቁስል አለ። አርበኛው በአዳዲሶቹ ሁኔታዎች ላይ አልተደሰተም። ከስደተኛውም አንዳንዱ ቅሬታ አድሮበታል። በዘመናዊ የመንግሥት ሥራ አካሄድ በቂ ችሎታና ልምድ ያለው ሰው እጅግ በጣም ጥቂት ነው። ከተማረው ሕዝብ ሦስት ሩብ በጣልያኖችና በእነሱ አገዛዝ አልቆአል። በየበረሃው የወደቁ አርበኞች አፅም እየተለቀመ ከቤተ ክርስቲያን መቀበር አለባቸው። የመኳንንቱ አዲስ አበባ



ቅድስት ሥላሴ ። ባንዳው ገንግኖአል። ንብረትም አካብቶአል። የአሠራር ሥልትም ከጠላት ቀስሞአል። ነገር ግን ታማኝነቱ አጠራጣሪ ታሪኩም አጸያፊ ነው። በሱ መደገፍ ላያዋጣ ይችላል። የተዘጉ ትምህርት ቤቶችን መልሶ መክፈትና ሌሎችም አዳዲስ መክፈት አስፈለገ። ትምህርት ቤት መክፈት ብቻ በቂ አልሆነም። ወላጆቻቸው በጠላት የተገደሉባቸውን፣ እነሱም ራሳቸው የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን እየሰበሰቡ በአዳሪነት ማስተማር አስፈለገ።

ከዚህ ችግር ኅብረተሰቡም ድርሻ ነበረው። የአርበኛው ድርሻ ከሁሉም የበለጠ ሆነ። ችግሩም ፋታ ሳይሰጥ ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው የገቡ ዕለት ጀመረው። እንደ አሻው፣ እንደ ችሎታው ይዞት በኖረው ችግር ላይ፤ ሌላ አዲስ እንግዳ ችግር ደረሰበት። ከማዕከላዊ ዕዝ ውስጥ ገባ። የአንዳንዶቹን ትዕዛዞች ምክንያት መረዳት አቃተው። ለማስረጃ ያህል አንዳንዱን እንመልከት። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ሲገቡ፤ የቡልጋ አርበኛ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ተቀበለ። ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተ መንግሥታቸው ሲገቡ፤ እሱ ከከተማ ሳይወጣ እንዳያድር ታዘዘ። ሰልፉ በእንጦጦ በኩል ስለነበር በዚያው በገባበት ወጥቶ እንጦጦ ብርድ ላይ ማደር ነበረበት። ከከሰም ቆላ ለወጣ የእንጦጦ ብርድ ቀላል አልነበረም። በከተማ የተወራው ምክንያት ፀጥታ እንዳይበላሽ የሚል ነበር። ለአርበኛው አልተነገረውም። አርበኛው ያገኘው ግንዛቤ በአዲሱ ሥርዓት - የማይፈለግ መሆኑን የሚያረጋግጥለት ሆነ። የሚበዛው በማግሥቱ ተበተነ። እንኳን አገራችን ነፃ ወጣች እያለ ተመልሶ እርሻው ገባ። ወደ ሀገሩ ያልተመለሰው በከተማው ዙሪያ ከረመ። በስንዳፉና በአቃቂ ጭቃ ተዘፍቀው ክረምቱን እንደ አሳለፉ የሚናገሩ ብዙ ናቸው።'

ንጉሠ ነገሥቱ ሐምሌ 16 ቀን 1934 ዓ.ም የአርበኝነት አገልግሎትን የሚመለከት አዋጅ ተናገሩ። አምስት ዓመት ለተዋጋና ምንም ለሌለው ሥራዊት አሥራ አምስት ወር መጠበቅ ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ረዳ። የአዋጁ ፍሬ ነገር አምስት ዓመት የተዋጋ አርበኛ ወይም ስደተኛ አንድ ጋሻ መሬት በርስትነት ማግኘቱ /ቁጥር 2ኛ/፤ በጦርነቱ ወይም በአርበኝነት የቆሰለ ወይም ስደተኛ አንድ ጋሻ በርስትነት እንዲያገኝ /ቁጥር 3ኛ/፤ ባሎቻቸው በጦር ሜዳ ወይም በአርበኝነት የሞቱባቸው እኩል ጋሻ እስከ ዕድሜአቸው እንዲይዙ /ቁጥር 4ኛ/፤ አባቶቻቸው በጦርነት ወይም በአርበኝነት የሞቱባቸው በተለይ በሚቋቋምላቸው ትምህርት ቤት እንዲገቡ፤ የትምህርት ዕድሜያቸው የተላለፈባቸው ወንዶች በወታደርነት እንዲቀጠሩ፤ ለሴቶች ግማሽ ጋሻ መሬት እስከ ዕድሜ ልካቸው እንዲሰጣቸው /ቁጥር 5ኛ እና 6ኛ/ የሚል ነበር።[2] ይህ

አዋጅ ለስደተኞችና አርበኞች በአዲስ አበባ ወይም በየአውራጃው፤ ለክፍለ ሀገሩ ሁሉ ምንም ልዩነት ሳይደረግ እኩል እንዲደለደል ተፈቀደ።[3]

በጀኔቭ እንዲያ አጥብቀው ለኢትዮጵያ የተከራከሩት ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝ በአዲሱ የሚኒስትሮች ድልድል ሹመት አልነበራቸውም። በሞስኮ አምባሳደርነት ተሹመው በጉዞ ላይ ሞቱ። ወሎና በጌምድርን በማስተባበር በአርበኝነት የተዋጉት ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ፤ ለዕድሜ ልክ እሥራት ወደ ጅማ ተወሰዱ። ሁኔታው ያላስደሰታቸው የመንዙ አባት አርበኛ ደጃዝማች አውራሪስ ዱላ አገራቸው ገብተው ሞቱ።

አዲሱ ሥርዓት ፅንዐት እያገኘ በሄደ ቁጥር በአርበኛው ላይ ክብደት አመጣበት። ወደ ቤተ መንግሥት ሲገባ፤ ከተፈቀደላቸው ጥቂቶች በስተቀር ትጥቅ መፍታት ሆነ። ይህ ጉዳይ ቀላል አልነበረም። አርበኛው የተዋጋው ከጣልያን ብቻ አልነበረም። ከባንዳም ጋር ነበረ። ደም ተቃብቶአል። አሁን ባንዳ የንጉሥ ባለምዋል እሱ ትጥቅ ፈቺ ሲሆን፤ ስጋትም ብስጭትም ገባው። ቀስ በቀስ እያለ አገሩ ገባ። ወገን ዘመድ አዲስ አበባ ውስጥ ያለው ትግሉን ቀጠለ። ንጉሠ ነገሥቱን እጅ መንሳት፣ ሚኒስትሮቻቸውን ደጅ መጥናት አስፈለገ። አብዛኞቹ ሚኒስትሮች በአርበኛው ዘንድ የታወቁ አልነበሩም። ቢታወቁም አክብሮት የሚሰጣቸው አልሆኑም። ከአዲሱ ሥርዓት ውስጥ ለመግባት አብዛኞቹ አርበኞች፤ ሚስቶቻቸውን እየተው በከተማ ሴት ወይዛዝርት ማግባት የተሻለ መስሎ ታያቸው። እንደዚሁም አደረጉ። ነገር ግን ችግሩ አልተቃለለም። መልኩን እየለዋወጠ ቀጠለ። በእኩሉ ከሳሽ ተነሳበት። እኩሉ በአገኘው መሬት ወይም ቤት ክርክር ተከፈተበት። "...የመንግሥታችንን ሥራ አሻሽለን ፍጹም አናደርገዋለን። የአበሻ አስተዳደር በአዲሱ ሥልጣኔ ይለወጣል።" "...ነፃና ሃብታም በሆነች ባንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነት፣ ትክክለኝነት...ያለው ሕዝብ ሆናችሁ እንድትኖሩባት እንፈልጋለን...[4] ተብሎ በንጉሠ ነገሡቱ የተነገረው አዋጅ ትርጉም አጣ።

የዳኝነት ሥራም እንደዚሁ ትርጉም አጣ። ከላይ በእንግሊዝ ከታች በባንዳ ተያዘ። አድልዎ፣ ሀሰት፣ ደባ ከፍርድ ገባ። የፍርድን ሥራ ለማስተካከል መምከርም አደገኛ ሆነ። አፈ ንጉሥ ገብረመድኅን ኃይለማርያም ከረጅም ጊዜ እሥራትና ከዕድሜ ልክ ግዞት የገቡት በዚህ ትንቅንቅ ነው። ከሁሉም የሚጉመዘዘው በበላይ ዘለቀ ላይ የተፈጸመው ነው። እሱን በቀረቤታ ማየት ይገባል። በላይ ዘለቀ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ በንጉሠ ነገሥቱ በራሳቸው ተጠየቀ። ጐጃም ቆይቶ በዚያ የወደቁ አርበኞችን አጽም እያሰበሰበ ከቤተክርስቲያን ሲያስቀብር ቆየ። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላም እንደዚሁ መልእክት ደረሰው።



"አገሩን ለጠላት አስረክቦ ወደ ኮበለለ ሰው የምሄድበት ምክንያት የለኝም" የሚል የግል ስሜቱን በወዳጆቹ ምክር አስታግሶ ወደ አዲስ አበባ መጣ። ከፍ ብሎ የተገለጸው ዓይነት ትዕግሥት አስጨራሽ መንገላታት ደረሰበት። ከጥቅምት ወር ጀምሮ ደጅ ሲጠና ቆይቶ ሚያዝያ 8 ቀን 1934 ዓ.ም ለጐጃም አርበኞች ሹመት ተሰጠ። ልጅ ኃይሉ በለው ራስ ተብለው የጐጃም ገዥ፣ ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ደጃዝማች ተብለው የጐጃም እንደራሴ ሆኑ። በላይ ዘለቀ ደጃዝማች ተባለ። ነገር ግን ሀገር አልተሰጠውም። ደጅ ጥናቱን ቀጠለ። በሰኔ ወር የብቼና አውራጃ ገዥ ሆነ።

ወደ ጐጃም ተመልሶ የተሰጠውን አገር ማስተዳደር ጀመረ። ከሐምሌ 1 ቀን 1934 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 1935 ዓ.ም ድረስ የሥልጣን ሹኩቻም ቢኖር ሌላ ችግር አላጋጠመም። ከዚያ በኋላ ችግር ተፈጠረ። መንሥዔው የግብር አሰባሰብ ነው። እሱ ግብሩን አገሩን አስተዳድርበታለሁ ሲል፤ አለቆቹ ለማዕከላዊ መንግሥት አስገባ ባይ ሆኑ። አከራክሮ ፍርድ ሰጭ አልነበረም። አለቆቹ ጦር አስልከው ግጭት ተፈጠረ። ከመንግሥት ወገን ሃያ አምስት ከእሱ ወገን አሥራ ሰባት ሰው ሞተ። አለቆቹ ክስ አቀረቡ። እሱ ባለፈው ዓመት የደረሰበት መጉላላት አልተረሳውም ነበርና፤ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። አለቆቹ እስከ ሃምሣ አንድ ሺህ የሚገመት የገበሬ ሠራዊት ላኩበት። እሱም ሶማ በረሃ ገባ። ጦሩ ተከታትሎ ስለደረሰበት የአሥራ አምስት ቀን ውጊያ ተካሄደ። ከመንግሥት ሠራዊት አምስት መቶ፣ ከእሱ ወገን አንድ መቶ የሚሆን ሰው ወደቀ። ንጉሠ ነገሥቱ "...በክፉ አላይህም። በክፉ ባይህ ልጄን ልዑል መኰንን ይንሳኝ..." የሚል የመሐላ ቃል ያለበት ደብዳቤ በሊጋባ በቀለ በየነ እጅ ላኩ። እጁን ሰጠ።

አዲስ አበባ ለፍርድ ቀረበ። የተከሰሰባቸው ወንጀሎች በረከቱ። ንጉሠ ነገሥቱ የሾሟቸውን ባለሥልጣኖች አለመቀበል፣ ግብር ለመንግሥት እንዳይገባ መከልከል፣ ፀጥታ ማደፍረስና የበርካታ ሰዎችን ደም ማፍሰስ ዋና ዋናዎቹ ሆኑ። ከጐጃም የተንቀሳቀሰውን የጣልያን ጦር ሳይዋጋ ወደ ወሎ እንዲሄድ ስለአደረገ ሊቀጣ ይገባል ተብሎ ከኰሎኔል ዊንጌት /ጄነራል/ ቀርቦበት የነበረውም ክስ በንጉሠ ነገሥቱ እጅ መቆየቱ ይታወሳል። ወንጀሎቹ ከባድ ስለሆኑ፣ ባንዶቹም አጥብቀው ስለተከራከሩ፣ እሱም ሕግ ሊቀበለው በሚችል ዓይነት ስለአልተከላከለ ይሙት በቃ ተፈረደበት። የይሙት በቃው ፍርድ አርበኛውን ስለአስቆጣው ወደ ዕድሜ ይፍታሕ ተለውጦ፤ ወሊሶ በደጃዝማች በቀሏ ወያ እጅ እንዲታሠር ተደረገ።

ሊያመልጡ ይችላሉ የሚል ጭምጭምታ ተሰማ ተብሎ፤ እሱና ጓደኞቹ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ደጃዝማች ውቤ ሠፈር በነበረው ወህኒ ቤት ውስጥ ታሠሩ። የተፈቀደላቸው ለምግብ በወር ዘጠኝ ብር፣ ለልብስ በዓመት ሃያ ብር ነበር ይባላል። የታሠረውም የጣልያን ሹም ሆኖ አሣሩን ሲያሳየው ከኖረው ከጣልያኑ ደጃዝማች ማሞ ኃይለሚካኤል ጋር ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች ጉምዛዛ ሆኑበት። ስለዚህ ለማምለጥ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶ ሱሉልታ ከተባለ ቦታ ተያዘ። በተደረገው ሙከራ ደግሞ ሌሎች ሦስት ያህል ሰዎች ሞተው ነበርና ወንጀሉ አለመጠን ከበደ። ለአርበኛውም አንዳች ለማለት አስቸገረው። ይሙት በቃ ተፈረደበት።

የአገዳደሉ ጉዳይ ደግሞ ሌላ ችግር አስከተለ። ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ብቻና እንዲሰቀሉ ተወሰነ። በብዙ መንገላታት ዓባይ ሲደርሱ ወንዙ የማያሻግር ሆነ። ያን ጊዜ ድልድይ አልነበረም። አይሮፕላን አልነበረም። ስለዚህ ውሣኔውን ማስፈፀም ሳይቻል ቀርቶ በሌላ ክባድ እንግልት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ጀግናው በላይ ዘለቀና ወንድሙ ጥር 30 ቀን 1937 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ተሰቀሉ። በላይ ዘለቀ የተሰቀለው መርካቶ አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ እንደሆነና፤ የመጨረሻ ቃሉም "ኢትዮጵያ ወንድ አይብቀልብሽ" የሚል እንደነበር በወቅቱ በቦታው ላይ የነበሩ በምሬት ይናገራሉ።[5] ይህ ጉዳይ አገንግኖ የነበረውን አርበኛ ፀጥ አደረገው። የተፈለገውም ይህ ነበር።

በአርበኞች ላይ ከደረሱት ችግሮች አንዱ የክስና የከሳሽ ብዛት ነበር። አንዳንዱ በመሬት ሌላው በሥራ ምክንያት ነበር። በሥራ ምክንያት በአርበኞች ላይ የተነሱትን ክሶችና ያስከተሉትን መጉላላት በሙሉ ለመዘርዘር እጅግ ብዙ በመሆኑ፤ በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ላይ የደረሰውን ብቻ እንመለከታለን። ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ በተራቀቀ ሥልት ጣልያንን የወጉ፣ ሙሴ ቀስተኛ የተባለውን የጣልያን ሰላይና ነገረ ሠሪ የገደሉ፣ ወደ ከፋ ተሻግረው የጋተሮን፣ የአበልቱን፣ የአረንገማንና የጢሮን የጣልያን ምሽግ የሠበሩ፣ የጅማን ከተማ ከብበው ሰኔ 12 ቀን 1933 ዓ.ም የ800 ኢጣልያውያንን ምርኮ ኢትዮጵያን በመወከል የተቀበሉ የኢትዮጵያ ጀግና ነበሩ። አርበኛው የራስነት ማዕረግ ሰጥቶአቸው የነበረና፤ ንጉሠ ነገሥቱ ኖኖ ጊሸን ድረስ ሄደው ጎብኝተዋቸው በአዲሱ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንደሚሰጣቸው ቃል የተገባላቸው ነበሩ።

ነገር ግን ከነፃነት መመለስ በኋላ ውስብስብ ችግር አጋጠማቸው። ተከታታይ ክስ ቀረበባቸው። የመጀመሪያውና በር ከፋቹ በአምስቱ ዓመታትና ጅማን በሚያስለቅቁበት ጊዜ የማረኩአቸውን መሣሪያዎች አላስረከቡም፤ በመንግሥት ላይ ተንኮል አስበዋል የሚል ነበር። ክሱ



አደባባይ ወጥቶ ክርክር ሳይደረግበት፤ መሣሪያዎቹ የነበሩበት ግምጃ ቤት በድንገት ተቃጠለ። ቢሆንም 14 መድፍ፣ 400 ባለውሃ መትረየስ፣ ብዙ ፈንጂዎችና ጠመንጃዎች፣ ብዙ ጥይት እንደነበረ ታውቆ ስለነበረ ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ብልሁ ገረሱ ይቅርታ ስለጠየቁ ቅጣት አላገኛቸውም። ዞሮ ግን እዳፊው አልለቀቃቸውም። ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ወሊሶ በግዞት መቆየታቸው በዚህ ምክንያት ጭምር ሳይሆን አልቀረም። እሳቸውም ወደ ወላይታ ሶዶ ተዛወሩ። አብረው ከጣልያን ጋር የተጋደሉ አርበኞችም መሣሪያዎቻቸውን ተገፈፉ።

እንደገና የጋሞ ጐፋ ገዥ በነበሩ ጊዜ በራሣቸው ውሣኔ የመንግሥት ገንዘብ አውጥተዋል ተብለው ስለተከሰሱ፤ አዲስ አበባ ኮልፌ የነበረውን የአባታቸውን እርስት ለመሸጥ እስከማሰብ ተበሳጭተው ነበር። ከዚህ ሲያመልጡ ደግሞ ለመንግሥት የሚገባውን ታክስ ይቃወማሉ የሚል ሌላ ነገር ስለተደቀነባቸው ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ግዞት ገቡ። መበሳጨታቸውን የተገነዘቡ ሰዎች ከሐምሌ 1943 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሤራ ውስጥ አስገቡአቸው። እሳቸው ግን ምሥጢሩን ለንጉሠ ነገሥቱ በመንገርና አድመኞቹንም ከቤታቸው ጋብዘው በማስያዝ ከጥፋት ዳኑ። ከንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋልነት አግኝተው የኢሉባቡር ጠቅላይ ገዥነትን ቢያገኙም፤ ከሕዝብ ትዝብት መግባታቸው አልቀረም። ኢሉባቡር ደግሞ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣን ለማስፈታት ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር አሲረዋል፣ የፍርድ ቤቱን ፕሬዚደንት በድለዋል፣ ሠራተኞችንም ጨቁነዋል የሚሉ ክሶች ቀረቡባቸው።[6] ለክሶቹ አራማጅ መስለው ስለታዩአቸው የጠቅላይ ግዛቱን ዴሬክተር በጅራፍ ስለገረፉአቸው፤ ለጥቂት ጊዜ በአመክሮ ቆይተው የአርሲ ጠቅላይ ገዥ ሆኑ። ከዚያ እንደ አሉ የታህሣሥ 1953 ዓ.ም የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ ደረሰ። በአባትና ልጅ መካከል ምን አገባን የሚል ስሜት ስለገዘዛቸውና ሙከራውን ለማክሸፍ ባለመተባበራቸው፤ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሌላ ቅሬታ ስለተፈጠረ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ጡረታ ገቡ።[7]

ደጃዝማች ገረሱ ዕድለኛም ዘዴኛም ነበሩ። ብስጭት ይብዛባቸው፣ ቀደም ብሎ ቃል የተገባላቸው የጦር ሚኒስትርነት ሹመት አይሰጣቸው እንጂ፤ የደጃዝማች ገረሱ ዕድል እምብዛም ክፉ አልነበረም። ክስና ወቀሳ ቢበዛባቸውም ሌላ እንግልት አልደረሰባቸውም። እኛም ከዚህ የጠቀስነው በአርበኞች ላይ የነበረውን ውጣ ውረድ ለማሳየት እንጂ ተበድለዋል ለማለት አይደለም። ሌሎች እንደ እሳቸው ዕድለኛ አልነበሩም። እስመራሪ ጭቆና የተደረገባቸውና ተደጋጋሚ ሤራ የተሰራባቸው ሌሎች ብዙ አርበኞች ነበሩ። ከእነዚህም አንዱ ፊታውራሪ ዋልደፃድቅ ዘውዴ ነበሩ።

ከፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ስለአልገቡ ከቅጣቱ አልደረሱም። ነገር ግን እንኳን ጠቅላይ ገዥነት የወረዳ አስተዳዳሪነትም በዛባቸው። በ1954 ዓ.ም በተካሄደው የምክር ቤት ምርጫ በአሣግርት ወረዳ የተወዳደሩበት ሣጥን ወደ ሌላ ሰው ተገለበጠባቸው። ተጉለት፣ ደብረክ በተባለ መሬታቸው አራት ባለጋራዎች ተነስተው ዕድሜ ልካቸውን አንገላቱአቸው። ከጽሕፈት ሚኒስትር በደብዳቤ እየታዘዘ ሲካሄድ የኖረው ይህ አራትዮሽ ክርክር ሊያበቃ የቻለው፤ ደርግ ተነስቶ የዙፋን ችሎትን በመዝጋቱ ብቻ ነበር። አርበኞችን እጅግ የጉዳና ያስመረራቸው ይህ ዓይነቱ ማብቂያና ማገጃ የሌለው ክስና ክርክር ነበር።

ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ ሁሉንም ነገር ትተው አገራቸው ገብተው በሀዘንና በብስጭት ሞቱ። እንደነ ቢትወደድ ነጋሽ የመሳሰሉት አርበኞች አልጋ የመገልበጥ ሙከራ አደረጉ። ይህ ደግሞ የአርበኞችን ኃይል ለማድቀቅ የሚካሄደውን ሤራ አጠናከረው።

ሌላው ችግር በአርበኝነት ጊዜ የተሰጡ ሹመቶች አለመጽናት ነበር። በሰሜን ሸዋ ንጉሠ ነገሥቱ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ፤ ለባላምባራስ አበበ አረጋይ የራስነት፣ ለቀኛዝማች ኃይሉ ወልደ መድኅንና ለፊታውራሪ ዘውዱ አባ ኮራን የደጃዝማችነት ማዕረግ፣ ለሌሎችም ለብዙ አርበኞች የፊታውራሪነት፣ የቀኛዝማችነትና የግራዝማችነትና ማዕረግ ሰጥተዋል። አርበኞቹም ተቀብለው ሲጠሩበት ኖረዋል። የደጃዝማችነት ማዕረግ ቢሰጣቸው ሳይቀበሉ የሞቱ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ብቻ ነበሩ።[8]

የጉንደር አርበኛ መኳንንቱና ሊቃውንቱ ላይ ተሰብስቦ ከመከረ በኋላ፤ በልጅ ዮሐንስ ኢያሱ አማካይነት ለግራዝማች አሞራው ውብነህ የራስነት፣ ለሌሎች 153 ጀግኖች የደጃዝማችነትና የፊታውራሪነት ማዕረግ ሰጥቶ ነበር። አርበኞቹም ተቀብለው ሲጠሩበትና የጀብዱ ሥራም ሲሰሩበት ቆይተው ነበር።[9] ይሁን እንጂ የማስረጃው ደብዛ ጠፋ። በጎጃምም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ለብዙዎች የደጃዝማችነት፣ የፊታውራሪነት፣ የቀኛዝማችና የግራዝማችነት ማዕረግ መስጠታቸው እርግጥ ነው። ያልሾሙት እራሳቸውን ብቻ ነበር። በጉራጌ አገር ያለውም አርበኛ ተመሳሳይ እርምጃ ወስዶ በላምባራስ ገረሱን ራስ እንደ አላቸው የሚያመለክቱ አንዳንድ አሻራዎች አሉ። እሳቸውም በበኩላቸው ለ775 አርበኞች ከግራዝማችነት እስከ ፊታውራሪነት ማዕረግ ሰጥተዋል። ከእነሱም አሥራ አንዱ ስመ ጥር የሀገር አስተዳዳሪነት ሥልጣን ጭምር የተሰጣቸው ነበሩ።[10]

በአጠቃላይ ለሦስት ጀግኖች የራስነት፣ ለጦር መሪዎች የደጃዝማችነት፣ ሌሎች ብዙ አርበኞች የፊታውራሪነት፣ የቀኛዝማችና



ግራዝማችነት ማዕረግ ተሰጥቶ ነበር። የእነዚህ ማዕረጎች አሰጣጥ ቀላል አልነበረም። የመሪነት ችሎታቸው፣ ለሀገራቸው ለመሞት የነበራቸው ቆራጥነት፣ የፈፀሙአቸው የጀብዱ ሥራዎች እየተመዘኑ ነበር። በመሆኑም እንደ አሉ መጽናት ነበረባቸው። ግን እነዚህ ሹመቶች በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ የልብ ተቀባይነት አላገኙም። የእያንዳንዱን ሰው ማዕረግ አጠናቅቆ ለመግፈፍ የሚቻል ባለመሆኑ ቀረ እንጂ ተወድዶ የተደረገ ነገር አልነበረም። ደጃዝማች ዘውዱ አበኮራን ደጃዝማችነታቸውን በፍርሀት ለቀቁ። አሞራው ውብነህና ገረሱ ዱኪ ወደ ፊታውራሪነት ወረዱ። የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ፊታውራሪነት በ1938 ዓ.ም ታደሰላቸው። ከሞቱ በኋላ በሰኔ 1962 ዓ.ም የተፈቀደው የደጃዝማችነት ማዕረግ ቀልድ ሆኖ ቀረ። ብዙ አርበኞች ሌላ ማዕረግ ሳያገኙ በእነዚያ በአርበኝነት ዘመናቸው በአገኙአቸው የማዕረግ ስሞች እንደተገደቡ ሞቱ። ይህ አደራረግ በንጉሠ ነገሥቱና በአርበኞች መካከል ትዝብት ፈጠረ። ጥላቻም አሳደረ። በዚህ ረገድ ንጉሠ ነገሥቱ አልተሳሳቱም ለማለት ያስቸግራል።

ባንዳም ለአርበኛ አልተኛለትም። አንዳንድ ቦታ በኃይል እስከ መሠናዘርም ደረሰ። ለምሣሌ ገብረፃድቅ የተባለ ባንዳ ቡልጋ፣ አሣግርት ልዩ ስሙ ሥራሮ የተባለው ቦታ፤ ፊታውራሪ ደብቁ ተክሌ የተባሉትን አርበኛ ሰኔ 10 ቀን 1936 ዓ.ም በዕለቱ ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ከነበሩ ሁለት አርበኞች ጋር በጥይት ገደላቸው። ከጠላት የወሰደውን አንድ መትረየስና አስራ አምስት ብረት ለምን ገፈፈኝ ብሎ።

አርበኛው በእልህ ከነገር ላይ የወደቀበት ጊዜም አለ። ቀኛዝማች በቀለ ግዛው የተባለው አርበኛ አንድ የእንግሊዝ መቶ አለቃ እሱን እንደ ሌላው ቅኝ አገር ሰው መስሎት፣ አዲስ አበባ ራስ መኮንን ድልድይ ላይ የወደቀን አንድ የፈረስ እሬሣ ጎትት በማለት በአክርባት ከፊቱ ላይ መታው። በቀለ ግን በያዘው መውዜር ከነመረቁ አጠጥቶት እጁን ለፖሊስ ሰጠ። እንዲያመልጥ ማድረግ የሚቻል የነበረ ቢሆንም፣ ገዳዩ አርበኛ ተመክሮ፣ በዋስ እንዲከራከር ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ተገኘ። ቀኛዝማች በቀለ ወንድሙን ፊታውራሪ ተሻገርን ዋስ ጠርቶ፣ ከተፈታ በኋላ ግን ትውልድ አገሩ፣ መርሐቤቴ ገባ። ሁኔታው እንግሊዞችን ስለአስቆጠና ንጉሠ ነገሥቱን ስለ አስቀየመ፤ ዳኛው ፊታውራሪ ኃይለራጉዔል ወልደፃድቅና ሁለቱ ወንድማማቾች ከግዞት ገቡ።

የጣልያን ባለምዋል የነበሩ ጸሐፊዎችና ዳኞች በዚያው ሥራቸው ቀጠሉ። አርበኛው ትምህርት ስለሌለው ካብ አይገባ ድንጋይ ሆነ። በልቡ ሀገሩን፣ በእጁ ጦሩን ይዞ ቆመ። ከማቅራራት በስተቀር አንዳች ማድረግ አልቻለም። አርበኛ ከባንዳ ዳኛ ችሎት መነጋገር አቃተው። ለማስረጃ ያህል

አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፤ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከነጋድራስ ይምሩ ገብረሥላሴ ላይ አርበኝነትህን አስመስክር ቢባሉ ከበደ አበሞጣው፣ ቀኛዝማች ዳኜ፣ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ የተባሉትን ቀንደኛ ባንዶች ቆጠሩ። በዚህም ባለሥልጣኖቹ ቢበሳጩም፣ ሊቃወሙ አልቻሉም፤ ስለዚህ አርበኛው ከራሱ ውስጥ ከተመረጡ ዳኞች ዘንድ እየቀረበ እንዲያስመሰክር ማድረግ ግድ ሆነባቸው።

አርበኛው ከመንግሥት አንዳች ነገር ማግኘት ካስፈለገው፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያመለክታል። ይጠራለት ተብሎ ሲታዘዝ፤ የጠየቀው ቤት ወይም መሬት ከሆነ፤ ለመንግሥት ሥራ የማይፈለግ፣ አስቀድሞ ያልተጠየቀና ያልተሰጠ፣ መንቀያ መትከያ መሆኑንና ሌሎችም ጉዳዮች እንዳገሩ ከጽሕፈት ሚኒስቴር ይታዘዛል። ይህ ትዕዛዝ በሀገር አስተዳደር በኩል ለክፍለ ሀገር፣ አውራጃ፣ ወረዳ፣ ምክትል ወረዳ ደርሶ እስኪመለስ እና ለጠያቂው መሥሪያ ቤት እስኪደርስ፣ እጅግ አሣር አለበት። በዚህ ዓይነት ሁለትም፣ ሦስትም ጊዜ የሚጠራበት ጊዜ አጋጥሞአል። ለምሣሌ እኔ ራሴ ከንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተፈቅዶልኝ በእጄ የነበረውን የዳዊት አገርን መልከኝነት፤ በየዓመቱ ለዘመን መለወጫ እያመለከትኩ ቆይቼ የተፈቀደልኝ በ1947 ዓ.ም ነው።

ይህንን ሲመለከቱ ብዙ አርበኞች ከተአቅቦ፣ ከብሕትውና ገቡ። እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ተብለው ከንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ጋር የነበሩት መምህር መነኑ። መጨረሻ ጊዜ የታዩት የረር አካባቢ ነው። ግራዝማች ገድለጊዮርጊስ ሀብተሚካኤል የተባሉት የቡልጋ አርበኛ ቅምብቢት እርሻ ገቡ። እሳቸው አርሰው ያላመረቱትን፣ ሚስታቸው ፈጭተው ያልጋገሩትን መብላት ተው። ቀኛዝማች ገብረመስቀል ኃይሌ ጉማ እንዲሸጥ አድርገሀል ተብሎ፤ በሐሰት ምስክር ከጣላት ንብረት ጥበቃ ኃላፊነቱ ተባረረ። ከዚያም የተሠረቀ ልጋ ገዝተሐል ተብሎ ተከስሶ፤ በሐሰት ምስክር ተፈርዶበት ደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት ታሠረ። ከዚያም በኋላ ከየትኛውም ከተማ ሳይገባ ባሶ ከተባለው ቦታ ኖረ። የሚደንቀው ይህ ሰው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን ሲወርዱ መቁረቡ ሲሞቱ መመንኮሱ ነው።

ከድል በኋላ በየመልኩ የተቀሰቀሰው ትግል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንንም ጠቀሰ። በጠላት ወረራ ጊዜ አደጋ ላይ ጥለዋት የሄዱትን ግብጻዊውን ሊቀ ጳጳስ መልሶ ለመቀበል ተጠየፈች። ለአጭር ጊዜ ተመልሰው ቢመጡም እሚዘልቁት አልሆነም። ተመልሰው ወደ ሀገራቸው ገቡ። ተሰደው የነበሩትን ንጉሠ ነገሥት መቀበል፤ ነገር ግን ተሰደው የሄዱትን ሊቀ ጳጳስ አልቀበልም ማለት፤ ለውጭ ተመልካች



የሚገባ ነገር አልነበረም። ነገር ግን ኢትዮጵያ አልተመለሰችበትም። ከዳር አደረሰችው። ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ኋላም ፓትርያርክ ተሾመ። በዚህም ረገድ አንድ መልካም ውጤት ተገኘ።[11]

ሌሎች እሥረኞች ሲመለሱ ዘርዓይ ደረሰ ሊመለስ አልቻለም። ምንም በሥራው ኢትዮጵያዊ ቢሆን በትውልዱ ኤርትራዊ መሆኑ ችግር ሳይፈጥር አልቀረም። ቢሆንም እሱ አጥብቆ እንደተከራከረላት ኢትዮጵያም አጥብቃ መከራከር ነበረባት። ይህንን አለማድረግም በታሪክ ፊት ያሳፍራታል።

የሻምበል አብዲሣ አጋ ሁኔታ ደግሞ ሌላው አሳዛኝ ታሪክ ነው። ጦርነቱ ሲያልቅ ወደ ካናዳ ተወሰዱ። ዜግነታቸውን እንዲለውጡ ተጠየቁ። በዚህ ጊዜ ተመልሰው ወደ ጣልያን አገር ተልከው እሥር ቤት ገቡ። በፍርድ ቤት ክስ ቀረበባቸው። ወንጀሉ በጦርነቱ ጊዜ 32 ገበሬዎች ገድለሀል የሚል ሆነ። ፊልድ ማርሻል ቫይካውንት አሌክሳንደር ለፍርድ ቤቱ አንድ ቴሌግራም አስተላለፉላቸው። ቴሌግራሙም ከጠላት አምልጠው ሽፍትነት እንደገቡ ከአስረዳ በኋላ "...ፋሽስትና ናዚሲስት የሚሠሩትን ተቃውሞ ለዓለም ነፃነት፣ ለኢትዮጵያ ክብር ተጋደለ። የመኮንኑ መሰቃየት ለእኛም ሆነ ለዓለም መንግሥታት የሚያሣማ ጥልቅ ሐዘን ነው" የሚል ነበር። ፍርድ ቤቱ ቴሌግራሙ እንደ ደረሰው የሠላሳ ሁለት ዓመቱን እሥራት ወደ 18,000 ብር ለወጠላቸው። በአከፋፈልም ረገድም እንግሊዞች 32% ረዱአቸው። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ 41% ከፈለላቸው።[12]

ይህ ሁኔታ አርበኛውን አጥብቆ አስመረረው። ብዙ ስሞታ ተነገረ። አቶ ሕይወት ኀደሩ ስለጠላት ዘመን የጻፉትን መጽሐፍ "ያቺ ቀን ተረሣች" አሉት። ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ "ቀሪን ገረመው" አሉት። አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ "እናት ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ሳለ የገደለሽ በላ" ብለው ወዲያው ሞቱ። አቶ አበራ ጀምበሬ ስለበላይ ዘለቀ በጻፉት ታሪክ ቅልቅል ልብ ወለድ መጽሐፋቸው፤ "ብዕሬ አልቅሽ" በሚል ርዕስ ግጥም ደረደሩ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ይህንን የመሰለ ሮሮ ለማድመጥ ጊዜ አልነበራትም። ዓለሙ ፋታ አለሰጣትም፤ ወዘወዛት እንጂ። መስሚያ ጆሮ ማመዛዘኛ አእምሮ አጣች። ከዚህም የተነሣ አሁን ከአለችበት ማጥ የዘፈቃትን ረጅም ጉዞ ቀጠለች።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. *ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 232-338።
2. ስለ መሬት ሥልት ጥንታዊ ታሪክ እና የአዲሱ ዘመን የመሬት አስተዳደር ባጭሩ። በመሬት ይዞታ ሚኒስቴር የተደረገ ጥናት።
3. ኅዳር 23 ቀን 1935 ዓ.ም በተነገረ ሌላ አዋጅ።
4. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 209።
5. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር፣ የደጃዝማት በላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ ገጽ 23-29።
6. በዚያ ዘመን አገረ ገዥው የማሕል ዳኛ ሆኖ በፍርድ ችሎት ይቀመጥ ነበርና።
7. *ታቦር ዋሚ፣ አባ በራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎችም አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 77-106።
8. የቡልጋና የሸንኮራ ትግል የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።
9. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 137-140።
10. *ታቦር ዋሚ*፣ ገጽ 52-53።
11. ዜና ባስልዩስ፣ ገጽ 35 እና 136።
12. *መርሥዔ ሐዘን አበበ፣ በኢጣልያ በረሃዎች*፣ ገጽ 64-73።




# ምዕራፍ ስድሳ ሁለት
# የሰላም ንግግር ከኢጣልያ ጋር

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ ጀርመን ፖላንድን በመውረርዋ ነሐሴ 26 ቀን 1931 ዓ.ም /ሴፕተምበር 1 ቀን 1939/ ተጀምሮ፤ ሚያዝያ 26 ቀን 1937 ዓ.ም /ሜይ 5 ቀን 1945/ የበርሊን ከተማ ሲያዝ አለቀ። የሩቅ ምሥራቁ ጦርነቱ ግን ቀጠለ። ከዚህ እኛ የምንመለከተው ጦርነቱ በአውሮፓ ሲያልቅ ምን እንደተደረገ ነው።

ሙሶሊኒ ሚያዝያ 20 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 28 ቀን 1945/ ሞተ። ሞቱም በማግሥቱ ለንደን ተሰማ። በዚሁ ቀን ማለትም ሚያዝያ 21 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 29 ቀን 1945/ ሂትለር ራሱን ገደለ። ነገር ግን የጀርመን ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ሂምለር፤ በስዊድን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል ከሚያዝያ 24 ቀን /ሜይ 2/ ቀን ጀምሮ ከምዕራባውያን ጋር የምሥጢር ግንኙነት አድርጐ ነበር። የሂምለር ሃሳብ በተለይ በምዕራብ ጦር ግንባር ላለው የጀርመን ሠራዊት የተኩስ አቁም ትዕዛዝ አስተላልፎ ትዕዛዝ ለመስጠት ሲሆን፤ በሁሉም ግንባር እጅ ከአልሰጠ እንደማይቀበሉት በሚስተር ቸርቸል ሃሳብ ፕሬዜደንት ትሩማንና ማርሻል ስታሊን ተስማሙበት። ነገር ግን ሂምለር ስለተሠወረ ከስምምነት ላይ ሳይደርስ ቀረ። የጀርመንን እጅ መስጠት የሚያበስረው ስምምነት፤ ኪየታል በተባለው በሌላ የጀርመን ጀነራል አማካይነት ሚያዝያ 29/ሜይ 7/ ቀን ተፈረመ። ተኩስም በማግስቱ ዕኩለ ሌሊት ጀምሮ ቆመ።[1]

በጦርነቱ ፍፃሜ ሶቭየት ራሺያ ብዙ አገሮችን ያዘ። እነ እስቶኒያ፣ ላትቪያ፣ ሊትዋንያን ጠቀለለ። ዩጐዝላቪያ፣ ሀንጋሪ፣ አልባኒያ፣ ቸኮዝሎቫኪያ፣ ፖላንድ፣ ሩሜንያና ቡልጋሪያ ኮሚኒስት አስተዳደር ውስጥ ገቡ። ከቅኝ ግዛት ሥር ይማቀቁ የነበሩ የአፍሪካና የእስያ አገሮች፤ ኮሚኒዝምን እንደ መድኅን አድርገው ተመለከቱ። በካፒታሊዝምና በኮሚኒዝም አስተዳደር በሚደርሰው ግጭት ሦስተኛው የዓለም ጦርነት እንዳይቀሰቀስ አሰጋ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መፈጸም የተገኘው ሰላም ብዙም እንደማይቆይ ብዙ ምልክቶች ታዩ። ይህ የፖለቲካ ክስተት የምዕራብ አገሮችን አሰጋቸው። ዓለምን ከሌላ ጦርነት ለማዳን የሚቻልበትን መንገድ ቀየሱ።[2]

1ኛ. የጦር ወንጀለኞችን ጉዳይ የሚመረምሩና በአጥፊዎች ላይ ቅጣት የሚወስኑ የጦርና የሲቪል ፍርድ ቤቶች ተቋቋሙ። ነገር ግን እነዚህ ፍርድ ቤቶች በጣልያኖች ላይ፣ በተለይም በኢትዮጵያ የፈጸሙትን ወንጀል ከቁጥር ሳያገቡት ቀሩ።

2ኛ. በኢትዮጵያ አቤቱታ ተገንዞ በተቀበረው በዓለም መንግሥታት ጉባኤ ምትክ፤ የዓለም መንግሥታት ህብረትን አቋቋሙ። ኢትዮጵያ የድርጅቱን መመሥረቻ ደንብ ታህሣሥ 23 ቀን፡1935 ዓ.ም ፈረመች። ሰኔ

18 ቀን 1937 ዓ.ም የድርጅቱን ቻርተር ፈርማ አባል ሆነች። ድርጅቱም ልዩ ልዩ ሥልጣን ይዞ ከጥቅምት 13 ቀን 1938 ዓ.ም ፀና።[3]

3ኛ. በጦርነቱ የደቀቀችውን አውሮፓን በማርሻል ፕላን መልሶ አቋቋመ።

4ኛ. የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ እየታየ ነፃነት የሚቀዳጁበት መንገድ በሕቡዕ አሠራር ተጀመረ።

እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ከተሸከሙአቸው ጉዳዮች አንዱ፤ እርስበርሳቸው በተዋጉ አገሮች መካከል የሚደረገው ስምምነትና የሚፈጠረው የአሠራር ሥልት ሆነ። ከዚህም በስተቀር በወንጀለኝነት የሚጠየቁት ሀገሮችና የሚጠየቁበት ጉዳይ እንዲወሰን አስፈለገ። በ1937 /1945/ መጨረሻ አሸናፊዎች አገሮች ሞስኮ ከተማ ባደረጉት ስብሰባ፤ ተጠያቂዎቹ አገሮች ከጃፓን በስተቀር ጀርመን፣ ኢጣልያ፣ ሩማንያ፣ ሐንጋሪ፣ፊንላንድ መሆናቸውን ወሰኑ። የሚከፍሉትም የጦር ካሣ ኢጣልያ 360፣ ቡልጋሪያ 70፣ ሀንጋሪ፣ ሩማንያና ፊንላንድ እያንዳንዳቸው 300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሆነ ተወሰነባቸው። አንዱ ፍጥጫ በትሬኤስት ምክንያት ሆነ። ብዙም ችግር ሳይደርስ እንግሊዝና አሜሪካን ከዮጉዝላቪያ በጦር ኃይል ነጥቀው እጅ አደረጉ። ጀርመንን እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ፈረንሣይና ራሺያ ተከፋፈሉአት። ድርሻቸው በይዞታቸው መጠን ሆነ።

ከስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ውል እንዲፈርሙባቸው ከሚያስፈልጉ አገሮች አንድዋ ኢትዮጵያ ሆነች። ስምምነት እንዲደረግ የሚያስፈልገውም፤ ከወራሪዋ ከኢጣልያና በነፃ አውጭነት ከቆመችው ከእንግሊዝ ጋር ሆነ። መጀመሪያ የእንግሊዙ ስምምነት ጥር 22 ቀን 1934 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ተፈርሞ እንደነበር ቀደም ብለን አስረድተናል። አሁን ደግሞ ስምምነቱ በወሰን ክልል ረገድ የነበረውን ቅርፅ እንመለከታለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ስምምነቱ የባቡር ሐዲዱን በእንግሊዝ ጦር ሥር አድርጎታል። ከድሬዳዋ እስከ ሱማሌ የሚደርስ መጠኑ ያልታወቀ መሬት ለእንግሊዝ ጦር ማቋቋሚያ አድርጎአል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይ ምን ያህል ችግር እንደፈጠረ ዛሬም መገመት ይቻላል። አንዱ መስተካከል የነበረበት ጉዳይ ይህ ሆነ።

ሁለተኛው ጉዳይ ከወራሪዋ ከኢጣሊያ ጋር ያለው ነው። ጥያቄዎቹ:-

ሀ. ኢጣልያ በኢትዮጵያና በአልባኒያ ላይ ያሳትን የይገባኛል ጥያቄ እንድታነሣ ተጠየቀች። ያለምንም ማንገራገር አነሳች።

ለ. በአፍሪካ አሕጉር የነበሩት የኢጣልያ ግዛቶች፤ ማለትም የሊቢያ፣ የኤርትራና የሶማሊያ ጉዳዮች ግን አነጋገሩ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቅኝ ግዛት ማስወገጃ ጉባዔ ተጠባባቂነት/ትረስትሽፕ/ ሥር እንዲቆዩ ተወሰነ። እነዚህ ግዛቶች በእንግሊዝና በፈረንሣይ ይዞታ ሥር ቆዩ። የኢትዮጵያ ጥያቄ አድማጭ አጥቶ አንዳንድ አካባቢዎች በእንግሊዝ ይዞታ



ሥር እስከ አሥር ዓመት ያህል ሊቆዩ ቻሉ። በዚህ ላይ ደግሞ እንግሊዝ ታላቅዋ ሶማሊያ የሚለውን ሃሳብ አነሣስታ ሰሜን ሶማሊያንም ጨመረችበትና፤ አሁን ወደሚታየው ሁኔታ ያደረሱትን ጉዳዮች አስጀመረች። የኤርትራ ጉዳይ ከሁሉም የበለጠ አከራከረ። ኢትዮጵያ አጥብቃ ስለያዘች አሁን የታየው በጦርነትና በኃይል የመገንጠል ክስተት ተፈጠረ።[4]

ሐ. የጦር ካሣው ጉዳይ ሌላው አነጋጋሪ ጉዳይ ሆነ። የጣልያን ጠብ አጫሪነትዋና ወራሪነትዋ አላከራከረም።

መ. ኢጣልያ ከኢትዮጵያ ዘርፋ የወሰደቻቸውን የታሪክ ቅርሶች እንድትመልስ የሚለው ደግሞ ሌላ ጥያቄ ሆነ። አሁን አዲስ አበባ ባቡር ጣቢያ አደባባይ የሚገኘው የሞዓ አንበሳ ኃውልት ተመለሰ። የአክሱም ሐውልትም ቆሞ ከቆየበት ከሮም ከተማ በቅርቡ ሊመለስ ችሏል። ጥያቄው ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለማልማት ከፍተኛ ወጭ አድርጋለች ወደሚል አመለካከት ዞረ። ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደችው የልማትና የጥፋት ሥራ ሲመዛዘን፤ የጥፋቱ ወገን እንደ አመዘነ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ነገር ግን ለአውሮፓ እንደዚያ አልታየውም። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አርባ ሚሊዮን ብር ካሰች። ኢትዮጵያ የተከራከረችው ስለ ሕግ ጭምር እንጂ ስለጥቅም ብቻ አልነበረምና ተቀበለች።



ሁለቱ ባላንጣዎች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

የአውሮፓን የፖለቲካ ባሕርይ ጥቂት ለመመልከት ያህል፤ ኢጣልያ ከጦርነቱ በኋላ ምን እንደ ተደረገላት ማየት ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ላይ በአጥቂነት መነሳትዋን፣ በጦር ኃይል መውረርዋን፣ ሰላማዊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዓለም ሕግ በተከለከለ የጋዝ መርዝ መፍጀትዋን ማንም አይክድም። ሁሉም ያምናል። ነገር ግን የሚደመጠው የኢትዮጵያ ጥያቄ አይደለም



ሁለቱ ባላንጣዎች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

የኢጣልያ እንጂ፡፡ ኢጣልያ ጦርነቱን በማስነሳት የመጀመሪያዋ ናት፡፡ ነገር ግን በኃላፊነት የተጠየቀችው ከጀርመን ጋር በመተባበርዋ ብቻ ነው፡፡ በአውሮፓ አድላዊ አመለካከት ጣልያን ኢትዮጵያን መቀጥቀጥዋ ተገቢ ነው ማለት ነው፡፡ በፖትስደም የድል አድራጊዎቹ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉባዔ ላይ የኢጣልያ ጉዳይ ተነሣ፡፡ ለድል አድራጊዎቹ መንግሥታት የጦር ጓደኛ እንደነበረች ሆኖ ተቆጠረች፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነው ሰር ዊንስተን ቸርችል ለኢጣልያ መንግሥትና ሕዝብ በሬዲዮ አስተላልፈው በነበረው መልእክት ተደናግጠው፤ ጥቂት የኢጣልያ ሹማምንት ሙሶሊኒን ከሥልጣኑ በማውረድ ኢጣልያን ከጀርመን ለመነጠል ጥቂት ሙከራ አድርገው ስለነበር ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ መሠረት ኢጣልያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሆነች፡፡ እሷም የቀድሞ ግዛትዋን ሊብያን፣ ኤርትራንና ሶማሊያን መልሣ ለመያዝ እንዲፈቀድላት፤ በነሐሴ 1938 ዓ.ም በፓሪስ ከተማ ለተደረገው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉባኤ ለማቅረብ በቃች፡፡

ከዚህም የተነሣ ሁኔታዎች ተለዋወጡ፡፡ በኅዳር ወር 1940 ዓ.ም ለንደን በተደረገው የእነዚያው መንግሥታት ጉባዔ ላይ ደግሞ የሕዝቦች ድምፅ እንዲጠየቅ ተወሰነ፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ኤርትራ ከኢትዮጵያ መዋሐድን፣ ሶማሊያ ነፃነትን መረጡ፡፡ በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ የወሰን ጉዳይ ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ሥርወ ነገር ተመልሶ ገባ፡፡ በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል አለመግባባት እየተፈጠረ በተደጋጋሚ ግጭት ተነሣ፡፡ ከሁለቱም ወገን ብዙ ደም ፈሰሰ፡፡ በአድልዎ የተሰጣት ዕድል ለኢጣልያም አልጠቀማት፡፡ አጥቂ ሆነው ድንገት ቀደምዋት፡፡ እርስዋ በፖለቲካ እየዘቀጠች ሄዳ በሃምሣ ስምንት ዓመት ሃምሣ ሰባት መንግሥት እስከ ማቋቋም ደረሰች፡፡ ማፊያ እየተባለ በዓለም የታወቀ የወንበዴ ቡድን መፈንጫ ሆነች፡፡


<u>**ማጣቀሻ ፅሑፎች**</u>

1. Winston Churchill, *The Second World War*, pp. 464-470.
2. Winston Churchill, *The Grand Alliance*, pp. 434-444.
3. Kimons Skordiales, *Kagnew*, p. 1.
4. Carlton Hayes, *Contemporary Europe Since 1870*, pp. 682-689.




# ምዕራፍ ስድሣ ሶስት
# ኢትዮጵያና ነፃነትዋ

ኢትዮጵያ በመንግሥታት ታሪክ ዘመን ሁሉ እንደኖረች አላከራከረም፡፡ ወገንም ጠላትም የተቀበለው ሐቅ ነው፡፡ የሚያከራክረው ለምን ያህል ዘመን የሚለው ጥያቄ ብቻ ነው፡፡ አንድ መቶ ዓመት በሚለው የሻዕቢያ ቀልድና ሦስት ሺህ ዓመት በሚለው የደርግ ፌዝ መርካት የለብንም፡፡ ጉዳዩን በጥልቅ መመርመር ይገባናል፡፡

ኢትዮጵያ ክርስቶስ ሊወለድ 2800 ዓመት ሲቀረው በተፃፈ ታሪክ ውስጥ ስምዋ እንደተጠቀሰ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንደ አለ ተመዝግቦል፡፡[1] ክርስቶስ ሊወለድ 2500 ዓመት ሲቀረው ከግብጻውያን ጋር የንግድ ግንኙነት እንደነበራትም በታሪክ ተዘክሮአል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም በተደጋጋሚ ተጠቅሳ ትገኛለች፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ከውጭ አገር የተገኙ ናቸው፡፡ ወደ ሀገራችን የታሪክ ጽሑፎች ስንመለስ ይበልጥ ተጨባጭነት ያላቸው ማስረጃዎች እናገኛለን፡፡ በኢትዮጵያውያን ታሪክ ፀሐፊዎች ዘንድ የመጀመሪያው ንጉሥ ሰብስታህ ነው፡፡ የነገሠው ክርስቶስ ሊወለድ 2545 ዓመት ሲቀረው ነው፡፡ ከእሱ ወዲህ ያለውን ቀረቤታ እንመለከታለን፡፡

| መንግሥቶች | የነገሥታት ብዛት | ዘመን |
|---|---|---|
| 1. ከሰብስታህ እስከ ጲኦሪ | 22 | 560 |
| 2. ከጲኦሪ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ | 52 | 1003 |
| 3. ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ባዚን 8ኛ ዓመት የክርስቶስ ልደት | 67 | 982 |
| እስከ ክርስቶስ ልደት | 141 | 2545 |
| 4. ከባዚን 9ነኛ ዓመት እስከ ዛጉዌ… | 93 | 920 |
| 5. ከዛጉዌ እስከ ይኩኖ አምላክ | 11 | 333 |
| 6. ከይኩኖ አምላክ እስከ ሠርፀ ድንግል.. | 26 | 201 |
| 7. ከሠርፀ ድንግል እስከ ተክለ ጊዮርጊስ /ከ1553 እስከ 1777 ዓ.ም/.. | 18 | 224 |
| 8. ከተክለ ጊዮርጊስ እስከ ዳግማዊ ቴዎድሮስ | 14 | 68 |
| 9. ከቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጅ ኢያሱን ጨምሮ… | 7 | 121 |
| 10. የአብዮት ዘመን………… | 4 | 20 |
| ከክርስቶስ ልደት በኋላ | 173 | 1987 |
| ጠቅላላ ድምር…….. | 314 | 4532 ነው[2] |

የመንግሥቶች ዓይነት የተለያየ መሆኑ አያስደንቅም። የወሰኑ በየጊዜው መስፋትና መጥበብም በአንድ ሀገር ላይ ብዙ ጊዜ የሚታይ ነገር ነው። የመናገሻ ከተማው ከቦታ ወደ ቦታው መዘዋወርም አያስገርምም። መታየት ያለበት የሀገሪቱ ሕልውና ፀንቶ መኖሩ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ በመንግሥትነት መሥፈርትየኖረችበት ዘመን ከ4532 ቢበልጥ እንጂ አያንስም። አንድ ሕዝብ ተሰብስቦ ወዲያው በአንድ ሥርወ መንግሥት ሥር አይከተትም። ረዘም ያለ ጊዜ ያስፈልገዋል። ስለዚህ ዛሬ በ1987 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለ5000 ዘመን እንደኖረች ቢቆጠር ልዩነቱ ከ468 ዓመት ስለማይበልጥ ማጋነን አይሆንም።

በስም አጠራርዋ ጭምር የአፃፃፍ ተፋለስ በታሪክ ውስጥ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ ስድሳ ሦስት ጊዜ ያህል ይጠቅሳታል። በነገሥታትዋም ስም ሲጠራት ንግሥት ሳባ፣ ንግሥት አዜብ ይላታል። ኩሽ የሚላትም ጊዜ አለ። ቅዱስ ዳዊት ግን ደጋግሞ ኢትዮጵያ ይላታል። ቁርአን ሕዝቦችዋን ሃበሻ ይላቸዋል። የእንግሊዝ ጸሐፍት አቢሲንያ ይሉአታል። ሙሶሊኒ ስምዋን ከእንጭራሹ ደምስሶ ምሥራቅ አፍሪካ ብሎአት ነበር። ኢትዮጵያ በኢትዮጵያዊነትዋ ኖራለች። ወደፊትም ትኖራለች።[3]

ታሪክዋን በዘመን አቆጣጠር፣ በስም አጠራር የጀመርነው ለዋዛ አይደለም። ኢትዮጵያ በኢትዮጵያዊነትዋ ታውቃ ነፃነትዋን ጠብቃ ከ5000 ዓመት ላላነሰ ጊዜ መኖርዋን ለማጠየቅ ነው። በዚህ ረጅም ዘመን ማዕከላዊ መንግሥቱ ከበረሃማው ከሜርዌ ወደ ደጋው የወጣው፤ ከወራሪዎች ለመከላከል ጭምር ሳይሆን አልቀረም። የአሶር፣ የፋርስ፣ የግሪክ እና የሮም ተፅዕኖ ከብዶ ነበርና።[4] አክሱም፣ ላሊበላ፣ ፈጠጋር፣ ጎንደር፣ ደብረ ታቦር፣ መቀሌ፣ አዲስ አበባ ተዘዋውሮአል። ወሰንዋም እንደ ጊዜው ሁኔታ ሲጠብና ሲሰፋ ኖሮአል። የኢትዮጵያ ሕልውና ግን ታሪክ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ጸና ቆይቶአል።

በአገር ውስጥ አስተዳደር ረገድ የኢትዮጵያ ሁኔታ ጭንቅና መከራ የበዛበት እንደ ሆነ የሚያመለክቱ ብዙ የታሪክ አሻራዎች አሉ። የሀገሪቱ ማዕከል ከቦታ ወደ ቦታ መንቆራጠጥ በየጊዜው ለተነሱ መሪዎች ይጠቅም እንጂ ለሕዝብ የሚበጅ አልነበረም። የሀገር ዳር ድንበር የሚጠበቀው ሁል ጊዜም በጦርነት ነው። ሥልጣን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚዘዋወረው በፍልሚያ ነው። ይህ ሁሉ የሚገፋው በድሐው ሕዝብ ነው።

አሁን የታሪክ ቅርስ አድርገን የምንመለከታቸው የአክሱም ሐውልቶች የተሠሩት፣ የላሊበላ የአለት አብያተ ክርስቲያናት የተፈለፈሉት፣ የጎንደር ቤተ መንግሥቶች የታነጹት፣ በጊዜው የነበረውን ሕዝብ እየጠቀሙ አልነበረም። እየጎዱ እያሰቃዩት እንጂ። እነዚህን ሁኔታዎች ለመለወጥ ብዙ ድካም ተደክሞአል።



ከባሕረ ሠላጤ ነገሥታት ጋር ለነበረው ፍጥጫ መከላከያ የሚረዳ ወዳጅ ማፍራት አስፈለገ። በንግሥት ሣባና በንጉሥ ሰለሞን መካከል እንደ ዘመኑ ሁኔታ የወዳጅነት ግንኙነት ተፈጠረ። እስከ መዋለድም ተደረሰ። ይህ ሀገርን ከውጭ ወራሪ ለማዳን የተደረገ ሙከራ፤ እሥራኤላውያንን ኢትዮጵያ ውስጥ አስገባቸው። በቀዳማዊ ምኒልክ መንገሥ ምክንያት ለሥልጣን አበቃቸው። በጥቁሮቹ ኢትዮጵያውያንና በነጮቹ እሥራኤልውያን መካከል የተፈጠረው የዘር ልዩነት ወጣቶችን እርስ በርስ በማጋባት የአስተዳደር ጥበብ ወረሰ። አበሻ ማለትም ድብልቅ ክልስልስ ሕዝብ ተነሣ። አረማዊ የነበረው እምነት በጽላተ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፤ በብሉይ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ተሸጋገረ።[5] ወራሪ ጠላት ጽላተ ሙሴን እየተሸከሙ በእግዚአብሔር በመተማመን የመከላከል ዘዴ ተገኘ።

ከቤተ እሥራኤል በመጣው አዲስ አስተዳደርና በቀድሞው ሥርዓት መካከል የተቀሰቀሰው ግጭት፤ ዮዲትን /ጉዲትን/ አስነስቶ የመንግሥቱን ማዕከል ከአክሱም ወደ ላስታ አዛወረው። ሥርወ መንግሥቱንም ከንግሥት ሳባና ከሰሎሞን ዘር ወደ ዛጉዬ ወገኖች አሸጋገረው። ይህ የሥልጣን ቅሚያ ከውጭ ተፅዕኖ ለማምለጥ ጭምር የተደረገ ሳይሆን አልቀረም። ስለዚህ ሀገርን የመከላከል ጉዳይም አለበት ሊባል ይበቃል። ቢሆንም ረዥም ጊዜ የወሰደ ዕልቂትና ጥፋት አስከተለ።

በዚያም ጊዜ የውጭ ወራሪዎች ኢትዮጵያን ለማጥቃት፣ ቢቻልም ለመያዝ ሞክረዋል። ሁሉም በኢትዮጵያውያን ድል እየተመቱ ወደየመጡበት ተመልሰዋል። ዋና ዋናዎቹን እንጠቅሳለን። ክርስቶስ ሊወለድ 336 ዓመት ሲቀረው ታላቁ እስክንድር መቄዶንያ በምትባለው የግሪክ አገር ተነሣ። ከግብፅ እስከ ህንድ ያለውን አገር ሁሉ ገዛ። ኢትዮጵያን ለመያዝ በአደረገው ሙከራ እሱ ራሱ በስለላ ሥራ ላይ እንደ ተሰማራ ተይዞ ከንግሥት ሕንደኬ አደባባይ ቀረበ። በንግሥት ሕንደኬ ሠራዊት ብዛትና በስለላ ጥበብዋ በመደነቅ የወረራ ሃሳቡን ትቶ በሰላም ተመለሰ።

አውግስጦስ ቄሣር የተባለው የሮም ገዥ ከአውሮፓ፣ ከአፍሪካና ከእስያም አህጉር ብዙ አገር አስገበረ። ኢትዮጵያንም ለማስገበር ፈልጎ አይሎስ ጋሉስ በሚባል የጦር አዛዡ አማካይነት፤ 10,000 እግረኛና 8,000 ፈረሰኛ ጦር ላከ። ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንዳይረግጥ ከጠረፋቸው ላይ በጦር አገዱት። ከዚያም ለብዙ ዓመታት ተዋግተው ሠራዊቱን ፈጅተው መለሱት። ኔሮ የሚባለው የሮም ንጉሥም ኢትዮጵያን ለመያዝ ፈለገ። ሰላዮቹና አማካሪዎቹ የሰጡትን ምክር ጥሶ በኃይሉ ተማምኖ፤ ከምቤሰስ በሚባል አዛዥ መሪነት ታላቅ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ላከ። እሱንም ኢትዮጵያውያን ወግተው ድል በማድረግ መልሰውታል።[6]

ሃያ ዓመት ገደማ /ከ1516-1536 ዓ.ም/ የፈጀውና ብዙ ጥፋት ያደረሰው በግራኝ መሐመድ መሣሪያነት የተካሄደው የቱርክ ወረራ ነው።

ይህንን ጦርነት የሀገር ውስጥ የርስበርስ ውጊያ አድርገው የሚመለከቱ፤ የሃይማኖት ጦርነት አድርገው የሚያዩም አሉ። በእጅ አዙር የተካሄደ ወረራ መሆኑን ከአለማጤናቸው ነው እንጂ፣ ጦርነቱ የቱርክ ወረራ ነው።[7] ይህንን የቱርክን ወረራ ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን ሊመልሱት አልቻሉም። የፖርቹጋሎችን ዕርዳታ መጠየቅ ነበረባቸው። ፖርቹጋሎችም ለዕርዳታ ገብተው ቱርኮቹን አሸነፉና የኢትዮጵያን ነፃነት አረጋገጡ።[8] ነገር ግን ግራኝን በማሸነፍ ወረራ ከመለሱ በኋላ፤ እነሱ እራሳቸው ሥር ሰድደው አስቸገሩ። ከእነሱ የመላቀቁም ሥራ ቀላል አልነበረም። በአባቶቻችን የፖለቲካ ጥበብ ያለ ግጭት በሰላም ተፈጸመ። የሱስኒዮስ "ፋሲል ይንገሥ፣ ሃይማኖት ይመለስ" የሚለው አዋጅ የዚህ ሂደት መደምደሚያ ነበር።

ከዚህ ቀጥሎ ተከታታይ የወረራ ሙከራ በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደው፤ ከአስራዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ ነው። ዘመኑ የቅኝ ግዛት የተስፋፋበት በመሆኑ አንዱ ሲመለስ ሌላው እየተተካ በኢትዮጵያ ላይ ተረባረቡባት። ከ1824 እስከ 1927 ዓ.ም ድረስ የነበረው ምዕተ ዓመት ያላቋረጠ የጦርነት እሳት የነደደበት ጊዜ ነበር። በዚህ አንድ መቶ ዓመት ውስጥ በድምሩ 32 ወራሪዎች በኢትዮጵያ ላይ ዘምተው ሁልጊዜም እየተሸነፉ ተመልሰዋል። ከእነዚህ ወራሪዎች 11 በምዕራብ፣ 4 በሰሜን፣ 15 በምሥራቅ፣ 2 በደቡብ የመጡ ነበሩ። ከወራሪዎቹ ቱርክ 10 ጊዜ፣ ጣልያን ደግሞ 8 ጊዜ ሙከራ አድርገዋል። ግብጾች፣ ሱዳኖች፣ እንግሊዝና ፈረንሣይም የተቻላቸውን አድርገዋል። ከእነዚህ ጦርነቶች ትልቁና ወሣኙ ኢጣልያ የተሸነፈችበት የአድዋው ነበር። ከዚህም በስተቀር የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማፍረስ፤ ሦስት ጊዜ በእንግሊዝና በጣልያን፣ አንድ ጊዜ ደግሞ በእንግሊዝ፣ በፈረንሣይና በጣልያን መንግሥታት መካከል ውል ተፈርሞአል።[9]

የ1928 ዓ.ምቱ የኢጣልያ ወረራ የተቀሰቀሰው ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ በተገለጹት 32 ዓለም አቀፍ ጦርነቶች ብዙ ችግር ከደረሰባት በኋላ ነው። በሀገር ውስጥ የተካሄደው የርስበርስ ውጊያ ደግሞ ብዙ ጉዳት አድርሶባታል።

ኢትዮጵያና ኢጣልያ ጦርነታቸው እንደምን እንደአካሄዱት ከታየ በኋላ፤ በተመራማሪ አእምሮ የሚነሳው ጥያቄ "ለመሆኑ ጦርነቱን ማስቀረት የሚቻልበት ዘዴ አልነበረምን?" የሚል ይሆናል። ነፃነትዋ እስከተጠበቀላትና የግዛት አንድነትዋ እስከተከበረላት ድረስ፣ በኢትዮጵያ በኩል ጦርነቱን የማስቀረት ከፍተኛ ፍላጐት ነበር።[10] ስለዚህ በኢጣልያ በኩል የነበረውን ሁኔታ መመልከት ግድ ይሆናል።

ኢጣልያ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝ ሃሳብዋ ቁርጠኛ ነበር። ምክንያቶቹ ቀደም ብለው ተዘርዝረዋል። በኢጣልያ በኩል ጥናት የሚካሄደው "እንደምን?" በሚል ጥያቄ ላይ ብቻ ነበር። ይህ በጉልህ እየታወቀ፣ ጦርነቱ እንዲቀር በኢትዮጵያ በኩል ጥረት አለመደረጉን የእነሱ በኩል ተከራካሪዎች ያወግዛሉ። የኢትዮጵያ መንግሥት ኢጣልያ የንግድና የልማት ሥራዎች



እንድታካሂድ በ1920ዓ.ም /1928/ የተደረገውን ስምምነት ቢያከብር ኖሮ ጦርነት ይነሣ እንዳልነበረ ያስባሉ። የሆርና ላቨል የዕርቅ ሃሳብ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን፣ ጦርነቱ ይቆም እንደነበረ አድርገው ያስባሉ።[11] እውነት ነው። ይህ መንገድ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ያለጦርነት እጅ ታደርግበት ስለነበር፤ ያ ሁሉ የደም መፋሰስ አይደርስም ነበር። ምናልባት የኢጣልያ ቅኝ ገዥነት እንደ ጸና ይቀርም ነበር። እንደዚህ አለመሆኑ ኢጣልያውያንን ያጸጽታል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ጥቅም አልነበረም። ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ጠብቃ፣ ወሰንዋን አስከብራ የምትኖርበት ዕርቅ በዛ ውስጥ አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን እጅ አስጥ እርቅ አለመቀበላቸው ያስመሰግናቸዋል። በወቅቱ ቀርበው በነበሩት አማራጮች፣ ጦርነቱን ለማስቀረት የሚቻልበት አንዳች ዘዴ እንደ አልነበረ እስማማለሁ።

በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተካሄደውን ጦርነት ከዚህ በላይ ባሉት ምዕራፎች ሁሉ በዝርዝር ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ከታሪካችን መማር የሚገባንን እንመርምር። ስለዚህ ቀጣዩ ጥያቄ "ኢትዮጵያ ከዚህ ሁሉ ወራሪ ነፃነትዋን አስከብራ ለመኖር ያበቁአት ምን፣ ምን ናቸው?" የሚል ይሆናል። ይህንንም ጥያቄ መመርመር ትምህርት ይገኝበታል። ስለዚህ በነፃነት ለመኖር ያበቁአትን ነገሮች አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን።

1ኛ. እንደእኔ፡- ኢትዮጵያን በነፃነት ጠብቆ ያቆያት እግዚአብሔር ነው። ልብ ለአለው፣ ለዚህ ብዙ ማስረጃ አለ፤ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጠቅሳለች። ቅዱስ ዳዊት "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" አለ። "እግዚአብሔር ይነሣ፣ ጠላቶቹም ይበተኑ።... ጢስ እንደሚበን እንደዚሁ ይብነኑ።... ጻድቃንም ደስ ይበላቸው። በእግዚአብሔርም ፊት ሐሤት ያድርጉ..." በአለበት መዝሙሩ፤ ደግሞም "...አንተም የዘንዶውን ራስ ቀጠቀጥህ። ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሀቸው..." አለ።[12] እስላሞችም ነቢዩ መሐመድ "አበሾችን አትንኩ ያለዚያ ትጠፋላችሁ" እንደ አሉ። እነዚህ ቃላት ለኢትዮጵያ በትክክል ተፈጽመውላታል። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን የሚረዳት እርስዋን በማዳን ብቻ አይደለም። ጠላቶችዋን በማጥፋት ጭምር እንጂ። ኢትዮጵያን የነኩ ኃይሎች ጠፍተዋል። አንባቢ ሊገነዘበው ስለሚችል ማስረጃ ለማቅረብ አንሞክርም። ልበ ቢሶች ልብ አይሉትም እንጂ፣ አሁንም እየታየ ነው። ወደፊትም ይቀጥላል። ኢትዮጵያ በእምነት እስከ ጸናች ድረስ አይናወጽም። ቃለ መለኮት ነውና።

2ኛ. ኢትዮጵያ ነፃነትዋን አስከብራ የኖረችው በልጆችዋ ደም ነው። በዘመናችን አነጋገር "በትግል" ነው። ኢትዮጵያውያን ታላቁ ችግራቸው እርስበርሳቸው አለመስማማትና አለመተባበር ነው። ሆኖም የሚለያዩትና እርስበርሳቸው የሚጋጩት በሰላም ጊዜ ነው። የውጭ ወራሪ በመጣ ጊዜ የርስበርስ ጠባቸውን ወደ ጐን በመተው፤ የመጣባቸውን ጠላት ተባብረው

ይመልሳሉ። በተለይ የአማራው ነገድ የሀገርን ነፃነት በመጠበቅ ረገድ የከፈለውን መሥዋዕትነት መካድ ሞኝነት ነው። ይህ ነገር መልካም ነው። የርስበርስ ልዩነታቸውን በመሣሪያ ፍልሚያ ሳይሆን በሰላምና በመመካከር ለማቃለል የሚችሉበትን ሥርዓት ቢመሠርቱ ደግሞ እጅግ መልካም በሆነላቸው ነበር። እያደር በመቀጨጭ ፈንታ ይዳብሩ ነበር።

3ኛ. ኢትዮጵያን በነፃነት ለማኖር ከረዱት ነገሮች አንዱ ዘውድ ነው። በሰላም ጊዜ የዘውድ አገዛዝ ተፅዕኖ ከባድ ነው። ብዙዎቹን አስመርሮአል። አወራረሱም ከሥርዓት እየወጣ ብዙ ደም አፋስሶአል። ብዙ ጥፋት አድርሶአል። የውጭ ወራሪ በመጣ ጊዜ ግን ሕዝቡን አንድ በማድረግ ረገድ ያለው ችሎታ ፅኑዕ ነው። ነገሥታቱም ብዙ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። የኢትዮጵያን ነፃነት በመጠበቅ በኩል ዘውድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጕአል። ዘለባጅ እንጂ እውነተኛ ታሪክ ይህንን እውነት ሊክድ አይችልም።[13]

4ኛ. ለኢትዮጵያ ነፃነት ደጀን ሆኖ ያገለገለው የመሬት አቀማመጥ ነው። ለምንትዋ ብዙ ጠላት አፍርቶባታል። በአንፃሩ ደግሞ የጅኦግራፊ አቀማመጥ ለነፃነት በተደረገው ትግል በጕ አስተዋፅኦ አድርገዋል። በሀገሪቱ በመላ ታላላቅ ተራሮችና ሸንተረሮች አሉ። በውስጣቸውም ውሃና ለም መሬቶች አቅፈው፣ የውጭ ወራሪ በወጣ ጊዜ ለመከላከል የተመቹ እጅግ ብዙ ናቸው። ተዋጊው ሠራዊት ስንቅና ውሃ በማጣት አይቸገርም። ሕዝብም እነዚህን በሮች በጥንቃቄ ይጠብቃቸዋል። ለምሣሌ እኔ በተወለድኩበት አካባቢ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣለት በር አለ። በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት። ያለአግባብ በጠላት ከአስያዘ ቤተሰቡ ይዋረዳል ይናቃል። በንጉሡ ነገሥቱ ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ መዝሙር

ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፣
አትፈሪም ከጠላቶችሽ፣

ይል የነበረው በከንቱ አልነበረም። እስከ አሁን የገለጽነው የደጋውን ነው። የቆላውን አገር ከወራሪ ለመከላከል ግን እጅግ አስቸጋሪ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር በሮችዋን ያጣችው ከዚህ የተነሣ ነው።

5ኛ. አውሮፓውያን ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ጠብቃ ለመኖር የቻለችው በአውሮፓውያን እርስበርስ መከፋፈል እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ። በመጠኑ እውነትነት አለው። አንዱ በጠላትነት ሲነሣ፣ ሌላው በወዳጅነት ከኢትዮጵያ ጕን ይቆማል። ይህንን የሚያደርጉት የርስበርስ ሚዛናቸውን ለመጠበቅ በሚያደርጉት ጥንቃቄ እንጂ፣ ለኢትዮጵያ ደንታ ኖሮአቸው አይደለም። አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ይህንን ሁኔታ ተገንዝበው አውሮፓውያንን እርስበርሳቸው የፖለቲካ ጨዋታ እንዲጫወቱ በማድረግ፣ የኢትዮጵያን ነፃነትና ጥቅም አስጠብቀዋል። በተለይም ብልሁ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ።



6ኛ. የኢትዮጵያን ነፃነት የረዱ አገሮች አሉ። ስለኢትዮጵያ ነፃነት ስናስብ፣ እነሱንም ማስታወስና ማመስገን ይገባናል። ፖርቱጊዞች በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከተሰነዘረብን የኦቶማን መንግሥት ወረራ ስለአዳኑን እናመሰግናቸዋለን።[14] እንግሊዞች በ1927 እስከ 1930 ዓ.ም ከቆየው የጣልያን ወረራ ስለአላቀቁን ትውልድ የማይረሳው ምስጋና እናመሰግናቸዋለን። የቀድሞው የሶቪየት ሕብረት መሣሪያ በመሸጥ፣ ኪዩባና ደቡብ የመን ወታደር በመስጠት በ1969 እስከ 70 ዓ.ም ከተቃጣብን የሶማሊያ መንግሥት ወረራ ተከላክለውልናል። እነሱንም እናመሰግናቸዋለን።

ይህንን ምዕራፍ ከመደምደማችን በፊት "ለወደፊቱስ ምን ይሻላል?" በሚል ጥያቄ ላይ ጥቂት ማስተዋል ይበጃል። አንድነትና ብርታት የሚሉት ገራገር ፈሊጦች በቂ አይደሉም። እውነተኛ ነገሮች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ጠላት የሚያበዙባት ፀጋዎች አሏት። ከእነዚህም ጠላት አፍሪ ፀጋዎች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. **ለም አፈር**፣ ኢትዮጵያ አፈር አላት። እያያዛችንን በማበላሸት እያጠፋነው ነው እንጂ፣ በእህል፣ በእፅዋት፣ በዛፎች፣ በእንስሳትና በአራዊት ያለው ሀብት ቀላል አይደለም።

ለ. **ለስላሳ አየር**፣ ኢትዮጵያ መላውን ዓመት የሚቆይ ለስላሳ አየር አላት። ከቆላው አገር በስተቀር። ይህ ፀጋ ቀላል አይደለም። በርካታ አገሮች ይህን አልታደሉም።

ሐ. **ውሃ**፣ በዓለም ላይ ውሃ ታላቅ ሀብት ነው። ኢትዮጵያ ከዓመት ዓመት ጥሩ ውሃ በብዛት የሚያፈስሱ ታላላቅ ወንዞች አሏት። የእነዚህ ውሃዎች አጠባበቅና አጠቃቀም የራሱ የሆነ ችግር አለው። በተለይም የዓባይ።

መ. **ማዕድን**፣ ማዕድን የሀብት ምንጭ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ ማዕድናት አሉአት። አውጥቶ መጠቀም አልተቻለም። ያልተቻለውም በእውቀትና በአቅም ማነስ ምክንያት ነው። በእነዚህም ጠላት ከመግዛት ይልቅ የመጠቀምን ፈሊጥ መከተል ይሻላል።

ሠ. **አቀማመጣችን**፣ የኢትዮጵያ የጂኦግራፊ አቀማመጥ በአውሮፓና በአፍሪካ፣ በመካከለኛውና በሩቅ ምሥራቅ መተላለፊያ ላይ ነች። ስለዚህም በየጊዜው የሚነሱ ኀያን መንግሥታት ይተናኮሉአታል።

ረ. ቅኝ ግዛትን ተናንቃ በማሸነፍ ከ5000 ዓመት በነፃነት ኖራለች። ይህም ጥሩ ታሪክ የሌላቸውን አገሮች ያስቀናቸዋል። የኢትዮጵያ ታሪክ የአንድ መቶ ዓመት ነው እስከማለት የደረሱት ከዚህ የተነሣ ነው።

ሰ. ኢትዮጵያ ለጥቁሩ ሕዝብ መልካም አርአያ ናት። የአፍሪካ አገሮች ምክርዋን ማዳመጥ ጀምረዋል። የዘር ልዩነት በሽታ የተጠናወታቸው አገሮች ይህንን አይወዱም።

ሸ. በእምነት ምክንያት የሚቃረኑአት የውጭ ኃይሎች አሉ። ክርስቲያኖቹ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶችም አልተኙላትም። እስላሞችም እንደዚሁ።

ቀ. ሌላው ችግር የውጭ ጉዳይ ነው። አንድ ጊዜ ከአንዱ ሌላ ጊዜ ከሌላው መሆን አይጠቅምም። የሚሻለው በተቻለ መጠን ከሁሉም ወዳጅ መሆን፤ ይህ ባልተቻለ ጊዜ ገለልተኛ መሆን ነው።

ከዚህ በላይ ከሀ እስከ ሸ የተመለከተው የውጭ አገር ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን አመለካከት የሚያሳይ ነው። በዚሁ ላይ ደግሞ የሀገር ውስጥ ችግር አለ። እነሱንም እንደ ውጭ አገሮቹ ጉዳዮች በየፈርጃቸው መመልከት ያስፈልጋል።

ትልቁ ችግር የመልካም መንግሥት እጦት ነው። ሀገርዋ መልካም፣ ሕዝብዋ ሠላም ፈላጊ፣ ሠላም ወዳድ ነው። ስለዚህ ገዥዎች ይሚሟቱባታል። በማዘን፣ በመራራት አይተዋትም። ሥልጣን ለመያዝ ብዙ ደም ያፈሳሉ። ከያዙ በኋላ በሥልጣን ላይ ለመቆየት፣ በሕዝብ ላይ ብዙ የጭካኔ ሥራ ይሠራሉ። ታላላቅ ብዝበዛ ያካሂዳሉ። ሥራቸውን ስለሚያውቁ፣ በራሳቸው አይተማመኑም። ስለዚህ ምሥጢራቸውን ከውጭ አገር ሰዎች ጋር ያደርጋሉ። ገንዘብም የሚያስቀምጡት በውጭ አገር ይሆናል። ይህ ሁኔታ ሕዝብን አስመርሮአል። ሀገሪቱን አራቁቶአል።

ሁለተኛው ችግር የሕዝብ አንድነት መቀነስ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ ጐሣዎች፣ እንደ ዘመናችን አነጋገር ብሔረሰቦች ያሉባት አገር ናት። በ1945 ዓ.ም አካባቢ በትምህርት ሚኒስቴር የተካሄደ አንድ ጥናት የብሔረሰቦቹን ብዛት በቋንቋ ረገድ ተመልክቶ እስከ 115 አድርሶት ነበር። እንደ መመዘኛው ነው። በማንኛውም መመዘኛ ቢሆን ከ80 አያንስም። በዚህ ላይ ደግሞ የእምነት፣ የባሕልና የሥርዓት ልዩነቶች አሉ። እነዚህ ልዩነቶች ሥምረት ካላገኙና ተከባብረውና ተደጋግፈው የሚኖሩበት ሥርዓት ካልተፈጠረ፣ ኢትዮጵያ ጽንአት ልታገኝ አትችልም። ኢትዮጵያ ጽንአት ካላገኘች ጥቃት አይቀርላትም።

ስለዚህ፤ አዲሱ ትውልድ የአገሩን ነፃነትና አንድነት ለመጠበቅ፤ ሁለት አፎት ያለው ሠይፍ ጨብጦ መዋጋት ይኖርበታል። በአንድ ወገን በሀገር ውስጥ ከመጥፎ መንግሥታት፣ ከዘርና ከሃይማኖት ልዩነት። በሌላ ወገን ደግሞ ከውጭ ወራሪዎች። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ጣልያን እስከ ዛሬም ድረስ በመጥፎ ሥራዋ ተጸጽታ ኢትዮጵያን ይቅርታ አለመጠየቅዋ ነው።

***ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በነፃነት ትኑር!***
***(እንደእኔ፣ በበኩሌ፡- አሜን!)***



## አባሪ 1

## የንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ አነጋገስ

ልጅ ኢያሱ በወደቁ ጊዜ ከልጆቻቸው አንዱ መድኃኒዓለም በተባለ ገዳም፣ አባ ይርዳው በተባሉ አበምኔት እንዲጠበቁ ተደርጎ ነበር። ይህ ልጅ የተወለደው ጨፋ በተባለው ሥፍራ ነዋሪ ከነበሩት ከወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ዳርጌ ሲሆን፤ ስሙም የኂሳሽት ነበር።

የጣልያን ጦር ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ አርበኞችን የሚያንቀሳቅስ አንድ መሪ ስላስፈለገ፤ ከፍ ሲል የተጠቀሰው በወቅቱ እድሜው 18 ዓመት የነበረው የኂሳሽት ኢያሱ፤ በአለቃ ወልደፃድቅ ዘውዴ አቀነባባሪነት ነሐሴ 29 ቀን 1929 ዓ.ም እሁድ ዕለት ወክፈሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በተከናወነ ሥርዓት ነገሠ። እሱም ከነገሠ በኋላ በተራው፡-

- ባላምባራስ አበበ አረጋይን "ራስ"፤
- ቀኝ አዝማች ኃይሉ ወልደመድህንን "ደጃዝማች"፤
- ፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራንን "ደጃዝማች"፤
- አለቃ ወልደፃድቅ ዘውዴን "ፊታውራሪ"፤
- አቶ ወልደ ዮሐንስን "በጅሮንድ"፤
- ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴን "ከንቲባ"፤
- አቶ ዝቅ አርጌን "ፊታውራራ"፤
- አቶ ሞገስን "ፊታውራሪ"፤
- አቶ ገብረመስቀል ኃይሌን "ቀኛዝማች"፤
- አለቃ ሥዩም ተክሌን "ግራዝማች"፤
- ወጣት ምስካ ሥዩምን "ቀኛዝማች"፤ እንዲሁም ሌሎችንም ብዙ የጦር መሪዎችን በመሾም አርበኝነትን ሥርዓት አስይዞ አቋቋመ።

በዚህ ዓይነት አርበኛውን ካጠናከረ በኋላ በረከት፣ ስድስቶ ላይ መሽጎ የነበረውን የጣልያን ጦር ለመጨረስና ምሽጉን እጅ ለማድረግ ነሐሴ 27 ቀን 1930 ዓ.ም ትልቅ ጦርነት መራ። የጦርነቱ ዝግጅት የተቀነባበረው በምስጢር ነበር። ነገር ግን ምሥጢሩ ለጠላት ቀድሞ ደርሶ ኖሮ ሙከራው ሳይሳካ ቀረ። ብዙ ሰውም አለቀ።

ይህንንም ተከትሎ መልዓከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም የሰው ብልሃትና የሰው ተንኮል አለበት በሚያሰኝ አጠያያቂ ሁኔታ ሞቱ። መሞታቸውም በወክፈሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ወዲያውኑ ዜናው ደርሶ ሊነገር ችሏል።

# አባሪ 2
# የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማሕበር አመሠራረት

የጣልያን ወራሪ ጦር በሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብቶ ኢትዮጵያን መያዙን ለዓለም አስታወቀ። አርበኝነት ሳይውል ሳያድር በየቦታው ተጀመረ። በቡልጋ አርበኝነት የተጀመረው በየአካባቢው የጎበዝ አለቃ በመምረጥ፣ በአፄ ምኒልክ /ቀደም ሲል ማይጨው፣ ኋላ ላይ ደግሞ አዛውረው/ ኮረማሽ በተባለው ሥፍራ በሚገኝ ዋሻ ተቀምጦ የነበረውን ዳር ድንበር ማስከበሪያ የጦር መሣሪያ በመከፋፈል እና በእጅ የነበረውን እንደ ናስማሰር የመሳሰሉ ኋላ ቀር መሣሪያዎች በማንገብ፣ ጦር በመያዝና ጨቤ በመታጠቅ ነበር። እንዲሁም አንድ መሣሪያ ለሦስት ተጃጅቦ በመያዝ የጠላት ወታደርን ገድሎ መሣሪያውን በመቀማት ነበር።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር ጥር 2 ቀን 1931 ዓ.ም ተጉለት፣ አንቂፊኝ በተባለ ቦታ ተመሰረተ። ሌሎች ደግሞ አንቀላፊት በምትባል ሌላ ሥፍራ ላይ እኛም ቀደም ብለን ጥቅምት 23 ቀን ማኅበር አቋቁመን ነበር የሚል ድምፅ በየካቲት ወር ቢያሰሙም፣ ጉዳዩ ለታሪክ ቅሚያ ተብሎ የተቀነባበረ ተንኮል እንጂ እውነተኛ መሠረት ስላልነበረው አልሠራም።

**ጥር 2 ቀን የተመሠረተው ትክክለኛው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር የተመሠረተበት**

**1ኛ ዓላማ፡-**

1.1 አርበኞች እርስበርሳቸው እየተረዳዱና እየተደጋገፉ፣ በየቆሙበት ግንባር የወራሪ ጣልያንን ጦር በአቅማቸው ሁሉ እንዲከላከሉ።

1.2 በአንዱ ላይ ጥቃት ቢደርስ በጋራ እንዲከላከሉ።

1.3 የሚገኙ ማስረጃዎችን እና መረጃዎችን በምስጢር እንዲላላኩ፣ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ

2ኛ ዓላማ፡-

2.1 አርበኞችን እንዲመሩ በአርበኞች ስምምነት ትንሽ ቀደም ሲል የነገሡት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ የተባሉት የ18 ዓመቱ ወጣት ንጉሥ፣ መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም ድንገተኛና አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ስለሞቱ አርበኛው እንዳይላላ ስጋት ስለተፈጠረ፣

2.2 የንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይን ሞት ተከትሎ፣ ሙሴ ቀስተኛ በተባለ አንድ የስዊስ ተወላጅ በሆነ ሰው በተቀሰቀሰ ዕርቅ ምክንያት፣ በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም ሮርች በተባለ ቦታ የዕርቅ ነጥቦች በመቅረባቸው ምክንያት፣ ብዙ አርበኞች ወደ ግል ኑሯቸው በመመለሳቸው የአርበኛው ክንድ እንዳይላላ ስላሰጋ ነበር ማኅበሩ የተመሠረተው። ዕርቁም ሚያዝያ 7 ቀን 1931 ዓ.ም ፈረሰ። አርበኞችም ትግላቸውን በማሕበራቸው አማካኝነት አጠናክረው ቀጠሉ።



2.3 በአንዳንድ የአርበኛ መሪዎች መካከል በተነሱ ጥቃቅን ግጭቶች ምክንያት ጉዳት ስለደረሰ። ለምሳሌም፡- ፊታውራሪ ዝቅአርጌ እና ፊታውራሪ ሞገሤ መኩሪያ እርስበርሳቸው ተዋግተው ስለሞቱና ሠራዊታቸውም ስለተፈታ።

በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴና በፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ የሚመሩ አርበኞች የቀረበላቸውን ዕርቅ ሊቀበሉ ከቻሉበት ቅድመ ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ፡-

3.1 ሞቃዲሾ፣ ደናኔ /ሶማሊያ ግዛት ውስጥ/ እንዲሁም በኤርትራ ናኩራ ወደ ተሰኙ ቦታዎች ተወስደው የታሰሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲፈቱ፤

3.2 ኢትዮጵያዊ ያለ ፍርድ እንዳይገደል፤

3.3 የኢትዮጵያውያን ጉዳይ በኢትዮጵያውያን ዳኞች ብቻ እንዲታይ፤

3.4 በምግብ እጦት ሲጎሳቆል ለነበረው አርበኛ ጣልያን ልብስ እና ምግብ እንዲሰጥ የሚሉ ነበሩ።

በተለይ የታሰሩ ኢትዮጵያውያን እንዲፈቱ ተብሎ በተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ መሠረት ብዙዎች ሊፈቱ በቅተዋል።

## አባሪ 3
## የሙሶሊኒ አጭር የሕይወት ታሪክ

ቢኒቶ ሙሶሊኒ በኢትዮጵያም፣ በኢጣልያም ታሪክ ውስጥ ስሙ ሲጠቀስ ይኖራል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሚጠቀሰው በጨካኝነቱ ነው። በኢጣልያ ታሪክ ውስጥ ግን ኢትዮጵያን የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ለማድረግ በአካሄደው የጦር ሥራና በፋሽስት ፓርቲ መሥራችነቱ ይታወሣል። መጥፎ ዕድሉ ሆኖ ሁለቱም በእሱ በራሱ ግብር ተበላሹበት።

ሙሶሊኒ አሌዘንድሮ ሙሶሊኒና ወይዘሮ ሮዛ ከተባሉ ባልና ሚስት ሐምሌ 22 ቀን 1875 ዓ.ም /ጁላይ 29 ቀን 1883/ ቫራኖ ዲ ኮስታ በተባለች ቦታ ተወለደ። ስሙም ቢኒቶ ተባለ። ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ በእናቱ ብርታት ትምህርት ቤት ገባ። በትምህርቱ ስልቹ ይሁን እንጂ ጉበዝ ነበር። ሩየንዛ በተባለችው ከተማ ወደ አለው ሣልሲያን መነኮሳት ወደሚያስተዳድሩት ትምህርት ቤት እንዲገባ የተደረገው፣ ጠባዩን ለማረም ይችላሉ በሚል አስተያየት ጭምር ነበር። ነገር ግን አልቻሉም። አባቱ አሌዛንድሮ የፖለቲካ ጠረን የሸተተው ነበርና፣ ልጁን ቢኒቶን በእረፍት ጊዜው ሮማኛ ከተባለው ከተማ ወስዶ የሥራ አጦችን ብዛት ስለአሳየው ቢኒቶ ልቡ ተነካ። የመምህርነት ትምህርት ተከታትሎ ቢመረቅም ይህ ስሜቱ አልቀዘቀዘ አለ።

የቢኒቶ ሙሶሊኒ የፖለቲካ ስሜት ዳበረ። ከትምህርት ቤት ወደ ሕዝብ ተሸጋገረ። በተለይም በየካቲት 1894 ዓ.ም /በፌብሪዋሪ 1902/ ኢሚልያ በተባለ አካባቢ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርነት ከተቀጠረ በኋላ በሃይማኖትና በማኅበራዊ ጉዳይ ጭምር አተኮረ። በአደባባይ ይናገርና ከተቃዋሚዎች ጋር ይከራከር ጀመር። "…ጋሪባልዲ በሚያርፍባት ኢጣልያ ውስጥ ከመኖር ሞት ይሻላል…" አለ። ይህ ቃል ሠራተኞችን ቀሰቀሰ። ባለሥልጣኖቹን አስቆጣ። እሱም ከአስተማሪነት ሥራው ተባረረ።

በነሐሴ ወር 1895 ዓ.ም /1903/ ወደ ስዊስ አገር ተሰደደ። የተሰደደበትን ምክንያት ሲያስረዳ ደግሞ "…ኢጣልያን በደም ማጥለቅለቅ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር መተባበር አልፈልግም…" አለ። ስደት የሄደው ከብሔራዊ ውትድርና ሸሽቶ ነበርና። በተሰደደበትም አገር ከፖለቲካ ሥራ አልታገስ ስለአለ ተደጋግሞ ታሠረ። ሲያቅታቸው ስዊሶች ከአገራቸው አስወጥተው አባረሩት።

ወደ ሀገሩ ተመልሶ ካሪን በተባለ ቦታ እንደገና በአስተማሪነት ሥራ በ1897 ዓ.ም /1904/ በመስከረም ወር ተቀጠረ። ለአስተማሪነት ሥራ አክብሮትና አለመስጠትና በደመወዝ ማነስ፣ ሲጠጣና ሲያመነዝር ቂጥኝ ስለያዘው ራሱን ለመግደል እስከመሞከር ድረስ ተበሳጨ። በበሉፕ ዩኒቨርስቲ አማካይነት ለሁለት መቶ ያህል ሰዎች የተሰጠውን ፈተና ስለአለፈ፣ አኒልያ በተባለ የግል ትምህርት ቤት በአስተማሪነት በየካቲት 1900 ዓ.ም /1908/



ተቀጠረ። በዚህ ሥራው ላይ እንዳለ ሁለት ጊዜ ታሠረ። አንዱ እሥራት የ3 ወር ነበር። ገበሬዎችን ከዘረፉ ሰዎች ጋር በመያዝና አንዱን አሳሳሪ ሰው በማስፈራራት ነው። ሁለተኛው እሥራት ግን ባልተፈቀደ ጉባዔ ላይ ንግግር በማድረጉ ሲሆን፣ የተፈረደበትን 10 ሊሬ አልከፍልም ብሎ በፈቃዱ ለአሥር ቀን ነበር። እንደዚህ በመሳሰሉ የአካባቢ ጉዳዮች ላይ ተንጠልጥሎ በብሔራዊ ጉዳይ ላይ እስከ ማተኮር ደረሰ።

በመጋቢት 1904 ዓ.ም /1912/ ሣልሣዊ ኢማኑኤልን ለመግደል የተደረገውን ሙከራ በመቃወም የኢጣልያ ብሔራዊ ምክር ቤት ተወካዮች ሲልክ፣ ሦስት የሶሺያሊስቱ ፓርቲ አባላት አብረው ወደ ቤተ መንግሥት ሄዱ። ሙሶሊኒ ተቃውሞ አስነስቶ አባሪ የነበሩትን ሦስት የሶሺያሊስት ፓርቲ አባላት ከፓርቲው እንዲባረሩ አደረገ። በወቅቱ የነበረው መንግሥት ትርኤስት ለአውስትሪያ ትሰጥ ያለውን ሃሳብ "የሀገር ሽያጭ" ብሎ ተቃወመው። የራሱን ፓርቲ ማቋቋም ያዘ። ስሙንም "ፋሺ" አለው። ይህ ቃል ጊዜያዊ ትርጉም ቡድን የሚል ነበር። ነገር ግን እየዋለ እያደረ ሮማውያን ጥንት በጦር ሜዳ ላይ ይይዙት በነበረ ዱላ ተመሰለ። ተከታዮችም ፋሺስት ተባሉ። ርእዮተ ዓለሙም ፋሽዝም ሆነ። በዚህ ተንቀሳቃሽ የፋሽስት ፓርቲ ተቋቋመ። በዚህ የስደትና የትግል ጊዜው ፈረንሣይኛና ጀርመንኛ ቋንቋ አጠና። እንግሊዝኛንም በመጠኑ።

የትግሉ ጽናት፣ የገንዘብ ማጣትም፣ ስደትም፣ የማስተማር ሥራ መለልቸትም፣ መታሠር መፈታትም፣ ብቸኝነትም ተደማምረው ሚስት የማግባት ፍላጐት አሳደሩበት። ከብዙ ልጃገረዶች መካከል ወይዘሪት ራሼልን አጨ። ለመዳት፣ ወደዳት። ነገር ግን የእሱ አባትና የእርስዋ እናት ስለተቃወሙ፣ በጋብቻው አንስማማም ስለአሉ እንደገና ራሱን ለመግደል ሞከረ። ተፈቀደላቸው ተጋቡ። ልጆች ተወለዱ። ቤት ንብረት ሞቀ። ራሼል መልካም ሚስት ደግ እናት ሆነች። እሱ ግን ከሌሎች ጋለሞቶች ጋር ቀጠለ። ከብዙዎቹም አንድዋ ክለሬት ፔታኪ ሕይወትዋን እስከ መስጠት ድረስ ታማኝ ሆነችው።

መስከረም 17 ቀን 1904 ዓ.ም /1911/ ባደረገው ንግግር "…ኢጣልያ መዋጋት የማይችሉ የፈሪዎች አገር ናት…" ስለአለ፣ ክሱ ሮም በማዕከላዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ተደረገ። እሱም "…በነፃ ብትለቁኝ ሥራዬን እቀጥላለሁ፣ ብትቀጡኝ ደግሞ ክብር ይሆንልኛል…" በማለት መከራከሩን ትቶ የፍርድ ቤቱን ውሣኔ እንደሚቀበል አስታወቀ። ዳኞቹም በቀረበበት የበጥባጭነት ወንጀል የአንድ ዓመት እሥራት ፈረዱበት፣ ነገር ግን በዚያው ዓመት በየካቲት ወር ተፈታ። የሶሺያሊስት አብዮት መሪ እንደሆን ያህል ተቆጠረለት። "አቫንቲ" ማለትም ወደፊት የተባለው ጋዜጣ አዘጋጅ ሆነ። የፓርቲውንም የጋዜጣውንም ሥራ በትጋት አካሄደ። ደመወዙም በወር 500 ሌሬ ሆነለት።

በዚያ ዘመን ለተደረገው የምክር ቤት ምርጫ ለውድድር ቀረበ፡፡ ነገር ግን ከአንድ ቀን በስተቀር ስለራሱ አልተናገረም፡፡ ጓደኞቹን ረዳ፡፡ ሃምሣ ሦስት ባልደረቦቹ ሲመረጡ እሱ ሳይመረጥ ቀረ፡፡ በውጭ ሆኜ ብረዳ ይሻላል አለ፡፡ መቼም ሥልጣን አላገኝ ብሎ ነው፡፡ እንደ አለውም ማበጣበጡን ቀጠለ፡፡ እሱ ሥልጣን ካልያዘ ኢጣልያ ሰላም እንደማታገኝ እስኪ.ታወቅለት ድረስ፡፡

አቫንቲ በተባለው ጋዜጣ የጥቅምት 8 ቀን 1906/18 አክቶበር 1914/ እትም ሙሶሊኒ ለፓርቲው ተከታዮች ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጠ፡፡ የፓርቲው ፖሊሲ ምኞት የሚሰጥና ትዕግስትን እንጂ ማሰብን የማይጠይቅ እንደሆነ ገለጸ፡፡ መመሪያን ለማክበር በሚደረግ ሙከራ የሶሺያሊዝም መንፈስ ከመጥፋት እንደደረሰ አስጠነቀቀ፡፡ የሶሺያሊስት ፓርቲ ምክር ቤት በጉባዔ ቢጠይቀው መልስ አልሰጥ ስለአለ፤ ከአቫንቲ ጋዜጣ አዘጋጅነት ሥራው ተባረረ፡፡ ደመወዙን እንዲወስድ ቢጠየቅ እምቢ አለ፡፡

ኅዳር 6 ቀን 1907 ዓ.ም /ኖቬምበር 1914/ ኢል ፖፖሎ ደ ኢታልያ፣ ማለትም የኢጣልያ ሕዝብ የሚል አዲስ ጋዜጣ አወጣ፡፡ በመጀመሪያ እትሙ "...መጠበቅ መዘግየትን ያስከትላል..." በማለት ፈጣን እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ አስረዳ፡፡ አዲሱ ጋዜጣ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት እያገኘ ሄደ፡፡ በቀን እስከ 25,000 ቅጂ ይሸጥ ጀመር፡፡ የሶሺያሊስት ፓርቲ ሙሶሊኒ ጋዜጣውን ከውጭ አገር በሚገኝ ዕርዳታ ለማካሄዱ ማስረጃ ለማግኘት ልዩ ጥናት ቢያደርግም ማስረጃ ሳያገኝ ቀረ፡፡ ኅዳር 16 ቀን 1907 ዓ.ም /ኖቬምበር 25 ቀን 1914/ የሶሺያሊስት ፓርቲ ባደረገው ጉባዔ ሥራውን ማስረዳት አቅቶት ስብሰባው ከተደረገበት ትያትር ቤት ሸሽቶ ወጣ፡፡ ብቻውን ቀረ፡፡ ሰው ከዳው፡፡ እሱ ግን ተስፋ አልቆረጠም "...በዕርና ሽጉጥ በእጄ ላይ እስከአለ ድረስ ማንንም አልፈራም" አለ፡፡

ቀደም ብሎ የጀመረውን አዲስ ፓርቲ የማቋቋም ሥራ ቀጠለ፡፡ ስሙንም ፋሺ ደ አስዮን ሬቮሊሲዮናርያ አለው፡፡ በግንቦት 1907/1915/ ዓ.ም ኢጣልያ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ከምዕራባውያን ጐን በመሆን ገብታ ነበር፡፡ ሙሶሊኒ በሮምና ሚላን ከተሞች በየምክንያቱ ሰልፍ እያካሄደ አስቸግሮ ነበርና ለሁለት ጊዜ ለብሔራዊ ውትድርና ተጠራ፡፡ ማምለጥ ስለአልቻለ ደስተኛ መስሎ ገባ፡፡ የአሥር አለቅነት ማዕረግ አገኘ፡፡ የካቲት 15 ቀን 1909 ዓ.ም /ፌብሪዋሪ 23 ቀን 1917/ ከአንድ የጦር ልምምድ ላይ አንድ የእጅ ቦምብ ፈንድቶ ሌሎች አምስት ወታደሮች ሲሞቱ፤ እሱ አርባ አራት ቦታ ቆስሎ ዳነ፡፡ ሞቶ በሆነ ኖሮ ምንኛ ደግ ነበር! እሱ ግን "ወደ ትሬኤስት የሚወስደውን መንገድ በደሜ በማቅላቴ እደሰታለሁ" አለ፡፡ በዚህም ተጨማሪ ሞገስ አገኘ፡፡

ጦርነቱ በሙሶሊኒ ላይ ሌላ ችግር ሳያስከትል አለቀ፡፡ ነገር ግን ኢጣልያ በጦርነቱ በቂ ተሳትፎ ስለአደረገች፤ በቬርሳይ ውል የፈለገቻቸውን በከፊል እንጂ አምዋልታ ሳታገኝ ቀረች፡፡ ዳልማትያና ፍዩም የተባሉትን



አውራጃዎች ልታገኝ አልቻለችም፡፡ የሙሶሊኒ ትንቢት ደረሰ፡፡ በጦርነቱ የሞቱት 652,000 ወታደሮች ደም በከንቱ እንደ ፈሰሰ ቆጠረው፡፡ ግንኙነቱንም ከጦርነቱ ከተመለሱ ወታደሮች ጋር አደረገ፡፡

በኢጣልያ መንግሥት በኩል የነበረው ሁኔታ ለሙሶሊኒ ብጥብጥ ማካሄጃ ተስማሚ ነበር፡፡ በባለሥልጣኖች ዘንድ ጉቦኝነት፣ መደለል፣ ጥቅም ማጋበስ በዝቶ ነበር፡፡ ከወንጀል ብዛት የተነሣ በ1916 ዓ.ም ብቻ በገንዘብ ወይም በእሥራት የተቀጡ ሰዎች ብዛት እስከ 362,000 ደረሰ፡፡ ከጦር ግንባር ተመልሰው ሥራ የአጡ ሰዎች ቁጥር ከሚሊዮን አለፈ፡፡ ሙሶሊኒ እነዚህን ሁኔታዎች ምክንያት በማድረግ፤ መንግሥቱን በሕዝብ ዘንድ ለማስጠላት ታላቅ የፖለቲካ ዘመቻ አካሄደ፡፡ በሠራተኞች ዘንድ ድጋፍ አገኘ፡፡

በአንድ ወገን መንግሥቱን እያዳከመ፣ በሌላ ወገን የራሱን የፖለቲካ ቡድን አጠናከረ፡፡ ለመጋቢት 10 ቀን 1911/1919/ ዓ.ም ጠቅላላ ስብሰባ ጠራ፡፡ ለስብሰባው የተጋበዙት የማንኛውም ፓርቲ አባል የሆኑ ሁሉ ነበሩ፡፡ የስብሰባው ዓላማ ኢጣልያን ሊያጠፉአት በመንቀሳቀስ ከአሉት ኃያላን ለማዳን እንደሆነ በጋዜጣ ተገለጸ፡፡ ስብሰባው በሚላን ከተማ በአንድ የንግድ ማኅበር መሥሪያ ቤት ክላይ በተጠቀሰው ቀን ተደረገ፡፡ በጠቅላላው 119 ሰዎች በስብሰባው ላይ ተገኙ፡፡ ከተገኙት ሰዎች አማጽያን ሶሺያሊስቶች፣ በጥባጮች፣ የሪፐብሊክ መንግሥት ማቋቋም የሚፈልጉ፣ የቀድሞ ወታደሮችና ሌሎችም ነበሩባቸው፡፡ ነገር ግን ታዋቂ ሰዎች አልነበሩም፡፡ ሙሶሊኒ ቀደም ብሎ ያዘጋጀው ቻርተር ይዘት ግልጽ አልነበረም፡፡ ዝልጉስጉስ ሆነ፡፡ ቢሆንም ያለ ተቃወሞ ጸደቀ፡፡ ሙሶሊኒ ፈነደቀ፡፡ ዋናው ነገር የፋሽስት ፓርቲ ሕልውና ማግኘቱ ነበር፡፡

የፋሽስት ፓርቲ በፍጥነት ተስፋፋ፡፡ በአንድ ወር ውስጥ 82 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በኢጣልያ ዋና ዋና ከተሞች ተቋቋመ፡፡ በዚሁ ወቅት 14,000 አባላት ተመዘገቡ፡፡ በዚሁ ወቅት 107 ብጥብጦች ተካሄዱ፡፡ አብዛኞቹ የሶሺያሊስት ፓርቲን በመቃወም ነበር፡፡ ሚያዝያ 7 ቀን 1911 /1919/ ዓ.ም አቫንቲ የሚባለው የሶሺያሊስት ጋዜጣ መሥሪያ ቤት ተቃጠለ፡፡ ሠራተኞቹ ኢል ፖፖሎ የሚባለውን የፋሽስት ፓርቲ ጋዜጣ መሥሪያ ቤት ለማለቃጠል ተነሳስተዋል ተብሎ ሙሶሊኒ ገነነ፡፡ ዕርዳታ እንደ ውሃ ፈሰሰለት፡፡ ብጥብጡ በየመልኩ ቀጠለ፡፡ የፋሽስት ፓርቲ ተጠናከረ፡፡ በመላ ሀገሪቱ 149 ቅርንጫፎች አቋቋሞ 45,000 አባላት መዘገበ፡፡ በሥልጣን ላይ የነበረው ዩኒቲ መንግሥት ሥራውን ለቅቆ አዲስ ምርጫ ጠራ፡፡

በኅዳር 1912 ዓ.ም /1919/ በተደረገው የብሔራዊ ምክር ቤት ምርጫ የፋሽስት አባላት መመረጣቸውን ሙሶሊኒ ተቃወመ፡፡ ምርጫው ለሥልጣን እንዲያበቃው አውቆ "በውስጡ ጥቂት ወንበሮች ከመያዝ ይልቅ፣ በምክር ቤቱ ዙሪያ ብዙ ሕዝብ አሰልፎ ማንጫጫት የበለጠ ተደማጭነትን ያስገኛል" አለ፡፡ ተቃዋሚዎቹ አልቀበል አሉት፡፡ በመጨረሻ እሱም ራሱ በሚላን ከተማ

ለውድድር ተመዘገበ። ነገር ግን አንድም የፋሽስት አባል ሳይመረጥ ቀረ። ሙሶሊኒ የፈራው ውርደት ደረሰ። በዚህ ላይ ደግሞ ፋሽዝምን ይደግፉ የነበሩት ጳጳስ ሞተው የሚቃወሙት ሌላ ጳጳስ ተሾሙ። በሙሶሊኒና በባልደረባቹ ላይ የፖለቲካ ተፅዕኖ ተደረገባቸው። ሙሶሊኒ ግን ተስፋ አልቆረጠም። ከቶውንም በረታ። መላዋን ኢጣልያ በብጥብጥ አጥለቀለቃት። በ1912 ዓ.ም /1921/ ብቻ 1881 ብጥብጥ ተመዘገበ። ኢጣልያ ከማጥ ውስጥ ገባች። የሌሬ ዋጋ ቀነሰ። ኢንዱስትሪዎች በከሰል እጥረት ቆሙ። ዳቦ ተወደደ።

የሶሺያሊስት ፓርቲ በጥር 1913 ዓ.ም /1921/ ሊቦርኖ በተባለች ከተማ ተሰበሰበ። ፓርቲው ወደ ኮሚኒስት ፓርቲነት እንዲለወጥ ሃሳብ ቀረበ። በአክራሪዎችና በለዘብተኞች መካከል አንድ ሣምንት ሙሉ ክርክር ከተካሄደ በኋላ በአሣር በመከራ አክራሪዎች ተረቱ። ነገር ግን ጦሱ ሳይበርድ ቀረ። ራሺያ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ በሚቀጥለው ሦስት ወር ውስጥ ስድሣ ሚሊዮን ሊሬ ኢጣልያ ውስጥ አፍስሳ ምንም ውጤት ሳታገኝ ቀረች። ካፒታሊስቶች ለሕልውናቸው ሲሉ የፋሽስት ፓርቲን ደገፉ። የፋሽስት ፓርቲ ናረ። አንድ መቶ ሺህ አባላት ከሶሺያሊስት ፓርቲ ዞሩ።

በሶሺያሊስት ፓርቲ ውስጥ ልዩነት እንደ ተፈጠረ ሲያይ፤ ሙሶሊኒ በሣልሣዊ ኢማኑኤል እናት አማካይነት ከንጉሡ ጋር የምሥጢር ግንኙነት ፈጠረ። ንጉሡን ላይነካ፣ ንጉሡም ሊደግፉት ተስማሙ። በአንድ ወገን ከንጉሡ ጋር ሲስማማ፣ በሌላ ወገን ተቀናቃኙን የሶሺያሊስት ፓርቲን ማውደሙን አጣደፈ። እስከ ግንቦት ወር ድረስ 120 የሠራተኛ ጽሕፈት ቤቶች ተቃጠሉ። ከ200 በላይ የሶሻሊስት ፓርቲ መሰብሰቢያ ቦታዎች ተመዘበሩ። በድምሩ 261 ሰዎች ሞቱ። ሌሎች 1267 ቆሰሉ። ጂዮሊቲ የተባለው ጠቅላይ ሚኒስትር አዲስ ምርጫ እንዲደረግ አዘዘ።

ግንቦት 7 ቀን 1913 ዓ.ም /1921/ በተደረገው ምርጫ ከ8535 ወንበሮች 35 ይዞ ምክር ቤት ገባ። ሙሶሊኒም ራሱ ከሚላን ከተማ ተመረጠ። ቀድሞ ይቃወመው የነበረውን የካቶሊክ እምነት አከበረው። ከዚያም አልፎ "የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለኢጣልያኖች ጥቅምና ክብር የቆመች ናት" በማለት በምክር ቤቱ ውስጥ ተናገረ። ከንጉሡም ከጳጳሱም ተስማማ ማለት ነው።

በሰኔ ወር አዲሱ መንግሥት ክርክር ሲደረግባት የቆየችውን ደልማጥያ የተባለችውን የኢጣልያ ግዛት ለዩጐዝላቪያ ለቀቀ። ለሙሶሊኒ ተመቸው። ሀገሪቱን በብጥብጥ አቀጣጠላት። ንጉሡ የምክር ቤቱን አባላት አነጋግሮ፤ ቦኖሚ የተባለው ሰው መንግሥት እንዲያቋቁም አዘዘው። ነገር ግን ለሙሶሊኒ በአዲሱ መንግሥት ውስጥ ቦታ ሳይሰጠው ቀረ። ደጋፊዎቹ ጥቂት እሱም ለመንግሥት ሥራ ባይተዋር ነበር። እሱ ግን ማበጣበጡን ቀጠለ። በሐምሌ ወር ሣርዛና በተባለች መንደር ብጥብጥ ተነስቶ ብዙ የሶሻሊስት



ፓርቲ ደጋፊዎች በፖሊስ ተገደሉ። ከፋሽስት ፓርቲ ግን አንድም ሳይሞት ስለቀረ፤ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል የነበረው ተቃርኖ ይበልጡን ተጋጋመ። ሙሶሊኒ ራሱ ተቃውሞ ተቀሰቀሰበት። ቢሆንም ተስፋ አልቆረጠም፤ ማበጣበጡን ቀጠለ። ብጥብጥ አካሄያጅ ቡድን አቋቋመ። ጥቁር ሸሚዝ አለበሳቸው። ሶሺያሊስቶችን እንዲያጠቁ አደረገ። የፋሽስት ፓርቲ በትረ መንግሥት ለመያዝ ብቁ መሆኑን በይፋ አስታወቀ። "...ቢወድዱ ይስጡን፣ ያለዚያም እኛው ራሳችን እንወስደዋለን" አለ። በምሥጢር ደግሞ ከንጉሡ እናት ጋር ጀምሮት የነበረውን ግንኙነት አጠበቀ። አዲስ በተቋቋመው መንግሥት ውስጥ የሚሪን፣ የገንዘብ፣ የእርሻና የቅኝ ግዛት ሚኒስትርነት ሥራዎችና፤ እንደዚሁም ሌሎች አራት የምክትል ሚኒስትርነት ቦታዎች ለፋሽስት ፓርቲ ተመደቡ። እሱ ግን አልቀበልም አለ። ንጉሡ ቢያስፈልጉት ጠፋ። በብዙ ልምምጥ ሲከሰት የራሱን መንግሥት ከማቋቋም በስተቀር፤ በሌላ ፓርቲ መንግሥት ውስጥ ለማሳተፍ አለመፈለጉን ይፋ አደረገ። ብጥብጡ ቀጠለ። የአደጋ መከላከያ አዋጅ ማውጣት አስፈለገ። ነገር ግን ንጉሡ አዋጁን አልፈርምም አለ። ዘውዱን ለማዳን ሙሶሊኒን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጐ መሾም ግድ ሆነበት። ሌላ አማራጭ ጠፋ። ሙሶሊኒ ሮም ከተማ መጥቶ መንግሥት እንዲያቋቁም የተፈቀደለት መሆኑን የሚያስታውቅ መግለጫ በንጉሡ ቃል ወጣ። ጥቅምት 20 ቀን 1915/1922/ ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ።

ለምክር ቤት የሥራ ፕሮግራም አቀረበ። የውጭ ጉዳይን በተመለከተ ኢጣልያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች እንደሚያከብር አስታወቀ። የሀገር ውስጥ ጉዳይን በተመለከተ ሕዝብ የሚፈልገውን አስተዳደር እንደሚመሠርት፣ ሕግ እንደሚያከብር፣ ጸጥታና መረጋጋትን እንደሚያሰፍን፣ የልማት ሥራዎችን እንደሚያጠናክር ቃል ገባ። ምክር ቤቱም የሥራ ፕሮግራሙን አጸደቀለት። የሕዝብ አክብሮት አገኘ። ኤትና በተባለው ተራራ ላይ እሳተ ገሞራ ሊፈነዳ እሳት መርጨት ከጀመረ በኋላ፤ ሙሶሊኒ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን ተመልሶ መቀዝቀዙ ጭምር በምሥራች መልክ በጋዜጣ እስከ መውጣት ደረሰ።

አቅዋሙን ለማጠናከር በወሰደው እርምጃ የሮምን ከተማ ለማደስና ለማስፋፋት ጥረት አደረገ። ዋናው ጉዳይ ከተማይቱን የማጽዳቱ ሥራ ሆነ። ገጠሩን እየተዘዋወረ ችግሮችን ለመረዳት ሞከረ። ዋናው ጉዳይ መልካም ወሬ የመንዛቱ ጉዳይ ነው። የፖለቲካ ኃይልን ከሕዝብ ፍላጐት ጋር ለማጣጣም ከጀለ። ነገር ግን አንድ ችግር ሲቃለል ሌላ እየተተካ አስቸገረ። ጉዳዮችን እያጠና ውሣኔ የሚሰጥ የፋሽስት ምክር ቤት አቋቋመ። ሥልጣን ሰጠው። እሱ ራሱ ሰብሳቢ ሆነ። የፋሽስት ፓርቲ ያሠለጠነና ያስታጠቀው እስኳድርሲት ለተባለው ሠራዊት ሕጋዊ አቅዋም ሰጠው። ለደህንነቱ ሥራ ኃላፊ አደረገው። ቀጥሎ የፋሽስት ፓርቲ አባል ያልሆኑትን ሚኒስትሮች

አንድ በአንድ ከሥልጣን አባረረ። በዚህ ሁሉ ሕዝብ ተባብረው። የነበሩት ጥቃቅን ተቃውሞዎች ሂደቱን የማገድ አቅም አላገኙም። ጉዞው ቀጠለ።

ነገር በእንዲህ እንዳለ በልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኰንን የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ሮም ገባ። በሮም ቆይታውም በአዲሱ አምባ ገነን ከዱቼ ሙሶሊኒ ተገናኝቶ ተነጋገረ። በንግግሩ ላይ በኢትዮጵያ በኩል ስለ አሰብ ጉዳይ ተነስቶ በዲፕሎማቲክ መሥመር ለአዲስ አበባ መልሶ እንደሚሰጥ ከኢጣልያ በኩል ቃል ተገባ። በተግባር እንደታየው የኢትዮጵያን ዓለም ማህበር መግባት ኢጣልያ ደገፈች።[1]

ቀጣዩ ትንቅንቅ ሕዝብ ከመረጠው ምክር ቤት ጋር ሆነ። በ1916 /1924/ ዓ.ም አዲስ የምርጫ ሕግ አወጣ። ሕጉም ቀደም ብሎ በተደረገው ምርጫ ከምክር ቤቱ ወንበሮች 6.5% ብቻ የነበረውን የፋሽስት ፓርቲ፤ በቀጣይ ምርጫ ወደ 66.7% ከፍ ከሚያደርግ ነበር። በአዲሱ ሕግ መሠረት በዚያው ዓመት መጋቢት 28 /ኤፕሪል 6/ አዲስ ምርጫ ተካሄደ። በምርጫው የፋሽስት ፓርቲ ከምክር ቤቱ ወንበሮች 65% ያዘ። የተፈለገው ነገር ተገኘ።

ምክር ቤቱ ሥራውን ቀጠለ። በዚያው ዓመት ግንቦት 22 ቀን ምክር ቤቱ በአደረገው ስብሰባ ላይ ጊያክሞ ማቲዮቲ የተባለው የሶሺያሊስት ፓርቲ አባል የሙሶሊኒን አሠራር ነቀፈ። የምክር ቤቱን አባላት እርስ በርሳቸው ያደባደበ ክርክር ተካሄደ። ከሙሶሊኒ ዛቻ ተሠንዘሮበት ነበርና ማቲዮቲ ከምክር ቤት እንደወጣ ለጋዜጠኞች በሰጠው ቃል፤ ዛቻውን በተመለከተ "...አትስጉ..." ለሙሶሊኒ ዛቻ ቃል እንጂ፣ እንዳች አይደለም... አለ። ነገር ግን ሰኔ 3 ቀን የደረሰበት ጠፋ። በማቲዮቲ መጥፋት በተነሳው የርስበርስ ጭቅጭቅ ደቦኖ የሕዝብ ደህንነት ሥራውን ለቀቀ። በዚህም ጠቡ አልበርድ አለ። በጋዜጣ ለተጠቀጣጠለው ውዝግብ ሙሶሊኒ ኃላፊነቱን ወሰደ። "እኔ ለጋዜጠኞች የመጻፍ ሥልጣን በመስጠቴ ነው" ቢልም ውዝግቡ አልበርድ አለ። የመንግሥት ግልበጣ አሰጋ። ለዚህም ሙሶሊኒ "ንጉሡ ከጠየቁኝ ሥልጣኔን በፈቃደኛነት እለቃለሁ" አለ። ብዙ የፋሽስት ፓርቲ ደጋፊዎች ደነገጡ። ነገር ግን ንጉሡ ሥልጣን ልቀቅ ብሎ ሙሶሊኒን ለመጠየቅ አልደፈረም። ሙሶሊኒም ልምምጡን በምሥጢር ቀጠለ።

ተቃዋሚዎቹ ሌላ መገልገያ ሲያጡ ወደ ግድያ ዞሩ። ሙሶሊኒን ለመግደል አራት ሙከራ አደረጉ። አንዱም አልተሳካ። መጋቢት 29 ቀን 1918 የሚያዝያ 7 ቀን 1926/ ዓ.ም አንዲት እንግሊዛዊት ሴት በሽጉጥ ጥይት አፍንጫውን ጨረፈችው። ይህ ሁኔታ ሥልጣኑን ለማጠናከር ይበልጡኑ ረዳው። በግንቦት 1919 /1927/ ዓ.ም የፖለቲካ እሥረኞች ብዛት 698 ደረሰ። በ1920/1928/ ዓ.ም የወጡት ድርጅቶች ፈርሰው የፋሽስት ዓላማዎችን ሊያራምዱ በሚችሉበት ሁኔታ ተሻሽለው ተቋቋሙ። በዚህ ዓይነት መቀጠሉን ሲገነዘብ ምክር ቤቱ ሥልጣኑን ለፋሽስት ፓርቲ ለቀቀ። ድምድሙም በሕግ መምሪያ 216 ለ15፤ በሕግ መወሰኛ ደግሞ 161 ለ46



ነበር። በዚህ ውሣኔ መሰረት ሥልጣን ወደፋሽስት ምክር ቤት ተዛወረ። ሕዝብ የመረጠው ምክር ቤት ኅዳር 29 ቀን 1921 ዓ.ም /ዲሴምበር 8 ቀን 1928/ ከነጭራሹ ተዘጋ። ሂደቱን የንጉሡም ተቃውሞ ሊያግደው ሳይችል ቀርቶ ሙሶሊኒ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሆነ። ከንቀቱ ጽንአት የተነሣ ከንጉሡ ጋር ያለውን የሥልጣን ግንኙነት "በሁለት አልጋ የሚካሄድ ጋብቻ" አለው። ዱቼ የተባለው የክብር ስም ዋና መጠሪያው ሆነ።

ቀጣዩ ትግል ደግሞ ከሮም ካቶሊክ ቤተክህነት ጋር ሆነ። ሙሶሊኒ ስለሃይማኖት ደንታ አልነበረውም። የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት ሲል ብቻ ከቤተክህነቱ ጋር የካቲት 4 ቀን 1921 ዓ.ም /ፌብሪዋሪ 11 ቀን 1929/ አንድ ስምምነት እሱ ራሱ ተፈራረመ። ውሉን የተፈራረመበትን የወርቅ ብዕር ከተሸለመ በኋላ ባደረገው ንግግር፤ ከእንግዲህ ቤተክርስቲያኒቱን እንደሚደግፍ አስታወቀ። ሁኔታው በሕዝብ ስሜት ላይ ተፅዕኖ አሳድሮ ስለነበር እንደ እፎይታ ተቆጠረ። ጳጳሱም "እግዚአብሔርን ለኢጣልያ፣ ኢጣልያንም ለእግዚአብሔር ሰጠን" አሉ። ጳጳሱ እንዲህ ያሉት ኢጣልያን ለፋሽዝም ማለትም ለሙሶሊኒ መስጠታቸውን ልባቸው እያወቀ ሳይሆን አልቀረም። ወጣም ወረደ ሙሶሊኒ በዚህም ሌላ ድል አገኘ።

በሀገር ላይ ያለውን ሥልጣን ሁሉ እንደዚህ ጠቅልሎ ከተሸከመ በኋላ፤ ሙሶሊኒ የአመራር ጉዞውን ቀጠለ። ጣልያኖች በሃሳብ ተንቀሳቀሱ። ለብዙ ዘመን አንገታቸውን ደፍተው በኖሩበት አገራቸው፤ አንገታቸውን ቀና አድርገው መራመድ ጀመሩ። ሙሶሊኒም ክብርና ኩራት ተሰማው። በሚላን ከተማ ባደረገው አንድ ንግግር ላይ "...ኢጣልያ ለሦስተኛ ጊዜ የሰው ልጅ ሥልጣኔ መዲና ሆናለች..." አለ። እውነትም ዓለም አደነቀው። ሚስተር ቸርቸል "...ኢጣልያዊ ብሆን ኖሮ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እከተልህ ነበር..." አሉት። መሐተማ ጋንዲ "የአዲሲቱ ኢጣልያ መድኅን" አደረጉት።

አስገራሚ ሥራዎች ተካሄዱ። የጣልያንን ሕዝብ ለማብዛት፣ ሕፃናት በብዛት እንዲወለዱ ከመንግሥት ድጋፍ ተሰጠ። በወንደላጤዎች ላይ ተጨማሪ ግብር ተጣለ። በድምሩ 1300 ልጆች የወለዱ 93 እናቶች በየአሉበት ተሰብስበው ሮምን በገና ወራት እንዲጎበኙ ተደረገ። ዱቼ አነጋገራቸው። በኅዳር 1926 /1933/ ዓ.ም በአንድ ወር ውስጥ በሮም ከተማ ብቻ 2,620 ጋብቻዎች ተፈጸሙ። ሁሉም ከሙሶሊኒ ስጦታ ደረሳቸው። ለድሆች ነፃ ሕክምና፣ ምግብና ልብስ ተሰጠ። የልጆች የመዝናኛ ቦታዎች ተዘጋጁ። ለገበሬዎች ልዩ ድጋፍ ተሰጠ። ጁለስ ሲዘር አስቦት የነበረው የመስኖና የግድብ ሥራዎች እንደገና ተጠኑ። በገጠር አዳዲስ ከተሞች እንደ እንጉዳይ ፈሉ። ወባ ከአገር ጠፋ። በግንቦትና በሰኔ ወር 1925/1933/፣ የመጀመሪያውን የዓለም ጦርነት ከአቆሙት ኃያላን መንግሥታት ጋር የሰላም ውል ሮም ላይ ተፈረመ። የአባለ ዘር በሽታ ተቀነሰ።

ነገር ግን እነዚህ ሥራዎች ብዙም ሳይቆዩ መክሰም ጀመሩ። ጠንካራ መሠረት አልነበራቸውምና። አንዳንዶቹም በጅምር ቀሩ። ለልማት የተመደበው ገንዘብ ከባለ ሥልጣኖች ኪስ ገባ። የወሊድ መጠን በመጨመር ፋንታ ከ2.7% ወደ 2.3% ዝቅ አለ። ጠንካራ የነበረውን የመሬት ሥሪት ለማሻሻል ምንም ሙከራ ስለአልተደረገ የገበሬው ድካም መና እየቀረ ሄደ። ደመወዝ በሌሎች አገሮች ከነበረው ጋር የማይስተካከል ሆነ። የሥራ አጥ ቁጥር በረከተ። አሳፋሪ ውጤቶች እየተደበቁ፣ ደህና ደህናዎቹ በሕዝብ መገናኛ ይገለጹ ጀመር። ኢኮኖሚው ወደቀ። ሙሶሊኒ ወደ ግል ሕይወቱ አዘነበለ። ለስብሰባዎች እንደ ወትሮ በሰዓት መድረሱ፣ የመነጋገሪያ ጉዳዮች መዘጋጀታቸው፣ ስብሰባዎች በትክክል መካሄዳቸው ቀረ። ስብሰባዎች የባለ ሥልጣኖች መነታረኪያ ሆኑ። ቀሪ ሲበዛ ስም ይጠራ ጀመር። ሙሶሊኒ በዚህ ዓይነት ሊወጣው ከማይቻል የፖለቲካ ማጥ ውስጥ ሲገባ፤ የትኩረት ዓይኑን ወደ ኢትዮጵያ አዞረ።

ከሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመቆናጠጥ ሲፍጨረጨር የኢትዮጵያን ጉዳይ በምሥጢር ለባለሥልጣናትና ለታማኞቹ መግለጹ አልቀረም ነበርና ሙከራው ተቃናለት። ፕሮፓጋንዳውን አጠናከረ። የአድዋን ቂም፣ የኢጣልያንን ክብርና ጥቅም የሚኮረኩሩ ንግግሮች ተደረጉ። ጋዜጦች ታተሙ። በጐንደር የኢጣልያ ቆንሲል ላይ ጉዳት እንደደረሰ፣ በወልወል ግጭት ኢጣልያ እንደተጠቃች እየተደረገ ተነገረ። ንጉሡና መኳንንቶቻቸው፣ ጳጳሱ አባ ፓየስ 11ኛና ካህናት፣ ሕዝብ በጠቅላላ ደገፈው።

በኢትዮጵያ ላይ ታላቅ ዘመቻ መራ። የዘመቻውን ሂደት እርምጃ በእርምጃ እየተከታተለ፣ የተጣመመውን እያቃና፣ የጐደለውን እየሞላ ጦርነቱን አካሄደ። በወረራው ምክንያት በአውሮፓ የተነሣውን የፖለቲካ ውዝግብ አረገበ። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ያዘ። ጦርነቱ ያከተመ ሰላም የተመሠረተ አስመሰለ። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ተበላሽቶበት የነበረውን አቅዋሙን እንደገና መልሶ አጠናከረው። ሥልጣን ሞቀ፤ ክብር ደመቀ። ነገር ግን ራሼል "እንግዲህ ይበቃል" አለች። ሙሶሊኒ ይህቺን ምክር አላዳመጠም። በኑሮ ጉዳይ ላይ የአመለካከት ልዩነት በባልና ሚስቱ መካከል ተፈጠረ። ሙሶሊኒ ከራሼል ሲቃቃር ከቀድሞ ወዳጆቹ ሌሎች ጋለሞቶቹን አፈራረቀ። በመጨረሻም ከክላሬታ ፔታኪ ጋር ተጣበቀ። እርስዋም እስከ መገደል ታማኝ ሆነችለት።

በእስፔይን ሀገር ጄነራል ፍራንኮ ሐምሌ 11 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁላይ 18 ቀን 1936/ ብጥብጥ አስነሳ። ብጥብጡ ወደ እርስበርስ ጦርነት ተሸጋገረ። ሙሶሊኒ ወዲያው 70,000 ወታደር ላከለት። የኢትዮጵያው እንደ አለቀ በመቁጠር። በዚህ የተነሣ በአንድ ጊዜ ሁለት ጦርነት ማካሄድ ግድ ሆነበት። ከሂትለር ያለውን ግንኙነት አጠናከረ። ታዳጊ የፖለቲካ ኃይሎች ፋሽዝም፣ ናዝሲዝምና ኮሚኒዝም እንደ ሆነ አድርጐ ገመተ።



ጃፓንንም ከመልካም ግምት አገባት። ሌላውን ዓለም ከቁም ነገር መቁጠሩን ተወ። ከእነዚሁ መንግሥታት ጋር በኅዳር 1930 /1937/ ዓ.ም ውል ተፈራረመ። ለይምሰል ያህል ከእንግሊዝ ጋር እንደዚሁ። በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ገዥነት እንዲያውቅለት በሀገር ውስጥ የነበሩት አይሁዳውያን 47,000 ብቻ እንደሆኑ አሳወቀ። በኅብረተሰቡ ዘንድ ምንም ችግር ሳያጋጥም ዘርን በተመለከተ የጣልያኖችን ግንኙነት አርያን ከሚባለው የነጭ ዘር መሆኑን የሚገልጽና "...አይሁዳውያን ከኢጣልያኖች ጋር የደም ጥልቀት የላቸውም..." የሚል አዋጅ ሐምሌ 7 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁላይ 14 ቀን 1938/ አወጣ። በዚህም ሂትለር በጀርመን የሚያካሂደውን አይሁዳውያንን የመጨረስ ተግባር ደገፈው። ሙሶሊኒ ጀርመንን፣ ሂትለር ጣልያንን በመጐብኘትና መግለጫ በማውጣት አንድነታቸውን አጠናከሩ።

አዲሱ የሞሶሊኒ ሕልም ከዚህ ተጀመረ። ኮርሲካ፣ ቲቺኖና ሌሎችም በአካባቢው ያሉ ጥቃቅን አገሮች ወደ ኢጣልያ የሚጠቃለሉበት መንገድ ተጠና። ቼኮዝሎቫኪያን በሰዎች የተፈጠረች እንጂ፣ ብሔርነት የሌላት አገር አድርጐ ገመተ። አልባኒያ፣ ግሪክ፣ የጐዝላቪያ፣ ሐንጋሪ፣ ሩማንያና ቡልጋሪያ የኢጣልያ እንዲሆኑ ታሰበ። እንደዚሁም የማልታ እና የኮርሲካ ደሴቶች ወደ ኢጣልያ እንዲጠቃለሉ ታቀደ። የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛትም ቱኒዝያን፣ ግብፅን፣ ሱዳንን፣ ሰሜን ሶማሊያንና ደሴቶቿን እንዲያካትት ተፈለገ።[1] ይህ ይዞታ በሜዲትራኒያንና በቀይ ባህር ላይ የሚያስገኘውን የበላይነት ማጤን ይገባል። ይህንን ዓላማ ይዞ ሰኔ 3 ቀን1932 ዓ.ም /ጁን 15 ቀን 1940/ ከሂትለር ጐን ለመቆም ወሰነ።

ሙሶሊኒ ከዚህ ውሣኔ ላይ የደረሰው በደንብ አስቦበት እንጂ በስሜት ተገፋፍቶ አልነበረም። ከዚህ ውሣኔ ላይ ያደረሱትን ነጥቦች መመልከት ይባገል። እነሱም፣

1ኛ. ኢጣልያ ከጀርመን ጋር ያላት ጉርብትና፣

2ኛ. ፋሽዝምና ናዝሲም ያላቸው የርዕዮተ ዓለም ዝምድና፣

3ኛ. በጊዜው የነበረው የኃይል ሚዛን በጀርመን እጅ መሆኑ፣

4ኛ. የአውቶሚክን ምሥጢር ለማግኘት መቃረቡ፣

5ኛ. ከጀርመን ጐን ቢሆን በሀገሮች ቅርምት ኢጣልያ የምታገኘው ጥቅም ነበሩ።

ስለዚህ ውሣኔው ከኢጣልያ ጥቅምና ከጊዜው ሁኔታ ጋር ሲታይ የሚነቀፍ አልነበረም። ነገር ግን በሙሶሊኒ ሕይወትና ሥልጣን፤ እንደዚሁም በፋሽስት ፓርቲና በኢጣልያ ላይ ታላቅ ለውጥ አመጣ። የእነዚህን ሁኔታዎች ግምጋሜ በኋላ እንመለስበታለን።



የፋሽስቱ መሪ ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

አልባንያን መጋቢት 29 ቀን 1931 ዓ.ም /አፕሪል 7 ቀን 1939/ ያዘ። ጀርመን የአውሮፓ አገሮችን መውረር ስለጀመረ በመሽቀዳደም ሙሶሊኒ መስከረም 18 ቀን 1933 ዓ.ም /ሴፕቴምበር 1939/ ግሪክን ደገመ። አከታትሎም በርበራን ያዘ። ግብጽና ሱዳን ግዛት ውስጥ በጦር ኃይል ዕድገት ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ።

ወይዘሮ ራሼል የፈራችው ደረሰ። ከጥቅምት ወር 1933 ዓ.ም ጀምሮ ሥሉስ ዞረ። ጦርነቶቹ በሙሉ በኢጣልያ ላይ ሚዛን ደፋ። በኢትዮጵያ ላይ ጦርነቱ ከመቸውም የበለጠ ጠነከረ። በኢትዮጵያ ላይ ወጭ የተደረገው በከንቱ እንደከሰረ ታወቀ። እስፔይን የገባው ወታደር ከዚያው ቀልጦ ቀረ። ግሪክ የገባው ተባረረ። በዩጐዝላቪያ የተቀሰቀሰው ጦርነት የማይቻል ሆኖ ወደ አልባኒያም ተሻገረ። የኢጣልያ ወታደሮች ከሰሜን ሶማሊያና ከሱዳን ተባረሩ። ግብፅን ለማጥቃት ከሞከረው የኢጣልያ ጦር 113,000 በአንድ ጊዜ ተማረከ። በኢጣልያ ባለሥልጣኖች መካከል ሲካሄድ የቆየው አለመግባባት ጠነከረ። ሥልጣኑን ለማጠናከር ሲል እሱም ራሱ ባለሥልጣኖቹን እርስበርስ ሲያጋጭ ቆይቶ ነበርና ጠቡን ማብረድ አቃተው።

ኢትዮጵያ ነፃ ወጣች። ጄነራል ሎሬንሲኒ ሞቶ ኤርትራ ከእንግሊዝ እጅ ገባች። ሶማሊያም እንደዚሁ። ዱካ ደ አዖስታ አምበላጌ፣ ጄነራል ናዚ ጐንደር ተማረኩ። የስዊዝ ካናል ተዘጋ። የሰሜን አፍሪካ ጦርነት እየገፋ ሄደ። የኢጣልያ ድርሻ ይሆናሉ ተብለው የነበሩትን ዩጐዛላቪያን፣ ሩማንያንና ሀንጋሪን ጀርመን ተሽቀዳድሞ ሲይዝ የጦር



ጓደኛነቱ ዋጋ አጣ። ደግሞም ሂትለር ከዚያም አልፎ ሰኔ 15 ቀን 1934 ዓ.ም /22 ቀን 1942/ ራሺያን ወረረ።

ሞሶሊኒ ከክላሬታ ፒታኪ ጋር የሚሠራው ሥራ በፋሽስት ፓርቲ ጽህፈት ቤት ተመረመረ። ቤተሰቦችዋ በብዙ የመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ገብተው ተገኙ። ክላሬታ ዳግመኛ አጠገቡ እንዳትደርስ ተከለከለች። የራሼል መደሰት ሙሶሊኒን ሊያጽናናው አልቻለም። ተከዘ። የአንጀት በሽታ /አልሰር/ ያዘው። ሂትለር ይህንን ሲገነዘብ ኢጣልያን በኃይል ለመያዝ ከጀለ። ይህ ደግሞ የኢጣልያን ባለሥልጣኖች አስቆጣ።

ሁኔታዎች ሁሉ እንደዚህ ሲበላሹ በሙሶሊኒ ላይ ጠላቶቹ ገነኑበት። በዱና ግራንዲ አነሳሽነት የፋሽስት ምክር ቤት እንደገና እንዲከፈት፣ ሕዝብ የመረጠው ምክር ቤት ተመልሶ እንዲጠራ፣ ንጉሡ ሥልጣናቸውን መልሰው እንዲይዙ ነገር ተጠነሰሰ። በብዙዎቹ የፋሽስት ባለሥልጣኖች ዘንድ ሃሳቡ ድጋፍ አገኘ። ሙሶሊኒ አንድም ፋሽስቶችን ለማስፈራራት፣ አንድም ንጉሡን ለመለማመጥ፣ አንድም ደግሞ ካልቀረልኝ ብሎ "ሥልጣን መልሶ ለንጉሡ ማስረከብ የምትሉትን አማራጭ እቀበላለሁ" አለ። በዚሁ ተወሰነ። የምክር ቤቱን ውሣኔ ለንጉሡ ማቅረብ መጥፎ ዕድሉ ሆነ።

ሁለቱም ሴቶች ሙሶሊኒ ሥልጣን ለንጉሡ መልሶ ማስረከቡን ተቃወሙ። የሙሶሊኒ ጥያቄ "ኋላ ምን ላድርግ?" ሆነ። ራሼል "ንጉሡ ከሀዲ ነው ይገድልሀል" አለችው። ማምለጫ ዘዴ ግን አላቀረበችም። ክላራ "አሞኛል ብለህ ብትተኛስ?" አለች። ሕመምም የሞት መጀመሪያ ነው። የተቃወሙት 19 የፋሽስት ባለሥልጣኖች እንዲያዙ የሰጠው ትዕዛዝ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። ስለዚህ ሙሶሊኒ የፋሽስት ምክር ቤት ያሳለፈውን ውሣኔ ለንጉሡ ከማቅረብ የሚያመልጥበት ዘዴ አጣ። በአንድ በኩልም ንጉሡ እንደማይጨክንበት አድርጐ ገመተ። ቀደም ብሎ የውስጥ ግንኙነት ነበረውና፤ ንጉሡን ከሥልጣን ሊያወርደው ይችል በነበረበት ጊዜ አልጨከነበትም ነበርና። ደግሞም ያለእሱ ኢጣልያ የምትቆም አልመሰለውም ነበርና።

የሚስቱንም፣ የሴት ልጁንም፣ የቁባቱንም ምክር ጥሶ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሄደ። ንጉሡም በመልካም ተቀበለው። ሙሶሊኒ የፋሽስቱን ምክር ቤት ውሣኔ ከአቀረበ በኋላ፤ ምክር ቤቱ ሃሳብ የማቅረብ እንጂ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንደሌለው ገለጸ። ነገር ግን ንጉሡ ይህንን ክርክር አልተቀበለም። ምክንያቱም ሙሶሊኒ በሕዝብ የተመረጠውን ምክር ቤት የዘጋው፤ ሥልጣኑን ወደ ፋሽስት ምክር ቤት እንዲዛወር በማድረግ ነበርና። ደግሞም የንጉሡ ጥቅም ሥልጣኑን መልሶ በመረከብ ሙሶሊኒን



የፋሽስቱ መሪ ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

ከሥልጣን ማባረር ነበርና፤ ንጉሡም "...አንተ የተጠላህ ሰው ነህ። ከእኔ በስተቀር ደጅ የለህም። እኔም ለሕይወትህ ጥበቃ አደርግልሀለሁ..." በማለት ንግግሩን ደምድሞ አሰናበተው። ሙሶሊኒ ወደ እሥር ቤት ጉዞውን ቀጠለ።

ሙሶሊኒ ምን እንደተወሰነበት አልተረዳም። ነገር ግን ከቤተ መንግሥቱ ሲወጣ ያልጠበቀው ነገር አጋጠመው። አንድ መኰንን ተጠጋው። እንዲጠብቀው ከንጉሡ መታዘዙን ነገረው። ሙሶሊኒ አሁንም አልገባውም። "አስፈላጊ አይደለም" የሚል መልስ ሰጥቶ ጉዞውን ቀጠለ። ነገር ግን መኪናው በአካባቢው አልነበረም። በዚህ ጊዜ ተደናገረው። መኰንኑም አስገድዶ ከአንድ የእሥረኞች መኪና ውስጥ አስገባው። ከመንገድ እሱን የሚያጅብ ሳይሆን ፋሽሲዝም ይውደም የሚል ሰልፈኛ አየ። ከዚያም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። በዚህ ዓይነት ሙሶሊኒ ሐምሌ 17 ቀን 1935 ዓ.ም /16 ቀን 1943/ እሥር ቤት ገባ።

ማርሻል ባዶልዩ በሙሶሊኒ ምትክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ተሾመ። "የት መኖር ትፈልጋለህ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ሙሶሊኒ ሮካ ዴል ካሚናቴ የተባለውን ቦታ መረጠ። ነገር ግን ምርጫውን አላገኘም። ፖንዛ ወደ ተባለችው ደሴት ተወሰደ። ይህች ደሴት ብዙ ኢትዮጵያውያን እሥረኞች የሚለቀቁባት ነበረች። የፖንዛ እሥራት አስተማማኝ ባለመሆኑ ደግሞም ዱካውን ለማጥፋት ሲባል ማደሌና ወደ ተባለችው ሌላ ደሴት ተወሰደ። የታሠረበት ቦታ ከባሕር ወለል በላይ 6,500 ጫማ እንደሆነ ሲነገረው፤ ሙሶሊኒ ከከፍተኛው እሥር ቤት ገብቻለሁ ማለት ነዋ! ብሎ ተደነቀ።

የሙሶሊኒ መታሠር ለሂትለር እጁን እንደ መቆረጥ ያህል ሆነበት። አዲሶቹ መሪዎች የፖሊሲ ለውጥ ስለአደረጉ በጦርነቱ ሂደት ላይ አደገኛ ነገር ተፈጠረ። ስለዚህ ሂትለር ሙሶሊኒ የታሠረበትን ቦታ ያፈላልግ ጀመር። ሙሶሊኒ ተፈቅዶለት ነበርና አንድ ቀን ሲንሸራሸር አንድ የበጐች እረኛ ወደ እሱ ቀርቦ "ጀርመኖች ይፈልጉሀል። አሁን ሄጄ እነግራቸዋለሁ" ብሎት ከፊቱ በረረ። ሞሶሊኒ አላመነም። ከጥቂት ቀናት በኋላ አራት የጀርመን አይሮፕላኖች ተከታትለው በአቅራቢያው አረፉ። ወታደሮችም ከአይሮፕላኖች እየወረዱ በመሮጥ ሙሶሊኒ የነበረበትን ቤት ከበቡ። የኢጣልያ ፖሊሶች ለመተኮስ ተዘጋጅተው ሳሉ ሙሶሊኒ በመስኮት ይመለከት ነበርና። "አትተኩሱ! በመካከላቸው ኢጣልያዊ ፖሊስ አለ" ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ፖሊሶቹ ፈዘዙ። በአንድ ኦቶ እስኮዚኒ በሚባል ሻምበል የሚመሩ የጀርመን ወታደሮች ሙሶሊኒ ከአለበት ቤት ገቡ። ወደ ጀርመን አገር ሊወስዱት እንደመጡ ነገሩት።



ሞሶሊኒ ሲፈታ ኢጣልያ ተበጠበጠች። ማርሻል ባዶልዮ ማረጋጋት አቃተው። የኢጣልያ ንጉሡና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ የነበረው ሣልሣዊ ኢማኑኤል አገር ጥሎ ጠፋ። ይህንን ሁኔታ ተገንዝቦ የነበረው ጄነራል ሶሌቲ ሙሶሊኒ ሮም ገብቶ አዲስ መንግሥት እንዲያቋቁም ፈለገ። ሙሶሊኒ በመካከላቸው ኢጣልያዊ መኰንን አለ በማለቱ ለወታደሮቹ እንዳይተኩሱ ትዕዛዝ የሰጠው እሱን አይቶ ነበር። ነገር ግን በሃሳብ ጭምር በመንገላታት ተዳክሞ ነበርና፤ የጄነራል ሶሊቲን እቅድ መቀበል አልቻለም። ከዚህም በስቀር ሂትለር ወደ እሱ እንዲሄድ አስተላልፎለት የነበረውን ቃል ማክበር ስለነበረበት፤ ወደ ጀርመን አገር መስከረም 2 ቀን 1936 ዓ.ም /ሴፕተምበር 12 ቀን 1943/ ሄደ። ሌሎች የጀርመን ወታደሮች ወይዘሮ ራሼልን ከኢጣልያ ወደ ጀርመን አገር በዚያው መስከረም 2 ቀን ወስደዋት ነበርና፤ ባልና ሚስቱ ሚዮኒክ ከተማ መስከረም 3 ቀን ተገናኙ።

ሚዮኒክ ከደረሰ በኋላ ሙሶሊኒ የሂትለርን ድንፋታ ማዳመጥ ነበረበት። ሂትለር ጣልያኖች ስለከዱት ጦርነቱን ብቻውን መቀጠል እንደአለበት ገልጾ፤ ወደ ሥልጣን እንዲመለስ ሞሶሊኒን ጠየቀው። አሻንጉሊት አድርጐ እንደ አሻው ሊጫወትበት። ሙሶሊኒ ወደ ሥልጣን የመመለስ ጉጉት አልነበረውም። የእሱ ወደ ሥልጣን መመለስ በኢጣልያ ውስጥ የርስበርስ ጦርነት እንደሚያስነሣ ገለጸ። ነገር ግን ሂትለር አልተቀበለውም። በግድ መመለስ እንደአለበት አስታወቀው። ሞሶሊኒ መልሶ በሂትለር ላይ ጮኸበት። ጀርመኖች ጣልያኖችን እንጂ፣ ጣልያኖች ጀርመኖችን እንዳልከዱ ነገረው። ከዚያም አልፎ ጀርመኖች የኢጣልያን ምድር ለቅቀው መውጣት እንደ አለባቸው በድፍረት አስታወቀው። ሆኖም ሂትለር አልተበገረለትም። እምቢ ከአለ ገድሎት በአይሮፕላን አደጋ እንደ ሞተ መግለጫ በማውጣት፤ በምትኩ ሌላ ሰው ሹሞ ኢጣልያንን ያለርኅራሄ እንደሚቀጣት ገለጸለት። አያደርግም አይባልም። በሌላ በኩል ደግሞ ሚስቱ ወይዘሮ ራሼልና ልጁ ወይዘሮ ኤዳ ወደ ሥልጣን መልሱን ብለው አጥብቀው ተቃወሙ። ወይዘሮ ራሼል ገና በደህና ቀን "እንግዲህ በቃ" ብላ ነበርና የፈራችው እንደ ደረሰ ገለጸች። ኤዳ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኮንት ቺያኖ ሚስት ነበረችና ምክርዋ ከብዶት የነበረው ሙሶሊኒ በጉዳዩ በደንብ ከአሰበበት በኋላ ወደ ሥልጣን ለመመለስ ወሰነ። ወደ ሥልጣን የሚመለሰው ወድዶ ሳይሆን ለኢጣልያ ብሎ ነበርና "ኃላፊነቱን እስከ መጨረሻው መወጣት አለብኝ" አለ።

መስከረም 5 ቀን 1934 ዓ.ም /15 ቀን ሙሶሊኒ/ ድምጹን ለኢጣልያ ሕዝብ በጀርመን ሬዲዮ አሰማ።' ሶሺያሊስት መንግሥት

እንደሚያቋቁም አስታወቀ። የፋሽስት ፓርቲ በሕዝብ እንደተጠላና እንደረከሰ ተረድቶ ነበርና። ድምጹ ከመቅጠኑ የተነሣ ድምጹን ለይተው የሚያውቁ ጣልያኖች የእሱ አልመሰላቸውም። ብዙዎቹም እንደገና ወደ ሥልጣን ባይወጣ ወደዱ። ፈቅዶ እንጂ ተገድዶ አልመሰላቸውም ነበርና።

ሙሶሊኒ ጥቂት ደጋፊዎቹን አስከትሎ ወደ አገሩ ተመለሰ። ነገር ግን ሮም መግባት አልቻለም። ጋርዳ ከተባለው ደሴት ምዕራብ በሆነች ሣሎ በተባለች ትንሽ ከተማ መንግሥት አቋቋመ። ሕዝቡን ለማስቲባበር ሕመምተኛና ደካማ ሰውነቱ የሚፈቅድለትን ሁሉ አደረገ። አገር የመምራቱ ሥራ ከበደበት። በዚያ ላይ የጀርመኖች ተፅዕኖ ተጨመረበት። ሂትለር እሱን እንደ ሎሌ ኢጣልያን እንደ ቅኝ ግዛት ቆጠራት። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢጣልያ ዜጐች እየተገደዱ ለጀርመኖች የጉልበት ሥራ ከመሥራት ደረሱ። ይህም ታላቅ ሀዘንና ሥቃይ ፈጠረ። አዲስ የሾማቸው ሚኒስትሮች የቀድሞዎቹ የፋሽስት ፓርቲ ባለሥልጣኖች በሀገር ላይ የክህደት ሥራ ስለፈፀሙ በወንጀል እንዲከሰሱ ሃሳብ አቀረቡ። የአዲሱን መንግሥት ሥልጣን ለማጠናከር፤ ተቃዋሚዎችን ማጥፋት አስፈላጊ መስሎ ታያቸው። እሱ ግን አዲስ ሥራ መሥራት እንጂ፤ ወደ ቀደሞው የፖለቲካ አዘቅት ተመልሶ መውረድ አልፈለገም። ደግሞም ሥራቸው የሀገርን የማዳን እንጂ፤ የማጥፋት ሙከራ መስሎ አልታይህ አለው። ደግሞም አማቹን ቺያኖን ከሞት የሚያደርስ፣ ከሚወዳት ልጁ ከኤዳ የሚያለያየው ሆነበት። ደግሞም ብዙዎቹ የፋሽሲት ፓርቲ ባለሥልጣኖች ከሀገር ስለወጡ ለፍርድ የሚቀርቡት ስደስቱ ብቻ ሆኑ።

በጉዳዩ ብዙ ከአሰበበት በኋላ ጥያቄውን ማገድ ስለአልቻለ እንዲከሰሱ ፈቀደ። የፍርድ ቤት ሥራ ተካሄደ። ሞት ተፈረደባቸው። እሱም የፍርዱን ሂደት ለማገድ ስለአልፈለገ ጥር 3 ቀን 1936 ዓ.ም /ጀንዋሪ 11 ቀን 1945/ ቺያኖና ሌሎቹ አምስት ጓደኞቹ በጥይት ተደበደቡ። ወይዘሮ ኤዳ የባልዋን የኮንት ቺያኖን የምሥጢር ማስታወሻዎች ይዛ ስዊዝ ሀገር በመግባት ለእንግሊዞች አስረከበች። የጠረጠሩ አመለጡ። ያልጠረጠሩ ተመነጠሩ። ይህ ሁኔታ ሙሶሊኒን እጅግ አሳዘነው። ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ለመመለስ አስቦ የአጥቢያውን ቄስ ቢያማክር "ቁረብ" አለው። ይህንን መቀበል አልቻለም። "ገና ጊዜ አለኝ" አለ። ጊዜ ሞቱ መቃረቡን አላወቀም።

እሱ በታሠረ ጊዜ ቁባቱ ወይዘሪት ክለራ ፒታኪ ሮም ከተማ ታሥራ ነበር። እሱ ሲፈታ እርስዋም ተፈታች። ገሥግሣ ከአለበት ከሣሉ ከተማ ደረሰች። የእርስዋ መምጣት ለሙሶሊኒ ተጨማሪ ራስ ምታት ሆነበት። በመንግሥት ባለሥልጣኖች ዘንድ የተወደደች አልነበረችም።



ለክብሩ መልሶ ግንባታ አመች ሁኔታ አይፈጥርም። በዚያ ላይ ደግሞ በሁለቱ ሴቶች፣ ማለትም በሚስቱ በወይዘሮ ራሼልና በቁባቱ በወይዘሪት ክላራ ፔታኪ መካከል ታላቅ ጭቅጭቅ ተነሣ። ሙሶሊኒ ተዳከመ። "ቺያኖ ከሞተ ወዲህ እኔውም ራሴ ቀስ በቀስ በመሞት ላይ ነኝ" አለ።

አዲሱ መንግሥት በመጠኑ ተጠናከረ። የ600 ቀናት ዕድሜ አገኘ። ነገር ግን ወደ ሮም ሊያስገባው አልቻለም። የኢጣልያ ሕዝብ ጥላቻ ሲቀዘቅዝ በእንግሊዝ የሚካሄደው ጦርነት ተጋጋመ። ሰሜን አፍሪካን ጠቅልሎ ይዞ ወደ ሲሲሊ ደሴት ተሻገረ። ከዚያም የኢጣልያን መሬት ጫማ ረገጠ። ከዚያም እንደ ቅልጥም በተዘረጋው አገር ከደቡብ ወደ ሰሜን ወጣበት። የኢጣልያ ጦር መከላከል አልቻለም። ደግሞም ተከፋፈለ። የጀርመን ጦር ቀደም ብሎ በእንግሊዝ በተሠራ ጥበብ ወደ ኮርሲካ ሄዶ ስለነበር አንዳች ማድረግ አልተቻለም። በሙሶሊኒ መንግሥት ላይ ያመፀው ሠራዊት ከእንግሊዝ ጦር ጉን ቆመ።[2] ሮም ከተማ ወድዳ እስክትጠላ ድረስ በቦምብና በመድፍ ተደብድባ በእንግሊዝ ተያዘች። ሙሶሊኒ ያለ አንዳች ውል እጁን እንዲሰጥ ተጠየቀ። ከሁሉም ይበልጥ ያስገረመው እጁን እንዲሰጥ የተጠየቀው የገዛ ሀገሩ ተወላጅ በነበሩ ሽፍቶች በመሆኑ ነበር።

ሞሶሊኒ እጁን ለሽፍቶች ከመስጠት ሞትን መረጠ። በእጁ የነበሩትን የምሥጢር ወረቀቶች በጥንቃቄ መረጠ። ጥቂቱን በቦርሳው ከትቶ ያዘ። ሌላው በጀልባ ተወስዶ ከባሕር ውስጥ እንዲለቀቅ አደረገ። ባለቤቱ ወይዘሮ ራሼል ወደ ሞንዛ እንደትሔድ አድርጐ ከሣሉ ከተማ ሚላን ወደ ምትባል ሌላ ትንሽ ከተማ ሸሸ። ክላራ "ከአንተ አልለይም" ብላ ተከተለችው። የአሜሪካንና የእንግሊዝ ጦር በሎኛ የተባለውን ከተማ ያዘ። ራሺያኖች በርሊን ለመግባት መቃረባቸው ታወቀ። ቫልተሊና በተባለችው መንደር ውስጥ አብረውት ከነበሩ ጥቂት ሚኒስትሮችና የጦር ሹማምንት ጋር ስብሰባ አደረገ። ለመከላከል ሙከራ እንዲደረግ ቢያሳስብ ተቀባይ አጣ። በፋሽስት ፓርቲ መራራ ጥላቻ መፈጠሩ አሳዘነው። በካርዲናል ሹተር አማካይነት ከሽፍቶቹ ጋር ግንኙነት ፈጠረ። እነሱ ግን የልብ ልብ ተሰምቶአቸው ነበርና በሁለት ሰዓት ውስጥ እጁን እንዲሰጥ ጠየቁት። በድፍረታቸው ተደንቆ ጥያቄውን ሳይቀበል ቀረ።

ጥቂት ታማኞቹን አስከትሎ ከሞ ወደ ተባለች ሌላ ትንሽ መንደር ሸሸ። ወደ ስዊዝ አገር እንዲሰደድ ምክር ቢቀርብለት "በምንም ምክንያት ከኢጣልያ ውጭ አልሄድም" አለ። ሚያዝያ 19 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 27 ቀን 1945/ ለሚስቱ ለወይዘሮ ራሼል የመጨረሻ ደብዳቤ ጻፈ። ብዙ እንደ በደላት ያውቅ ነበርና ይቅርታ ጠየቃት። "በርግጥ የማፈቅረው

አንቺን እንደ ሆነ እመኝ...ልጆቹን ይዘሽ ወደ ስዊዝ አገር ሂጂ።... ከጣልያኖች ይልቅ እነሱ ይራሩ ይሆናል..." አላት። ወረቀቱ ሲደርሳት ወይዘሮ ራሄል "ወደ ስዊዝ አገር ሂድ" አለችው። እሱ ግን "አላደርገውም! ተስፋ የለኝም። የመጣውን እቀበላለሁ። ...ሹፌሬም እንኳን ከዳኝ..." የሚል መልስ ላከላት።

ከዚያም ሚናጅ ወደምትባል ሌላ ትንሽ መንደር ሸሸ። ክላራ የስፔይንን ሰንደቅ ዓላማ በሚያውለበልብ አውቶሞቢል ደረሰችበት። እሱም አይቶአት ተደነቀ። "የምትከተይኝ ለሞት ነውን?" አላት። ራሄል ስዊስ አገር እንዳትገባ መከልከልዋን ሰምቶ አዘነ። አብረውት የነበሩት 12 ወታደሮች ብቻ ስለነበሩ መፈናፈን አልቻለም። ምድር ጠበበችው። ሙሶ ወደተባለች ሌላ ትንሽ መንደር ሸሸ። የሚጓዘው ከጀርመን ወታደሮች ጋር ነበር። በመንገድ ላይ ሽፍቶች አቆሙአቸው። ጀርመኖቹ ብቻ እንዲያልፉ ስምምነት ተደረገና ጉዞው ቀጠለ። ሞሶሊኒ የጀርመን ወታደር ልብስ ለብሶ የጀርመን ወታደር መስሎ አንድ ካሚዮን ላይ ተደብቆ ነበር። ደንጉ ከተባለች ትንሽ ከተማ ሲደርሱ ሽፍቶቹ ማጣራት ጀመሩ። ጣልያኖቹን ወዲያው ከመኪና አስወርደው ወሰዱአቸው። ሙሶሊኒን ግን ለጊዜው አላወቁትም ነበርና ከመኪናው ላይ ቆየ። ፍተሻው ሊያልቅ ሲል ከአሥራ ሁለት የጀርመን ወታደሮች ጋር አንድ የተወለወለ ቦት ጫማ ያደረገ ሰው ከነዳጅ በርሜሎች መካከል ተዘርሮ ታየ። በጫማው ሁኔታ የገነገነው ፈታሽ "ኢጣልያዊ ነህ?" ብሎ ቢጠይቀው "አዎን ነኝ" ብሎ መለሰ። ሙሶሊኒ መሆኑ ታወቀ። እሱም ክላራ ፔታኬም ተያዙ።

ሽፍቶቹ መልሰው ወደ ደንጎ ወሰዱት። የከተማዋ ባለሥልጣኖች ከእንግሊዞች ለመሠወር ከከተማይቱ በላይ ወደሚገኝ ተራራ አወጡት። ራሱን አሥረው ቁስለኛ አስመሰሉት። ፒታኪም ነርስ ሆነች። ሁለቱንም አንድ ክፍል ውስጥ አስገቡአቸው። ኰሎኔል ቫላሪዮ የተባለ የሽፍቶች አለቃ በአንድ አሜሪካዊ መኰንን የተፈረመ ወረቀት በማቅረብ እሥረኞቹን እንዲሰጡት ጠየቀ። የከተማዋ ሹም አልሰጥም በማለት ተከራከረ። ነገር ግን ሙሶሊኒን ማዳን አልተቻለም። ሙሶሊኒ ከሽፍቶቹ እጅ ወደቀ።

በሰደፍ እየጐሸመና እያዳፋ ወስዶ ከግንብ አስጠጋው። በሌለበት የሞት ፈርድ እንደተፈረደበት የሚገልጽ ጽሑፍ አነበበለት። ሙሶሊኒ አንድ ቀን ለፍርድ መቅረብ እንደማይቀርለት አውቆ፤ በአንድ በቆዳ በተጠረዘች ማስታወሻ ጽፎ ይዞ ይዞር ነበር። ከእጁ አይለያትም ነበር። በዚያም ቀን ይዞአት ነበር። ባለሰበው ሞት እንደተፈረደበት ሲሰማ ሳይጨነቅ አለቀረም። "ምን አደረግሁህ?" ብሎ መኰንኑን ጠየቀው። በግል ቂም እንጂ በፍርድ እንደተወሰነበት አድርጐ አልቆጠረውም ማለት ነው።



በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንጂ በሽፍቶች ያውም በሌለበት "እንዲፈረድበት" አልጠረጠረም ነበር። መኰንኑ መልስ ሳይሰጠው ሊገድለው ተዘጋጀ። ወይዘሪት ክላራ ፒታኪ ልታድነው ሞከረች። እሱን ከገደላችሁት እኔንም ግደሉኝ ብላ ጮኸች። ነገር ግን ልታድነው አልቻለችም። የግደያው ሥራ ቀጠለ።

ቫላሪዮ የተባለው ሽፍታ ጠመንጃውን በፍጥነት አነጣጥሮ ምላጩን ሳበ። ነገር ግን ጠመንጃው አልተተኮሰም። ከሸፈ። በጠመንጃ ሰደፍ ራሱን ሊከስክሰው ሲዘጋጅ ያየ ሌላ ወታደር መትረየስ አቀረበለት። ቫለሪዮም በቶሎ ተቀብሎ በሙሶሊኒ ላይ አምስት ጥይት አፈሰሰበት። ወደቀ። ክላራ ፒታኪ ሮጣ ከሬሳው ላይ ወደቀች። ቫለሪዮ እርስዋንም ደገማት። ዱቺ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ሚያዝያ 20 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 28 ቀን 1945/ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተገደለ።

የሙሶሊኒ አበሳ በዚህ አላበቃም። ሬሣው ከክላራ ፔታኪና አብረውት ከተገደሉ ሌሎች 21 ፋሽስቶች ጋር በካሚዮን ተጭኖ ወደ ሚላን ከተማ ተወሰደ። እዚያም ፔያሳ ሌሎሬቶ በተባለችው ትንሽ አደባባይ ካለ ቤንዚን ማደያ የዝቅዝቂት ተሰቅሎ መሣለቂያ ሆነ።[3]

ሞሶሊኒ ጨካኝ ሰው ነበር። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን የፈጸመው ግፍ እጅግ ከፍተኛ ነው። በጥይት በቦምብ ፈጃቸው። የመርዝ ጋዝ አዘነመባቸው። በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት የቀሰቀሰውና የመራው እሱ ራሱ ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈፀመው በደል በታሪክ ፊት ተጠያቂው እሱ ነው። ነገር ግን አውሮፓውያን ይህንን በደል ከበደል አልቆጠሩበትም። ለኢጣልያ ጥቅም እንደ ተፈጸመ አድርገው ቆጠሩት እንጂ። ሞሶሊኒ ብዙ ጣልያኖችንም ገድሎአል፣ ሐሥሮአል፣ አሰቃይቷአል። ነገር ግን ለኢጣልያ ታላላቅ ሥራዎች ሠርቷል። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ላፍታም ቢሆን ሰጥቶአታል። በኢጣልያ ውስጥ ያንቀሳቀሳቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ሥራዎች ቀላል አልነበሩም። ነገር ግን ያ ሁሉ ሥራ ከእሱው ጋር አብሮ ጠፋ። ኢጣልያ ከአዲስ ማጥ ውስጥ ገባች። በእሱ ስሕተት ብቻ አልነበረም። በዓለም የፖለቲካ ሁኔታና በተለይም በሂትለር እብደት ጭምር እንጂ። ቢሆንም ለሀገሩ እስከ መጨረሻ ህቅታው ድረስ ሠራ። ሂትለር በአስጨነቀው ጊዜ እንኳን የወገኖቹን ጥቃት ቸል ሳይል ተከራከረላቸው።

በአመራር ረገድ ሙሶሊኒ ክብር እንጂ፣ የግል ጥቅም ማጋበስ አልፈለገም። በአደባባይ ጯሂ ነው። ዓለሙም የሚያውቀው በዚህ ጠባዩ ነው። በግል ሰውነት ሲታይ ያስባል፣ ብዙ አማራጮችን የማየትና የሚያዋጣውን የመምረጥ ችሎታ ነበረው። የሕግ፣ የእምነት፣ የኀሊና፣

የጥቅም ጉዳዮች ለእሱ ምንም አይደሉም። እሱ የሚከተለው የሚያዋጣውን ብቻ ነው። ከንጉሡም፣ ከጳጳሱም፣ ከመኳንንቱም፣ ከመነኲሳትም መስማማቱ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ብልጠት አበዛና በዚሁ በተጠቀመበት ዘዴ ተመልሶ ወደቀ። ነገር ግን የወደቀው በራሱ ስሕተት ብቻ አልነበረም። በሂትለርም ጭምር እንጂ።

የግል ሕይወቱ ውጣ ውረድ የሞላበት ነበር። ወደ ሥልጣን ኮርቻ ለመፈናጠጥ ባደረገው ጥረት ቤተሰቡ ብዙ መሥዋዕት ከፍሎአል። ለገንዘብ ግድ አልነበረውም። ከአቫንቲ ጋዜጠኝነት ሥራው በተባረረ ጊዜ ደመወዙ መከፈሉ እንደሚቀጥል ተነግሮት ነበር። እሱ ግን እምቢ አለ። ግንበኛ ሆኜ መኖር አያቅተኝም አለ። በሚስቱ በወይዘሮ ራሼል ብዙ በደል ፈጽሞባታል። እሱ ከሌሎች ጋለሞቶች ጋር ሲምነሸነሽ ራሼል በኑሮ ችግር ትጠበስ ነበር። ለምሣሌ ከሥልጣን በወረደ ጊዜ ከልዩ ልዩ የጦር ክፍል የተወጣጡ ወጣት መኰንኖች ለመፈተሽ ከቤቱ ሄዱ። አደጋ እንዳይደርስባቸው ሰግተው ተጠንቅቀው ነበር። ከቤቱ አካባቢ ሲደርሱ እለመጠን ጭር አለባቸው። በር ቢያንኳኩ አንዲት ያሸረጠች ሴት ወጣች። ራስዋን አስተዋውቃ ለመግባት ቢጠይቁ ፈቀደችላቸው። የሚፈተሽ ነገር አልነበረም። በቤቱ ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች በማንኛውም ኢጣልያዊ ሹም ቤት የሚገኙ ዓይነት ነበሩ።

ክፍሎቹን እየተዘዋወሩ ሲጐበኙ በአውሮፕላን አደጋ የሞተው ልጁ ይተኛበት ከነበረው ክፍል ደረሱ። የምዋቹ ፎቶግራፍ ተሰቅሎአል። ሻማ ተበርቶለታል። ከመኰንኖቹ አንዱ "ከዚህ ልጅ ጋር ሚላን አንድ ትምህርት ቤት ነበርን" አሉ። ሌላውም አየር ኃይል እንደሚያውቀው ተናገረ። አንዱ መኰንን ደግሞ "ታውቂዋለሽ?" ብሎ ራሼልን ጠየቃት። ገረዱ እንጂ የዱቼ ሚስት አለመሰለቻቸውም ነበርና። "እናቱ ነኝ እኮ!" ባለቻቸው ጊዜ ደነገጡ። አለቀሱም። እርስዋም "በቤት ውስጥ ያለው ይህ ነው" ብላ አንድ ጠርሙስ ወይን አቀረበችላቸው። መጠጡ ለገና መቆያ ጄነራል ፍራንኮ የላከላት ነበር። እጅግ ተደነቁ። ዱቼ እንደገና ወደ ሥልጣን እንደሚመለስ ያላቸውን ተስፋ ገልጸውላት እያዘኑ ሄዱ። ራሼል ግን በደሉን ሁሉ ችላ ብላ ኖረች። ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው የወይዘሪት ክላራ ፒታኬ ነው። እሱ ራሱ እስኪደነቅ ድረስ ታማኙ ሆነች። የጭንቁ ተካፋይ ሆነች። በመጨረሻም "እሱን ከገደላችሁት እኔንም ድገሙኝ" ብላ ሬሣው ላይ ተጠመጠመች። እንዳለቻቸውም ተገደለች። አብራው በሚላን ከተማ የዝቅዝቂት ተሰቀለች። ይገርማል ከልብወለድ የረቀቀ ድርጊት!



# አባሪ 4
# የፋሽስት ፓርቲ አነሣስና አወዳደቅ

የ19ነኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ በአውሮፓ አዳዲስ ርዕዮታት ዓለም የተጠነሰሱበት ዘመን ነበር። የኮሚኒዝም ፍልሥፍና የተቀመረው በዚህ ጊዜ ነው። ከዚያ ቀደም ብሎ በትምህርት መልክ ሲነገሩ፣ በፍልሥፍና መልክ ተራቅቆ ሲደረግባቸው የቆዩ የፖለቲካና የሕዝብ አስተዳደር ባሕረ ሃሳቦች ቅርጽ እያገኙ ሄዱ። ይህ ሁኔታ ኢጣልያንም መዳሰሱ አልቀረም። በዚህ ላይ ደግሞ የአድዋ ቁስል ተጨመረበት።

ሃያኛው ክፍለ ዘመን ሲብት ኢጣልያ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ነበረች። በዚህ ላይ ደግሞ የኢኮኖሚ ድቀት፣ የሥራ አጥ ብዛት፣ በየጊዜው የሚነሱና የሚወድቁ መንግሥታት ግልብጥብጦሽ ሕዝቡን እያስመረረ ሄደ። የፋሽዝም አፈጣጠርና አስተዳደግ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነ። ዕምነትን የሚጋፋ፣ ባለሥልጣኖችን የሚደፍር፣ አዲስ ለውጥ የሚሻ ትውልድ ተነሣ። የነበሩት ፓርቲዎች ጥሙን የማያረኩለት ሆኑ። ለጭቁኑ በማለት የተንቀሳቀሰው የፋሽት ፓርቲም የማይጠቅም ወጣው። ስለዚህ አዲስ ፓርቲ ማቋቋም አስፈለገ። በዚህ ላይ ደግሞ የቤኒቶ አእምሮ ለሚብላላው አመለካከት በር ከፈተ።

ፋሽዝም እንደ ሌሎቹ ርዕዮተ ዓለሞች በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ምርምር ተደርጐበት የተነሣ አይደለም። ለምሣሌ ኮሚኒዝም በፍሬድሪክ ኤንግልስና በካርል ማርክስ ጥናትና ምርምር ከተደረገበት በኋላ ነው በሌኒንና ከእሱም በኋላ በእስታሊን የተንቀሳቀሰው። ፋሽዝም ግን መጀመሪያ እየተንቀሳቀሰ ነው ርዕዮተ ዓለሙን ለመቅረጽ የሞከረው።

ሂደቱን ብንመለከት ሙሶሊኒ ከሶሺያሊስት ፓርቲ ጋር በሥልጣን ፍለጋም፣ በአመለካከትም ተጋጨ። ሶሺያሊስቶች ከብልህነት ይልቅ የጀብደኝነት መሥመር ተከተሉ። ሙሶሊኒን በአንዳንድ ጉዳይ አለገዘበው አብሮአቸው እንዲቆም በማድረግ ፈንታ ገፈተሩት። እሱም እንደነርሱ እልህ ያዘውና አዲስ ፓርቲ በማቋቋም የራሱን ፍላጐት በሥራ ላይ ማዋል ፈለገ። ከሁለት እንጨት ፍጭት እሳት እንዲወጣ የፋሽስት ፓርቲ ከዚህ የርስበርስ ግጭት ወጣ።

የሙሶሊኒን የሕይወት ታሪክ በሚመለከተው ምዕራፍ እንደ ተገለፀው፤ ሙሶሊኒ አዲስ ቡድን አሰባስቦ ስሙን "ፋሺ" አለው። የዚህ ቃል የመጀመሪያ ትርጉሙ "ቡድን" ከማለት እምብዛም የተለየ አልነበረም። የሙሶሊኒንም ሃሳብ ተከታዮችን አፍርቶ ለሥልጣን የሚያበቃ አንድ የሆነ ድርጅት ከመቋቋም የተለየ አልነበረም። በትግሉ ውስጥ እየነቃና መካርም እያገኘ ሄደ እንጂ፤ ለመጀመሪያው ጊዜ ሥልጣን ቢይዝ ምን ሊሠራ እንደሚፈልግ አያውቅም ነበር። ግልጽ ዓላማ አልነበረውም።

በ1904 ዓ.ም የተጠነሰሰው የፋሺ. ቡድን እየተጠናከረ ሄደ። ተከታዮቹ ፋሽስቶች ተባሉ። በሀገር ጉዳይ ላይ እያተኩሩ ሄዱ። በወቅቱ የነበሩት የኢጣልያ መንግሥቶች ላይ አቃቂር ማውጣትን አዘወተሩ። ቀስበቀስም አድማጭ እያገኙ ሄዱ። የሕዝቡንም የልብ ትርታ ማድመጥ ጀመሩ። በዚያን ወቅት ለሕዝብ ቅርበት ነበራቸውና ፍላጐቱን ለማወቅ፣ የእነሱንም ሃሳብ ለማሳወቅ ቻሉ። ተፎካካሪአቸው ሶሺያሊዝም ሆነ። እሱን ለመቋቋም ሲባል በፓርቲነት መቋቋም አስፈለገ። ስለዚህ ፓርቲው መጋቢት 14 ቀን 1911 ዓ.ም /ማርች 23 ቀን 1919/ በይፋ ተቋቋመ። ፓርቲው የተቋቋመው በሚላን እንጂ በኢጣልያ ዋና ከተማ በሮም አልነበረም። የተመሰረተውም በሚላን ከተማ በአንድ የነጋዴያን ማህበር መሥሪያ ቤት በተሰበሰቡ 119 ሰዎች ነበር። ይሁን እንጂ በምሥረታው ጉባዔ ላይ የሃሳብ ልዩነት አላጋጠመውም። ነገርግን የሁሉን አስተያየት ለማስተናገድ በተደረገው ጥረት የመመሥረቻው ደንብ በጣም ልል ሆነ። ፓርቲው ፋሽዝም፣ አባላቱ ፋሽስት፣ ጽህፈት ቤቶቹ ፋሺ፣ መሪው ቢኒቶ ሙሶሊኒ ዱቼ /ጌታ/ ተባሉ።[1]

ከዚህ በኋላ ድጋፍ ሰጭ ሊቃውንት ተንቀሳቀሱ። ስሙን በተመለከተ በጥንት ዘመን ሮማውያን ለሚይዙት እንደ ፋስ መጥረቢያ ያለ መሳሪያ የሚያሠሩበት ጠንካራ ገመድ "ፋሺ" ይባል እንደነበሩ ድርሳናትን አገላብጠው አገኙ። ፋሽዝምም ሰዎችን ያስተባብራል የሚል ሃሳብ በመከተል ባሕላዊ ስሜትን እንዲቀሰቅስ አደረጉ። ቡድን ወይም ክበብ የሚለው የመጀመሪያው አስተሳሰብ በዚህ በአዲሱ ትርጓሜ ተተካ። ርዕዮተ ዓለምን በተመለከተ ፋሽዝም የአዲስ ለውጥ አራማጅ፣ ለሀገር ጥቅም የሚሠራ፣ ድሆችን የሚታደግ እንደሚሆን አጠቃላይ ግንዛቤ ተገኘ። በወቅቱ የነበረው የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም ዓላማውን በሰላም በሥራ ላይ እንደሚያውል ሲቀሰቅስ፤ ፋሽዝም የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ኃይል አስፈላጊ እንደሚሆን አስታወቀ። ከዚህ ላይ እውነትን የመናገር ችሎታውን ማድነቅ ይገባል። በጦር ሜዳ፣ በባዕድ ሕዝብ ላይ የተፈፀመ በመሆኑ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመው ግፍ ካልተቆጠረበት በስተቀር፤ ፋሽዝም ከኮሚኒዝምና ከናዚስም የበለጠ የደም አፋሳሽነት ግብር አላሳየም። ነገር ግን ኮሚኒዝምና ናዚስም የገዛ ሕዝባቸውን በደም አጥለቅልቀው ስማቸው በክፉ አይነሳም። ፋሺዝም ግን መዘባበቻ ሆኖ ቀረ።

ሃሳቡና ግብሩ ተለያዩ። አዲስ የስርዓት ለውጥ የማምጣት ዓላማ ይዞ፣ ለዚህም የኃይል ሥራ አስፈላጊ መሆኑን አምኖ ተነሣ። ከምርጫም ውስጥ ገባ። በሚያዝያ 1913 ዓ.ም /1921/ በተደረገው ምርጫ ከ535 ወንበሮች 35 /6.5%/ ብቻ አገኙ። ይቺን መቆናጠጫ እርካብ አድርጐ ወደ ሥልጣን ለመውጣት ተፍጨረጨረ። አበጣበጠ፣ ደም አፋሰሰ። ስለዚህ አካሄዱ በልጆች ጨዋታ የውሬ፣የጭፍን የሚባለውን ዓይነት ሆነ። በሙሶሊኒ



ብርታትና በእርሱ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ጥቅምት 20 ቀን 1915 ዓ.ም /30 ቀን 1922/ በትረ መንግሥት ቀማ።

በትረ መንግሥት በጨበጠም ጊዜ ማንኛውም አዲስ መንግሥት እንደሚያቀርበው ዓይነት የሥራ ፕሮግራም አቀረበ እንጂ፤ በርዕዮተ ዓለም ላይ የተመሠረተ የለውጥ ሥርዓት ለማምጣት አልሞከረም። ሙሶሊኒ ፋሽዝም ለሠራተኛው ወገን የቆመ በመሆኑ የመደብ ትግል ማካሄድና ካፒታሊዝምን መቃወም እንደሚገባው ከመግለጹ በቀር፤ በፓርቲ ደረጃ የተወሰደ እርምጃ አልነበረም። ሆኖም በድርጅት ረገድ ፋሽዝም ፈጣን ዕድገት አሳየ። ፓርቲው ከተቋቋመበት ከመጋቢት 1911 እስከ ጥቅምት ወር 1912/1919/ ዓ.ም ባለው ሰባት ወር ብቻ 149 ጽህፈት ቤቶች ከፈተ። በደምሩ 45000 አባላት አሰባሰበ። ከዚያም በኋላ አቅዋሙን እያጠናከረ ሄደ።

ለውጥ አራማጅ መስሎ ሥልጣን ከያዘ በኋላ፤ ፋሽዝም ለውጥ ከማምጣት ይልቅ ሥልጣኑን ማጠናከርን አስቀደሞ፤ ንጉሡን ለመነቅነቅ አንዳች ሙከራ አላደረገም። እንዲያውም ባለምዋል ሆነ። ፀረ-ሐይማኖት አመለካከቱን ለወጠ፤ ከካቶሊክ ቤተ ክህነት ጋር ተስማማ። ከመኳንንቱ ከካህናቱ ተባበረ። እንደዚህ አድርጐ ከላይ ቤቶች ጋር ከተስማማ በኋላ ዓይኑን ወደ ታች ቤት አዞረ። ተቃዋሚዎችን ለመቆጣጠር ልዩ ጥረት አደረገ። ሃሳብን አስተያየትን በነፃ መስጠት ቀረ። ስብሰባና ሰልፍ ማድረግ ተከለከለ። ጋዜጠኞች ወደ ውጭ አገር ተሰደዱ። ዛቻና ማስፈራራት ዋና ሥራ ሆነ። ከ1918 ዓ.ም ጀምሮ ፋሺዝም ተቃናቃኝ የሌለበት ብቸኛ ፓርቲ ሆነ። ሙሶሊኒም ፈላጭ ቆራጭ ባለሥልጣን ሆነ።

ለፋሽስት ፓርቲና ለመሪው ለሙሶሊኒ ታማኝ ያልሆኑ ሠራተኞች ከሥራ የሚባረሩበት ደንብ ወጣ። ሙሶሊኒን መንካት በከፍተኛ ደረጃ የሚያስቀጣ ወንጀል ሆነ። ሕዝብ ጸጥ ሲል የፋሽዝም ትኩረት ወደ ምክር ቤት ዞረ። ለምክር ቤት የመወዳደርና የመመረጥ መብት ለፋሽስት አባላት ተሰጠ። በ1917 ዓ.ም ከምክር ቤት ወንበር ሁለት ሲሦው ከእነሱ እንዲሆን ተደረገ። ይህም የማይበቃ ሆኖ በ1919 ዓ.ም የመምረጥን መብት ሙሉ በሙሉ ለፋሽስት አባላት እንዲሆን የሚደነግግ አዋጅ ወጣ።

የዚህን ሕግ አወጣጥ ሥልት ማጤን ደግ ነው። የሕግ መምሪያው ምክር ቤት መቀመጫዎች 535 ነበሩ። የምርጫው ሕግ በተሻሻለበት ስብሰባ ላይ የተገኙት 231/43.2%/ ነበሩ። ምልዐተ ጉባዔ አልነበረም ማለት ነው። ለይሉኝ እይሉ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ምልዐተ ጉባዔ አለመኖር ምንም አይደለም። ዋናው ነገር ከተሰበሰቡት አባላት 216/93.5%/ መደገፋቸው ብቻ ነው። የምርጫው ሕግ በዚህ ዓይነት ተለውጦ የመመረጥ መብት የፋሽስት ፓርቲ አባላት ብቻ ሆነ። የሕዝብ መብት በተወዳዳሪነት በቀረበው ግለሰብ ላይ "ይሁን አይሁን" ሆነ።

ይህንን ሕግ ለማስፈፀም በመላ ኢጣልያ አሥራ ሦስት የምርጫ መሥሪያ ቤቶች /ሴንዴኬትስ/ ተቋቋሙ። የፓርቲውን ሥራ የሚያካሂድ ማዕከላዊ የፋሽስት ፓርቲ ምክር ቤት ተቋቋመ። የፓርቲ አባላት የሚመረጡት በዚህ ምክር ቤት ነበሩ። ለምሣሌ በ1929 /1933/ ዓ.ም ምርጫ፤ ለአባልነት ከአመለከቱት 600000 ግለሰቦች መካከል የተመረጡት 200000 ነበሩ። እነዚህም ለ10000 የፋሽስት መሥሪያ ቤቶች እንደየድርሻቸው ተከፋፈሉ። የምርጫው ጉዳይ በዚህ ዓይነት ተጉዞ ምክር ቤቱ በፋሽስት አባላት ተሞላ። ይህም ሆኖ የምክር ቤቱን ባሕርይ መቆጣጠር ስለአልተቻለ ከእንጭራሹ ተዘጋ። የፋሽስት ምክር ቤት ሙሉ ሥልጣን ያዘ። ነገር ግን እሱም የሚተዳደረው በሙሶሊኒ ሥልጣን ሆነ።

በሌላ በኩል አንዳንድ በጐ ውጤቶች ታዩ። ከታዩት በጐ ውጤቶች አንዱ ሮም የኢጣልያ ዋና ከተማ ከሆነችበት ከ1862 /1870/ ዓ.ም ጀምሮ ሲያጨቃጭቅ የቆየው የቤተመንግሥትና የቤተክህነት ክርክር በስምምነት ማለቁ ነበር። በስምምነቱ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጳጳሱ በሚሰጡት ሹመት መንግሥትን ሊያማክሩ፣ መንግሥት የጳጳሳቱን ደመወዝ ሊከፍል፣ ተሿሚዎቹ ለሀገሪቱ ለንጉሡና ለመንግሥቱ ታማኝነታቸውን በመሐላ እንዲያረጋግጡ፣ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሃይማኖት ትምህርት ሊሰጥ፣ ቤተክርስቲያን ከፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ላትገባ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። በ1923 /1931/ ዓ.ም የካቶሊክ ክበቦች በመዘጋታቸው፣ በ1930 /1938/ ዓ.ም ደግሞ የዘር ልዩነት ሕግ በመውጣቱ ጳጳሱ ቅሬታ ቢሰማቸውም፤ ስምምነቱ እፎይታ አስገኘ።

በልማት ሥራዎችም ረገድ በፋሽስት አመራር አንዳንድ በጐ ውጤቶች ታዩ። ለድሆች ነፃ ሕክምና፣ ለገበሬዎች ድጋፍ የሚሰጥ ሥርዓት ተፈጠረ። ትምህርት ተስፋፋ። በ1913/1921/ ዓ.ም 3 ሚሊዮን የነበረው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በ1927/1935/ ዓ.ም ወደ 4.5 ሚሊዮን /50%/ ከፍ አለ። በመሠረተ ትምህርት መሥፋፋት በዚሁ በተጠቀሱት ሁለት ዘመናት የመሐይምናን ቁጥር ከ75% ወደ ዜሮ ወረደ። ነገር ግን መምህራኑ የፋሽስቱን ርዕዮተ ዓለም የተቀበሉ፣ ሥርዓተ ትምህርቱ በፋሽስት ርዕዮተ ዓለም የተቃኘ ስለነበር፤ ትምህርት የፖለቲካ ሥራ ማካሄጃ መሣሪያ ሆነ። ከዚህም የተነሣ የወታደራዊ ሥልጠና ጠነከረ። የጦረኝነት መንፈስ ሠፈነ።

የዜግነት ስሜት ተጠናከረ። የቀድሞ የባህል ቅርሶች ተከበሩ። ብሔራዊ ታሪክ ክብር አገኘ። እንደ ዮልዮስ ቄሣር ለመሳሰሉ የቀድሞ መሪዎች ሐውልት ተቋቋመ። አዳዲስ መንገዶች ተሠሩ። ባቡር ተሻሻለ። ከሮም ከተማ በተጠረገው ቆሻሻ ከተሞላው ባሕር ላይ አሁን ፋዎንቺኖ እየተባለ የሚጠራው አይሮፕላን ማረፊያ ተሠራ።

በዚህ ላይ ደግሞ ንጉሡንና ጳጳሱን፣ መኳንንቱንና ካህናቱን፣ ሴቱንና ወንዱን፣ ልጁንና አዋቂውን መላዋን ኢጣልያን ያስደሰተ ሥራ ተከናወነ። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት በመያዝ ፋሽዝም አበበ። ቀደም ብሎ በአንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች አስተሳሰብ ይንከባለል የነበረው "ፋሽዝም ያሸንፋል እንጂ አይሸነፍም" የሚለው አመለካከት፤ በኢጣልያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ጭምር ሠፈነ። ተቃውሞ አከተመ።

ሥልጣን ሲደረጅ ቀስ በቀስ ችግር ተፈጠረ። ባለሥልጣኖቹን ፍቅረ ንዋይ አደረባቸው። በተለይም ከኢትዮጵያ አስተዳደር ጋር ግንኙነት ባለው ሥራ የቆሙት፤ ለልዩ ልዩ ሥራ ከሚመደበው ገንዘብ አብዛኛው ከአንዳንዱም እስከ 81.4% ወደ እነሱ ኪስ መፍሰስ አመጣ።[2] ከዚህ ድርጊት ከሙሶሊኒ ከራሱ በስተቀር ሌሎች ነፃ አልነበሩም። ሙሶሊኒ ግን የፍቅረ ንዋይ ደዌ አልተጠናወተውም።

በባለሥልጣኖች መካከል የርስበርስ መናቆር ጠነከረ። የአመለካከት ልዩነት፣ የሥልጣንና የክብር ጥያቄ፣ የጥቅም ክፍፍሉሽ ሚዛን ዋናዎች የጠብ ምንጮች ሆኑ። በኢትዮጵያ ላይ በአለው እንደራሴና ሮማ በቅኝ ግዛት ጉዳይ ሚኒስትር መካከል የተካሄደውን ጭቅጭቅ ማጤን የነገሩን ክብደት ሊያስገነዝብ ይችላል።

ስብሰባዎች በሥነ ሥርዓት መካሄዳቸው ቀረ። ሙሶሊኒን ምቾትና የቤተሰብ ጣጣ አንቆ ያዘው። የመንግሥቱን ጉዳይ ትቶ ቀባቱን በማስታመም ከአንድ ወር በላይ ሥራ የፈታበትን ጊዜ በታሪኩ ውስጥ ተመልክቶአል። ተቆጣጣሪ ስለጠፋ የፓርቲው ውስጣዊ ሁኔታ እየተበላሸ ሄደ።

የፋሽስት ፓርቲ ተቃዋሚዎች በዚህ ሁኔታ በእጅጉ ተጠቀሙ። የፓርቲውን አቋዋም በሕዝብ ዘንድ ማስጠላት፣ ከውስጥም በልዩ ልዩ ዘዴ መቦርቦር ያዙ። በሉ በርቱ ባይ እንጂ፣ ተው ባይ ጠፋ። ንጉሡ ቀስ በቀስ ሥልጣኑን መልሶ ለመያዝ እጁን አስተዳደር ውስጥ ማስገባት ቀጠለ። ለምሣሌ ሂትለር ሮምን ሲጎበኝ ሲመጣ መስተንግዶው በርዕሰብሔር ደረጃ መካሄድ ስለነበረበት ንጉሡ አስተናጋጅ ሆነ። ጉብኝቱ ሙሶሊኒ እንደ አሰበው ሳይሆን ቀረ።

ቤተክህነትም ቀደም ከተፈረመው ስምምነት ሊገኝ ከሚችለው ፀጋ ከተቋደሰ በኋላ፤ በአንዳንድ ጉዳዮች ከመንግሥት ፖለቲካ ማፈንገጥ አመጣ። ለምሣሌ የዘር መድልዎን አዋጅ መቃወም። በዚያው ላይ ደግሞ የፋሽስት ፓርቲን ይደግፉ የነበሩት ጳጳስ አባ ፓየስ 12ኛ ሞተው፤ ፋሽዝምን የማይደግፉ ጳጳስ ተመርጠው ተሾሙ።

በኢትዮጵያ ጦርነቱ ከባድ ሆነ። ብዙ የተደከመባቸውና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰባቸው የልማት ሥራዎች ከንቱ ሆኑ። የፋሽስት ፓርቲ በሕዝብ እየተጠላ ሄደ። ፓርቲው እነዚህን ችግሮች ማቃለል ተሣነው። ከሙሶሊኒ አምባ ገነንነት መላቀቅም መቆጣጠርም አቃተው። የሙሶሊኒም የፖለቲካ ስሜት አውታሮች ደነዘዙ። የአእምሮው ጤንነት እስከሚያጠራጥር ድረስ ክፉን ከደግ መለየቱ ቀረ።

ኢጣልያ በዚህ ሁኔታ ላይ እንደአለች በአውሮፓ ጦርነት ተቀሰቀሰ፡፡ የሕዝቡን አንድነት የሚያሰባስብና ለሀገር ጥቅም ማስገኘት የሚችል አቅዋም መያዝ ግድ ሆነ፡፡ ከጦርነቱ ገለልተኛ መሆን የማይቻል ሆነ፡፡ ከእኔ ካልሆናችሁ ጠላቶቼ ናችሁ የሚለው የሂትለር ጥያቄ መደመጥ አስፈለገው፡፡ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ጉዳዮች ተተብትቦ የታሠረውና የዛገው የፋሽስት ፓርቲ፣ ለችግሩ መፍትሔ ማግኘት ወይም ለጥያቄው መልስ መስጠት አቃተው፡፡ ስለዚህ በሙሶሊኒ ልዩ ውሣኔ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን በመቆም ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ገባች፡፡ ከጦርነቱም ሊገኝ የሚቻለውን ያህል አገር ለመያዝ የፋሽስት ፓርቲ ሙከራ አደረገ፡፡ አልባንያንና ግሪክን ወረረ፡፡ ዩጐዝላቪያን ለመያዝ፣ የሜዲቴራኒያንን ባሕር ለመቆጣጠር ሞከረ፡፡ የአፍሪካን ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት ጣረ፡፡ ይህ ሁሉ በፓርቲው ተሠራ ይባል እንጂ፣ በሙሶሊኒ ሃሳብና ጥረት ተደረገ፡፡

ውሎ አድሮ ግን በሙሶሊኒ ላይ ጥፋት በዛ፡፡ ሐምሌ 1935 ዓ.ም /ጁላይ 26 ቀን 1943/ ከሥልጣን ወረደ፡፡ የፋሽስት ፓርቲም በዚያው ቀን አብሮት ከሥልጣን ወረደ፡፡ ከዚያ በኋላ እንኳን ለሥልጣን ሊበቃ፣ በፓርቲነት ሊቀጥል አልቻለም፡፡ ምንም ለፋሽስት ፓርቲ ፍቅር ቢኖረው ሙሶሊኒ በሂትለር አስገዳጅነት በሣሉ ከተማ አዲስ መንግሥት ያቋቋመው በፋሽስት ፓርቲ አልነበረም፡፡ በኢጣልያ ሶሻሊስት ፓርቲ /በሪፐብሊክ ሶሲያሌ ኢታልያና/ እንጂ፡፡ ከዚያም በኋላ በኢጣልያም ሆነ በማንኛውም ሌላ ሀገር ፋሽዝም በፓርቲነት አልተቋቋመም፡፡ በጭካኔ ምልክትነት የዓለም ኅብረተሰብ መዘባበቻ ሆኖ ቀረ፡፡

ቀጣዩ ጥያቄ "ይህ ንቅናቄ እንደዚህ መሠረት የሌለው ሆኖ ሳለ፣ ጥንቱን እንደምን ለሥልጣን?" በቃ የሚል ይሆናል፡፡ የፋሽስት ፓርቲ ለሥልጣን የበቃው ራሱን በፓርቲነት በማጠናከር ሳይሆን፣ በሌሎች ላይ ችግር በመፍጠር እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ተከታዩ ጥያቄ "ችግር መፍጠሩንስ ቢሆን እንደምን ቻለው?" የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሀገሪቱን ጠቅላላ ሁኔታና በወቅቱ የነበረውን መንግሥት አቅዋም፣ እንዲሁም የሌሎች ፓርቲዎችን ባሕርይ አጠር ባለ ሁኔታ መቃኘት ያስፈልጋል፡፡

ኢጣልያ አንድነትዋን መሥርታ ሮምን መናገሻ ከተማዋ ከአደረገችበት ከ1862/1870/ ዓ.ም ጀምሮ የምትተዳደረው በሊበራል ፓርቲ ነበር፡፡ ይህንን ፓርቲ የአድዋ ሽንፈት ቢያንገላታውም፣ ለዘብተኛ ከመሆኑ የተነሣ ተቃራኒ ኃይላትን እያስተባበረም፣ ተቃውሞን እየታገሰም ቆየ፡፡ የኮሚኒዝም እንቅስቃሴ እየተጠናከረ ሲሄድ ይህ ልል አስተዳደር ግራ እየተጋባ ሄደ፡፡ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ከ1906 እስከ 1910 ዓ.ም /1914-1918/ ፣ መጀመሪያ ወደ ጀርመን በኋላ ደግሞ ወደ እንግሊዝ ወለም ዘለም በማለት ዳነ፡፡ ነገር ግን ጦርነቱ ከአስከተለው ችግር ሊያመልጥ አልቻለም፡፡ ኢጣልያ በጦርነቱ በቂ ተሳትፎ ስለአልነበራት በቬርሳይ ውል ጥምዋን የሚያረካ ውጤት ሳታገኝ



ቀረች፡፡ ስድስት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ወታደሮችዋን አስፈጅታ፡፡ በዚህ የፖለቲካ ችግር ላይ የኢኮኖሚ ድቀት ደረሰ፡፡ ሥራ አጥ በዛ፣ ውንብድና ጠነከረ፡፡ ልዩ ልዩ ፓርቲዎች መንፈራገጥ ጀመሩ፡፡ ለዘብተኛ አስተዳደር የማይችላቸው ሆኑ፡፡ በኅዳር 1912 /1919/ ዓ.ም ጠቅላላ የምክር ቤት ምርጫ ተደረገ፡፡ ውጤቱ ጠንካራ መንግሥት ለማቋቋም ሳያስችል ስለቀረ፣ በሚያዝያ ወር 1913 /1921/ ዓ.ም ሌላ ጠቅላላ ምርጫ ተደገመ፡፡ እሱ ደግሞ የባሰ ሆነ፡፡ የሁለቱ ምርጫዎች ውጤት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፡፡

| | የ1912 | % | የ1913 | % |
|---|---|---|---|---|
| የምክር ቤት ወንበር | 574 | 100 | 535 | 100 |
| ሊበራል ፓርቲ | 312 | 55 | 255 | 47 |
| ሶሺያሊስት ፓርቲ | 156 | 27 | 122 | 23 |
| ሕዝባዊ/ፖፑላር/ ፓርቲ | 101 | 17 | 107 | 20 |
| ኮሚኒስቶች | - | - | 16 | 3 |
| ፋሽስቶች | - | - | 35 | 7 |

በዚህ ዓይነት ገዥ የነበረው የሊበራል ፓርቲ የአባላት ቁጥር ቀነሰ፡፡ እነዚያውም ደግሞ እርስበርሳቸው የማይስማሙ ሆኑ፡፡[3] አዳዲሶቹ ሶስት ፓርቲዎችም ራሳቸውን ችለው መንግሥት ማቋቋም አልቻሉም፡፡ የሕዝባዊ /ፖፑላር/ ፓርቲ አባላት የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፣ ከሶሺያሊስቶቹ ብዙዎቹ ዝንባሌአቸው ወደ ኮሚኒስቶች ስለሆነ፣ ሁለቱ ፓርቲዎች በጥምር መሥራት አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ፋሽስቶች በሙሶሊኒ የፖለቲካ ጥበብ በመጠቀም ጥቅምት 17 ቀን 1915 ዓ.ም /ኦክቶበር 27 ቀን 1922/ ሮም ከተማ በሰልፍ በመግባት፣ በምርጫ በተገኘው የ7% የፖለቲካ አቅም ያለአንዳች ርዕዮተ ዓለም ሥልጣን ያዙ፡፡ የፋሽስት ፓርቲ መና የቀረው ግብሩ ብቻ ሳይሆን አነሳሱም ጭምር እንደዚህ መናኛ ስለነበር ሳይሆን አልቀረም፡፡

ፋሽዝምን በተመለከተ የመጨረሻውና ዋናው ጥያቄ "ለመሆኑ ርዕዮተ ዓለሙ ምን ነበር?" የሚል ነው፡፡ ዋናው የፋሽዝም የፖለቲካ ጥበብ በአንድ በተወሰነ ርዕዮተ ዓለም አለመታሠር ነው፡፡ እንዳሻ ለመሆን፣ እንዳሻ ለማድረግ እንዲያመች፡፡ ሌሎቹ ፓርቲዎች በተለይም ኮሚኒዝም በጠነከረ ርዕዮተ ዓለም ላይ ተመሥርቶ በመንቀሳቀሱ፣ ፋሺዝምም ርዕዮተ ዓለም እንዲኖረው አስገድዶታል፡፡ በመሆኑም ሥልጣን በያዘ በአሥር ዓመት፣ ማለትም በ1921/1933/ ዓ.ም ሙሶሊኒ የፓርቲ መመሪያ አወጣ፡፡ እሱም፣

1ኛ. ሰብዓዊ አመለካከቶችን ሁሉ መጠራጠር፣
2ኛ. የሰውን የተፈጥሮ እኩልነት መካድ፣
3ኛ. ዓላማን ከግብ ለማድረስ በሀሰትም፣ በኃይልም መጠቀም፣
4ኛ. በምሑራን የሚመራ መንግሥት ማቋቋም፣

5ኛ. ሥራን በአንድ ወጥ አመራር ማካሄድ፣

6ኛ. የዘርን ንጽሕና መጠበቅና የበላይ ገዥነትን ማራመድ፣

7ኛ. ዓለም አቀፍ ህግጋትንና ሥርዓቶችን መዋጋት ነበሩ።

የእነዚህ መርዛማ ሰባት "ቃላት" ውጤት፤ የኢጣልያን ሕዝብ በአምልኮተ እግዚአብሔር ከጸኑ ሥርዓቶች ውጭ አደረገው። አምባገነኑ መሪ፣ ማለትም ሙሶሊኒ ምንጊዜም ትክክል ነው የሚል አስተሳሰብ ቀርጾ። የሰውን የተፈጥሮ እኩልነት ደመሰሰ። የዘር መበላለጥን አሰፈነ። እንኳን ወታደር ለመሆን ወጣቶቹን ለወታደርነት ሥራ ለማዘጋጀት አይችሉም በሚል አመለካከት፤ ሴቶቹን ከማንኛውም ሥራ ከአስተማሪነት ጭምር አገዳቸው። የኃይልና የውሸት ሥራን አነገሠ። የሕዝቡን የዕለት ኑሮ ከአዋቂዎች ነን ባዮች ቅኝት ውስጥ ከተተው። ሃይማኖትን፣ ትምህርትን፣ ልዩ ልዩ የመተዳደሪያ ሥራዎችን፣ ንግድና እርሻን ጭምር ከፖለቲካ መዘውር ውስጥ አስገባቸው። መንግሥቱን ከሌሎች መንግሥታት ጋር አፋጭቶ ከዓለም ማኅበር አስወጣው። በመጨረሻም ኢጣልያን ከውድቀት አደረሳት። ፋሺዝም በጀርመን፣ በጃፓን፣ በአርጀንቲናና በሌሎችም አገሮች ያሳየው ባሕርይ ልዩነትም ተመሳሳይነትም አለው። እኛ ግን ወደዚያ አንሸጋገርም።[4]


## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Stanley Cooperman, *Mussolini Research Notes*, pp.25-32.
2. የኢትዮጵያ ገበሬዎች የመሬት ግምት አከፋፈል።
3. Carlton Hayes, *Contemporary Europe*, pp.569-571.
4. William Einstein, *Today's Isms*, pp. 100-126




## አባሪ ሠሌዳ *

## የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ ጉዳት

### በኢትዮጵያ ላይ የደረሰ ጉዳት

1. በመንግሥት ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የተጠየቀበት[8]

| | | |
|---|---|---|
| 1.1 | ለጦር መሣሪያ የወጣ | 268,131,550 |
| 1.2 | ሳይገባ የቀረ ግብር | 254,028,680 |
| 1.3 | የተለያዩ ኪሣራዎች | 1,325,300,000 |
| የቁጥር 1 ድምር | | 1,847,460,200 |

2. በሕዝብ ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ የተጠየቀበት[9]

| | | |
|---|---|---|
| 2.1 | ለተቃጠሉ 2000 ቤ/ክ/ኖች | 20,000,000 |
| 2.2 | ለተቃጠሉ ቤቶች | 105,000,000 |
| 2.3 | በጦርነቱ ለሞቱ 257 ሺህ ወታደሮች | 275,000,000 |
| 2.4 | ለሞቱ አርበኞች | 78,500,000 |
| 2.5 | ለሞቱ ሴቶችና ሕፃናት | 17,800,000 |
| 2.6 | የካቲት 12 ቀን 1929 ለሞቱ 30 ሺህ ሰዎች | 30,000,000 |
| 2.7 | ተማርከው ለተገደሉ 24 ሺህ አርበኞች | 24,000,000 |
| 2.8 | በእሥራት ለሞቱ 35 ሺህ ሰዎች | 35,000,000 |
| 2.9 | በስደትና በረሀብ ላለቁ 300ሺህ ሰዎች | 300,000,000 |
| 2.10 | ለ5 ሚሊዮን የቀንድ ከብት. | 250,000,000 |
| 2.11 | ለ7 ሚሊዮን በግና ፍየል | 70,000,000 |
| 2.12 | ለ1 ሚሊዮን ፈረስና በቅሎ | 50,000,000 |
| 2.13 | ለ700 ሺህ ግመሎች | 70,000,000 |
| የቁጥር 2 ድምር | | 1,325,300,000 |

3. በሕዝብ ላይ ከደረሰው ጉዳት ካሣ ሳይጠየቅ የቀረ[10]

| | | |
|---|---|---|
| 3.1 | በኢትዮጵያ ስደተኞች ከሀገር የወጣ | 10,000,000 |
| 3.2 | በኢጣልያኖች የተወሰደ | 50,000,000 |
| 3.3 | በእንግሊዞች የተወሰዱ | 50,000,000 |
| 3.4 | የጣልያን ወታደር የዘረፈው | 37,500,000 |
| 3.5 | ሕዝብ የተዘራረፈው | 3,000,000 |
| 3.6 | ለገበሬ ሊከፈል ተፈቅዶ ሳይከፈል የቀረ | 2,175,300 |
| 3.7 | ከ50 ሺህ እሥረኛ የባከነ የሥራ ጊዜ | 18,250,000 |

| | |
|---|---|
| 3.8 ለ213000 የመንገድ ሠራተኞች ሳይከፈል | 8,520,000 |
| 3.9 ለ920000 ባንዳ አገልግሎት የቀረ | 92,000,000 |
| 3.10 ለ450000 ሥራ የፈታበት | 82,125,000 |
| 3.11 ለ16000 ስደተኞች ሥራ የፈታበት | 11,680,000 |
| 3.12 ለ30000አካለ ጐደሎ | 82,125,000 |
| 3.13 የ3 ሚሊዮን አራዊት ዋጋ ድምር | 60,000,000 |
| 3.14 የኢጣልያኖች ከሕዝብ የገፈፉት መሣሪያ | 86,762,200 |
| 3.15 ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የተሠራውን መንገድ | 30,000,000 |
| በኢትዮጵያ ላይ ደየረሰ የቁ.3 ድምር | 894,137,700 |
| ጠቅላላ ድምር | 4,066,897,900 |



## የፀሐፊው አጭር የሕይወት ታሪክ እና ፎቷቸው

የእኔ የአቶ ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1. የልደት ቦታ ሙገሬ ዛለ፣ ቡልጋ፣ ሸዋ።
2. የአምስት ዓመት አርበኛ። ባልደረብነት የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ሀብቱ።
   ትምህርት፣
   ሀ. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እስከ ጾመ ድጓ /ከመምህር ጌታሁን/ ብፅዕ አቡነ ጢሞቲዎስ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘሲዳሞ።
   ለ. በዘመናዊ ትምህርት ቢ.ኤ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ /አዲስ አበባ/ ዩኒቨርስቲ በኤክስቴንሽን።
3. በመንግሥት ሠራተኛነት 42 ዓመት ከ3 ወር፣ ከመስከረም 1942 እስከ ኅዳር 1984 ዓ.ም። በትምህርት ሚኒስቴር እስከ ዋና ዳሬክተርነት፣ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት በምክትል ኮሚሽነርነት፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅነት ማዕረግ።



አቶ ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ



# ዋቢ መጻሕፍት

## የአማርኛ መጻሕፍት


የማስታወቂያና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የድል መታሰቢያ 25ኛ ዓመት፤ ከ1933 እስከ 1958 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1958 ዓ.ም።

ታደሰ ዘወልዴ /ቀኛዝማች/፣ ቀሪን ገረመው፣ የአርበኞች ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1960 ዓ.ም።

ታደሰ ሜጫ፣ ጥቁር አንበሳ በምዕራብ ኢትዮጵያ፣ አሥመራ፣ ኩሪየሬ ኤረትሬዎ ማኅበር ማተሚያ ቤት፣ከ 1953 ዓ.ም።

ፈለቀ ዳኜ /ፊታውራሪ/፣ አምስቱ የመከራ ዓመትና ፍፃሜው አጭር ማስታወሻ፣ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ሐምሌ 1944 ዓ.ም።

ጳውሎስ ኞኞ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ መስከረም 1980 ዓ.ም።

ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።

ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1961 ዓ.ም።

ሽፈራው መንገሻ፣ የኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 42ኛ ዘመን።

ሙሉ ሰው ምትኩ /አዛዥ/፣ የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር፤ ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1937 ዓ.ም።

አክሊሉ ገብረ ኪሮስ /አፈ ሊቀ ሊቃውንት/፣ዜና ባስለዮስ፣ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣዔ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ ሰኔ 10 ቀን 1950 ዓ.ም።

የኢሉባቡር ኢሠፓ ኮሚቴ፣ ለ10ኛው አብዮት በዓል የተዘጋጀ "የኢሉባቡር መድበለ ታሪክ"፣ ነሐሴ 1975 ዓ.ም።

እንዳለ ቢረሳው /ሊቀ ጠበብት/፣ "በኢጣልያ ጉሬ ከተማ ስለተገደሉ ሰዎች የተፃፈ ማስታወሻ" /የእጅ ጽሑፍ/፣ ኅዳር 1929 ዓ.ም።

አሐዱ ሣቡሬ፣ከታሪክ ማኅደር፣ ኢትዮጵያን ሬቪው መጽሔት፣ ቅጽ 2፣ ቁጥር 2፣አዲስ አበባ፣ የካቲት 1991 ዓ.ም።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ /ንጉሠ ነገሥት/፣ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1965 ዓ.ም።



አቶ ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ /ንጉሠ ነገሥት/፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ ሁለተኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1966 ዓ.ም::

መኮንን እንዳልካቸው /ራስ ቢትወደድ/፣መጽሐፍ የዓለምን ምሬት ማጣፈጫ ማር ነው፣አዲስ አበባ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፣ 1960 ዓ.ም::

የሮማ ብርሃን፣አዲስ አበባ፣ የጥር 1932 ዓ.ም እትም::

የራስ ቲያትር የሕዝብ ግንኙነት ማስታወቂያ፣ የፊልም ጥበብ በኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ፣ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፣ 1976 ዓ.ም::

ይልማ ማናዬ፣ ገሞራው ዘርዓይ ደረስ፣ አዲስ አበባ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፣ 1964 ዓ.ም::

ዘውገ ዘገየ፣ አባ ኮስትር፣ የጀግናው የበላይ ዘለቀ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ ኅዳር 1983 ዓ.ም::

ሕይወት ኅዳሩ /ፊታውራሪ/፣ ያቺ ቀን ተረሣች፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1967 ዓ.ም::

ተክለ ማርያም /አባ/፣ የምስካየ ሕዙናን ገዳም አመሠራረት፣አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ በ41ኛው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት::

ታደሰ ዘወልዴ /ቀኛዝማች/፣ የአባሳሽኝ ዘመን፣አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1955 ዓ.ም::

ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983 ዓ.ም::

አያሌው እምሩ /ሊቀ ጠበብት/፣ መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1953 ዓ.ም::

ፍካሬ መጽሔት፣ አንደኛ ዓመት ቅጽ 1፣ ቁጥር 1፣ የካቲት 1985 ዓ.ም::

ላጲስ ጌታቸው ደሌቦ፣ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1983 ዓ.ም::

መድረክ መጽሔት፣ ቅጽ 1 ቁጥር 1፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ሚያዝያ 1985 ዓ.ም::

ክፍለ ጽዮን ማሞ፣ የጦር ወንጀል ምንድነው? ማለዳ መጽሔት፣ቅጽ 1 ቁጥር 2፣ ጥር 1985 ዓ.ም ::

አደፍርስ አየለ፣ ጦቢያ መጽሔት፣ መስከረም 1985 ዓ.ም::

ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ኑብያ /ናፖታ-መርዌ/፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ የካቲት 1 ቀን 1965 ዓ.ም::

ይልማ ደሬሣ፣የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ኅዳር 20 ቀን 1959 ዓ.ም::



ገብረሥላሴ ወልደ አረጋዊ /ፀሐፊ ትዕዛዝ/፣ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1959 ዓ.ም::

ጥንታዊት ኢትዮጵያ አገራዊ የጀግኖች ማኅበር፣ ማኅበረ ሰማዕታት መዋዕያን፣መሠረታዊ ደንብ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1956 ዓ.ም::

ጆርጅ ኤፍ ኤች በርክሌይ፣ ትርጉም ዳኜው ወልደ ሥላሴ፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1979 ዓ.ም::

ቢ. ዴዝሞንድ፣ የኢትዮጵያ አርባ ኩንታል ወርቅ የት ደረሰ? ትርጉም፣ ታደሰ በየነ እርገጤ፣ ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ 1985 ዓ.ም::

ሙራድ ከማል /ዶክተር/፣የፖርቹጋሎች ጀግንነት፣ ትርጉም ዮናስ ቦጋለ፣አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1952 ዓ.ም::

ጆን ሐዛወይ ስፔንሰር፣ጥርስ የገባች አገር፣ ትርጉም መንግሥቱ ኃይለማርያም አርአያ /ሌ.ኮ/፣መዝገቡ ምትኬ ቢልልኝ፣ ኅዳር 1986 ዓ.ም::

ጋስፖሬኒ ገ.ማ /አባ/፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ አሥመራ አርቴግራፊክ ማ.ቤት፣ ለ25ኛው ዓመት በዓል ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አምሃ የቀረበ::

ግርማ ዘውዴ፣ኢትዮጵስ፣ ት.መ.ማ.ማ ድርጅት፣ የካቲት 1985 ዓ.ም

## English Books


Araya Habtay. *The Role of Eritrean Askaris In the Italo-Ethiopian War.* H.S.I.U., A.A. 1970.

Bahru Zewde. *A History of Modern Ethiopia*. A.A.U. Press; 1992.

Campbell, John C. *Defence of the Middle East.* The Harold Praff House; New York, 1960.

Churchil, Winston S. *The Grand Alliance.*Houghton Mifflin Co.: London, 1950.

Cooperman, Stanley. *Mussolini*. Monarch Press Inc; New York.

Einstein, William. *Today's ISMS.* Prentice Hall Inc.; California, 1964.

Frusci, Luigi. *Sue Fronte Meridianale.* Cappelli, Lichinia (ed); Bologna, Italy.

Greenfield, Richard. *Ethiopia, A New Political History*. Frederick A. Praeger; New York, Washington D.C London, 1965.

Hayes, Carlton J.H. *Contemporary Europe since 1870.* The Macmillan Co; New York, 1958.

Mosely, Leonard. *Haile Selassie.* Wedenfled and Nicolson; London, 1964.

Pankhurst, Sylvia. *Ethiopia: A Cultural History*. Lolivela House; London, 1955.

Pankhurst, Sylvia.*Why Do we Destroy Ethiopian Ports?*

Petrides, Pierre. *The Boundary Question between Ethiopia and Somalia.* Peoples Publishing House; New Delhi, 1983.

Rubenson, Sven. *The Survival of Ethiopian Independence.* Kuraz Publishing Agency; Addis Ababa, 1991.

Sabacchi, Alberto. *Ethiopia under Mussolini, Fascism and the Colonial Experience.* Z Books Ltd.: London, 1985.

Skordiales, Kiman. Kagnew. *The Story of Ethiopian Fighters in Korea.* Radio Press: Tokyo, 1954.

Steer, George L. *Sealed and Delivered.* Hodder and Stovghton Ltd: London, 1942.

Vellari, Luigi. *The Ethiopian Crises.* Health and Co.; Boston.




## ኢጣልያ በኢትዮጵያ ለሚለው መጽሐፍ
## የምስክርነት ቃል የሰጡ

1. **ተካነ ባንቲ /መልአከ መዊዐ/**
   በ1985 ዓ/ም ተጉለት፣ የድንባሮ /ግንባርም/ ማርያም
   አለቃ የደብረ መዊዕ ቅድስት ማርያምን ጽላት በቅስና ሥልጣን፣
   ታቦትዋን ይዘው ማይጨው የዘመቱ፤
2. **በየነ ደምሴ /መምሬ/**
   በቅስና ሥልጣን የአራዳ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጽላት ይዘው
   ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ ጋር ተቀላቅለው እስከ መጨረሻው
   ታቦቱን ይዘው በአርበኝነት የሠሩ አርበኞች::
3. **ሥዩም ያዕቆብ /አቶ/**
   ኤርትራዊ፣ የኢጣልያኖች ሃሳብ፣ በኢትዮጵያ ላይ ለመዝመት መሆኑን
   በተኩስ ልምምድ አስመስሎ ለወገኖቹ በፊሊፕ ያስረዳውን ኤርትራዊ
   የሚያውቁ::
4. **ደምሴ አብዮ ሆይ ቄርሎስ /መምሬ፣ በኋላ ደግሞ አባ/**
   በጦርነቱ ጊዜ የባላምባራስ /ራስ/ አበበ አባ ነፍሱ፣ ቀዳማዊ ኃይለ
   ሥላሴ ለራስ አበበ የላኩአቸውን መልእክቶች፣ ከኢጣልያ ጋር
   የሚደረገውን የመደለያ ዓርቅ ምሥጢር፣ እንደዚሁም የንጉሠ መልአከ
   ፀሐይን አሟሟት ለማጣራት የተደረገውን ሙከራ የሚያውቁ ቆስለው
   በመማረክ ሞቃድሾ የታሠሩ አርበኛ::
5. **ወልደ ፃድቅ ሸንቁጤ፣**
   በፊታውራሪ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ ባልደረብነት የቡልጋ አርበኛ::
   ገልጌላ በተሰጠው የጦር ሥልጠና የተካፈለ::
6. **መልእኩ በቀለ ዘውዴ /ባለቃ/**
   በዕርቅ ጊዜ ከቡልጋ ከአርበኞች ቡድን ጋር አዲስ አበባ የገባ::
7. **ንጋቱ ወልደ ዮሐንስ፣ ዘመዴነህ /አቶ/**
   ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ/ም ከደባ ጉጆ፣ ሽንኩራ፣ አልፏት ድኖ የ50
   ዓመት መታሰቢያውን ሰኔ 15 ቀን 1981 ዓ/ም በማክበር የእልቂቱን
   ሁኔታ ያስረዳ::
8. **አባ ገብረ መስቀል /አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ዘትግራይ/**
   በቀጨኔ መድኃኔዓለም አለቅነታቸው ተጠርተው ኢጣልያኖች አዲስ
   አበባ ላይ ለመዋጋት የነበራቸውን ሃሳብ በምክር ያፈረሱ::
9. **እንቁ ኃይለ መስቀል /ኮሎኔል/**
   ደጃዝማች ፈቀረ ማርያም በወደቁበት በራምቡቲው ጦርነት የተካፈሉ፣
   በኋላም የኬንያ ስደተኛ::
10. **ይላቅ ጌታነህ /የ50 አለቃ/**

ሸዋ፣ ሸንኮራ፣ ከራምቡቲ ጦርነት የተማረኩት አርበኞች በመርዝ መገደላቸውን ያየ።

11. **ኃይሌ ዳርጌ /ግራዝማች/**
የቀድሞ ስሙ የኒላአሸት ኃይሌ የነበረውን መልአከ ፀሐይ ኢያሱ፣ ምኒልክን ከአብዮ ገዳም ካወጡት የቡልጋ አርበኞች አንዱ።
እንደዚሁም መጽሐፍ የተማረከበትን ሁኔታ የሚያውቅ።

12. **ቀጸላ አባትዩ /አቶ/**
በዲቁና ሥልጣን መልአከ ፀሐይ ኢያሱን ጭንቂት ማርያም፣ ቡገሬ ዛለ፣ ቡልጋ፣ ሥጋ ወደሙ ያቀበለ።

13. **በቃሉ ተገኘ /አባ/**
ጉጃም፣ ገና ሐይቅ አራ ኪዳነ ምህረት አንድ የጣልያን የጦር አዛዥ በገባ ጊዜ ከመቅደሱ በር ወድቆ መሞቱን ዲያቆን ሆነው ያዩ።

14. **እሸቴ ባዩ /አቶ/**
ወደ ኬንያ የተሰደዱና በዚያ የደረሰውን ሁኔታ የሚያውቁ

15. **መኰንን ደነቀ /ጀነራል/**
ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ስደት ሲሄዱ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ያወረዱአቸውን መኪንንት በመቶ አለቅነት የተረከቡ ፖሊስ።

16. **ዓለመ ሥላሴ ገላ /አቶ/**
በሞቃድሶሾ እሥረኛ የነበሩና፣ በዚያ የነበረውን አበሳና ሥቃይ የቀመሱና ያዩ።

17. **ወልደ ጊዮርጊስ ኪዳኔ /መ.አለቃ/**
በፊታውራሪ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ ባልደረብነት፣ የቡልጋ አርበኛ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ባቃጠለ በአንድ ላይ ፍርድ በተሰጠ ጊዜ የነበረ። የፊታውራሪ ዝቅ አርጋቸውንና የፊታውራሪ ሞገሴን አሟሟት የሚያውቅ አርበኛ።

18. **ጌታቸው በቀለ ዘውዱ /አቶ/**
የመድፍ አፈሙዝ ከእንጨት ተፈልፍሎ መተኮሱን ያየ የቡልጋ አርበኛ።

19. **ኃይሌ ወልደ ፃድቅ /ፊታውራሪ/**
መልአከ ፀሐይ ኢያሱን ለማንገሥ በተደረገው ምክር ላይ የነበሩና ያነገሡ፣ በኋላም ለአካባቢው ሕዝብ አዋጅ የነገሩ የቡልጋ አርበኛ።

20. **ሠርጤ፣ ወልደ ፃድቅ /ሻለቃ/**
እነ ፊታውራሪ አጕናፍር መደዲማ ላይ በርስ በርስ ጠብ ያለቁበትን ምክንያትና የፈጃቸውን የሚያውቁ የቡልጋ አርበኛ።

21. **ልሣነ ወርቅ ተሰፋዬ /አቶ/**
መልአከ ፀሐየ ኢያሱ በታመሙ ጊዜ ሠራዊቱ በሊቀ መኳስ አሉላ መመራቱን ያዩ የቡልጋ አርበኛ።



22. **ምሥካየ ሥዩም ተክሌ /ቀኛዝማች/**
ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አዲስ አበባን ያጠቁበትን ሁኔታና እንደዚሁም በእራን ቡቲ ጦርነት ላይ መሞታቸውን ለቡልጋ አርበኛ ነግሮ ዲደታ ቡልጋ በአርበኝነት የሞተ።


23. **ሞላ ገዘሙ /አቶ/**
በአራንቡቲ ጦርነት ላይ የተካፈሉና ደጃዝማች ፍቅረ ሥላሴ ወደ ሣማ ሰንበት ዋሻ እንደገቡ ለቤት አሽከሮቻቸው ሲነገር የሰሙ።

24. **መኰንን ወልደ ሚካኤል /አቶ/**
መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ጀሎ አገር ማርያም በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እጅ በድጋሚ ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት መባላቸውን በደብተርነት ማኅሌት በመቆም ያዩ የቡልጋ አርበኛ።

25. **ቃለ ክርስቶስ ዓባይ /ኰሎኔል/**
የትግራይ አርበኞች ከማይጨው ጦርነት በኋላ እንደምን ወደ አገራቸው ወደ ትግራይ እንደተመለሱ የሚያውቁ።

26. **በቀለ ፀጋዬ /አቶ/**
ከእነ ፊቴውራሪ ወንድምነህ ጋር ተጉለት ተማርከው ለመረሸን ከቀረቡ በኋላ አዛገፍ ኢጣልያዊ ከሞት ካዳናቸው በኋላ አምልጠው አርበኝነታቸውን የቀጠሉ።

27. **ወልደ ገብርኤል ወልደ ሚካኤል /አቶ/**
በደጃዝማችነት አውራሪስ ዱሉ ባልደረብነት የመንዝ አርበኛ። ደጃዝማቹ ጠላት ከተባረረ በኋላ በብስጭት መሞታቸውን ያየ።



RED SEA
ERITREA
SUDAN
ARABIA
Asmara
Dahlak Archipelago
GONDER
TIGRAY
Mekele
Gonder
WELO
DJIBOUTI
GULF OF ADEN
GOJAM
Dese
Debre Markos
SHEWA
Addis Abeba
WELEGA
Nekemte
ARSI
Asela
Harer
SOMALIA
HARERGE
ILUBABOR
Metu
Jima
KEFA
Awasa
Goba
BALE
Arba Minch
GAMO GOFA
SIDAMO
KENYA
AFRICA
N
0 100 200 300 Kilometers
0 50 100 150 Miles

የታሪክ ጥናት ተቀዳሚ ሚና የህብረተሰብን አላፊና ዘላቂ እሴቶችን መመርመርና በነዋሪ እሴቶቹ ላይ ማቆም ነው፡፡ ታሪክ በአንድ አገር ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ ሁነኛ ሚና እንዲጫወት ከተፈለገ በትንሹ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡፡ አንደኛ ለታሪክ ጥናት የማያወላውል መሰጠትና ታማኝነት፡፡ ሁለተኛ የላቀ የሀገር ፍቅርና አላማ፡፡ እነዚህ ፍጹም ባልተዋሃዱበት የሚጻፍ ታሪክ ሚዛን ያልጠበቀና ረብ የለሽ ከመሆን አይድንም፡፡

እንዳለመታደል የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ-ታሪክ ገና ክጮርቃ እድሜው ላለፉት አራት አሰርት ዓመታት በተፃራሪ ርእዮቶች ከግራ ቀኝ በመ ንገላታቱ ዘመን የሚያሻግር ብሔራዊ ራእይ ለመያዝ አልቻለም፡፡ በብዙ ድካም የተሰሩ ጥናቶች ከአካዳሚያዊ ንፍቀ ክበብ ባለፈ ህዝባዊ ተደራሽነት ሊኖራቸው አልታደሉም፡፡ ምናልባት በበጎ ጎኑ አካዳሚያዊ የታሪክ ጥናትና ዘገባ ራሱን በገሃድ "የአሸናፊዎች ደንገጡር" ከመሆን ተከላክሏል ማለት ይቻል ይሆናል፡፡

ከዚህ አካዳሚያዊ ቅጥር ውጭ ታሪክን በትርፍ ጊዜያቸው የሚመረምሩና የሚጽፉ በርካታ ዜጎች አሉን፡፡ "ዘልማዳውያን" በሚል የሽሙጥ ፈርጅ ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ጸሐፍት ህዝብን ተደራሲ በማድረግ፣ በራሱ ቋንቋ በመቅረብና ለ"መንግሥታዊ" ታሪክ አማራጭ በማቅረብ ረገድ የማይናቅ ተግባር አከናውነዋል፡፡

የዚህ የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት በሚል ርዕስ የተጻፈ ታሪክ ደራሲ ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ በዘመናቸው ያዩትንና የሰሙትን የአንድ ጀግና ትውልድ ታሪክ ከመዛግብትና ከሰዎች ምስክርነት ጋር በማወራረስ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ስራ አቅርበዋል፡፡ እጅግ እንደደከሙበት አያጠራጥርም፡፡

በተለይም ደግሞ እንዲህ አይነት ብሔራዊ አንድምታ ያላቸው ርእሶች በአገር የታሪክ ባለሙያዎች "አይነኬ" ሆነው በመቆየታቸው፤ ኢትዮጵያውያን የገዛ ታሪካችንን የወቅቱ ባላጋራችን ከነበረችው ከጣልያን ምሁራን የማንበብ አሳፋሪ ግዴታ ውስጥ ነበርን፡፡ ደራሲው እጅግ የተበታተነውንና ሰፊውን የአርበኝነት ዘመን ተጋድሎ ከኢትዮጵያውያን ወገን ብሔራዊ ቅርጽ ሰጥተው አቅርበውልናል፡፡ በከፍተኛ ቀናኢነት የተጻፈ ቢሆንም ሚዛኑን የጠበቀ ነው፡፡

ደራሲው ተድላ ዘዮሐንስ የቱንም ያህል ተመልካች ፈረንጆችና ባይተዋር ትውልዶች ሊያሳዩን ያልቻሉትን የጊዜውን መንፈስና ህይወት በየመሃሉ ብልጭ ያደርጉልናል፤ ያስገርሙናል ያዝናኑናል፡፡ ቋንቋቸው ባለዜማ ነው፣ ምናልባት ታላቁን ተክለጻድቅ መኩሪያን ያስታውሱናል፡፡ ባለውለታችን ናቸው ብዮ አምናለሁ፡፡

መጽሐፉ ከዘመናዊ የታሪክ አጻጻፍ ረገድ በመረጃና ተጠየቅ፣ በዘገባ ስልትና ንድፈ ሃሳባዊ መሰረት እንከን የለሽ ነው ባይባልም፤ በኢትዮጵያና በጣልያን ጦርነት ድርሳን ውስጥ ግን የራሱን ድርሻ እንደሚይዝ አያጠራጥርም፡፡ ለታሪክ አጥኝዎች ጠቃሚ ምንጭ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ባለታሪኩ ህዝብ ደግሞ በህሊናው ሸንጎ ይዳኛቸዋል፡፡

ቴዎድሮስ ኃይለማርያም ገድሉ
ፒኤችዲ ካንዳ[illegible] አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

$ 26 99

ማንኩሳ አሳታሚ
Cover Design: Jake 0923 157643
ዋጋ ብር 75.00
ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢንስቲትዩት ህትመት ሥራ